አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮምዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# "የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ዕይታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን"

በ

ዐያሌው አማረ

የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# “የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ዕይታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን”


አዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት ፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ - ግብር


ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የኤም. ኤ. ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ዐያሌው አማረ

አማካሪ

ዘለዓለም መሠረት


የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ፣የሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ - ግብር

# "የጥምቀተ ክርስትና፣የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ዕይታ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን"

በ

ዐያሌው አማረ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ስም ______________________ ፊርማ ______________

የውስጥ ፈታኝ ስም ______________________ ፊርማ ______________

የውጭ ፈታኝ ስም ______________________ ፊርማ ______________

የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ምስጋና

ይህ ጥናት እዚህ ደረጃ እስኪደርስ ጊዜያቸውን ሰውተው አቅጣጫ በማሳየትና ረቂቁን በማረም እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ዘለዓለም መሠረት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ኮምፒውተር በመስጠትና የማበረታቻ ድጋፍህ ላልተለየኝ ወንድሜ ብርሃኑ ጣሰው ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትብብር ደብዳቤዬ እንዲፋጠን በማድረግ፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን በማስተዋወቅና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ከጎኔ ለነበርሽው ጋዜጠኛ ሔርሞን መለሰ ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና መሥሪያ ቤቶች በመንዝ መረጃ በምሰበስብበት ወቅት አብራችሁኝ በመንዝ፣ ቪዲዮ በመቅረጽ፣ ፎቶ በማንሳት ለተባበራችሁኝ ጓደኞቼ ወ/ሪት ወይንሸት ሙሉጌታ፣ ሰላማዊት በየነ፣ ወጣት ዳዊት ብርሃኑና ዲያቆን ሚሊዮን ተሾመ የዚህ ጥናት ደጋፊ ናችሁና ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

የመስክ ጉዞ ባደረግሁበት ወቅት የገንዘብና የሀሳብ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ እህቴ ሶፊያ አወል፣ ወንድሜ ማርቆስ ፈለቀ እና ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ሳትሰለቺ በኮምፒውተር በመጻፍና በማረም እገዛ ላደረግሽልኝ ወ/ሪት አዜብ ቦጋለ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

የድጋፍ ደብዳቤ በመስጠት ለተባበራችሁኝ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነትና ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከልብ አመሰግናችኋለሁ፡፡ የትምህርት ዕድሉን ለሰጠኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና መረጃ በመስጠት ለተባበራችሁኝ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ምዕመናንና ሰንበት ተማሪዎች ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ዕይታ በሚል የተጠና ነው። የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡት በዋናነት በሰነዶች ምርመራ፣ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ከአምስት የተመረጡ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆን፤ በመረጃ አቀባይነት የተመረጡትም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ የሰንበት ተማሪዎች፣ ካህናት፣ የእምነቱ ተከታይ ወጣቶች፣ አረጋውያንና እናቶች ናቸው። በነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ጥናቱ በኢኦተቤ የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታን ማሳየት ዓላማ አድርጎ በመነሣቱ የሥርዓተ ክዋኔዎቹን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለማሳየት የክዋኔ /performance/ ቲዎሪ ዘዴን ተጠቅሟል። በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አቅጣጫ መሠረትም በገላጭ የምርምር ስልት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓት ክዋኔ ወቅት የሚታዩ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ተግባራት ተምሳሌታቸው ተተንትኗል። የክርስቲያን ልጆች ሕፃናት ወንዶች በተወለዱ በ40ኛው ቀናቸው፤ ሴቶች ደግሞ በ80 ቀናቸው ክርስትና ይነሣሉ። በተጨማሪም ማንኛውም ሰው በየትኛውም ዕድሜ ክልል ላይ ከተማረና ካመነ መጠመቅ እንደሚችል በጥናቱ ተረጋግጧል። በዚህ ዕለት ተጠማቂዎች በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወልደው ጸጋቸውን የሚቀበሉበት ቀን ነው። ወዲያውም የተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው ሜሮን ይቀባሉ። ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ እንዳለሆኖ፣ ማኅበረሰቡም ከሃይማኖታዊው ሥርዓት ውጪ በልማድ ዘወትር ከሚመገበው እንጀራ ላይ ተጠማቂዎችን ያንከባልሏቸዋል፣ ይህም ወደፊት እንጀራ ይስጥህ፣ ሀብም ሁን፣ የተሰጠህን ጸጋ በተግባር የምታውል ፣ ያድርግህ ማለታቸው እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል። የ ክርስቲያን ልጆች በሃይማኖት ውስጥ ኖረው፣ በድንግልና ቆይተው፣ ለጋብቻ ሲደርሱ ተክሊል ይፈጽማሉ። በተክሊላቸውም ወቅት ሜሮን ይቀባሉ፤ ይህም ጋብቻቸው በመንፈስ ቅዱስ የተባረከ የተቀደሰ ጋብቻ እንደኾነ የሚረጋገጥበት ነው። የክርስትና እናትና አባት ተግባር ዓላማው ሃይማኖትን ማስተማር ቢሆንም በማኅበረሰቡ ባህላዊ ዝምድና የመፍጠሪያ ትስስሩ በልጦ መታየቱን በጥናቱ ግኝት ተረጋግጧል። ይህም ጥምቀተ ክርስትና ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ተግባራትን የሚያሳይ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። የጥምቀተ ክርስትናና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፋይዳው ተጠማቂዎች ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈሥ ቅዱስ ተወልደው፣ የእግዚኣብሔር የጸጋ ልጅነታቸው እንዲረጋገጥ መድረግ እንደኾነ ጥናቱ አሳይቷል። በተጨማሪም የተክሊል ጋብቻ የቤተሰብ አንድነት፣ የጋብቻ ዘላቂነት፣ የትውልድ ቀጣይነት እንዲኖር ፋይዳ ያለው መኾኑን ለማወቅ ተችሏል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓተ ክዋኔ ወጥ ሆኖ ሳለ በክርስትና ምክንያት ምዕመናኑ ከአኗኗራቸው የራሳቸውን ልማዶች ሲከውኑ ይስተዋላል፤ እነዚህም ተጠማቂ ሕፃናትን እንጀራ ላይ ማንከባለል፣ እንጀራውን ቆራርሶ ለታዳሚዎች መብላት፣ የክርስትና ድግስና አበልጆች ሲያገቡ የሚሰጡ ስጦታዎች በልማድ የሚከወኑ ናቸው። እነዚህና በየጊዜው የሚታዩትን ጨምሮ በፎክሎራዊ ገጽታቸው የሚታዩ ሆነዋል።

# ሙዳየ ቃላት

መበለት፡- በቤተ ክርስቲያን የግብር ስንዴ በመልቀም፣ ማይ በመቅዳት የምታገለግል ሴት

መቅረዝ(ተቋም)፡- የመብራት ዕቃ፣ የመብራት መሸከሚያ፣ የሻማ፣ የቀንዲል መኖሪያ(ማብሪያ) ነው፡፡ በግዕዙ ተቋመ ማኀቶት ይባላል፡፡ መብራቱ ሻማ ወይም ቀንዲል ሊሆን ይችላል፤ መቅረዙ ለመሸከሚያነት የሚያገለግል ነው፡፡

መቋሚያ፡- መደገፊያ፣ መመርኮዣ ማለት ነው፡፡ የመስቀል ቅርጽ እንዲይዝ ተደርጎ ከቀንድ፣ ከእንጨት፣ ከነሐስ፣ ከብረት፣ ከብር ሊሠራ ይችላል፡፡ ምዕመናን ካህናት ለመደገፊያነት ይጠቀሙበታል፤ በማኅሌት ጊዜ ካህናት ያለ ከበሮና ጸናጽል ለዝማሜ ይጠቀሙበታል፡፡ በመዝሙር ወቅት በትከሻቸው ተሸክመው፣ በእጃቸው ከፍ እድርገው በመያዝ ያሸበሽቡበታል፡፡

መጐናጸፊያ፡- ትልቅና አራት ማዓዝን ያለው፣ ባለ ገበር፣ ከወር ቀዘቦና ከመሳሰሉት የሚሠራ፣ ታቦተ ሕጉ የሚለብሰው፣ ለአክብሮተ ሥጋ ውደሙ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀምበት ፣ሙሽራውና ሙሽሪት በአንድነት የሚለብሱት ትልቅ ጋቢ የሚመስል ልብስ ነው፡፡

ማተብ፡- በኢኦተቤ በአንገት ዙሪያ ክርስቲያኖች በኢትዮጵያ የሚያስሩት ጥለት፣ የእምነቱ ምልክት ነው፡፡ ለሃይማኖት ምልክትነት የሚታሰር ነው፡፡

ማዕጠንት፡- በኢኦተቤ በተለያዩ የጸሎት ጊዜያት የሚጨስ ዕጣን

ማይ፡- ውኃ፣ በኢኦተቤ በክርስትና ጊዜ ጸሎት ተደርጎበትና ተባርኮ ለጥምቀት አገልግሎት የሚውል ውኃ፣ ዐቃቢት ለቤተ ክርስቲያን ለቅዳሴ ጸበል የምትቀዳው ውኃ ፡፡

ሥርዓት ፡- "ሠርዓ" ከሚለው የግዕዝ ግስ የመጣ ስም ነው፤ ትርጓሜውም ደምብ፣ አሠራር፣ መርሐ ግብር ማለት ነው፡፡

ስን፡- መቁረርት/ኩስኩስት/ ይባላል፡፡ ካህኑ በቅዳሴ ጊዜ እጁን ሲታጠብ የሚጠቀምበት ማንቆርቆሪያ ነው፡፡ ለቅዳሴ ጸበል መያዣም የሚያገለግል ነው፡፡

ብርት፡- የእጅ መታጠቢያ የሚኾን ሳሕን ነው፤ ካህኑ ወደ ቅዳሴ ሲገባ እጁን የሚያነጻበት (የሚታጠብበት) ነው፡፡ ውኃን ከስን ወይም ከመቁረርት ለመቀበያም ያገለግላል፡፡

ንፍቅ ካህን፡- ገባሬ ሠናዩን ካህን የሚረዳ ቄስ፡፡

አበ ምኔት፡- የገዳም አባት ወይም የገዳም አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡

አበ ልጅ፡- የክርስትና አባትና እናት ቀኝ አውራ ጣት የሚይዝ፣ የምትይዝ የሃይማኖት ባለ ቃል ኪዳን፡፡

አትሮንስ፡- በቤተ ክርስቲያን መጽሐፍን ዘርግቶ ለማንበብ የሚያገለግል፡፡ ተቀምጦ ወይም ቆሞ ለማንበብ የሚያገለግል ነው፡፡ ከብረት እና ከእንጨት ሊሠራ ይችላል፡፡

አንብሮተ ዕድ፡- እጅ በመጫን መንፈስ ቅዱስን ማሳደር፡፡

አክሊል፡- ኵፊት፣ ቆብ፣ ጥምጥም፣ የራስ ልብስ፣ ቀጸላ፣ መሸፈኛ፣ ጌጥነት ያለው ፍፁም ሽልማት ይባላል፡፡ ካህናትና ዲያቆናት በቅዳሴ ጊዜ አክሊል ደፍተው ይቀድሳሉ፡፡

ካባ ላንቃ፡- ካህናት በቅዳሴ ጊዜ የሚለብሱት የመቀደሻ ልብስ ነው፤መደረቢያ ልብስ ነው፤ ቀዳስያን ለመቀደሻ ከሚለብሱት ቀሚስ በላይ የሚደርቡት ነው፤ ሙሽሮች በተክሊላቸው ቀን ከሥር ከሚለብሱት ነጭ ልብስ ላይ የሚደርቡትም ነው፡፡

ዕጣን፡- በበረሃ ከሚበቅል ከዕጣን እንጨት የሚገኝ ሲሆን፤ሽቱ፣የሽቱ ቅመም፣ለቤተ መቅደስ ተበጀ፤ተዘጋጀ፤ መስዋዕት የሚኾን፤የሚጤስ፣ የሚታጠን ነው፡፡

ገባሬ ሠናይ፡- መሪ ካህን፣ በቅዳሴ ጊዜ ጸሎቱን የሚመራ ካህን፡፡

ጸባቴ፡- የደብረ ሊባኖስ ዳኛ፣ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ፡፡

ጸናጽል፡- ቃጭል፤ ሻኩራ ማለት ነው፡፡ የመዝሙር መሣሪያ ነው፡፡በማኅሌት፣ በመዝሙር ወቅት ያማረ ድምጽ የሚያወጣ መሳሪያ፤ የ`ሀ` ቅርጽ ኖሮት ከነሐስ፣ ከወርቅ፣ ከብር ሊሠራ ይችላል፡፡

ጽንሐሕ፡- የዕጣን ማጠኛ፣ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ዕጣን ለማጠኛነት የሚጠቀሙበት ነው፡፡

## አኅጽሮተ ጽሑፍ

ከዚህ በታች የቀረቡት ምህጻረ ቃላት በዚህ ጥናት ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ ናቸው፡፡

ዘፀ.፡- ኦሪት ዘጸአት

ዘሌ.፡- ኦሪት ዘሌዋውያን

ሕዝ፡- ትንቢተ ሕዝቅኤል

መዝ.፡- መዝሙረ ዳዊት

ማቴ፡- የማቴዎስ ወንጌል

ማር.፡- የማርቆስ ወንጌል

ሉቃ.፡- የሉቃስ ወንጌል

ሐዋ.፡- የሐዋርያት ሥራ

ዮሐ.፡- የዮሐንስ ወንጌል

1ቆሮ.፡- የመጀመሪያዪቱ የጳውሎስ መልዕክት ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች/ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች፡ ፩/

ኤፌ.፡- ወደ ኤፌሶን ሰዎች

1ዮሐ፡- የመጀመሪያዪቱ የዮሐንስ መልዕክት/የዮሐንስ መልዕክት፡ ፩/

ፍ.ም፡- እስከ ፍጻሜ ምዕራፍ

ፍት.ነገ፡- ፍትሐ ነገሥት

ፍት.መ፡- ፍትህ መንፈሳዊ

አን፡- አንቀጽ

ኢኦተቤ፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና.....I

አጠቃሎ.....II

ሙዳየ ቃላት.....III

ማውጫ.....VI

ምዕራፍ አንድ.....1

መግቢያ.....1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.....4

1.3. የጥናቱ ዓላማ.....4

1.4. የምርምር ጥያቄዎች.....5

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት.....5

1.6. የጥናቱ ወሰን.....6

1.7. የጥናቱ ዘዴ.....7

1.7.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ.....7

1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ.....7

1.7.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ.....8

1.8. የመስክ ተሞክሮ.....9

1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች.....11

ምዕራፍ ሁለት.....12

ክለሳ ድርሳናት.....12

2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት.....12

2.1.1 የጥምቀተ ክርስትና ምንነትና አጀማመር ........................................................ 12
ሀ. ጥምቀት በብሉይ ኪዳን....................................................................................14
ለ. ጥምቀት በሐዲስ ኪዳን ...................................................................................15
2.1.2 የሜሮን ምንነትና አጀማመር ....................................................................... 17
ሀ. የሜሮን አጀማመር በሐዲስ ኪዳን ........................................................................18
ለ. የሜሮን አጀማመር በብሉይ ኪዳን........................................................................20
2.1.3 የተክሊል ምንነት........................................................................................ 20
2.1.4 ሥርዓተ ከበራ (ክብረ በዓል) ........................................................................ 22
2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ..........................................................................................24
2.2.1. ክዋኔ ........................................................................................................ 24
2.2.2 አውድ......................................................................................................... 27
2.3 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት .....................................................................................29
ምዕራፍ ሦስት...........................................................................................................35
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ..............................................35
3.1.የክርስትና አመሠራረት.............................................................................................37
3.1.1. ክርስቲያን መባል መቼ ተጀመረ ......................................................................... 37
3.1.2. የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥያሜ .............................................................................. 38
3.2. ጥናቱ የተካሄደባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዳራ........................................................39
3.2.1 የደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሠራረት ....................................................................... 39
3.2.2. እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት ......................................... 42
3.2.3. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም አመሠራረት ............................................ 44
3.2.1. የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም አመሠራረት .................... 48

ምዕራፍ አራት ......51

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ......51

4.1. የክርስትና አነሣሥ ሥርዓተ ክዋኔ ......51

4.1.1. ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ......51

4.1.2 ሥርዓተ ክዋኔ......55

4.1.3. ድኅረ ሥርዓተ ክዋኔ......78

4.2. የተክሊል አፈጻጸም ሥርዓተ ክዋኔ......88

4.2.1. ከተክሊል በፊት የሚደረግ ሥርዓተ ክዋኔ......88

4.2.2. የተክሊል ሥርዓተ ክዋኔ ......89

4.2.3 ድኅረ ሥርዓተ የተክሊል ክዋኔ......102

4.3 የሦስቱ ሥርዓቶቹ ተማሳሎና ልዩነቶች ...... 105

ምዕራፍ አምስት ......107

ማጠቃለያ......107

ዋቢ ጽሑፎች ......112

አባሪዎች

አባሪ 1 የተለያዩ ፎቶዎች

አባሪ 2 የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

አባሪ 3 ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

አባሪ 4 ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለምን የዐዲሱን ቤተክርስቲያን የመሠረተ ድንጋይ ሲያኖሩ ያደረጉት ንግግር

አባሪ 5 የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ዴር ሱልጣን ገዳም የተላከ ደብዳቤ

## የፎቶ መግለጫ


ፎቶ 1፡ አሁን ያለው የደብረ ሊባኖስ ገዳም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ...............42
ፎቶ 2፡ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቤተ ክርስቲያን .......................................44
ፎቶ 3፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም አሁን ያለው ቤተክርስቲያን......................................46
ፎቶ 4፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም አሁን ያለው ቤተክርስቲያን ............................48
ፎቶ 5፡ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም..............................................49
ፎቶ 6፡ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም አሁን ያለው ቤ/ክርስቲያን ..................................................................................................50
ፎቶ 7 የክርስትና ማንሻው ገንዳ በከፊል..........................................................................57
ፎቶ 8፡ የሕፃኗ እናት ፊቷን ወደ ምሥራቅ አዙራ ተቀምጣ እና ቄሱ ዕያጠኑ .......................58
ፎቶ 9 በክርስትናው ወቅት የነበሩ ካህናት አቋቋም በከፊል ....................................................59
ፎቶ 10 መነኩሴው ዲያቆን ሕፃኗን ወደአራቱም አቅጣጫዎች ሲያዞሯት ..............................62
ፎቶ 11 መሪው ካህን አሐዱ አብ ቅዱስ… ሲጸልዩ፡፡ .........................................................64
ፎቶ 12 ካህናት በውኃ ሲያጠምቁ በከፊል........................................................................67
ፎቶ 13 ካህኑ ለተጠማቂዋ ማተብ ሲያስሩላት በከፊል .........................................................71
ፎቶ 14 መሪው ካህን የሕፃኗን የተለያዩ የአካል ክፍሎች ሜሮን ሲቀቧት በከፊል...................72
ፎቶ 15፡ ሕፃናት እንጀራ ላይ ሲንከባለሉ በከፊል ................................................................79
ፎቶ 16 የክርስትና ምግብ ዝግጅት በከፊል .........................................................................80
ፎቶ 17 ሙሽሮች ጧፍ እያበሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ...................................................90
ፎቶ 18 ሙሽሮች ከመቅደሱ ፊትለፊት ሥርዓቱ ሲጀመር በከፊል .........................................91
ፎቶ 19 ሙሽሮች ቃል ሲገቡ በከፊል..............................................................................93
ፎቶ 20 ሙሽሮች ካባ ለብሰው በከፊል.............................................................................96
ፎቶ 21 ሙሽሮች ካባ ለብሰውና አክሊል ከተደረገላቸው በኋላ በከፊል ..................................97
ፎቶ 22 ክህናቱ ከሙሽሮቹ ፊት ወረብ ሲያቀርቡ ...............................................................99
ፎቶ 23 መዘምራን ሙሽሮችን አጅበው ቤተክርስቲያኑን ሲዞሩ ............................................100

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ሲኖር የሚያልፍባቸው የሕይወት ሽግግሮች አሉት፡፡ በእያንዳንዱ የሽግግር ሂደትም የራሱን ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ሥርዓት ይሠራል፡፡ በግለሰብም ሆነ በማኅበረሰብ ደረጃ ሲኖር ራሱ ለሚያበጃቸው ልማዶችና ሥርዓቶች ይታዘዛል፣ይገዛል፡፡ በዚያ ሥርዓትም ይኖራል፡፡ እነዚህም ከመወለዱ ጀምሮ በየደረጃው የሚያልፍባቸው የሕይወት መንገዶች ናቸው፡፡ አንዱን ካለፈ በኋላ ወደ ሌላኛው ደረጃ ያልፋል፡፡ ከበርካታዎቹም መካከል በኢኦተቤ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ልማድ የሚታይባቸው የክርስትና፣የተክሊልና የሜሮን ሥርዓት ክዋኔዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አንድ ሕፃን ሲወለድ በአርባኛው ቀን ሴት ከኾነች ደግሞ በሰማኒያኛው ቀን ክርስትና ይነሣሉ፡፡

ክርስትና የሚፈጸመው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የእምነት ሥርዓት ውስጥ ነው፡፡ በቤተክርስቲያኒቱ ተኮትኩተውና ሕጓን ጠብቀው ካደጉ በኋላ ለጋብቻ የሚደርሱ ግለሰቦች ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል ይፈጽማሉ፡፡ እነዚህም በማኅበረሰቡ በትወፊት ተቀብሎ የራሳቸው ጊዜ ሰጥቷቸው የሚከወናቸው ልማዶች ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ሂደት የሚፈጸሙት ልዩ ልዩ ክዋኔዎች ሃይማኖታዊና ባህላዊ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ በክርስትናም ኾነ በተክሊል ወቅት የተመረጡ የአካል ክፍሎች የእጅ መዳፍ፣ እግር፣አፍ፣አግጭ፣ ግንባር፣ የመራቢያ አካላትና የመሳሰሉት ሜሮን ይቀባሉ፡፡

ይህ ጥናት የክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፎክሎራዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው፡፡ ክዋኔዎቹ ከሃይማኖታዊ ዕይታቸው ባሻገር በማኅበረሰቡ የሚፈጸሙትን ሀገረሰባዊ ልማዶች ምን እንደኾኑ ለማሳየት ጥረት አድርጓል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ፎክሎር ሰዎችን እና የፈጠራ ችሎታቸውን፣ ማንነታቸውን፣ እምነትና እሴቶቻቸውን የምንተረጉምበት የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ ቀድሞ የፍክሎር ጥናት ያተኩር የነበረው እየጠፉ ባሉና በጠፉ ቅርሶች ላይ ነበር፡፡ የጥናት ዘርፉንም በመጥፋት ላይ ያሉ ቅርሶች ጥናት በሚልም ነበር የሚከናወነው፡፡ የፎክሎር ጥናት የወቅቱ ዓላማም በመጥፋት ላይ ያሉና የጠፉ ቅርሶችን ሰብስቦ መሰነድ ነበር፡፡ በመሆኑም ለፎክሎር ጥናት መሠረት የኾነው ጉዳይ በመጥፋት ላይ ያሉ ቅርሶች ናቸው (ፌኔጋን1992 :35)፡፡

በዚህ ሂደት በዋናነት የፎክሎር ጥናት መከናወን እንደየአገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩ ሁነቶችን አምጥቷል፡፡ ለምሳሌ የፎክሎር ሥነ ቃላዊ ተረቶች ጥናት ሲከናወን በጀርመንና በፊን ላንድ የፈጠረው ሁኔታ የተለያየ ነበር፡፡ ምክንያቱም ጀርመኖች የተረክ ፎክሎራቸውን በማጥናታቸው ራሳቸውን እንደ ልዩ ፍጡር ዐይተው ብሔርተኝነትን ያስፋፉበት ሲሆን፤ በዚህም ለከፋ ጦርነት ጭምር ዳርጓቸዋል፡፡ በአንጻሩ ፊንላንዶች የፎክሎር ጥናትን አንድነትን በማጠናከር አገር ለመመስረቻ አውለውታል፡፡ የተበተነ ማንነትን መልሶ ለመገንባት ሲሉ ተረኮቻቸውን ሰብስበው አጥንተዋል፡፡ ምክንያቱም ፊንላንዶች (የአከባቢው ትናንሽ አገር ኾነው የቆዩት) የዘመናት የጦርነትና ግጭት ታሪካቸውን ለመሻር ሲሉ በሥነ ቃሎቻቸው ውስጥ ያለውን ተመሳስሎ በመፈለግ፣ አንድነታቸውን በማስተሳሰር፣ ከቀደመ የግጭት ታሪካቸው ተላቅቀውና አንድ በመሆን የጋራ አገር እንዲመሠርቱ አስችሏቸዋል፡፡ ከዚህ ሂደት የምንረዳው የፎክሎር ጥናት የነበረው አንድም እየጠፉ ያሉን፣ የጠፉ ቅርሶችን በመሰብሰብና በመሰነድ ቅርሶችን ጠብቆ ለማቆየት ሲሆን፤ ኹለትም አንድነትን በማጎልበት አገር ለመመስረት እንዳስቻለ ነው፡፡ ይህ ማለት የፎክሎር ጥናት አንድም ቅርሶችን መሰነጃ፤ አንድም አገር መመስረቻ ኾኖ አገልግሏል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ጀርመን ዐይነት ብሔርተኝነትን ለማስፋፋት የተጠቀሙበት እንዳሉም መዘንጋት አይገባም፡፡

በፎክሎር ጥናት ከተነሱ ሀሳቦች አብዛኞቹ በፈርጅ ከፋፍሎ ማጥናት ተገቢ እንደኾነ ያምናሉ፡፡ የተወሰኑት በሦስት ለመክፈል የሞከሩ ቢሆንም የሀገራችን ምሁራንን ጨምሮ በአብዛኛው የሚስማሙት አራቱን ክፍሎች ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ (Sims and Stephen 2005:12-13) ቃላዊ፣ ቁሳዊ እና ልማዳዊ በማለት የከፈሉት ሲሆን፤ ሌሎቹ ደግሞ ሥነ ቃል፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በማለት ለጥናት አመቺ እንዲሆን ከፍለውታል (Dorson, 1972:3)፣ (ፈቃደ፣ 1991፡10)፣ (Sims and Stephen, 2005:2-3)፡፡

ለጥናት አመቺ እነዲኾኑ በዘውግ ይከፋፈሉ እንጂ በመካከላቸው ድንበር መሥራት ተገቢ አለመሆኑን ይገልጻሉ፡፡ አንዱ ባንዱ ውስጥ ሊኖር ስለሚችል መርጦ ማጥናቱ የተሻለ እንደሚሆን ይስማማሉ:: (Sims and Stephen,2005: 17):: የማኅበረሰብ ታሪክ፣ አስተሳሰብ፣ ከአምላኩ ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ሥነ ልቡናዊ ማንነቱን ለመረዳት በሃይማኖቱ ውስጥ በቅብብል የሚከውናቸውን የተለያዩ ትውፊቶች መመርመር የተሻለ ይሆናል ይላሉ፡፡

ፈቃደ (1991፣ 13-14) ከአራቱ የፎክሎር ዘውጎች ሀገረሰባዊ ልማድ አራት ርዕሰ ነገሮች እንደሚይዝ ያስረዳሉ፡፡ እነርሱም፡- ክብረ በዓል (ከበራ) "ፌስቲቫል"፣ መዝናኛዎችና ጨዋታዎች፣ ሀገረሰባዊ መድኃኒት እና ሀገረሰባዊ ሃይማኖት ናቸው፡፡ በሀገረ ሰባዊ ሃይማኖት ሥር ሊጠኑ የሚችሉትን ሲያስረዱ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍረዋል፡፡

> *የሀገረሰብ ሃይማኖት ምርምር በልዩ ልዩ በዓላት ላይ በመንደር፣ በቤተሰብ፣ በሃይማኖት (መስጊድ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ምኩራብ ወዘተ) የሚካሄዱትን ክንዋኔዎች በልደት፣ በግዝረት፣ በክርስትና፣ በጋብቻ፣ በሞት እና እነዚህን በመሳሰሉ ክንዋኔዎች ውስጥ የሚከሰቱ መስተጋብሮችን ያጤናል፡፡ … ለምሳሌ በሃይማኖት ሥርዓቶች ላይ በሚደረገው ጥናት ትኩረቱ በታወቁ የሃይማኖት መጻሕፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ ሰዎች በየራሳቸው የሃይማኖቱ አማኝና ተከታይ መሆናቸው ሳይቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምነቶች የሚፈጽሟቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው (ፈቃደ 1991፣ 14)፡፡*

የኢኦተቤክ ሃይማኖታዊ ዶግማና ቀኖና ከሚደነግጋቸው ሥርዓቶች ውስጥና ውጪ በትውፊት እየተቀባበሉ የመጡ በርካታ ሀገረ ሰባዊ ልማዶች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ማኅበረሰቡ በክርስትናና በሥርዓተ ተክሊል ወቅት የሚፈጽማቸው ልማዳዊ ሥርዓቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ለክርስትና ተነሺዎችና ለተጋቢዎች ክብረ በዓል ይዘጋጃሉ፤ *የምግብ ዝግጅት ያደርጋሉ፣ የክርስትና እናትና አባት ከክርስትናው ሳምንት በኋላ የክርስትና ልጆቻቸውን ይጠይቃሉ፡፡ ዕድላቸው የተቃና ሆኖ እንዲዘልቁና ለሌላ የሕይወት ሽግግር እንዲበቁ የሚፈጽሟቸው እንደ ምርቃት፣ የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ባህላዊ ክዋኔዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡*

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔዎች ያላቸውን ፎክሎራዊ ገጽታ ያሳያል፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከሃይማኖቱ ባሻገር የሚታዩ ሀገረሰባዊ ልማዶች ሲከወኑ ያላቸውን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ተምሳሌትነት

ክዋኔያቸውን መሠረት በማድረግ ዳሷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለባህሉ ባለቤቶች የሚሰጡትን መንፈሳዊና ባህላዊ ፋይዳ አቅርቧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት የመጀመሪያው ከልጅነቴ ጀምሮ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስመላለስ በጥምቀተ ክርስትና፣ በሥርዓተ ትክሊል የጋብቻ ክዋኔ ወቅት የክርስትና ተነሺዎች ከጥምቀት በኋላ እንዲሁም የተጋቢዎቹ የተለያዩ የአካል ክፍሎች ሜሮን ሲቀቡ ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ የተመረጡ የአካል ክፍሎች ሜሮን የሚቀቡበት ምክንያት ምንድን ነው? ያላቸውስ ትዕምርት ምን ይጠቁማል? ፋይዳውስ ምንድን ነው? የሚለውን ለማወቅ ያለኝ ፍላጎትና ከክርስትና ሃይማኖታዊ ሥርዓት በኋላ የሚደረጉ ልማዳዊ ክዋኔዎችን ስመለከት ተምሳሌታቸውና ትእምርታዊ ጠቀሜታቸው ያሳደረብኝ መገረም ነው፡፡

ኹለተኛው ማኅበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ችግር ሲገጥመውና በኢኮኖሚና በሌሎች ጎዳዮች ሲሳካለት ከዐርባ ቀን አድል ጋር ሲያገኛኙት አሰማልሁ ይህ አባባል ከምን አንጻር የሚባል ነው? ስኬትንና የ40 እና የ80 ቀኖች ምን አገናኛቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመረዳትና ለማወቅ ስለጓጓሁ፡፡

ሦስተኛው በሥርዓተ ተክሊል የሚጋቡ ግለሰቦች ድንልግናቸውን ጠብቀው የቆዩ ከመሆኑም ባሻገር በዓለማዊ ሕይወታቸውም አንድ ለአንድ ተወስነው የሚኖሩ ናቸው፡፡ የእነዚህ ሰዎች ለዚህ ምስጢር መብቃት፣ለማኅበረሰቡ ያለውን እሴት፣ ፎክሎራዊ ፋይዳና ትውፊት ለመግለጽ፤

አራተኛው በነዚህ ዙሪያ በሚመለከት የፎክሎር ዘርፍ የተጠና ጥናት ባለማግኘቴ፣ በሃይማኖታዊና ልማዳዊ፣ ሥርዓቶችና ክዋኔዎች ወቅት የሚታዩ ድርጊቶች ፎክሎራዊ ገጽታቸው የጎላ ሊሆን ይችላል ብዬ ሰላመንኩ ለትውልድ ከማስተላለፍም አንጻር ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢኦተቤ የክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት

1. የሥርዓተ ክዋኔው መነሻ ከየት እንደኾነ፣ ለምን እንደሚፈጸም እና መቼ እንደሚፈጸም ማሳየት፤

2. የእነዚህ ምስጢራት መፈጸም ለግለሰቦች እና ለማኅበረሰቡ የሚኖረውን ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ፋይዳ መግለጽ፤
3. በክርስትና እና በተክሊል ጊዜ የሚለበሱ አልባሳት ያላቸውን ትዕምርት መግለጽ፣እና
4. ክርስትናና ተክሊል የሚፈጸምላቸው ግለሰቦች ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት እንዳለባቸው ማሳየት የሚሉ ናቸው፡፡

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

1) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የክርስትና፣ የተክሊልና ሜሮን ሥርዓት የት እና እንዴት ይካሄዳል?
2) ክዋኔዎቹ ከሃይማኖታዊ ተግባራቸው ባሻገር የሚታይባቸው ፎክሎራዊ ገጽታ ምንድን ነው?
3) ክርስትና እና ተክሊል የሚፈጽሙ ግለሰቦች ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለባቸው?
4) የእነዚህ ምስጢራት መፈጸም ለግለሰቦቹ እና ለማኅበረሰቡ ያለው ፎክሎራዊ ፋይዳ ምንድን ነው?
5) በተክሊልና በክርስትና ጊዜ ተጋቢዎች፣ ክርስትና ተነሺዎች የሚለብሷቸው አልባሳት ያላቸው ተምሳሌት ምንድን ነው?
6) ክርስትና ማንሳት ሃይማኖታዊና ባህላዊ ዓላማው ምንድን ነው?

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የመጀመሪያው በክርስትና፣ ተክሊል እና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ውስጥ የሚታዩ ትውፊቶችን ሥርዓቶችንና ልማዶችን ማወቅ ለሚፈልጉ ይበልጥ ለመረዳት ሊረዳ ይችላል፡፡

ኹለተኛው በተክሊል ሥርዓተ ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ ግለሰቦች ራሳቸውን ጠብቀው በመቆየታቸውና በዚህ ሕይወት ውስጥ የማለፋቸው አርዓያነት፣ የተክሊል ጋብቻ ለማኅበረሰቡ ያለውን ማኅበረሰባዊ እሴትና በተለያዩ ምክንያቶች በመለወጥ ላይ ያለው ድንግልናን ጠብቆ የማግባት ባህል እንዲቀረስ/ እንዲሰነድ ሊረዳ ይችላል፡፡

ሦስተኛው ክርስትና ከሃይማኖታዊ አስተምህሮ ባሻገር ያለውን ባህላዊ ዝምድና የመፍጠሪያ መንገዶች፣ የክርስትና እናትና አባት ያላቸውን ሃይማኖታዊና ባህላዊ ኃላፊነት በማኅበረሰቡ ውስጥ ይበልጥ እንዲታወቁና ተጠብቀው እንዲቆዩ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይችላል፡፡

አራተኛው በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ጋብቻቸውን አጽንተው ለመኖር፣ ከጋብቻቸው በኋላ በፍቅርና በጽናት እንዲቆዩ የተክሊሉ ድርሻ ምን እንደኾነ ለማኅበረሰቡ ትምህረት ሊሰጥ ይችላል፡፡

አምስተኛው በተክሊል፣ በጥምቀተ ክርስትና እና ሜሮን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የተጠና ጥናት ባለመኖሩ ወደፊት ማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች መረጃ ይሰጣል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ ላይ የሚያተኩረ ነው፡፡ ከክዋኔ በፊት፣ በክዋኔ ወቅትና ከክዋኔ በኋላ የሚኖሩ ሥርዓቶችንና ድርጊቶችን መሰረት አድረጎ የተቃኘ ነው፡፡ ከፎክሎር ዘርፎችም ሀገረ ሰባዊ ልማድን ተመልክቷል፡፡

መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማጠናከር ጥምቀተ ክርስትና እና ሥርዓተ ተክሊል የሚከወንባቸውን የተመረጡ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በኹሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኖች የክርስትናም ኾነ የተክሊል ሥርዓት የሚፈጸም ቢኾንም በጥናቱ የሚታዩ የፎክሎር ዘርፎችን ለመመርመር ከአዲስ አበባ ሦስት ከአዲስ አበባ ውጪ ኹለት አብያተ ክርስቲያናት ተመርጠዋል፡፡ እነርሱም መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ገዳም፣ በሰላሌ ሀገረ ስብከት ሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ ሊባኖስ ገዳም፣ በደብረ ሊባኖስ ሥር የሚተዳደር አማኑኤል ደብር፣ ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳምና እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም ናቸው፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የተመረጡበት ምክንያት ከጥንታዊነታቸውም ባሻገር፣ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ገዳም፣ጳጳሳት በዚያ ስለሚገኙ የተክሊል ሥርዓት በብዛት ስለሚካኼድበት ሲሆን፣ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳምና እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ደግሞ ጥንታዊ ከመሆናቸውም ባሻገር በስለት ብዙ ጥምቀተ ክርስትና ስለሚደረግባቸው ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉት ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማነጻጸር ያመች ዘንድ ነው፡፡ በተጨማሪም በስለት ምክንያት ወላጆች ልጆቻቸውን በድብረሊባኖስ ገዳም ጥምቀተ ክርስትና በብዛት ስለሚያስነሱም ነው፡፡ ይህ ጥናት በጥር 11 የሚደረገውን የጥምቀት ሥርዓት አይመለከትም ምክንያቱም ይህ ሥርዓት ለአዲስ ተጠማቂዎች የሚዘጋጅ ሥርዓት አይደለም፡፡ በመኾኑም ራሱን ችሎ መጠናት የሚችል ክብረ በዓል ስለኾነ በዚህ ጥናት አልተካተተም፡፡ በተጨማሪም የማዓስባን ተክሊልንም አይመለከትም ምክንያቱም ይህ የጋብቻ ሥረዓት የራሱ የጸሎት ሥርዓትና ክዋኔ ስላለው ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1. የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በኢኦተቤ ኹሉም አብያተ ክርስቲያናት የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓት አፈጻጸም ተመሳሳይ ቢሆንም ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው የሃይማኖት አባቶች የተመረጡት በተለያየ መንገድ ነው። ይኸውም ሰዎችን በመጠየቅ፣ በጥቆማ፣ በመስሪያ ቦታቸው፣ በመኖሪያ ቤታቸው በክዋኔው ላይ፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ነው። በዚህም መሰረት መረጃ አቀባዮቹ በቅድስተ ማርያም፣ በሰላሌ ሀገረ ስብከት ደብረ ሊባኖስ፣ በምስካየ ኅዙናን፣ በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ቤተክርስቲያናት ተመርጠዋል። በደብረ ሊባኖስ ገዳም የተክሊል ሥርዓት ስለማይካሄድ በገዳሙ ስር በሚተዳደርና ከገዳሙ ኹለት ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው "ውሻ ገደል" በተሰኘ ስፍራ የሚገኘው የአማኑኤል ደብር ተመረጧል። በአጠቃላይ አምስት አብያተ ክርስቲያናት ለምልከታ ተመርጠዋል። ለመረጃ ሰጪነት የተመረጡትም፡- ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ በተክሊል እና በክርስትና ሥርዓት ላይ የተገኙ ታዳሚዎች፣ ክርስትና እንሺዎች (የክርስትና ተነሺ ሕጻናት ወላጆች)፣ የክርስትና እናቶች፣ የክርስትና አባቶች፣ የክርስትና እናት ወይም አባት ያላቸው ግለሰቦች፣ የኦርቶዶክስ ክርስትና ዕምነት ተከታይ ሰዎች (በእድሜ የገፉ አዛውንቶች፣ ጎልማሶችና ወጣቶች) ናቸው። በዚህ አካሄድም ሰላሳ አራት ግለሰቦች መረጃን ሰጥተዋል። ከነዚህም ውስጥ 19ኙ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ በቡድን ውይይት የተሳተፉ ናቸው።

### 1.7.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የዚህን ጥናት መረጃዎች ለመሰብሰብ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል። በመጀመሪያ በቤተ መጻሕፍት ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽሑፎች፣ የጥናት ስራዎች እና ንድፈ ሀሳቦች እንደ አስፈላጊነታቸው ዳሰሳ ተደርጓል።

መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተጠቀምኩት በዋናነት የሰነዶች ምርመራ፣ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። በዚህም መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ፣መጽሐፈ ክርስትና፣ መጽሐፈ ተክሊልና ፍትሐ ነገሥት የሃይማኖታዊ ሥርዓተ ክዋኔዎቹን ለማሳየት ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት በተፈጥሯዊ አውዳቸው ሲሆን፤ መረጃዎቹን የተሟሉ ለማድረግ ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲዮና መቅረጸ ድምጽ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። (ፈቃደ 1991፤90) አንድ የመስክ ተመራማሪ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀሙ የተሻለ እንደሆነ

ገልጸዋል፡፡ ምክንያቱም በአንዱ ዘዴ ማግኘት ያልተቻለውን በሌሎች ማግኘት ስለሚያስችል አጣምሮ መጠቀሙ ተመራጭ ነው ይላሉ፡፡ በመሆኑም ከምልከታ በተጨማሪ በሥርዓተ ክዋኔው ላይ የሚፈጸሙ የተለያዩ ተግባራት ለምን እንደሚፈፀሙ፣ ያላቸውን ፋይዳ፣ ምሳሌና ትርጉማቸው ምን እንደሆነ ለመረዳት ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያንን፣ ዲያቆናትንና፣ መምህራን በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት በተጨማሪም ሰነዶችን በመመርመር መረጃዎችን ማግኘት ተችሏል፡፡ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮ ውጪ ያሉ ባህላዊ ክዋኔዎችን ለመረዳት በየአብያተ ክርስቲያናቱ ያሉ በእድሜ የገፉ እናቶችን፣ አባቶችን ወጣት ክርስቲያኖችን፣ ሰንበት ተማሪዎችን፣ ክርስትና አባትና እናት ያላቸውን፣ ክርስትና ልጅ ያላቸውን ግለሰቦች በመጠየቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

በሥርዓተ ክዋኔው ያሉ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ከአዲስ አበባ ውጪ ሁለት በአዲስ አበባ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን ተመርጠው መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ በክርስትና እና በተክሊል ሥርዓት ላይ በመገኘት ለሙሽሮች፣ ለታዳሚዎች ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡

### 1.7.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት በሥርዓተ ክዋኔው የተፈፀሙ ተግባራትን፣ ምልክቶችን እና ምሳሌዎችን ለመተንተን፣ ለመተርጎምና ለመመለስ የሚከተለውን ዘዴ ተጠቅሜያለሁ፡፡

መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት ከተሰበሰቡ በኋላ በመጀመሪያ ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔዎችን በመቀጠል በሥርዓተ ክዋኔ ወቅት የተፈጸሙ እና ድኅረ ሥርዓተ ክዋኔ በሚል አደራጀኋቸው፡፡ በምልከታዬ ያገኘኋቸውን መጀመሪያ በቅደም ተከተል መዘገብኳቸው፡፡ ከዚያም በእያንዳንዱ ሥርዓተ ክዋኔ የተፈጸሙትን ተግባራት በመጀመሪያ በምልከታ ወቅት የተፈጸሙትን፤ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይት እና ከሰነድ ምርመራ የተገኙትን የክዋኔን የቲዎሪ አቅጣጫ በመጠቀም ሥርዓተ ክዋኔዎችን በቅደም ተከተል ተነተንኩ፡፡ እንዲሁም በገላጭ የመረጃ ማቅረቢያ ስልት ሥርዓተ ክዋኔዎችን በየደረጃቸው በቅደም ተከተል ገለጽኳቸው፡፡ በክዋኔ ቲዎሪ መሠረትም ሥርዓተ ክዋኔውን ከነአውዱ ማለትም ምን፣ የት፣ መቼ፣ በማን፣ እንዴት እና ለምን የሚሉ ጥያቄዎችን በመያዝ የያዙትን ትርጉም እና ምሳሌ ገለጽኩ፡፡ እንዲሁም በስርዓተ ክዋኔ የታዩ ሃይማኖታዊ እና

ማኅበራዊ ፋይዳ አስረዳሁ። ከዚያም በሥርዓተ ክዋኔው በዋናነት የታዩ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ለየሁ ሥርዓተ ክዋኔው የሚያስገኘውን መንፈሳዊ እና ሥጋዊ ፋይዳ ገለጽኩ።

## 1.8. የመስክ ተሞክሮ

ለዚህ ጥናት መረጃዎችን ለማሰባሰብና ሥርዓተ ክዋኔዎችን በተፈጥሯዊ አውዳቸው ለመመልከት ወደ ጥናት ቦታዎቹ ጉዞ አድርጊያለሁ። በጉዞዬም በትምህርት ክፍላችን የተጻፈልኝን ደብዳቤ በመጀመሪያ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ይዤ በመሄድና የጥናቴን ዓላማ በማስተዋወቅ ለመረጥኳቸው አብያተ ክርስቲያናት የትብብር ደብዳቤ እንዲጽፉልኝ ጠየቅሁ።

ለአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትና ለሰላሌ ፍቼ ሀገረ ስብከት ጠቅላይ ቤተ ክህነት ከጻፉልኝ በኋላ ደብዳቤዎችን ለሀገረ ስብከቶቹ አቀረብኩ። ከዚያም ለመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም፣ ገዳም፣ ለምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም፣ ለሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጻፈልኝ። የመጀመሪያ ጉዞዬን ያደረግሁት የካቲት 8 ቀን 2010 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ነው። ወደ ገዳሙ በመሔድ ደብዳቤዬንና የጥናቴን ዓላማ ለገዳሙ ጽ/ቤት አስገባሁ። ማክሰኞ በ12/06/2010 ዓ.ም ጥምቀት ክርስትና እንዳለ ነገሩኝ። እኔም እስከ ማክሰኞ ድረስ በፍቼ ከተማ ቆየሁና ጥምቀቱ የሚካኼደው ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት ጀምሮ ነው ስላሉኝ ከአራት ቀን በኋላ ዝግጅቴን አጠናቅቄ ቀረብኩ የገዳሙ ዲያቆናት መነኮሳት አስፈላጊውን እገዛ አድርገውልኛል።

በዚህ ሥፍራ አንድ የክርስትና ሥርዓትን በፎቶ፣ በቪዲዮ፣ በመቅረጸ ድምጽ፣ በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። ከክርስትናው ቤት በመሔድም የቤቱን አጠቃላይ ሥርዓት ተከታትዬ፣ ከምልከታዬ በተጨማሪ ከክርስትና አስነሺ ወላጆች አንሺዎች፣ ታዳሚዎች፣ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ኹለተኛው በቅድስት ማርያም፣ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም፣ በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምኅረት ከየካቲት 20/2010ዓ/ም ጀምሮ እስከ መጋቢት 30/210 ዓም ድረስ ምልከታ አድርጊያለሁ። በዚህም መሠረት ሰባት የሕፃናት ጥምቀተ ክርስትና ምልከታ ያደረግሁ ሲሆን በሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት  አንድ የትልቅ ሰው ከሕፃናቱ ጋር አብሮ ጥምቀተ ክርስትናን ተመልክቻለሁ። እነዚህም በሐመረ ኖኅ ኹለት፣ በምስካየ ኅዙናን መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ሦስት በቅድስት ማርያም ኹለት ጥምቀተ ክርስትናን ተመልክቻለሁ። በእያንዳንዱ ምልከታዬ ወቅት ታዳሚዎችን የጥናቴን ዓላማ በማስረዳት በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ለማግኘት ችያለሁ።

በተጨማሪም ቀጠሮ በማስያዝ ቤታቸው መሥሪያ ቤታቸው በመኼድ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በነዚህ ምልከታዬ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ፣ በክዋኔ ወቅትና ከክዋኔ በኋላ በሚል በሥርዓተ ክዋኔያቸው በቅደም ተከተል ካደራጀሁ በኋላ የዐቢይ ጾም ስለተጠናቀቀ የሰርግ ምልከታ ከማድረጌ በፊት ተጨማሪ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይቶችን በማድረግ ክርስትናን በሚመለከት መረጃዬን አደራጀሁ፡፡

ከሚያዚያ 5/2010 ዓ/ም ጀምሮ የሰርግ ምልከታ አደረግሁ፡፡ በዚህም መሠረት ደብረ ሊባኖስ ገዳም የተክሊል ሰርግ የሚካኼደው በዋናው ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን ከገዳሙ አንድ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በዚያው በገዳሙ ሥር ባለ የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ኹለት እሑዶችን በዚያው በመቆየት ሦስት የተክሊል ሥርዓቶችን ተመልክቻለሁ፡፡ ከትንሣኤ አስራ አምስት ቀን በኋላ በ19/08/2010 ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ  በመረጥኳቸው አብያተ ክርስቲያናት በመኼድ የተክሊል ሰርግ ያለበትን ቀን ከሰበካ ጉባዔዎች መረጃ ወሰድኩ፤ መቼ መቼ ሰርግ እንዳለ አረጋገጥኩ፡፡ ምንም እንኳን ሰርግ ቢኖርም እሑድ ቀን የገጠመኝ የማዓስባን(የቁርባን) ሰርግ ነበር፡፡ ይሁንና በ28/08/2010 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ገዳም 4 የተክሊልና አንድ የማዓስባን( ሰርግ ስለነበር በዚህ ቀን ቅዳሜ በ27/08/2010 ዓ.ም የደብሩ ዲያቆናት ትብብር እንዲያደርጉልኝ የሰበካ ጉባዔው ዋና ጸሐፊ ነገሩልኝ፡፡ የኢኦተሲ ጋዜጠኛ ሔርሞን መለሰም ዲቆናቱን በስልክ አስተዋወቀችኝ፤ እገዛ እንዲያደርጉልኝ ነግራቸው ነበር፡፡ እንርሱም ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት እንድገኝ መረጃ ሰጡኝ፡፡ በዚህም መሠረት ከዲያቆናቱ ጋራ ተነጋግሬ በሰዓቱ በመገኘት መረጃዬን ተሳትፏዊ ምልከታ በማድረግ በፎቶ፣ በቪዲዮና በመቅረጸ ድምጽ በመደገፍ ሰበሰብኩ፡፡ ዲያቆናቱ ቪዲዮና ፎቶ በማንሳት ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛል፡፡ ከሚያዚያ 28/2010 እስከ ሰኔ 20/2010 ዓ.ም ድረስ ክፍተት ያለባቸው መረጃዎች በማጠናከር ከሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ከሰንበት ተማሪዎች ከምዕመናን በግልና በቡድን ቃለ መጠይቅና ውይይት ያደረግሁበት ጊዜ ነው፡፡

በመስክ ጉዞዬ በተጓዝኩበት ወቅት የመጀመሪያው ገጠመኝ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ደብዳቤ ባስገባሁበት ወቅት የጥናቱ  ዓላማ ለማስረዳት በቀላሉ ተገንዝበው የድጋፍ ደብዳቤዬን ወዲያውኑ እንዲጻፍልኝ ማድረጋቸውና እገዛቸው በአዎንታዊ መልኩ የሚያነሳ ነው፡፡ እንዲሁም በተለያዩ አብያተ ክርስቲያነት በተጓዝኩበት ወቅት ጥያቄዎቼን በተረዱት መልኩ ለመመለስ አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን አባቶች፣ ሰንበት ተማሪዎችና ምዕመናን ደስተኞች ነበሩ፡፡ ይህ በአዎንታዊ መልኩ የሚነሳ ነው፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህ ጥናት ሲደረግ የገጠሙ ችግሮች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ መረጃ በመሰብሰብ ወቅት ይገጠሙኝ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አንዳንድ ካህናትና ዲያቆናት መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ኾነው ቀጠሮ ካስያዙኝ በኋላ በመቅረጸ ድምጽ ለማስቀረት በምጠይቃቸው ወቅት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡ ያንንም በማስታወሻ በመያዝ ብቻ መረጃዎቹን ለመውሰድ ሞክሬያለሁ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በተደጋጋሚ ቀጠሮ ካሲያዙኝ በኋላ መቅረትና በቀጠሯቸው ተገኝተውም በቂ መረጃ አለመስጠት ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው፡፡ ለዚህም ሌሎች አባቶችና መረጃ ሰጪዎችን እንደገና ቀጠሮ በማስያዝ መፍትሔ ሰጥቻለሁ፡፡

ሳልጠቅስ የማላልፈው የመጨረሻው ገጠመኝ መረጃውን ለመስጠት ሙሉ ፈቃደኛ ኾነው መቅረጸ ድምጼን አዘጋጅቼ ልክ ጥያቄዬን ስጀምር ትተውኝ የተነሡ አባቶችን ነው፡፡ ይህ በአሉታዊ ምለኩ ይነሣ እንጂ አመስግኜ ከሌሎች አባቶች የምፈልገውን መረጃ ለማግኘት ችያለሁ፡፡ ባጠቃላይ በመስክ ተሞክሮዬ የተወሰኑ ችግሮች ቢገጥሙኝም ወዲያውኑ አማራጭ መፍትሄዎችን በመጠቀም መረጃዎቼን ለመሰብሰብና ለማደራጀት ችያለሁ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሶስት ርእሰ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ስለጥምቀተ ክርስትና፣ ሥርዓተ ተክሊልና ሜሮን ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ማብራሪያ የተሠጠበት ነው፡፡ በኹለተኛው ክፍል ደግሞ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የተዳሰሰ ሲሆን፤በሦስተኛው ክፍል ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው ጽሑፎች የተዳሰሱበት ነው፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የጥምቀተ ክርስትና ምንነትና አጀማመር

ምሰጢራተ ቤተ ክርስቲያን[1] የሚባሉት ሰባት ሲሆኑ አያንዳንዳቸውም የራሳቸው ትርጉምና አገልግሎት አላቸው፡፡ እነርሱም ምስጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ሜሮን ምሥጢረ ቁርባን፣ ምሥጢረ ክህነት፣ ምሥጢረ ተክሊል፣ ምሥጢረ ንስሐና ምስጢረ ቀንዲል ናቸው፡፡ አነዚህ ምሰጢራት የክርሰቶስን ጸጋ በእምነት የሚያስገኙ፣ በማይታየው ውስጠ ምሥጢራቸው፣ በጸሎት አማካይነትና በግብረ መንፍስ ቅዱስ ልጅነትን የሚያስገኙ ሥጦታዎች እንደሆኑ (ኃይለ መስቀል 1960፡ 106፣ አበራ በቀለ 1996፡ 240) ገልጸዋል፡፡

እነዚህ ምሥጢራት ለምን ምሥጢር ተባሉ? (ሀብተማርያም ወርቅነህ፣ 1963 ፣ 99-102) እንዳስረዱት

> *ምስጢር የሚለው ቃል ጽራዊ ሲሆን ግዕዝ መስሎ ከግዕዝ ጋር አንድ ሆኖ ይገኛል፤ትርጉሙም ጆሮን ከመስማት፣ ዓይንን ከማየት፣ አፍንም ከመናገር መግታት መከላከል እንደማለት ነው፡፡ ይህም ፈጽሞ መከልከል ሳይሆን ለባለ ቁርጥ ዘመድና ወዳጅ ብቻ የሚነገር፣ ማንም ሊሰማው የማይገባ፣ በወዳጅም ዘንድ ተጠብቆ የሚቀር፣ ለማንም የማይናኝ ነገር ማለት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢር የተባሉበት ምክንያት ለተለዩና ለተመረጡ በክርስቶስ ክርስቲያን ለተባሉ ሰዎች ብቻ እንጂ ለማንም የማይሰጡና የማይናኙ፤ በክርስቶስ ላመኑ ብቻ ጸጋን ረቂቅ ሀብትን የሚሰጡ ስለሆኑ ነው፡፡*

---

[1]ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን፣( ሉሌ መላኩ፣ 1986፣140) ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ይላቸዋል፡፡ (ፈቃዱ ሣህሌ 2008÷8) ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት ‹በሌላ አጠራራቸው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ናቸው› ይሏቸዋል፡፡ ኹሉም የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች በነዚህ ምስጢራት ውስጥ ይካተታሉ፡፡ እኔ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን የሚለውን ተጠቅሜያለሁ፡፡

እንደ (አበራ በቀለ 1996፣240) ገለጻ ደግሞ ‹‹ምሥጢር ማለት በእጅ የማይጨበጥና በዓይን የማይታይ በልብ ብቻ የሚመረመር፤ ተመርምሮም የማይደረስበት በእምነት ብቻ የሚታይ፣ የሚቀበሉት ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ከፍ ያለ ጸጋን የሚያሰጡ ሲሆኑ፤ እንዴት እንደሚያሰጡ ስለማይታዩ ምሥጢራት ተብለዋል››፡፡ በተጨማሪም በዓይናችን ልናያቸው በእጃችን ልንዳስሳቸው የማንችል ልዩ ልዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በእነዚሁ ምሥጢራት አማካይነት ስለሚያድር ምስጢራት ተብለዋል፡፡

በዚህ ጥናት ፎክሎራዊ ገጽታቸውን ለመመርመር የተመረጡት ምሥጢረ ጥምቀትና ምሥጢረ ሜሮን፣ ክርስቲያን ለመሆን ግዴታዎች ሲኾኑ ሌሎቹ አራቱ ምስጢራት ለበቁ ሰዎች ብቻ የሚሰጡ ናቸው በማለት (ክንፈ ገበርኤል 1983፣30)፣ ገልጸዋል፡፡

ጥምቀተ ክርስትና በኢኦተቤ ሰባት ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ከሚባሉት ውስጥ መጀመሪያ ላይ የሚፈጸመው ሥርዓት ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ ከተጠመቀ በኋላ ክርስትና ተነሣ ይባላል፡፡ ክርስትና በምስጢረ ሥጋዌ ለሚያምን ሰው ኹሉ የሚሰጥ የጥምቀት ሥርዓት ነው፡፡ አንድ ሰው መንፈሳዊ ልደትን የሚያገኘው በእምነትና በምሥጢረ ጥምቀት ነው፡፡ ጥምቀት ማለት ከአዳም የተወረሰው ኀጢአትና ሰዎችም የፈጸሙትን በደል ኹሉ ደምስሶ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንደገና እንዲወለዱ የሚያደርግ የመጀመሪያው የጸጋና የእምነት ምሥጢር ነው፤ይህም የሚፈጸመው ካህኑ በጸሎተ ክርስትና መሠረት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በውኃ ባጠመቀው ጊዜ ነው በማለት (አበራ 1996፣ 245)፣ (ያሬድ 2008፣81) አስፍረዋል፡፡

በተጨማሪም ጥምቀት ከሌሎች ምስጢራት ኹሉ ቀዳሚ የኾነበትን ምክንያት በ(ኤፌ.4፣ 5) የተገለጸውን ጥቀስ መነሻ አድርገው ሲያስረዱ የእግዚአብሔር ልጅነት፣ የቤተክርስቲያን አባልነትና የመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ የሚገኘው በምስጢረ ጥምቀት ነው፡፡ ስለኾነም ማናቸውም መንፈሳዊ ሥራዎች ኹሉ በመንፈሳዊ ልደት መጀመር ስላለባቸው ጥምቀተ ክርስትና ቀዳሚ ኾኗል፡፡ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ አንድ ሰውም አንድ ጊዜ ክርስትና ከተነሣና ከተጠመቀ በኋላ ድጋሜ መነሣት የለም ይላሉ፡፡ የክርስቲያን ሃይማኖትን ለሚየምን ሁሉ ለወንዱም ለሴቱም ለትንሹም ሆነ ለትልቁ ካመነ በኋላ ልጅነትን ለማግኘት የክርስትናን ጥምቀት መጠመቅ መጀመሪያ ላይ የሚሰጥ ተገቢው ሥረዓት ነው በማለት (ሀብተ ማርያም፤ 1963 ፣103)፣ (ኃይለ መስቀል 1960፣ 107)፣ (አበራ በቀለ 1996፣246) ገልጸዋል፡፡

ሀብተማርያም ወርቅነህ (1963፣103) እንደገለጹት ጥምቀት ማለት መነከር፤በውኃ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረጉ በአብ በወለወድ በመንፍስ ቅዱስ ስም አዲስ አማኒውን የሚያጠምቁት ጥምቀት፣የሚፈጽሙት ቅዱስ ተግባር ነው። ከውኃ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማለት ከመንፈስ ቀዱስ የሚወለዱት ልደት ጥምቀት ይባላል። (ልዑለ ቃልና ሊቃነ ጳጳሳት 1988፣16-18) ጥምቀተ ክርስትና በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ለሚያምን ሰው ሁሉ የሚሰጥ የኃጢአት መደምሰሻ፣ ከእግዚአብሔር የልጅነት ጸጋ መቀበያና የመንግስተ ሰማያት መውረሻም ነው፤ ምሥጢር መባሉም ካህኑ ለጥምቀት የተመደበውን ጸሎት አድርሶ ሲባርከው ውኃው ተለውጦ ማየ ገቦ ስለሚሆንና ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸጋ ልጅነትን ስለሚያሰጥ ነው፤ በማለት በ(ዮሐ. 19፣ 34-35) ተገለጸውን ሃሰብ ዋቢ አድርገው ገልጸዋል። ።[2]

## ሀ. ጥምቀት በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን የኖኅ መርከብ የጥምቀት ምሳሌ ሆነው ከሚነገሩ ታሪኮች አንዱ ነው። ኖኅና ቤተሰቡ የምእመናን ምሳሌ፣ መርከቢቱ የቤተ ክርስቲያን ውኃው የጥምቀት መሳሌ ናቸው። (ሀብተ ማርያም 1963 ፣105) በ(1ጴጥ 3፣20-21) የሰፈረውን ሃሰብ ዋቢ አድርገው እንስዳረዱት ‹‹ክርስቶስም በሠራት መርከብ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጥምቀት የጸጋ በር ያልገባ ኹሉ በውጪ ስለሚቀር መዳን አይገኝም። በተጨማሪም የእስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ ይመራቸው በነበረው ደመና ሥር መሆናቸውና በቀይ ባሕር ውስጥ ማለፋቸው የጥምቀት ምሳሌ ተደርጎ ተገልጿል ።

እስራኤላውያን የኤርትራን ባሕር ሲሻገሩ እንደተጠመቁ ስለተመሰለ እስራኤል የምእመናን ባሕር የጥምቀት ምሳሌ ነበርና፤እንዲሁም የኖኅ መርከብ በባሕር እየሰፈፈች ኖኅን ከነዘሩ አድናለች፤መርከብ የቤተ ክርስቲያን ባሕር የጥምቀት ኖኅና ቤተሰቡ የምእመናን ምሳሌ ናቸው። ድኅነት በመርከብ እንደተገኘች አሁንም በጥምቀት አማካይነት ድኅነት ይገኛል። በ(መዝ. 114፣5 ‹‹ባሕርኒ ርዕየት ወጎየት ወዮረዳኖስኒ ገባ ድኅሬሁ አድባር አንፈርአጹ ከመ ሀራጊት›› ባሕር ዐየች ሸሸችም፣ ዮረዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ... አንቺ ባሕር የሸሸሽ ዮርዳኖስም ወደ ኋላሽ የተመለስሽ ምን ሆናችኋል..? ምሳሌውም አብርሃም የሰዶምና የገሞራን ነገሥታት ድል ነሥቶ ከመልኬ ጼዴቅ ጋር ሲገናኝ የዮርዳኖስ ተሻግሮ ነበር (ዘፍ› 14 10-16)። አብርሃም

---

[2] ማየ ገቦ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅት ለንጊኖስ የሚባል ሰው ጐኑን በወጋው ጊዜ ከጐኑ የፈሰሰው ውኃ ነው።

የምእመናን፤ ዮርዳኖስ የጥምቀት አምሳል ነበርና። ኢዮብም በታመመ ጊዜ በትእግስት ላይ ትእግስት ሲጨምር አይቶ በዮርዳኖስ ተጠመቅ አለው። እንደትእዛዙም ተጠምቆ ከደዌ ተፈውሷል። ኢዮብም የምእመናን፤ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ አምሳል ነው። ንእማንም ብዙ ከተሰቃየ በኂላ በነቢዩ አማካይነት በዮርዳኖስ ወንዝ ታጥቦ ከደዌው ተፈውሷል ንእማን የምእመናን፣ ለምጽ የፍዳ የመርገም ዮርዳኖስም የጥምቀት ምሳሌ ናቸው (አበራ 1996፣ 146)።

ግዝረት በኦሪቱ በቤተ ክርስቲያን ሲሠራበት ኖሯል። ለአብርሃም የቃል ኪዳን ምልከት ኾኖ በመሰጠቱ በስምንተኛው ቀን ያልተገረዘ ሁሉ ከአብርሃም ቤተሰብ አይቆጠርም ነበር። ምድረ ርስትንም አይወርስም፤ ከተስፋው አይካፈልም፤ የእግዚአብሔር ወገንም አይባልም ነበር። (ዘፍ 17፣7) በሐዲስ ኪዳን ይህ በጥምቀት ተተክቷል ። ግዝረት በብሉይ ኪዳን ለማመን ምልክት ሲሆን፤ በሐዲስ ኪዳን በክርስቶስ ላመኑ ኹሉ መለያ ምልክታቸው ወይም ማኅተማቸው ጥምቀት ነው ሲሉ (ጎረጎርዮስ 1991፣15) ገልጸዋል።

## ለ. ጥምቀት በሐዲስ ኪዳን

በኢኦተቤ እምነት መሠረት ጥምቀትን የጀመረውና ስለጥምቀት ትእዛዝ የሰጠው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንን ሃሳብ  አበራ (1996፣ 109)፣ ሀብተ ማርያም (1963፣104) መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርገው  ሲገልጹ። ‹‹ኢየሱስም መለሰ "እውነት እውነት እላችኂለሁ ማንም ከውኃና ከመንፍስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይገባ ዘንድ አይችልም"። ሲል በ(ዮሐ. 3፣3-7) ራሱ ክርስቶስ አስረደቷል በማለት አስፍረዋል። ሀብተማርያም ወርቅነህ ስለ ጥምቀት ምሥጢርነት ክርስቶስ በቃል ብቻ አላስተማረም ይላሉ፤ራሱ ሠርቶ በማሳየት በሥራም ፈጽመው እንጂ። ሰላሳ ዘመን ሲኾነው በባሕረ ዮርዳኖስ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። በሰላሳ ዘመኑ በዮሐንስ እጅ ይጠመቅ ዘንድ ወደ ዮርዳኖስ ኼደ (1963.104)። በተጨማሪም በ (ማቴ. 3፣13-17)፣ማር1.9-11፣ሉቃ.3፣21፤ ዮሐ.1፣35) ይህ ሃሳብ ሰፍሮ ይገኛል።

ጥምቀት ማለት ዳግመኛ መወለድ ማለት ነው። የአዳም ልጆች ኹሉ ከእናታቸው ከአባታቸው ከተወለዱ በኂላ እንደገና በጥምቀት ከሥላሴ መወለድ ያስፈልጋቸዋል በ (ዮሐ. 5፣3)፣ (ማቴ 28፣19)፣ (ማር 16፣16) "የሰው ልጅ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም››፣ ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ያልተጠመቀ ይፈረድበታል።" ፣ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ኹሉ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፍስ ቅዱስ

ስም አጥምቋቸው›› የሚለውን ጥቅስ መሰረት አድርገው ጥምቀተ ክርስትናን ያዘዘውና ያስተማረው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ‹‹ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ኃጢአታቸውንም ለማስተስረይ በአብና በወልድ መበንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፡፡ በማለት ለሐዋርያት ትዛዝ መስጠቱን (ኃ/መስቀል 1960፤107) ፤(ኪዳነ ማርያም፤ 1957፤36)፤ (ያሬድ 2009፤81) ገልጸዋል፡፡

የዘካርያስ ልጅ ዮሐንስ ለንስሃ የሚያበቃ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ያጠምቅ ነበር፡፡ ኢየሱስም ዮሐንስ ወደሚያጠምቅበት ወደ ዮርዳኖስ በመምጣት ተጠመቀ፡፡ ይህንን ያደረገው ለሰው ልጆች አብነት ለመሆን ነው ሲሉ (ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን 1988÷5) ያስረዳሉ፡፡ ኢየሱስ በውኃ ተጠምቆ ክርስቲያኖችም በውኃ እንዲጠመቁ፣ ወደ ካህኑ ዮሐንስ ኼዶ በመጠመቅ ክርስቲያን የሚሆኑ ኹሉ ወደ ካህናት፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኼደው እንዲጠመቁ ራሱ አብነት ሆኖ ጥምቀትን በውኃ ተጠምቆ ጀመረው በማለት (ፍት ነገ ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 3 ዋቢ አድርገው ገልጸዋል፡፡

(ክንፈ ገብርኤል 1983፣ 30) ስለጥምቀት አመሠራረት ሲያስረዱ ጥመቀት በወንጌል የታዘዘ ከእግዚአብሔርም የምንወለድበት ነው፡፡ ሌሎችን ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ለመሳተፍ የሚቻለው ከጥምቀት በኋላ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዘመኑ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል ስለጥመቀቱም ቀደም ብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትነቢትና ምሳሌ አለ ይኸውም በ(መዝ. 67፤22፡፡ (መዝ. 28፤3)፡፡ (መዝ. 76 ፤16)፡፡ (መዝ. 113፤5-7)፡፡ (1ቆሮ. 10፤2፡፡ ሐዋ 1፤5) ሰፍሮ ይገኛል ይላሉ፡፡

በኢኦተቤ ጥምቀት ለሰዎች የሚያስገኘውን ፋይዳ የተለያዩ ጸሐፊዎች ገልጸዋል ጥምቀት ኃጢአትን መደምሰሻና የጸጋ ልጅንትን ከፈጣሪ የሚገኝበት ነው፡፡ ይህም አስቀድሞ እግዚአብሔር በነቢያት ‹‹የጠራ ውኃ አፈስባችኋለሁ ትጠሩማላችሁ፤ ከርኩሰታችሁም ኹሉ አነጻችኋለው›› አና ‹‹ ‹‹ኃጢአታችንንም ኹሉ ወደ ጥልቅ ባሕር ትጥላልህ›› በማለት በ(ሕዝ. 36፤25)፤ (ሚክ 7፤19) የተገለጸውን ጥቅስ በመጠቆም ጥምቀት ኃጢአትን እንደሚያስተስርይ ገልጸዋል (ኃይለ መስቀል 1960፡ 106)፡፡ (ክንፈ ገብርኤል 1998፤31) እንዳስረዱት ከጥምቀት የሚገኘው ክብር ጥምቀት ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ልደትን ማግኘትና ከኀጢአት መንጻት ነው፡፡ ሰው በጥምቀት ከኀጢአት በመለየቱና በጸጋ በመወለዱ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ይበቃል፡፡

## 2.1.2 የሜሮን ምንነትና አጀማመር

ሜሮን ማለት ቅባት ማለት ነው። ቃሉም የጽርዕ ነው፤ ቅባት፣ ሽቱነትና ዘይትነትን ያላቸው ሰባት ዕፅዋትን በማዋሐድ የሚገኝ ቅባት ነው። ከጥምቀት በኋላ የሚፈጸመውን ምሥጢር የሚያመለክት ነው። በእርሱም አፈጻጸም የእግዚአብሔር ጸጋ እንደተሰጠ ማመሳከር፤ ማረጋገጥ እንደኾነ (ሀብተ ማርያም 1963፤ 110-112) ያስረዳሉ። ትርጉሙም መሙላት፤ማረጋገጥ፤ ክፍት አለመተው ማለት ነው። ሀብተ ማርያም በተጨማሪም ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚጀምረው በጥምቀት ነው፤ ይህም የሰው ልጅ ደግመኛ ከመንፍስ ቅዱስ የሚወለድበት ነው፤ የመንፍስ ቅዱስ ጸጋ እንዳደረበት የሚረጋገጠው ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ሜሮን ሲቀባ እንደኾነ ገልጸዋል። ጥመቀት መወለድ ሲሆን ሜሮን ደግሞ ማደግ መጽናት ቅዱስ መንፈስንም ማግኘት ነው። በጥምቀት የተገኘውን ሀብትና ጸጋ የሚያረጋግጥና የሚያጸና ማኅተም ሜሮን እንደኾነ ያስረዳሉ። ሜሮን ተጠማቂው ከመጠመቂያው ሲወጣ የሚቀባው ቅዱስ ዘይት ነው። በጥምቀት የተገኘውን የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ማረጋገጫ እንደሆኾነና የሚቀባውም ወዲያውኑ ከጥምቀት በኋላ ነው ሲሉ (ልዑለ ቃል፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን 1988፣25) ገልጸዋል። ሜሮን የተቀደሰ ሽቱ፣ ሕፃን የክርስትናው ለትና ታቦት በመባረኪያው ቀን የሚቀባው ባገራችን የወይራ ፍልጥ ዘይት ነው ሲሉ (ደስታ ተክለ ወልድ 1962÷ 1023) አስፍረዋል ።

አበራ፣ ክርስቲያኖች ከአብራከ መንፍስ ቅዱሰ ከማኅጸነ ዮርዳኖስ መወለዳቸው የሚረጋገጠው በሜሮን ነው ይላሉ። ‹‹ሜሮን ማለት ከጥምቀት ጋር ከጥመቀት ቀጥሎ የሚፈጸም መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጥ፣ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችንን፣ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለዳችንን የሚያረጋግጥልን ታላቅ ምስጢር ነው ፤ ይህም ምስጢር አማኞች ከክርሰቶስ ጋር አንድ መሆናቸውንና የመንፈስ ቅዱስ ሕይወትንም መጀመራቸውን የሚያረጋግጥ ቅዱስ ዘይት ነው›› በማለት አስረድተዋል (1996፣248)

(ሐዲስ የሻነው 1988፡16-18) እንደገለጹት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግጋት ውስጥ ቅብዐ ሜሮን ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው የእምነት መሠረት ነው። ቅብዐ-ሜሮን ማለት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የሚረጋገጥበት የምስጢራተ ቤተክርስቲያን መገልገያና ማስፈጸሚያ የሀብተ መንፈስ ቅዱስ መስጫና መቀበያ፤ የልጅነት መታወቂያ ግርማና ማኅተም ማለት ነው። የአንድ ቤተ ክርስቲያን ሉዓላዊነት መግለጫና የክብር ምልክት ሊሆን ይችላል፤ በአጠቃላይ የተቀደሰና የተከበረ ሀብተ ወልድና ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማጽናት የሚሰጥ

ወይም የሚቀባ መንፈሳዊ ኃይል የሚወረስበት ቅብዐት ነው። በተጨማሪም የዚህ ሀብት መሠረቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኾነና የእምነት አንድነትን የሚያጠናክር፣ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የሚያሰጥ ስለኾነ በሱባዔ፣ በጸሎት፣ በእደ ጳጳሳት እንደሚባረክ ገልጸዋል።

በዚህ መሠረት በሕገ ቤተ ክርስቲያን የሀብተ ሜሮን ሚና ቅድስና ከተገለጠባቸው ዋና ዋና ምስጢራት አንዱ በመሆኑ ክብሩ ከፍተኛ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልክ እንደ እህት አብያተ ክርስቲያናት ይህን የተቀደሰ ቅብዐት ለእምነት ማጠናከሪያ በተለያዩ ጉዳዮች እንደ ሁኔታው ትጠቀምበታለች ብለዋል።

## ሀ. የሜሮን አጀማመር በሐዲስ ኪዳን

ሜሮንን የጀመሩት ሐዋርያት እንደኾኑ ልዑለ ቃል፣ ሊቃውንተ ቤተ ክረስቲያን ይገልጻሉ። በሐዋርያት ጊዜ አማኞች ከተጠመቁ በኋላ እጅ በመጫን መንፍስ ቅዱስ ያሳድሩባቸው ነበር (የሐዋ.20፣14-17)። ልዩ ልዩ ተአምራትንም ያደርጉ ነበር (ሉሌ መላኩ፣ 1986፣ 12-13)። ቤተክርስቲያን እየተስፋፋች ስትሔድ እጅ በመጫን ፈንታ በሐዋርያት የተተኩ ኤጲስ ቆጶሳት በቅዱስ ሲኖዶስ ሜሮን እያዘጋጁ ዐዲስ የተጠመቁ ኹሉ እንዲታተሙበት ፈቀዱ (1988፣25)። ሀብተ ማርያም ወርቅነህ(1963፣ 110-113) ይህንን ሐሳብ በተመለከተ የሚከተለውን አስፍረዋል።

> *‹‹ይህም ምስጢር እንደሌሎች ምስጢራት በጽሑፍ ባይገለጥ ግን ኢየሱስ መስርቶታል። ‹እናንተስ ከርሱ የወሰዳችሁት ቅባት በእናንተ፣ ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ኹሉ እንደሚያስተምራችሁ እውነተኛም እንደኾነ ውሸትም እንዳልኾነ እናንተም እንዳስተማራችሁ በርሱ ኑሩ››› (1 ዮሐ.2፣27)።*

ይህ ቅባት የቅዱስ መንፈስ መሰጠትን ማረጋገጥ ነው። ሐዋርያት ካጠመቁ በኋላ እጃቸውን ጭነው ይጸልዩ ነበር። በዚያን ጊዜ ቅዱስ መንፈስ ለተጠማቂዎች ይወርድላቸው ነበር። ወዲያውኑም ሜሮን መቀባት ጀምረዋል። መንፈስ ቅዱስም ለመሰጠቱ ምስክር ኾኗል። ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችውም ከሐዋርያት እንደሆነ ገልጸዋል።

አበራ በቀለ (1996፣ 249) የሜሮንን ሥርዓት የመሠረተው ራሱ ክርስቶስ እንደኾነ ገልጸዋል ። ለሐዋርያት የሚያጽና ወደ እውነት ኹሉ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል ገባላቸው። (ዮሐ. 14፣ 26) በበዓለ ኀምሳ በመንፍስ ቅዱስ አጠመቃቸው (የሐዋ 1፣5

፤2፤1-4) መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ መጽናናትን ኃይልና ብርታትን አገኙ በመንፈስ ቅዱስ ተሞለተው ጸጋን ከተቀበሉ በኋላ ለተሰበሰቡት ሰዎች ኹሉ በየቋንቋቸው ወንጌልን አስተማሩ፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ (1953፤105)፤ (ሐዋ. 2፤37-39)፡፡ ‹‹ ይህንንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት›- ወንድሞች ሆይ! ምን እናድርግ? አሏቸው››፡፡ ጴጥሮስም ንስሐ ግቡ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ትጠመቃላችሁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡ ›› ሐዋርያት በወቀቱ አማኞችን እያጠመቁ መንፈስ ቅዱስን ያሰጡ እንደነበረው ዛሬም ለተጠማቂዎች የሚሰጠው ሜሮን ለሐዋርያት የተሰጠው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንደኾነ ተገልጿል፡፡ ለሐዲስ ኪዳኑ የሜሮን ሥርዓት መነሻው በብሉይ ኪዳን የነበረው ንዋያተ ቅድሳትን  የመቀባት ሕግ እንደነበር (አበራ በቀለ1996፤ 249-250) የሚከተለውን ሃሳብ ገልጸዋል፡፡ ሜሮን የግሪክ ቃል ሲሆን ትረጉሙም ቅባት ማለት ነው፡፡ በተቀደሰው ቅባት የመቀባት ሥርዓት በኦሪት ሕግ የተደነገገ ነው፡፡ ‹‹ካህናቱና የመቅደሱ ንዋያተ ቅድሳት በተቀደሰው ቅባት እንደሚቀቡና፡፡ በዚህም ምክንያት እነርሱም  የተከበሩና የተለዩ እንደሆኑ›› በ( ዘፀ.30፤22-38) ተጽፏል፡፡ ይህም ለሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ለምስጢረ ሜሮንና ለቅባ ቅዱሱ ኹሉ ምሳሌ ኾኗል፡፡ የብሉይ ኪዳኑ የቅባት ሥርዓት ሰዎች ለእግዚኣብሔር የተለዩ ለአገልግሎቱም የተመረጡና የተቀደሱ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ኹሉንም የሚቀድሰው መንፈስ ቅዱስ በሐዲስ ኪዳን ለመሰጠቱም ጭምር ነው ፡፡

ክንፈ ገብርኤል (1983፤ 39) እንዳስረዱት ሜሮን በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ የሚደረግ ሥርዓት ነው ፡፡ በተጨማሪም ለቅዳሴ ቤተክርስቲያን ለአዲስ ቤተ ክርስቲያን ማክበሪያ፤ ለንወያተ ቅዱሳት ማክበሪያም ያገለግላል፡፡ ይህን ሀሳብ ሲያጠናክሩም ‹‹እግዚኣብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው …የወይራ ዘይትም አንድ የዚህን መስፈሪያ ትወስዳለህ በቀማሚም ብልሃት እንደተሠራ ቅመም የተቀደሰ የቅባት ዘይት ታደርገዋለህ የተቀደስ ቅባት ዘይት ይሆናል፡፡ የመገናኛውንም ድንኳን የምስክሩንም ታቦት ገበታውንም ዕቃውንም ሁሉ መቅረዙንም የእጣን መሰዊያውንም ለሚቃጠል መስወዕት የሚሆነውን መሰዊያና ዕቃውንም ሁሉ የመተጠቢያ ስንና መቀመጫውንም ትቀባበታለህ፡፡ ኹሉንም ትቀድሳቸዋለህ፡፡ ቅድሰተ ቅዱሳንም ይሆናሉ››፡፡

### ለ. የሜሮን አጀማመር በብሉይ ኪዳን

ሐዲስ የሻነው (1988፡16-18) በብሉይ ኪዳን አመሰራረት የሜሮንን አጀማመር ሲገልጹ እንዲህ አሥፍረውታል ‹‹ወንጌል በስፋት ከመሰበኩ በፊት ለእስራኤላውያን በሕገ ኦሪት ተደንግጎ የተሰጠና ሲያከብሩት እንደነበረ በ( ዘፀ. 30÷22-26) እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ሕግጋት ውስጥ ቅብዐ-ሜሮን የቅዱሳን ቅዱስ ቅብዐት በሚል ተሰይሞ እናገኘዋለን፡፡ (ዘሌ. 8÷12) ደግሞ ሙሴ በአሮን ላይ ቀብቶት እንደቀደሰው ይናገራል፡፡ ይኸውም የሀብተ መንፈስ ቅዱስ ማሳደሪያ ምሳሌ መሆኑን የሚያመለክት ነው››፡፡

በሣሙኤል ቀዳማዊ (10÷1) ነቢዩ ሳሙኤል ሳዖልን ቀብቶ እንዳነገሠው ይተርካል፡፡ እንዲሁም በዘመነ ሐዲስ ይኸው የቅድስና ምልክት የሆነው ቅዱስ ቅባት ለሐዋርያት በተሰጠው አምላካዊ ስልጣን ኀጢአትን ለማቅለል፣ አጋንንትን ለማውጣት ድውዮችን ለመፈወስ ያገለግላል፡፡ መንፈሳዊ ኃይልና የድኅነት ጉልላት ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ (ማር 6÷13፣ ያዕ. 5÷14)

በጥምቀተ ክርስትና ወቀት ሜሮን የሚቀቡት 36 የአካል ክፍሎች ሲሆኑ፤በ ቅደም ተከተል የሚከተሉት ናቸው፡፡ ግንባሩን ግራና ቀኝ ኹለት ቦታ (1)፣ ሁለቱን አፍንጫውን (1)፣ ኹለቱን ጆሮዎች (2)፣ኹለቱን ዓይኖች (2)፣ አፉን (ኹለቱን ከናፍር (2)፣ የኹለት እጆች መሀል ውስጡንና ውጪውን (4)፣ ደረቱን (1)፣ ልቡን (1)፣ እንብርቱን (1)፣ ጉልበቶቹን (2)፣ ጭኖቹን (2)፣ ብልቶቹን (1)፣ እግሮቹን ውስጣዊና ውጫዊ ክፍሎች (4)፣ የእጆቹን መገናኛዎች (2)፣ ትከሻውን (2)፣ ክርኖቹን (2)፣ አንገቱን (1)፣ ማጅራቱን (1)፣ የእግር መገናኛዎቹን (2)፣ ከመሀል አናት እስከ ወገብ ያለው አካል (1)፣ መሀል ጀርባውን (1) ናቸው (ክንፈ ገብርኤል፣ 1998፣35-36)፣(ፈቃዱ ሣህሌ፣ 2008፣56-58)፡፡

## 2.1.3 የተክሊል ምንነት

የጋብቻ ሥርዓት የሚፈጸምበት፣ ካህናት ሙሽራውንና ሙሽሪቱን አንድ የሚያድረጉበት ትእዛዘ እግዚአብሔርን የሚያጸኑበት ሥርዓት ‹‹ተክሊል›› ይባላል (ክንፈ ገበርኤል፣1983፣29-30)፡፡ ተክሊል የሚለው ቃል ከለለ፣ አከበረ ከሚለው ግስ የተገኘ እንደኾነና፤ ትርጉሙም አከበረ ማለት ነው የሚል ፍቺ ሰጥተውታል፡፡ የተክሊል ሥርዓተ ጸሎት ደግሞ ወንድና ሴት ተስማምተው በሚያደርጉት ጋብቻ ላይ ካህኑ የሚሰራው ሙሽራውና ሙሽሪት አንድ የሚኾኑበት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው፡፡ በተጨማሪም ክርስቲያኖች ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት የሚፈጽሙበት ጸጋ መንፍስ ቅዱስንም የሚያሰጥ ምስጢር ነው፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፣534) እንደገለጹት፣ “ተክሊል በቁሙ፤ የግቢ ሥርፀት ቃል ኪዳን፤ ካህናት በመርዓዊና በመርዓት (ሙሽራውን ሙሽሪት) ላይ የሚፈጽሙት፤ የሕግ ጋብቻ፤ ሊፈርስ የማይችል ነው። ቃል ኪዳኑ ተክሊል ያስኘው የሙሽሮች ልብስ፣ ጌጡ ሽልማቱ፣ ፈርጡ፣ ቀለበቱ፣ ያበባው አክሊል ነው ሲሉ አስፍረዋል ። እንደ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (1957÷51) ገለጻ ተክሊል ማለት ክብር ማለት ነው። ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሴት ልጅ ለአቅመ ሔዋን ከደረሱ በኂላ በቤተ ክርስቲያን በቁርባን የሚፈጸምላቸው የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ነው።

ተክሊል ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዱ ነው። ክርስቲያኖች ጋብቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ስለሚፈጽሙና ጸጋ መንፈስ ቅዱስንም የሚያሰጥ ስለሆነ ከሰባቱ እንደተካተተ (ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን 1988፣ 28-30) ገልጸዋል። ተክሊል ማለት የስምምነት ቃል ኪዳን ሥርዓት ነው። ኹለት ተጋቢዎች በፈቃዳቸው በሕገ ቤተ ክረስቲያን የሚፈጽሙት ፣ጸጋ መንፍስ ቅዱስን የሚያሰጥ ነው ፤ተክሊል በሥጋዊ ጋብቻ ላይ የተመሠረተ አይደለም። ተክሊል ማለት ወንደድና ሴት ተስማምተው በሚያደርጉት ጋብቻ ካህኑ የሚሠራው ጸጋ በረከትን የሚሰጥበት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው። ይህም ምሥጢር በሥጋዊ ጠባይ አስፈላጊነት ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን መንፈሳዊ ዓላማ ያለው ለዘር መብዛት፤ትውልድ ለመተካት፤ ለኑሮ ሕይወት እንዲገኝ ቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃዱ ኾኖ ለሰው ልጅ ያዘዘውና የሰራው ሕግ፣ ያስተማረውም ትምህርት ነው። (ዘፍ 2፣20-25) ሴትና ወንድ አንድ ኾነው መኖር እንዲገባቸው አዳምና ሔዋንን ፈጠረ በማለት ያስረዳሉ። ጋብቻ ዓላማ ያለው እግዚአብሔርም የባረከው የፈቀደው መሆኑ ኢየሱስ መጀመሪያ ተአምር የሠራው ሰርግ ላይ ነው በማለት በ(ዮሐ. 2 ፣1-14) ያለውን ጥቅስ ዋቢ አድርገው (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣1963፣121)፣ (ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣1988፣28-30) ገልጸዋል።

በተጨማሪም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ፈሪሳውያን ስለጋብቻ በጠየቁት ጊዜ ‹‹ጋብቻ ቅዱስ ሥራ ነው እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም ሊለየው አይችልም›› በማለት አስረድቷል። ኹሉም ማግባት እንደሚገባው ፣ጋብቻም ክቡር እንደኾነ ሐዋርያት በጠየቁት ጥያቄ ‹‹…ይህ ነገር ለሰዎች ሁሉ አይቻላቸውም ለተሰጣቸው በቀር ጃንድርባ ኾነው ከናቶቻቸው የተወለዱ ሰዎች አሉና፤ ሌሎችም፤ሰዎች ሰልበው ጃንደረባ ያደረጓቸው አሉ። ማስተዋል የሚችል ግን ያስተውል›› (ማቴ፣ 19 ፣11) ሲል የሰጠው መልስ ያስረዳል። በንጽህና በድንግልና እንዲኖሩ እግዚአብሔር ከፈቀደላቸው ሰዎች በቀር ኹሉ በጋብቻ እንዲኖሩ ጋብቻም የተባረከ እንደኾነ

ይህ ቃል ያስረዳል፡፡ በምስጢረ ተክሊልም እንደሌሎች ምስጢራት የሚታይ መንፈሳዊ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ አለው፡፡ ሙሽሪትና ሙሽራው ነጭ ልብስ ለብሰው አክሊል ተቀዳጅተው፣ ወደውም ለመጋባታቸው ቃል ኪዳን ሲገቡ፣ ካህኑም ሲባርካቸው፤ ሲጸልይላቸው፣ ቅዱስ ዘይቱን ሲቀባቸው ይታያል፡፡ ይህ የሚታይ መንፈሳዊ አገልግሎት ይባላል፤ በሚታየው አገልግሎት የማይታየውን ጸጋም ያገኛሉ (ሀብተ ማርያም ወርቅነህ፣ 1963፣99-121)፡፡

ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ማን መሠረታቸው? ምስጢራተ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ መሥራችነት የተመሰረቱ በርሱም አማካይነት ጸጋውን ጽድቁንም የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ለዚህም አስረጂ ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ያስረዳል፤ ‹‹ ከምላቱም እኛ ሁላችን ወሰድን ጸጋም በጸጋ ፈንታ አሪትም በሙሴ ተሰጥቶናል፤ ጸጋ ግን እውነትም በኢየሱስ ክርስቶስ ኾነን›› (ዮሐ፣16.17)፡፡ ምስጢራቱ ምንጫቸው ክርስቶስ በዕለተ አርብ ያደረገው የማዳን ሥራ ነው፡፡ ይህም ያለማቋረጥ እስከ ዓለም ኅልፈት እየቀጠለ የሚኼድባቸው፣ ኃይሉ የሚታይባቸው፣ ሥልጣኑ የሚታወቅባቸው፣ የማንጻትና የማጽናት ሥራውም የሚቀጥልባቸው፣ ታላቅ ምስጢሮች ናቸው ይላሉ፡፡ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ካህኑ የማንጻት ተግባሩን የሚፈጽምባቸው፣ የእግዚአብሔን ጸጋና ሀብት ልጅነትንም የሚያስተላልፍባቸው፣ ጸጋውን የሚገለጥባቸው ናቸው ሲሉ (ሀብተማርያም፣ 1963፣ 99) ገልጸዋል፡፡

### 2.1.4 ሥርዓተ ከበራ (ክብረ በዓል)

ሥርዓተ ከበራ ማኅበረሰቦች (ቡድኖች) ክብረ በዓል አዘጋጅተው በተደጋጋሚ የሚከውኗቸው የባህልና የእምነት እሴቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሥርዓተ ከበራዎች (Rituals) ልማዶችን፣ ለባህሉ ባለቤቶችና ከባህሉ ውጪ ላለው ማኅበረሰብ ወይም ቡድን እንዲገለጹ ወይም እንዲታዩ ያደርጋሉ፡፡ ሥርዓተ ከበራዎች የሚጀመሩበትና የሚያልቁበት፣ መጀመሪያና መጨረሻ የራሳቸው ቅርጽና መዋቅር አላቸው፡፡ አብዛኞቹ ክብረ በዓላት በከፍተኛ ደረጃ የሚዘጋጁ፣ የአንድን ቡድን አባላት ለሚያስተዋውቁ ትዕምርታዊ ድርጊቶችን የሚይዙ ናቸው፡፡ ከበራዎች የአንድን ቡድን ልማዳዊ ሀሳቦች፣ እሴትና እምነቶች ያሳያሉ (Sims and Stephens, 2005፡ 94-95)::

ሥርዓተ ከበራን ልዩ የሚያደርጉት የተለያዩ ባሕርያት ትዕምርቶችን ይሁን እነርሱም በቃል የሚከወኑ ቃል ግጥሞች/ዜማዎች/ እንጉርጉሮዎች፣ ጭፈራዎችን የሚይዝ ነው፡፡ የተለያዩ ቃላ

ዊና ቁሳዊ ፎክሎሮችን (አለባበሶች፣ ምግቦች፣ ቁሳቁሶች) ይይዛል፡፡ (Sims and Stephens,200 95-97} በሥርዓተ ተክሊል ወቅት ክዋኔው ሲጀመር ካህኑ የእንጨት መስቀል ይይዛል፤ ዲያቆኑ የእንጨት መያዣ ያለው ( መያዣው መጸር ይባላል) የብረት መስቀል ይይዛል፤ የሥርዓተ ተክሊሉን ጸሎት ሲያደርግ መብራት ቢኖርም ጧፍ በቀኝ እጁ ይይዛል ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ ይጸልያል፤ ሙሽሮች ፊታቸው ወደ ምሥራቅ ነው እነዚህ የራሳቸው ትዕምርት /Markers/ አላቸው(ክንፈ ገብርኤል አልታዬ 1983፣ 29-30)፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን 1988፣ 29)፣ (ፍት ነገ.ፍት.መን.1958፣ አን. 24 ሐምስ ክፍል) ምልከታ 28/08/2010 ዓ.ም፡፡

በሥርዓተ ከበራ የተለያዩ መብራቶች ይይዛሉ፣ ከዘወትሩ ልዩ የሆኑ ምግቦች ይዘጋጃሉ፡፡ ይህ ሌላኛው ባህርይ ነው፡፡ በክርስትና ክብረ በዓልና በተክሊል የሰርግ ሥርዓት፣ ሙሽሮች ጧፍ፣ ሻማ መብራቶችን ይይዛሉ፡፡ ምግቦችና መጠጦች በርከት ብለው በልዩ ሁኔታ ይዘጋጃሉ፡፡ የሰርጉ ታዳሚዎች፣እንዲሁም በክርስትና የክርስትና አቋቋሚነትና ለዝግጅቱ የተጠሩ ሰዎች የተዘጋጀውን ልዩ ምግብ በጋራ አብረው ይመገባሉ፡፡( ምልከታ 12/06/2010 ዓ.ም)፡፡

ሌላኛው ሥርዓተ ከበራ ልዩ የሚያደርገው ባህርይ አለባበስ ነው፡፡ በዝግጅቱ የሚገኙ ታዳሚዎች ያሸበረቁ ልብሶችን ይለብሳሉ፡፡ ልብሶቹ ዘወትር ከሚለበሱት የተለዩ ናቸው፡፡ በክርስትና ወላጆችና ክርስትና የሚነሡ ሕፃናት ነጭ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ አብዛኞቹ አጃቢዎችም ነጭ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ የተክሊል ልብስም የተለየ ነው ሙሽሮች፣ ሚዜዎቻቸው፣ሰርገኞች መዘምራን፣ ቤተሰቦች የየራሳቸው ልዩ አለባበስ አላቸው፡፡

ሥርዓተ ከበራውን ልዩ የሚያደርጉት የተለየ ክብር ያላቸው ቁሳቁሶች ይይዛሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉት መሪዎች ናቸው፡፡ ከተለመደው በተለየ ሁኔታ የጸጉር አሰራሮች ይታያሉ፡፡ ተክሊል የሚያደርገው ሙሽራ ዲያቆን ከሾነ መስቀል ይይዛል፡፡ ቁሳቁሶችን የሚያቀርቧቸው በዕለቱ የተሰየሙት ካህናትና ዲያቆናት ናቸው፡፡ (ምልከታ 28/08/2010 ዓ.ም)፣ (ምልከታ 12/06/2010 ዓ.ም)፡፡

እነዚህ የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎች ሥርዓተ ከበራውን ክብደት እንዲኖረው፣ የተለየና እውነተኛ ስሜት እንዲፈጠር ያደርጉታል። እያንዳንዱ የሚይዟቸው ጥቃቅን ቁሶች ተሳታፊዎችን በሥርዓተ ከበራው እንዲታደሙና እንዲጠቃለሉ ያደርጋቸዋል፤ ለቡድኑም መገለጫ ጠቋሚዎች ናቸው (Sims and Stephens 2005: 97)::

## 2.2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ

### 2.2.1. ክዋኔ

የክዋኔ ጥናት መታየት የጀመረው በሥነ ሰብ አጥኚዎች በ1970ዎቹ እንደነበር (Kapchan 1995:479) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህም አህዛዊ በሆነ ሂደት ሲጠኑ የነበሩ ናቸው፡፡ ይህም በፎክሎርና የሥነ ልሳን ምሁራን ጠቃሚ የሆነ ለውጥ አሳይቷል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ (Dell Hymes)፣ (Joel Sherzer)፣ (Dan Ben Amos 1972)፣ (Roger Abrahams 1977) እና (Richard Bauman) በጊዜው የራሳቸውን ፍላጎት አስተላልፈው መሰረት ጥለዋል፡፡ በወቅቱ አውድን መሠረት በማድረግ ብያኔን መስጠት በዘመኑ የነበሩትን ምሑራን ከአንድ ዘውግ አትኩሮት ወደ ባህልን መሠረት ያደረገ ብያኔ እንዲዞሩ አድርጓቸዋል ይላሉ፡፡

ክዋኔ ጥበባዊ ተግባር ነው፡፡ የአከዋወን ሥርዓቱ፣ ድግግሞሽ ያለው፣ የአነጋገር ይዘትንና አካለዊ እንቅስቃሴን በጋራ የሚይዝ፣ በቦታና በጊዜ ተወሰነ፣ በከዋኞች የሚቀርብና በግል ወይም በቡድን ሊዋቀር የሚችል የማንነት ማሳያ ነው ሲሉ (Kapchan, 1995:479)፣ (Richard Bauman, 1984: 3) ያስረዳሉ:: በተጨማሪም ክዋኔ ውስብስብ የሆኑ የዕለት ተዕለት ተግባራትን ውበትን በተላበሰ መልኩና ሥርዓቱን በጠበቀ መለኩ አንድን ጉዳይ የሚያንጸባርቁበት አውድ ነው በማለት አስፍረዋል፡፡ (Richard Bauman, 1992: 41) እንዳስረዱት ክዋኔ ውበትን መሠረት ያደረገ የተግባቦት ዘውግ በመሆኑ ለዛ ባለው መልኩ ለአድማጭና ተመልካች ማድረስን ዓላማ አለው፡፡ ስለሆነም የክዋኔ ትንተና የአንድን ማኅበረሰብ ባህልና የተግባቦት ጥበብን ማዕከል ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የክዋኔን ጥበባዊ ተግባራት፣ ባህልና ታሪካዊ አወድ (ጊዜና ቦታ) በጥልቀት በመመልከት የክዋኔ ጥናት ማሳለጥ ይቻላል ይላሉ፡፡

ክዋኔ ጥበባዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡ የፎክሎር አጥኚ የከዋኙንና የአድማጩን መስተጋብር በሚገባ በማጤን የክዋኔን ጥበባዊ ተግባራት እንዲመለከት ይረዳዋል፡፡

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በአንድ በተወሰነ አውድ ወይም ቡድን ውስጥ ያለውን ጥበባዊ ገለጻ ለማጥናት የሚያስችል፣ የፎክሎርን የጥናት መስክ የሚመራ ቁልፍ ነገር ነው፡፡ ለፎክሎር ተመራማሪ ክዋኔንን መመልከት ማለት የሰዎችን የፈጠራ ችሎታ፣ የፎክሎርን ተስተላልፎ ከድርሰቱ ጋር በማገናኘት ጥናቱን ለማስፋት ይረዳዋል ሲሉ (Sims and Stephens, 2005:26-27) አስረድተዋል፡፡

Sims and Stephens, (2005: 27) የአንድ ፎክሎር ጥበባዊ ተግባራት ከትውልድ ወደ ትውልደ እንዲተላለፍ ክዋኔ ወሳኝነት እንዳለው፤የፎክሎር አጥኚም አንድን ፎክሎር ሲከወን መመልከቱ የሚከወነውን ጉዳይ፣ የከዋኙንና የአድማጩን ግንኙነት፣ የመከወኛ አጋጣሚውንና መቼቱን በሚገባ ለመገንዘብ እንደሚረዳው ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌ በዚህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በክርስትና ሥርዓት ወቅት የክርስትና አስነሺዎች፣ ክርስትና አንሺዎች አቋቋሚዎች በጋራ በቤተ ክርስቲያን ይገናኛሉ፡፡ የክርስትናውን ሥርዓተ ክዋኔ ለማካሄድ የእምነት መሪዎቹ በሚያዟቸው የክርስትና ማንሻ ቦታ በየሥፍራቸው ይቀመጣሉ፡፡ እንዲሁም በሥርዓተ ተክሊል ወቅት ሙሽሮች፣ ሚዜዎች፣ ወላጆች አጃቢዎች ሌሊት ቤተ ክርስቲያን ይገኛሉ፡፡ የሥርዓቱ መሪዎች ባዘጋጁላቸው ከመቅደሱ ፊት ለፊት በሚገኘው ሥፍራ ሙሽሮች ይቀመጣሉ፡፡ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሲገቡ ሙሽሮች ከነአጃቢዎቻቸው ሁሉም ጧፍ እያበሩ ይገባሉ፡፡ ይህም አንዱ የክዋኔው ሂደት ነው፡፡ እነዚህንና የእያንዳንዱን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለማሳየት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በዚህ ጥናት ተግባር ላይ ውሏል፡፡

ክዋኔ ለፎክሎር አጥኚ በተወሰነ አውድና ቡድን ውስጥ የከዋኝና የታዳሚን ጥበባዊ ገለጻዎች፣ ያላቸውን የጋራ መስተጋብር፣ የሰዎችን የፈጠራ ችሎታና የፎክሎሩን ተስተላልፎ ከድርሰቱ ጋራ በማገናኘነት ለማጥናት ያስችለዋል፡፡ ክዋኔ አንዱ ከሌላው ልዩነት የሚያሳይበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉት፡፡ እነዚህም የከዋኙ የመከወን ብቃትና ዕድሜ፣ የክዋኔው መቼት፣ የመከወኛ አጋጣሚው ባህርይና ሁኔታ ለምሳሌ ሠርግና ምላሽ፣ ሞት፣ሃይማኖታዊ፣ ወይም የአንድ የተወሰነ ጎሳ መኾን፣ ክዋኔው የሙዚቃ መሣሪያ የሚያስፈልገው ከኾነ በተለይም ከዋኙ ሊይዘው የሚችለው ከኾነ፣ የቡድን ወይም የተናጠል ክዋኔ መኾኑ አንዱ ከሌላው የሚኖረውን ልዩነትና ባህርይ የሚያሳዩ ናቸው በማለት (Okepwho, 1992:42) አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ ክርስትና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው፡፡ ሃይማኖታዊው መሠረት አድርገው በቤት ውስጥ የሚከናውኑት ልማዳዊ ተግባራት ልዩነት ያሳያሉ፡፡ በሃይማኖቱ ሥፍራ የክርስትናው ሥርዓት በቅደም ተከተል ይከናወናል፡፡ ሥርዓተ ጸሎት አለ፤ ጥምቀት ይከናወናል፤ ሜሮን ይቀባል፤ማተብ ይታሰራል፡፡ ቤት ሲገባ እንጀራ ላይ ይንከባለላል፡፡ እንጀራ ላይ ማንከባለሉ ሃይማኖታዊ ሰነዶች ላይ አልተመለከትኩም በምልከታዬ ግን ሲከወን ተመልክቻለሁ፡፡ የእነዚህ የሚያሳዩት ልዩነት አለ ሃይማኖታዊና ልማዳዊ ድርጊቶች ተሳስረው ይታያሉ፤ የነዚህም ልዩነቶች በትንታኔው አገልግሎታቸውና ተምሳሌትነታቸው ተገልጿል፡፡

(Sims and Stephens, 2005:128-129) እንዳስረዱት ክዋኔ ገላጭ ድርጊት ነው። ክዋኔ የሰመረ የሚሆነው የተመቸ ጊዜና ቦታ፣ ከዋኝ፣ በንቃት የሚሳተፍ ታዳሚዎች ሲኖሩ ነው። ለምሳሌ ክርስትና ለመነሣት ወይም ሥርዓተ ተክሊል ለማካሄድ የታወቀ ቦታ አለው። ታዳሚዎችና ሥርዓቱን የሚፈጽሙ ካህናት ከዋኞች አሉ። በሥርዓቱ የሚሳተፉ አጃቢዎች፣ አቋቋሚዎችና ቤተሰቦች ይገኛሉ። እነዚህም በአንድ ላይ  በተገኙበት በቤተ ክርስቲያን የክርስትናና ተክሊል ሥርዓቱ ይፈጸማል።

የከዋኙ ኃላፊነት ልክ፣ የአድማጭ ወይም ታዳሚ አረዳድ፣ ለክዋኔው የሚሰጠው ግምትና ልኬት ክዋኔውን ይወስናወል ሲሉ (Bauman, 1992፣ 44) ያስረዳሉ። የክዋኔ አግባብነት የሚለካው የከዋኞችን ብቃትና ችሎታ መሠረት በማድረግ ነው። የከዋኞች የአቀራረብ ጥበባቸውና ልምዳቸው ለክዋኔ መሳካት አስፈላጊ ነው። የቡድኑ አባላት ለክዋኔው ምላሽ ለመስጠትና ለመተርጎም ይሞክራሉ። ነገር ግን ክዋኔውን መረዳትና መተርጎም ካልቻሉና ተሳትፎ ከሌላቸው ክዋኔው በትክክል ተገልጿል ለማለት አያስደፍርም። በመሆኑም ክዋኔ ተካሄደ የምንለው በሚገባ የተዋቀረ መቼት፣ ልምድ ያለው ከዋኝና ተሳታፊዎች፣ የሚቀርበው ጉዳይ በቅደም ተከተል ተደራጅተው ሲኖሩ ነው። ለምሳሌ በሥርዓተ ተክሊል ሰርግ ሙሽሮች ቤተ ክርሰቲያን ይገኛሉ። በካህኑ መሪነት ሥርዓቱን ይፈጽማሉ ሙሽሮች፣ታዳሚዎች ካህናቱ በቅደም ተከተል የድረሻቸውን ይወጣሉ። የቤተ ክርስቲያኑን ክዋኔ ጨርሰው ሲወጡ ሙሽራውን የሚያጅቡ መዘምራን አሉ፤ መዝሙሩን የሚያቀርቡ በእልልታና በጭብጨባ የሚያጅቡ፣ እንደ ከበሮ ጸናጽል ወዘተ ቁሶች በመያዝ የሚያደምቁ አሉ። የእነዚህ የጋራ ጥምረት የሰርጉን ሥርዓተ ክዋኔ የተሳካ ያደርገዋል።

"የክዋኔ መሠረቱ አውድ ነው" ሲሉ ፤(Debarah, 1995:449) ገልጸዋል። ስለዚህ አንዱን ክዋኔ ከነ ሙሉ አውዱ ለማጥናት ደግሞ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ነው። የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ክዋኔዎች ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ለማሰየት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ የሆነውም ለዚህ ነው። የዚህን ጥናት ሥርዓተ ክዋኔዎች ድርሰት በክዋኔው ውስጥ ያሉትን ተግባራት የሚገልጽ ነው።

በ19ኛው እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ የፎክሎር ሊቃውንት ትኩረት ከክዋኔው ይልቅ የክዋኔ ውጤት ላይ ነበር። የክዋኔን ጥናት ከፎክሎር ጥናት አንጻር እንዲጠና በማድረግ ጠንካራ መሠረት ጥለዋል። Bauman ምሁራንን ከተለያዩ የጥናት መስኮች እንደ ሥነ ልሳን፣ ሥነ ሰብና የፎክሎር አጥኚዎች ሰብስቦ አዲስ አንድነትን በመፍጠር በቃላዊ ጥበብ ውስጥ

የክዋኔን ጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ እንዲያድግ ጥረት አድርገዋል (Sims and Stephen 2005:133)፡፡

(Kapchan 1995:479) Abrahamsን ጠቅሰው እንደገለጹት መከወን ማለት ከተለያዩ አውዶች አንጻር አንድን ነገር ወደ ውጤት ማምጣት ወይም ድርጊትን መሠረት ማድረግን ያመለክታል፡፡ ማንኛውም ታሪክ፣ ማንነት፣ ጥንታዊ በእጅ የተሠሩ መሣሪያዎች (Artistic artifacts)፣ ታሪካዊ ትውስታዎች፣ ስነ ሰብ ጥናትን የበለጠ የምናውቃቸው፣ በሚገባ ልንረዳቸው የምንችለው በክዋኔ ነው፡፡ ክወኔን ለማጥናት ይክዋኔውን ሂደት በመጠየቅ የክስተቱን አተገባበር መሠረት መድረግ ተገቢ ነው (Abrahams, 1977)፡፡ አንድ ፎክሎርኛ ማንኛውም በክዋኔ ወቅት የሚካሄዱ ነገሮችን እንዲያውቅ፣ እንዲገነዘብ ያደርገዋል፡፡ የክዋኔውን ቅርጽ የሚያሲይዙ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ለምን ተከወነ ወይም ለምን በዚህ ጊዜና ቦታ ተከወነ የሚሉት ናቸው፡፡

## 2.2.2 አውድ

አውድ አንድ የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት የሚኖረውን አጠቃላይ የኾነ ድባብ የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም ክዋኔው የሚካሄድበትን ቦታና ጊዜ፣ የክዋኔው ድርጊቶች፣ የአድማጮች የታዳሚና የከዋኝ መስተጋብር የሚይዝ ነው፡፡ የትኛውንም የፎክሎር ቴክስት እና ክዋኔ ጠቅልሎ የሚይዝ ነው (Sims and Stephens, 2005:137)::

እንደ (Huford 1995:531) ገለጻ ደግሞ አውድ ለክዋኔ ጥናት መሠረታዊ የመነሻ ሀሳብ ነው፡፡ አውድ (Context) "Contexere" ከሚለው የላቲን ቃል የመጣ ነው፡፡ ትርጉሙም በአንድነት መተሳሰርን፣ መቆራኘትን፣ መገናኘትንና በጋራ ሆኖ መድረስን ለማመልከት ነው፡፡

ማንኛውም ክዋኔ አውድና መቼትን መሠረት በማድረግ አውዱን መሠረት ባደረገበት ማኅበረሰብ ውስጥ ትርጉም ያለው መልዕክት ያስተላፋል (Bauman, 1992፣45)፡፡ ቦወማን ሲንገርን ወቢ አድረገው እንደገለጹት፣ ‹አሜሪካዊውን የስነ ሰብ ምሁር Milton Singer ሲናገሩ ከአንድ ማኅበረሰብ ባህል ክዋኔውን ከአውድ ጋራ አያይዞ ማየት ተገቢ እንደኾነና እንደመስፈርትም መውሰድ እንደሚገባ ያስገነዝባል›፡፡ ስለዚህ የአንድን ማኅበረሰብ ክዋኔ ከነአወዱ ማጥናት ሚናው የላቀ ነው ይላሉ (Bauman, 1992, 46)፡፡ አንድን ክዋኔ ከነአውዱ ለማጥናት መርሐ ግብር መቅረጽን የሚሹ ናቸው፡፡ እያንዳንዱን ተግባር ከጊዜ አንጻር ማዘጋጀት ግድ ይላል፡፡ ክዋኔው የሚጀመርበትንና የሚፈጸምበትን ጊዜ መወሰን፤ የሚከወንበትን ቦታ ከተለያዩ አውዶች

አንጻር (ከትያትር፣ ከፌስቲቫልና ሃይማኖታዊ) አውዶችን ይመለከታል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ክዋኔዎች በወቅትና በመከወኛ ቦታ የተወሰኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጅማሬና መጨረሻቸው ቀድሞ የተበየነ ነው፡፡ ስለዚህ ቀደም ብሎ መዘጋጀትን ይሻሉ፡፡

አውድን ምሁራን በተለያየ መንገድ በይነውታል፡፡ Dundes (1964) አውድ ክዋኔ የሚደረግበት የሚታይ መቼት ነው ሲሉት፡፡ እንደ (Dell Hymes, 1974፡55) ገለጻ ደግሞ አውድ በማኅበራዊና ስነ ልቦናዊ ክዋኔዎች ውስጥ የሚኖርን አጠቃላይ ድባብ የሚገልጽ ነው፡፡ እነርሱም ተጨባጭ በሆነ መቼት ውስጥ የሚደረጉ ተግባቦታዊ ድርጊቶች ናቸው ፡፡

አውድ በሥነ ልቦናዊ እና ማኅበራዊ ድባብ ውስጥ በክዋኔ የተደገፉ ተግባራትን የሚገልጽ ነው፡፡ እነዚህም ተጨባጭ በሆነ አውድ ውስጥ የሚደረጉ ተግባቦታዊ ድርጊቶች ናቸው፡፡ Dan Ben-Amos ኹለት አይነት አውድ እንዳሉ ገልጸዋል፡፡ እነርሱም የሁኔታ አውድ እና የባህላዊ አውድ ናቸው፡፡ የሁኔታ አውድ ጠባቡና በአብዛኛው ቀጥተኛ የሆነ የፎክሎር አውድ ሲሆን፤ ይህም ክዋኔ የሚፈጸምበትን የተወሰነ ጊዜና ቦታ እንዲሁም የሚፈጸመውን ጉዳይ አጠቃላይ ድባብ የሚገልጽ ነው (Ben- Amos 1993, 216)::

ሁለተኛው የባህል አውድ ሰፊና ሁሉንም አውዶች የሚይዝ ነው፡፡ ይህ አውድ የተናጋሪውን የዕውቀት ተስተላልፎ የእምነት ስልት /Belief Systems/፣ የንግግር ውጤት፣ የቋንቋ አጠቃቀም የንግግር አይነት፣ የታሪክ ግንዛቤ፣ ሥነ ምግባርና ስብዕና የሚያካትት እንደሆነ (Ben Amos 1993:215-216) ገልጸዋል፡፡

የBen Amos ሰፊና ጠባብ የአውድ ገለጻ አንዱ በአንዱ ውስጥ የሚገለጽበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ክዋኔው የሚካሄድበትን ቦታ፣ ድርጊቶች፣ ክዋኔው በሚካሄድበት ወቅት ያለውን የቡድን አባላትና የከዋኙን ግንኙነት፣ በሚተረከው ወይም በሚከወነው ድርሰት (ቴክስት) ውስጥ ያለውን ሁኔታ የሚያጠቃልል ነው፡፡

(Sims and Stephens 2005:138-39) አውድን ስናነሳ መነሳት ያለባቸው ነገሮች፣ ክዋኔው ከመካሄዱ በፊት ምን ዕውቀት ነበረን? ከተከናወነ በኋላ ምን ተማርን? የሚሉ ነጥቦችን ገልጸው አውድን ተጨባጭ አውድና ማኅበራዊ አውድ በማለት በኹለት ከፍለውታል፡፡

ይህ ሰፊ የሆነ የክዋኔ አውድ የሚከተሉትን ነገሮች ያካትታል ቡድን፣ ማኅበረሰብ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ መገለጫ የሆነ ባህል የቤተሰብ ሁኔታ፣ ቤተሰብ ራሱ፣ የቤተሰቡ ውስጥ ያለው

መስተጋብር ለምሳሌ የጎሳው ዳራ፣ እምነት፣ ቦታዎች፣ የአካባቢ ግንኙነቶች፣ ባህሎች በአጠቃላይ የማኅበራዊ ክዋኔው ከዋኝ፣ ታዳሚው፣ መቼቱ በክዋኔው ወቅት የሚኖረውን አጠቃላይ ድባብ የሚመለከት ነው፡፡

### ሀ. ተጨባጭ አውድ /Physical Context/

ይህ አውድ የክዋኔውን ድርጊቶች በመመልከት አጠቃላይ ተጨባጭ ሁኔታውን ለመግለጽ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ክዋኔው የት ይካሄዳል የሚለውን ለማወቅ የሚረዳ ነው፡፡ የክዋኔው መቼት፣ የከዋኙ አድማጩ፣ ታዳሚዎች፣ ማንኛውም ተመልካች ፎክሎርኛውን ጨምሮ አጠቃላይ ድባቡን ለመግለጽ የሚቻልበት አውድ ነው፡፡

### ለ. ማህበራዊ አውድ /Social Context/

ይህ አውድ ሰፊ የሆነ የክዋኔ አላባ ነው፡፡ ይህም ከማኅበረሰብ፣ ከቡድንና የማኅበረሰቡ መገለጫ ከኾነው ባህል ጋር የሚገናኝ ነው፡፡ የቤተሰብ ሁኔታን ብንመለከት ለምሳሌ ቤተሰብ ራሱና በቤተሰቡ መካከል ያለው መስተጋብር የዚህ ሰፊ የሆነ ማኅበራዊ አውድ አካል ናቸው፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚኖር የድርጊቶችን መዋቅር ያሳያል፡፡ በከዋኙና በታዳሚው ማንነት (የጎሳው ዳራ፣ እምነት፣ ይዞታዎች፣ የአካባቢ ግንኙነቶች) እንዲሁም በመቼቱ ሁኔታ የሚፈጠረውን አጠቃላይ ማኅበራዊ አውድ የሚመለከት ነው፡፡ ወይም በክዋኔው ወቅት የሚኖሩ ድርጊቶችን አጠቃላይ ማኅበራዊ መዋቅር የሚመለከት አውድ ነው፡፡

## 2.3 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የተገናኙ የመጀመሪያና የሦስተኛ ድግሪ ጥናቶችን አላገኘሁም፡፡ ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ዲግሪ የቀረቡ፣ ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ለመደሳስ ተሞክሯል፡፡ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በፍሬሕይወት ባዩ (2000 ዓ.ም) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት በሚል ቀርቧል፡፡

ጥናቱ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮችን እንደተመለከተ መረዳት ይቻላል፡፡ የንዋያተ ቅድሳቱን ሃይማኖታዊ ገጽታ ማሳየትና የንዋያተ ቅድሳቱን ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት ናቸው፡፡ ፍሬ ሕይወት ለጥናቷ

ይዛ የተነሳችውን ዓላማ ከግብ ማድረሷን የሚያሳዩ ነጥቦች አሉ፡፡ በትንታኔዋ የንዋየ ቅዱሳት ሃይማኖታዊ ገጽታ በሚለው ርዕስ ውስጥ ስለ ንዋያተ ቅድሳት ምንነት፣ አሠራርና አገልግሎት አቅርባለች፡፡ በዚህም ንዋያተ ቅድሳት ከሌሎች መሰል ዕቃዎች በምን እንደሚለይ የሚሠሩት ጥሬ ዕቃና አሠራር፣ ምሳሌነታቸው ከመቼ ጀምሮ መሠረት እንደጀመሩና አሁን ያሉበትን ሁኔታ ገልጻለች፡፡

እነዚህ ንዋያተ ቅዱሳት የሚሠሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በመያዝና ቤተ ክርስቲያኗ በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ሕግ ደንግጋ በማስቀመጥ፣ በየጊዜው በየአብያተ ክርስቲያናቷ ለሚሠሩትም በታዘዘው መሠረት እንደሚሠሩና አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ፤ በአገልግሎት ወቅትም ማን? መቼ እና እንዴት መገልገል እንዳለበት በዝርዝር ሕግና ምሳሌያቸውንም በቀኖና ደንግጋ እንዳስቀመጠች ገልጻለች፡፡

በምዕራፍ አምስት የንዋያተ ቅድሳት ቁሳዊ ባህል በሚለው ውስጥ ሀገረሰባዊ እጅ ሥራ፣ ሀገረሰባዊ ሥዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና እና ሀገረሰባዊ ልብስ በማለት የንዋያተ ቅድሳትን ፎክሎራዊ ገጽታ አሳይታለች፡፡ በጥናቷ በተመለከተችው ቁሶች ውስጥ ቀደም የማይታወቁ በአማንያኑ ዘንድ ግን እየተዘወተሩ የመጡ ንዋያተ ቅድሳት እንዳሉ ገልጻ ቁስ መሆናቸው፣ ሀገረሰባዊ መንገድ ተከትለው መሠራታቸው፣ ከቁሳዊ ባህል፣ ከሃይማኖቱ ህግ ውጪ በልማድ ብቻ የሚሰሩ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ (በቅዳሴ)ና በዓመታዊ በዓላት የሚደረጉ ሥርዓቶች ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ እንዲሁ በየጊዜው የሚፈጠሩትን ጨምሮ በፎክሎራዊ ገጽታቸው እንደሚታዩ ገልጻለች፡፡

መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሰነድ ምርመራ፣ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ተግባር ላይ እንደዋለች ገልጻለች፡፡ የንዋያተ ቅድሳትን ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታቸውን ለመመርመር አሳሽና ገላጭ ዘዴዎችን ተጠቅማለች፡፡ የቤተ ክርስቲያኗ ደግሞና ቀኖና ሥርዓትና ትውፊቷ ወጥ ቢሆንም ለጥናቴ ትንተና አመቺነትና የተለየ ፎክሎራዊ ገጽታ አገኛለሁ በሚል አራት አብያተ ክርስቲያናትን ከሁለት ሀገረ ስብከቶች መርጣለች፡፡

ፍሬሕይወት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ለመመርመር ከተጠቀመችው ስልቶች ውስጥ ገላጭ ዜዴን መጠቀሟና ጥናቱ የመስክ መረጃ ላይ መደገፍ የጥናት ቦታ አመራረጥ ዘዴዋ ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ እንዲሁም ሀገረሰባዊ መንገድ ተከትለው ከተሠሩ ቁሳዊ ባህሎች ውስጥ ልብሰ ተክህኖን ተመልክታለች የእኔም ጥናት በክርስትና በተክሊል ወቅት

የሚለበሱ አልባሳትን በቁሳዊ ባህል ውስጥ የተመለከተ ስለሆነና በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በተክሊል ወቅት የተለበሱ የካህትና የመዘምራንን አልባሳት ስለተመለከተ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ፍሬሕይወት ጥናቷን ስታካሂድ የጠቀሳቸውም ኾነ የተጠቀመችው የቲዎሪ አቅጣጫ የለም የእኔ ጥናት የክዋኔ ቲዎሪን አቅጣጫ ስለተጠቀመና በእርሷ ርዕሰ ጉዳይ የሌሉ ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን ስለሚመለከት የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሊያ መዘግቡ "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓት ክዋኔ" በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለMA ዲግሪ ማሟያ አቅርባለች፡፡ ይህ ጥናት ይዞ የተነሳው ዓላማ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ የኾነውን ሃገረሰባዊ ልማድ ማሣየት ነው፡፡ በሥሩም ሥምንት ዝርዝር ዓላማዎችን ይዟል፡፡

ሊያ የክህነት አሠጣጡን፣ ሥርዓቱንና ክዋኔውን ተመልክታለች፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በምዕራፍ ሶስት በኢትዮጵያ ሃይማኖት እና የክህነት አጀማመር ታሪካዊ ዳራ ተመልክታለች፡፡ በዚህ ሥር የክህነት አጀማመርን ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን አንፃር፣ የሥልጣነ ክህነት ምንነት በሚለው ውስጥ የሥልጣን ምንነትና የክህነት ምንነትን፣ የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎችንና ምንነታቸውን ዲቁና፣ ቅስና፣ ጵጵስና የሚሉ ደረጃዎችን አቅርባለች፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያ ያለውን የሥልጣነ ክህነት ተዋረድ የገለጸች ሲኾን፤ እነዚህ የሥልጣነ ክህነት ተዋረዶች የሚፈጽሙትን ተግባርና የሚሰጡትን አገልግሎት አሳይታለች፡፡

በምዕራፍ አራት የንድፈ ሐሳባዊ ዳራዎች ትንታኔ ቀርበዋል፡፡ በዚህ ውስጥ ስለ ወግ ማዕረግ፣ ሥርዓተ ክዋኔ፣ የሥርዓት ምንነት፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና አስፈላጊነቱን፣ የክዋኔን ምንነት፣ የክዋኔ አላባውያን አቅርባለች፡፡ የክዋኔ መግለጫ ባሕርያት ዘርዝር ተደርገው ቀርበዋል፡፡ ትዕምርትና ትርጉም እና ተግባር ምን እንደሆኑ ፍቺ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይህም የሥልጣ ክህነት አሰጣጥ ክዋኔን ከሀገረሰባዊ ልማድ አንጻር እንዴት እንደሚካተት የሚጠቁም የሚያሳይ በመኾኑ ተገቢ ነው፡፡

በምዕራፍ አምስት የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች ሥልጣነ ክህነትን ለመቀበል መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች፣ አኹን ያለው የክህነት አሰጣጥ መሠረቱን ማን እንደኾነ አሳይታለች፡፡ ካህናት ከሌላው ማኅበረሰብ የተለየ የአኗኗር ልማድ እንዳላቸው እና ማኅበረሰቡን የመቈጣጠር፣ የመግራት፣ ከኀጢአት የመመለስ ተግባር እንዳላቸው፤ የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ

ሥርዓተ ክዋኔ ፋይዳ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንና ሥርዓተ አምልኮን ለመፈጸም የሚያስችል ኃይል የሚያጎናጽፍ እንደኾነና ሥርዓተ ክዋኔውም ከፎክሎር ዘርፎች ውስጥ ሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተት መኾኑን በጥናቷ ግኝት ውስጥ አመላክታለች፡፡ ይህም የጥናቱ አላማ ተግባር ላይ እንደዋለ የሚያሳይ ነው፡፡

ሊያ የሥልጣነ ክህነት አሠጣጥ ሥርዓተ ክዋኔን መረጃዎችን ተንትኖ ለመተርጎምና ሃገረ ሰባዊ ልማዱን ለማሳየት የክዋኔ /performance/ ቲዎሪ ዘዴን ተጠቅማለች፡፡ መረጃዎቹን ለመሰብሰብ አገልግሎት ላይ የዋሉት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ በእነዚህ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሰበሰበቻቸውን መረጃዎችን በገላጭ የአጠናን ስልት አቅርባለች፡፡ በዚህ የቲዎሪ አቅጣጫ መሠረትም የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ ላይ የሚታዩ ትዕምርቶችን ተርጉማለች፣ የሥርዓተ ክዋኔው ፋይዳንም ገልጻለች፡፡ ሊያ የተጠቀመችበትን የቲዎሪ አቅጣጫ መግለጿና በነዚህ ዘዴዎች መጠቀሙ የጥናቷ ዓላማ ከግብ ለማድረስ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳዮች በትኩረት መመልከቷን ያሳያል፡፡የእኔ ጥናት እነዚህን የቲዎሪ አቅጣጫና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተከተለ በመሆኑ ተመሳሳይ አካሄድ አለው፡፡

ሊያ በጥናቷ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሥልጣን አሰጣጥ ሥርዓተ ክዋኔ በሚለው ሥር የሥርዓተ ጥምቀት ምንነትን፣ የክርስትና መነሳት ተምሳሌት፣ የምስጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ምንነትና ተግባር እንዲሁም የጥምቀትን ዓላማና ተግባር ፎክሎራዊ ልማዶችን ገልጻለች፡፡ የእኔ ጥናት ዋና ርዕሰ ጉዳይ የክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታን ማሳየት በመኾኑ እነዚህም በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካተቱና የጥምቀት ምንነት፣ ፋይዳ፣ተምሳሌትነትን ስለሚዳስስ፣ የሜሮን ምንነት፣ ተግባርና ፎክሎራዊ ጉዳዮች ስለሚመለከት ተዛማጅነት አላቸው፡፡

የእኔ ጥናት የሥርዓተ ተክሊል ሥርዓተ ክዋኔ፣ የክርስትና ሥርዓተ ክዋኔ፣ ከሥርዓተ ተክሊልና ክርስርና በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ከቤተክርስቲያን ውጪ በቤተ ውስጥ የሚከናወኑ ሀገረሰባዊ ልማዶችን ፎክሎራዊ ጉዳዮችን፣ የሜሮንን ምንነትና ተምሳሌታዊ ተግባር የሚገልጽ በመሆኑና ሊያ እነዚህን ባለመዳሰሷ የተለየ ያደርገዋል፡፡

የዝና ወርቁ 2009 ዓ.ም በሰሜን ጎንደር የሚካሄድ የእሜቴ አይከል ሀገረሰባዊ እምነትና ክዋኔ በሚል ለድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር (MA) አቅርባለች፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ “የእሜቴ አይከል” ሀገረሰባዊ እምነት የአምልኮ ሥርዓቱን ለሚፈጽሙ የማኅበረሰቡ ክፍሎች ያለውን

ፋይዳ መግለጽ የሚል ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የተለያዩ የምርምር ጥያቄዎች ቀርበዋል እነርሱም የእሜቴ አይከል እምነትና የአምልኮ መነሻ ምንጭ፣ የእምነቱ ተከታዮች፣ እነማን እንደኾኑ፣ የአምልኮውን ክዋኔ እንዴት እንደሚያከናውኑት የሚጠይቁ ናቸው፡፡

የዝና ወርቁ መረጃዎቿን ለመሰብሰብ በቤተ መጻሕፍት ንባብ፣ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃዎችን ሰብስባለች፡፡ አውድ ተኮር የቲዎሪ አቅጣጫን በመከተል በማኅበረ ባህላዊ አውድ ውስጥ በማስገባት በገለጻ፣ በትንተና በትርጓሜ ስልቶች መረጃዎቿን መግለጿን፣ መተንተኗን፣ መተርጎሟን ገልጻለች፡፡

በጥናቷ የእሜቴ አይከል እምነትና የአምልኮ ክዋኔ ለእምነቱ ተከታዮች ማኅበራዊ ትስስርን የመፍጠር፣ በአስልምናና በክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ማኅበራዊ መቀራረብን የማዳበር ሚና እንዳላት አሳይታለች፡፡

የእሜቴ አይከል የአምልኮ ሥርዓተ ከበራዎችና ክዋኔዎች እንዳሏት ገልታለች፡፡ የእሜቴ አይከል ትዕምርታዊ የእምነት እሴትና የአምልኮ ከበራ በሚለው ሥር የመስዋዕት፣ የምስጋና ከበራ፣ የመማጸኛ ክዋኔና የመንጻት ሥርዓተ ከበራዎች ቀርበዋል፡፡

የምስጋና ሥርዓተ ከበራ መስዋዕት ማቅረብ ወቅት ከሚቀርቡላት መካከል ጸሎት፣ ያልተነጠረ ቅቤ በማምጣት ግንዷን መቀባት፣ ሽቶ ገዝቶ መቀባት ይገኙበታል፡፡ ይህንን የሚያደርጉት ከጭንቀታቸው እንድታላቅቃቸው እንደኾነ ገልጻለች፡፡ ይህ ሀገረ ሰባዊ እምነት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጉዳይ ከከበራው በፊት ጸሎት መደረጉና, የተለያዩ የመቀባት ሂደቶች ናቸው፡፡ በእኔ ጥናትም ምስጢራቱ ከመከናወናቸው በፊት የጸሎት ሥርዓት ይካሄዳል፡፡ በእሜቴ አይከል የሥርዓተ ከበራዎች ወቅት የሚቀርቡ ሰዎች ቀልባቸውን አጥርተው ወይም ንፁህ ሆነው ይቀርባሉ ብላለች፡፡ በዚህ ጥናትም የሥርዓተ ተክሊል ተጋቢዎች ከኃጢአት ንጹህ ሆነው ይቀርባሉ፡፡

ወደ ጋብቻ ከመኼዳቸው በፊት የቀኖና ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ንሥሐ ገብተው በስህተትና በዕውቀት የሠሩትን ተናዘው ንጹሕ ሆነው ይቀርባሉ፡፡ የመንጻት ሥርዓተ ከበራ በሚለው ሥር ከተለያዩ መናፍስት፣ ከኃጢአትና ከመሳሰሉት የመንጻት ሥርዓት እንዳለ አቅርባለች፡፡ በእኔ ጥናትም ክርስቲያኖች አምነው በሚጠመቁ ጊዜና ከእግዚአብሔር የጸጋ ልጅነትን አግኝተው በሜሮን ማኅተምነት ጸጋ መንፈስ ቅዱሳን ሲቀበሉ ከኃጢአት ንጹህ ይሆናሉ፡፡ ከመንፈስ ቅዱስም ዳግም ይወለዳሉ ተብሎ ይታመናል ይህም ተመሳሳይነት አሳይቷል፡፡ የክዋኔው ዓይነትና ሂደት

ቢለያይም ኹለቱም ከበራና ክዋኔ አላቸው፡፡ የእኔ ጥናት የተከተለው የቲዎሪ አቅጣጫ ክዋኔ ዘዴ በመሆኑና መረጃዎችን ለመተንተን ገላጭ የመተንተኛ ስልትን መጠቀሜ፣ ሃይማኖታዊና ሀገረሰባዊ የፎክሎር ገጽታዎችን የሚመለከት ሥለሆነ የተለየ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

ይህ መዕራፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ለጥናቱ የተመረጡት አብያተ ክርስቲያናት ታሪካዊ ዳራ ባጭሩ ገለጻ የተደረገበት ነው።

## የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አመሠራረት

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመጀመሪያው መቶ ዓመተ ምህረት እንደሆነ (ሳሙኤል 2000፡ XI) አስረድተዋል። ኢትዮጵያ ክርስትናን ከመቀበሏ በፊት በብሉይ ኪዳን እምነት አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምባት ሀገር እንደነበረችና ቤተክርስቲያኗም ከብሉይ ኪዳን ቀጥታ ወደ ክርስትና የተሸጋገረ ሕዝብ ቤተ ክርስቲያን እንደምትባል ገልጸዋል።

ጎርጎርዮስ (1991፡18) የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ፊልጶስ ሐዋርያ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ፣ ባኮስ፣ በ34 ዓ.ም ባጠመቀው ጊዜ እንደኾነ ይገልጻሉ። ይህንን ሀሳብ ሳሙኤልም (2000፡ XI) (ክንፈ ገብርኤል 2000፡ 45) የመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራን ዋቢ አድርገው እንዲህ ገልጸውታል።

> *የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በመጀመሪያው መቶ ዓመተ ምህረት በንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ ሐዋርያነት ነው። በ(ሐዋ. 8÷1) እንደተገለፀው "ጃንደረባው በኦሪት ሥርዓት መሠረት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዶ፣ የፋሲካ በዓል አክብሮ ሲመለስ ወንጌላዊው ፊልጶስ አስተምሮ፣ አሳምኖና አጥምቆ ክርስቲያን ስላደረገው ጃንደረባው ወደ ሀገሩ ሲመለስ የክርስትና እምነት ሐዋርያ ሆኗል።*

ምንም እንኳ ክርስትና ወደ ሀገሪቱ በመጀመሪያው ዓ.ም ይግባ እንጂ በትምህርትነት የተስፋፋው በመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ በኋላ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በተባለው እንደሆነ (ሉሌ መላኩ 1986፣ 246)፣ (ክንፈ ገብርኤል 2000÷16) ጎርጎርዮስ (1991÷18) ይገልጻሉ። ይህም የሆነው በ፬ኛው ምዕተ ዓመት ፍሬምናጦስ በእስክንድርያው ፓትርያርክ አትናቴዎስ በጵጵስና ማዕረግ ከተሾመ በኋላ ነው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ባኮስ የተመሰረተውን ክርስትና ፍሬምናጦስ በትምህርት አጠናክሮ እንዳስፋፋው ገልጸዋል። ኢትዮጵያም በመንበረ ጵጵስና ደረጃ የተደራጀችው በዚህ ዘመን እንደሆነ ተገልጿል።

ኢትዮጵያ ክርስቶስን ያወቀችውና መባ በማቅረብ ልደቱን ያከበረችው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቀዳማዊት ቤተ ክርስቲያን መባልዋ በትክክል እንደኾነ በ(ኢሳ 60፡ 6) እና በ(ማቴ 2÷1-11) የተገለጸውን ዋቢ በማድረግ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወልዶ ሳለ ወርቅና ዕጣን ከርቤ ካቀረቡለት ሦስት ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ባዜን እንደነበር ይነገራል፡፡ "የግመሎች ብዛት፣ የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፤ ወርቅና ዕጣን ያመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ" ብሎ ኢሳኢያስ በትንቢት የተናገረው ስለዚህ ኢትዮጵያዊው ንጉስ እንደኾነ ያስረዳሉ (ክንፈ ገብርኤል 2000÷15)፡፡

በዘመነ ሐዋርያት የክርስትና እምነትን በመቀበል የመጀመሪያው የኾነው ባኮስ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የእምነት ሥርዓተ አምልኮ ሕንፃ የመሠረት ድንጋይ ነው፡፡ ለሐዲስ ኪዳንም ኢትዮጵያ ዓለም ዓቀፍ ዕወቅና ያገኘ የኢኦተ መሥራች ነው፡፡ ሕገ ኦሪትና ሕገ ወንጌልን በአንድ ጉዞ የፈጸመ እንደሆነና ለክርስቲያን ወገኖቹ ኢትዮጵያውያንን እንዳስተማረ የጥንት ቤተክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ አውሳብዮስ ዘቂሳሪያ ጽፏል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም የተመሰረተችው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሲኖዶስ ሕግ፣ የኢጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣት በ፬ኛው ምዕተ ዓመት  በ330 ዓ.ም ነው፡፡ በአባ ሰላማ መምህርነት በአብርሃና አጽብሐ ዘመነ መንግስት የክርስትና ሃይማኖት በአዋጅ መሰበኩን ገልጸዋል (ክንፈ ገብርኤል 2000÷16)፣ (ኤፍሬም ኢሳቅ 1971፣ 240-241)፡፡

ክንፈ ገብርኤል በ4ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቀች ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ለመሆን መብቃቷንና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን በምልዓት መፈጸም እንደጀመረች ያስረዳሉ፡፡ አባ ሰላማ አንባረምን ሕዝበ ቀደስ ብሎ በኢጲስ ቆጶስነት ከሾመው በኋላ በሕዝበ ቀድስሞ ስብከት የኖባና የሳባ፣ የናግራንና የትግራይ፣ የአማራና የአንሳት፣ የቀጣ፣ የዘበግዱር ሕዝብ በክርስቶስ አምነው ተጠምቀው ክርስቲያኖች ሆኑ በማለት ገልጸዋል፡፡ ክርስትና በ34ኛው ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ ገባ በ4ኛው ክፍለ ዘመን በትምህርት ተጠናከረ ይባል እንጂ በመላው ሀገሪቱ የተስፋፋው ግን የዘጠኙን ቅዱሳን ኢትዮጵያ መምጣት ተከትሎ እንደኾነ (ሉሌ መላኩ፣ 1986÷246-253)፣ (ክንፈ ገብርኤል 2000÷17) ገልጸዋል፡፡

ከዘጠኙ ቅዱሳን መምጣት በኋላ የአክሱም ቤተ መንግሥትና መላው የኢትዮጵያ ግዛት በክርስትና ሃይማኖትና ስብከት ተዳርሶ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ35 ዓ.ም- 330 ዓ.ም ድረስ

ከኦሪት እምነቱ ጋር ጥምቀትን ተቀብሎ ቆየ። እስከ ዛሬ ድረስ በክርስቲያኖች ዘንድ የሚፈጸሙት ከሕገ ኦሪት የተወረሱት እንደ ታቦት፣ ግዝረት፣ የአሣማ ሥጋ አለመብላትና የመሳሰሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከኦሪት ወደ ክርስትና እምነት ሲሸጋገር የጠበቀው ነው ሲሉ (ሉሌ፣ 1986÷123) ያስረዳሉ። አባ ሰላማ የክርስትናን ሃይማኖት እንዲስፋፋ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ ሐዲስ ኪዳንን ከግሪክ፣ ከዮናኒ(ጽርዕ) ወደ ግዕዝ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር ተርጉመዋል። ለቀሳውስትና ለዲያቆናትም ማዕረገ ክህነት ሰጥተዋል ይላሉ። በወንጌላዊው ማቴዎስና በህንደኬው ጃንደረባ ተሰብካ የነበረች ክርስትና በኢትዮጵያ የተስፋፋች ቢሆንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 20ኛው መቶ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከግብጻውያን ብቻ ጳጳሳት ሲሾሙ እንደቆዩ አስረድተዋል። ይሁን እንጂ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጳጳስ፣ አቡነ ፊልጶስ ኤጲስ ቆጶስ ኾነው መሾማቸውን ገልጸዋል። ሉሌ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጎልቶ የሚነገረውና ለክርስትና ሃይማኖት ይበልጥ መስፋፋት አስተዋጽኦ የነበረው የዘጠኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መግባት ነው ይላሉ (1986፡ 124-125)።

"…. ክርስትና በሀገራችን የተመሠረተው ቅድመ ክርስትና በነበረው ሕገ ኦሪት መደብ ላይ ሲሆን ትምህርቱ ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ጎልቶና አይሎ በመምጣቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይና ተከታይ እያገኙ ስለመጡ ክርስትና በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት በብዛት መስፋፋት የሀገሪቱን ጠቅላላ ሁኔታ ሊለውጠው ችሏል በማለት (ሐዲስ የሻነው 1998፡ 15) አስፍረዋል።

## 3.1. የክርስትና አመሠራረት

### 3.1.1. ክርስቲያን መባል መቼ ተጀመረ

አክሌሲያ የሚለው የግሪኩ ቃል በግዕዙ ቤተክርስቲያን ወይም "ሕሩያነ እግዚአብሔር" በእግዚአብሔር የተመረጡ ማለት ነው። ይህም ክርስቲያኖች የሚለውን በቀጥታ ያመላክታል። ምዕመናን ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን የተባለውን ስያሜ ያገኙት በአንጾኪያ ነው ይላሉ (ሰሙ ምትኩ፣ቸሬ አበበ፣ 2000÷4)። ይሁንና ክርስቲያን የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኾነ በማቴዎ ወንጌል የተገለጸውን ዋቢ አድርገው የሚከተለውን ገልጸዋል።

*"….አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጃችም አይችሏትም። (ማቴ 16÷18)። ወንድምህ ቢበድልህ ሂደህ አንተና እርሱ*

*ብቻችሁን ሁናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ ወንድምህን ጠቀምኸው ባይሰማህ ግን በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ኹሉ እንዲጸና ዳግመኛ አንድ ወይም ኹለት ከአንተ ጋር ውሰድ እነርሱን ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንግራት፣ (ሐዲስ ኪዳን. 1953፣ 17-18)*

ቤተ ክርስቲያን ማለት አንድም የክርስቲያኖች ጉባኤ አንድም ክርስቲያን ማለት ነው። ስለዚህም ክርስቲያን፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በክርስቶስም እንደተነገረ ገልጸዋል። (ሉሌ መላኩ 1986፣ 16) አንደስረዱት አይሁድ፣ ክርስቲያኖችን ገሊላውያን ናዝራውያን ይሏቸው ነበር። ክርስቲያኖች ደግሞ እርስ በርሳቸው ወንድሞች፣ ደቀ መዛሙርት እየተባባሉ ይጠራሩ ነበር። ይሁንና ክርስቲያን መባል ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጀመረው በአንጾኪያ ነው። ይህንንም ስም ያወጡላቸው የአንጾኪያ ሰዎች ሲሆኑ፣ክርስቶስ የተባለውን በመከተላቸው ነው ይላሉ ።

## 3.1.2. የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሥያሜ

ኦርቶዶክስ ቃሉ የጽርእ ሲሆን ጥምር ቃል ነው። "ኦርቶስ" ቅጽል ነው፤ ርትዕት፣ ቀጥ ያለ ቀጥተኛ ማለት ነው። "ዶክስ" ደግሞ "ዶክ" ካለው ግስ የወጣ ሲሆን ፍቺው ማሰብ መገመት ማመን ማለት ነው። "ኦርቶዶክስ" እንደ አንድ ስም ሆኖ ተጠቃሎ ሲፈታ ቀጥተኛ ሀሳብ፣ ቀጥተኛ አስተያየት፣ በሃይማኖት ትምህርት ርዕትዕት ሃይማኖት፣ ቀጥተኛ ሃይማኖት ማለት ነው (ጎርጎርዮስ፣ 1991÷24)።

ኦርቶዶክስ የሚለው ቃል የተፈጠረው ምንም ለውጥ መሻሻል ያልተቀላቀለበት የክርስትና ሃይማኖት ለመመልከት እንደኾነ ይገልጻሉ። ስያሜውም የተጀመረው በ (325 ዓ.ም) "በኒቂያ በተደረገ ጉባኤ፣ 318ቱ ሊቃውንት፣ አርዮስ የሚባለውን ሰው ካወገዙ በኋላ፣ ሃይማኖታቸውን አጽንተው ሲለያዩ፣ ሃይማኖታቸውን፣ "ኦርቶዶክ" እንዳሉት ገልጸዋል። ጎርጎርዮስ ስለ ተዋሕዶ ሲናገሩ የሚከተለውን አስፍረዋል ‹‹ተዋሕዶ የሚለው ቃል የተመሠረተው በ200 ሊቃውንት በጉባዔ ኤፌሶን ነው። የጉባዔ ኤፌሶን ምክንያት ንስጥሮስ የሚባል የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ፣ "አምላክ በሰው አደረ" ብሎ በይፋ ስላስተማረ ጳጳሳት ከዓለም በመሰባሰብ ጉባኤ አድርገው "ቃል ሥጋ ሆነ" ይኸውም እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕዶ ነው›› ብለው ወስነዋል።የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስያሜዋን ያገኘችው የኒቂያ ጉባዔንና "የኤፌሶንን ጉባዔ (431 ዓ.ም)፣ (325 ዓ.ም)፣ 318 ሊቃውንትና 200ው ሊቃውንት የውሰኑትን ትምህርተ ሃይማኖት አክብራ ስለያዘች ነው ይላሉ (ጎርጎዮስ፣ 1991÷25)፣ (ሰሙ ምትኩና ቸሬ አበበ፣ 2000፣ 103-110)።

## 3.2. ጥናቱ የተካሄደባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዳራ

### 3.2.1 የደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሠራረት

ደብረ ሊባኖስ ገዳም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ሰላሴ ሀገረ ስብከት፣ ወደ ጐጃም በሚወስደው አውራ መንገድ 104 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ፣ በደብረ ሊባኖስ ወረዳ ደልደል ያለ ቦታ ላይ ይገኛል፡፡ ዋናው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ከአውራ መንገዱ 5 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ ገባ ብሎ ይገኛል፡፡

የገዳሙ አቀማመጥ ወጣ ገባ ሆኖ በተራሮች፣ በወንዞችና በብዙ ዕፅዋት የተከበበ ነው፡፡ በሰሜን ምስራቅ የጀማ ወንዝ፣ በደቡብና ደቡብ ምዕራብ በተራራ /በተለምዶ ውሻ ገደል ይሉታል/፣ በምዕራብ የአጋቶን ወንዝ ተከቦ ይገኛል፡፡ በገዳሙ ክልል ውስጥ ምዕመናን ከተለያየ ሥፍራ ሲመጡ ለመታጠቢያና ለመሳሰሉት አገልግሎት የሚጠቀሙባቸው የምንጭ ውኃና የጠበል ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ በገዳሙ ሥር ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን በተጨማሪ የቅዱስ አማኑኤልና የቅዱስ ፊልጶስ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ በዚህ ገዳም የሴቶች ደብር[3]፣ የሚኀበኙ የነገሥታት ሥጦታዎች፣ የመስቀል ቤት፣ ዐጽመ ቅዱሳን፣ የጳጳሳት መቃብሮች፣ ቅዱሳት መጻሕፍትና ቤተ መዘክር በገዳሙ ሥር ከሚኀበኙት መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ደብረ ሊባኖስ ገዳም በኢኦተቤ 4ቱ ጉባኤያት የአብነት ትምህርት ቤት ከሚገኙባቸው ቦታዎች ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ከንባብ ቤት ጀምሮ የቅዳሴ ቤት፣ የዜማ ቤት፣ የአቋቋም ቤት፣ የቅኔ ቤትና የትርጓሜ መጻሕፍት ቤት ይገኙበታል፡፡

ገዳሙ ተጠሪነቱ ለፓትርያርኩና ለቅዱስ ሲኖዶስ ነው፡፡ ዋና አስተዳዳሪው ጸባቴ[4] ሆኖ የተለያዩ የአስተዳደር ክፍሎችና መዋቅሮች አሉት፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኦረቶዶክስ ምዕመናን በብዛት የሚገኙበት ሦስት ዓበይት የንግሥ በዓላት አሉት፡፡ እነርሱም ታኅሣሥ 24 /የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የልደት ቀን/፣ ግንቦት 12 / የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አፅም ከደብረ አስቦ የፈለሰበት ቀን/ እና ነሐሴ 24 ቀን/ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የዕረፍት ቀን ናቸው፡፡

ደብረ ሊባኖስ ገዳም በዓጼ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በአባ ሊባኖስ አማካይነት እንደተመሠረተ ይነገራል፡፡ አባ ሊባኖስ ቦታውን ከገደሙ በኋላ በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ነበር፡፡ በኋላ ግን እግዚአብሔር በኅልማቸው ተገልፆ "ዛቲሰ መካን

[3] የሴት ደብር በእመ ምኔት ይመራል፡፡ አስተዳዳሪዋ ሴት መነኩሲት ነች፡፡

[4] ጸባቴ የደብረ ሊባኖስ ገዳም  አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡

ኢኮነት ዘዚአከ አላ ኅድግ ሎቱ ለዘ ይመጽዕ እምድኅሬከ ወበእንተ ጻማከሰ ትሰመይ በስምከ ደብረ ሊባኖስ"፤ "ይህ ቦታ ያንተ አይደለም፤ ከአንተ በኋላ ለሚመጣው ጻድቅ ሰው ተውለት፤ ቦታውን ለማቅናት ስለደከምክ ቦታው በአንተ ስም ይጠራል" አላቸው። አርሳቸውም እግዚአብሔር ከዚህ ቦታ እንድሔድ አዘዘኝ በማለት መነኮሳቱን ተሰናብተው ወደ ትግራይና ኤርትራ በመሔድ ብዙ ገዳማትን አቅንተዋል። ከእርሳቸው በኂላ ለ700 ዓመታት ያህል ቦታው ጠፍ ሆኖ ኖሯል። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ደብረ አሰቦ ከመምጣታቸው በፊት ሌሎች መነኮሳት በጸሎት ተወስነው በቦታው ይኖሩ ነበር። በ12ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ኮራ የተባለ ሽፍታ ተነስቶ መነኮሳቱን ገድሎ በአካባቢው ገናና ሆኖ ይኖር ነበር። አሁንም ድረስ እርሱ ከሞተበት ቦታ ላይ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ምስራቅ አዋሳኝ ኮራ የተባለ ገዳም አለ። አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደዚህ ሥፍራ ሲመጡ ጠንቋዮች ቦታውን ወስደውት ነበር። ነገር ግን እርሳቸው ቦታውን ባርከው የጸሎት ቦታ አድርገውታል። በዚህ ገዳም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት በጸሎትና በተጋድሎ መኖራቸው በየአካባቢው በመሰማቱ ብዙ መነኮሳት ወደዚህ ቦታ ተሰብስበዋል። እርሳቸውም በደብረ አስቦ ዋሻ ውስጥ ግማሹን በሰሌን ከፍለው፣ የድንግል ማርያምን ታቦት አኑረው፣ እኩሌታውን ደግሞ ከደቀ መዝሙሮቻቸው ጋራ ይኖሩ ነበር ( ትንሣኤ 1978፣ 20፣ ዳንኤል 1999፡ 428-433)።

ከደብረ አሰቦ[5] በአታቸው ራስጌ ደብረ ከርቤና ደብረ ጽጌ ተራሮች ይገኛሉ። ደብረ ከርቤ እንደ ሸንተረር ያለ ሆኖ የቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ይገኝበታል። ደብረ ጽጌ ደግሞ የድንግል ማርያም ታቦት አለበት።[6] አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዚሁ በደብረ ሊባኖስ ደብረ አሰቦ ዋሻ እንዳረፉ ይነገራል። አጽማቸውም አሁን ቤተ ክርስቲያኑ ወደተሠራበት አካበቢ የመጣው በዓጼ ሰይፈ አርእድ/1336 — 1364/ በእጨጌ ሕዝቅያስ አማካይነት ግንቦት 12 ቀን ነበር (ትንሳዔ 1978፣ 21፣ ሥርግው 1982፡ 1፣ ዳንኤል 1999፣ 433)።

ደብረ ሊባኖስ እየተባለ ስሙ ገንኖ መጠራት የጀመረው በ15ኛው ምዕተ ዓመት በተለይም በዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት /1426-1460/ ጀምሮ ነው። ዓፄ ዘርዓ ያዕቆብ የአዳል ገዢን ለመውጋት ሲነሳ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳትንና ሌሎች ገዳማትን ጸሎት እንዲያደርጉለት ጠይቆ ነበር። በድላይ የተባለውን የአዳል ገዢ ድል አድርጐ በመጣ ጊዜ አባ እንድርያስ በተባሉ እጨጌ መሪነት የደብረ ሊባኖስ መነኮሳት ሊቀበሉት መጡ። በዚህ ጊዜ ብዙ ስጦታ ለገዳሙ ካበረከተ

[5] ደብረ አሰቦ አሁን ካለው የደብረ ሊባኖስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በስተ ደቡብ በኩል ከፀበሉ አጠገብ ያለው ዋሻ ነው።
[6] በአሁን ጊዜ በደብረ ጽጌ ተራራ ዙሪያ ከተማ በመመሥረቱ ደብረ ጽጌ የሚባል ወረዳ ተሰይሞ ይገኛል።

በኋላ ደብረ ሊባኖስ ብሎ እንደሰየመው በዜና መዋዕሉ ላይ ተተርኳል፡፡ "ወለ ደብሮሙኒ ሰመየ ደብረ ሊባኖስ ቀዳሚሁሳ ነበረት እንዘ ይብልዎ ደብረ አስቦ" ይላል፡፡ ገዳማቸውን ደብረ ሊባኖስ አላት፡፡ ከዚህ በፊት ደብረ አስቦ ትባል ነበረች፡፡ ኹለት ጸባቴዎች መሾም የጀመሩት በዚህ ዘመን ነበር (ሥርግው 1982፣ 142፣ ዳንኤል 1999፣ 430)፡፡

ታቦተ ማርያም በደብረ አስቦ አቡነ ተክለ ሃይማት ከሞቱ በኋላ ለ57 ዓመት በዚያው ተቀድሶበታል፡፡ በዓፄ ይስሐቅ /1399 - 1414 ዓ.ም/ ኤሌም ላይ የመጀመሪያውን ቤተ ክርስቲያን ሰባት ዓመት በፈጀ ጊዜ ውስጥ አንጸውት ነበር፡፡ ቅዳሴ ቤቱ በተከበረ ጊዜ ዓፄ ይስሐቅም ተገኝተው ነበር፡፡ በውቀቱ ለገዳሙ ብዙ ንዋያተ ቅዱሳትን ለግሰዋል፡፡ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት አፅምም ከዚያ አርፏል፡፡ በዓፄ ናዖድ ዘመን/1486 — 1500/ ከኤሌም ዝቀ ብሎ አሁን ካለበት ሥፍራ ላይ ወርዶ ተሠርቷል፤ በጳጳሱ አቡነ ማርቆስ ተባርኮ ዓፄ ናዖድ በተገኙበት ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል፡፡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ቤተ ክርስቲያን ሐምሌ 24 ቀን 1524 ዓ.ም በግራኝ አሕመድ ተቃጥሏል (ሥርግው 1982፣ 149፣ ዳንኤል 1999፣ 430)፡፡

ደብረ ሊባስ ገዳም ግራኝ አሕመድ ካቃጠለው በኋላ ለ160 ዘመን እንደ ቀድሞው ጠፍ ሆኖ ቆይቶ ነበር፡፡ ገዬ፣ ጨፌ፣ ሊቁና ዳኛ የሚባሉ ዐራት ወንድማማቾች ከአማራ ሳይንት ወለቃ ከሚባል ሥፍራ ደብረ ሊባኖስን ለማቅናት ወደዚህ ቦታ መጡ፡፡ በወቅቱ በአካባቢው ሌሎች ማኅበረሰቦች ሰፍረው መኖር ጀምረውበት ነበር፡፡ ዐራቱ ሰዎች አካባቢውን ከያዙት ሰዎች ጋራ በጋብቻ ከተሳሰሩ በኋላ ከዐራቱ የአንደኛቸው /ገዬ የሚባለው/ የልጅ ልጅ፣ ወልደ ሐዋርያት በድጋሜ ገዳሙን እንዳቀናው ይነገራል (ገድለ ተክለ ሃይማኖት 1946፡ 251-253)፡፡

ዓፄ ገላውዴዎስ /1543 — 1551/ በግራኝ አሕመድ የተቃጠለውን ቤተ ክርስቲያን አሠራ፡፡ ከግራኝ በኋላ ገዳሙ ዜጋመል ከተባለው ቦታ ላይ ከገደል ሥር ተሠርቶ ነበር፡፡ ከዜጋመል ወደ አሁኑ ሥፍራ የተዘዋወረው በዓፄ ዮሐንስ ዘምን ነው፡፡ በዚህ ዘመን ዓፄ ምኒሊክና ዓፄ ዮሐንስ ዕርቅ የፈጠሩበት ዘመን ነበርና ቃል ኪዳን ለመቀባበል ደብረ ሊባኖስ እንደወረዱ ይነገራል፡፡ በ1870 ዓ.ም ዓፄ ዮሐንሰ በአክሱም ፅዮን አሠራር አስመትረው ቤተ ክርስቲያን ማሠራት አስጀምረዋል፤ በ1876 ዓ.ም ተጠናቆም ቅዳሴ ቤቱ ተክበሯል፡፡ በ1895 ዓ.ም ዓፄ ምኒሊክ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ራስ አባተን አዘው እርሳቸውም ያርጊ ከሚባል ግሪክ ጋራ ተፈራርመዋል፡፡ ቤተክርስቲያኑም በ1900 ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱም ተከብሯል፡፡

**ፎቶ 1፡ አሁን ያለው የደብረ ሊባኖስ ገዳም የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን**



**(ፎቶ ከገዳሙ ቤተ መዘክር)**

አሁን ያለው ቤተ ክርስቲያን የታነጸው በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት ነው፡፡ የሕንፃው መሠረት የተጣለው በ1952 ዓ.ም ሲሆን፣ የሕንፃ ሥራው የተጠናቀቀው ከሦስት ዓመታት በኋላ በ1955 ዓ.ም ነበር (ሥርግው 1982፣ 150፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት 1946፣ 251-253፣ ዳንኤል 1999 ዓ.ም፣ 432)፡፡

## 3.2.2. እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት

እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም በ5ኛው ምዕተ ዓመት በጻድቁ አባ ሊባኖስ እንደተመሰረተች (ዳንኤል 1999፡25) ያስረዳሉ፡፡ ገዳሟ ከአዲስ አበባ በስተሰሜን ምስራቅ የምትገኝ ሲሆን በተራራና በወንዞች የተከበበች ናት፡፡ ሐመረ ኖኅ የሚለውን ስያሜ በንግሥት ዘውዲቱ ከማግኘቷ በፊት በዙሪያዋ ባሉ ወንዞች ምክንያት አሸከላ ገዳም ተብላ ትጠራ ነበር (መስፍን 2011፡17)፡፡

ገዳሙ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ (1426-1460) ዘመነ መንግሥት በጣም ተጠናክሮ ነበር፡፡ የንጉሡ እህት የእሌኒ ልጅ አባ ኤልያስ ከመናገሻ ማርያም ብዙ መነኮሳትን በማምጣት ስመጥር እንዳደረጉት (መስፍን 2011፡17) ገልጸዋል፡፡ ይሁንና በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አሕመድ ወረራ ወቅት ቤተ ክርስቲያኗ ተቃጥላ ነበር (ዳንኤል 1999፡25)፡፡

መርስዔኀዘን (1999፡88) ስለ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም አመሠራረት በተመለከተ የሚከተለውን ሐሳብ አስፍረዋል፡፡

> *አባ ምትኬ የተባሉ የእንጦጦ ማርያም ቄስ ገበዝ ከእንጦጦ በስተ ምስራቅ በኩል በሚገኝ ሸለቆ ውስጥ በ1902 ዓ.ም ሕሙማንን የሚፈውስ ጠበል አግኝተው ነበር፡፡ ይህንኑም ለእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን አለቃ ነገሯቸው፡፡ ቀጥሎም ከእንጦጦ ካህናት ጋራ ወደ ጠበሉ ወርደው፣ ጸሎት አድርሰው፣ መስቀል ተክሉበትና ሕዝቡም ወሬውን ሰምቶ እየመጣ ይጠመቅበት ጀመር፡፡ የጠበሉም ፈዋሽነት ባለ ዝና ሆኖ ይወራ ጀመር፡፡ ከዚህ በኋላም በእቴጌ ጣይቱ ትእዛዝ በዚህ ዘመን የኪዳነ ምሕረት ታቦት ተተከለበት፡፡*

በዚህ ሥፍራ ጥንት ቤተክርስቲያን የነበረበትና ጠበል ያለበት መሆኑ አባ ምትኬ በራዕይ ተገልጾልኛል ብለው ተናግረው ስለነበር በጠበሉ ራስጌ ያለው ጉብታ ሲቆፈር የጥንቱ ቤተ ክርስቲያን የመሠረቱ ሕንፃ፣ እንዲሁም የብረት መስቀልና የብረት ጽንሐሕ ተገኝቷል (ዳንኤል 1999፡25፣ መርስዔ ኀዘን 1999፡88)፡፡

እቴጌ ጣይቱ መቃኞውን ካሠሩ በኋላ ካህናትን ከእንጦጦ ማርያም በመመደብ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲጀመር አድርገው ነበር፡፡ በወቅቱ በሸዋ ክፍለ ሀገር በአቃቂና በጊዶ የመተዳደሪያ መሬት በመስጠት ለሁለት ቄሶች አንድ ጋሻ መሬት፣ ለዲያቆናቱ ደግሞ በየወሩ እህል እንዲከፈላቸው በማድረግ የመጀመሪያውን መንፈሳዊ አገልግሎት አስጀምረዋል፡፡ በተጨማሪም ገዳሙን በማጠናከር በመነኮሳት ንፍሮና ዳቤ እንዲዘጋጅ አድርገዋል፡፡ በንግሥት ዘውዲቱ ትዕዛዝ በ1909 ዓ.ም በአቡነ ማቴዎስ አማካይነት የገዳሙ ቦታ እንዲከለል ተደርጓል (መስፍን 2011፡19)፡፡

**ፎቶ 2፡ እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቤተ ክርስቲያን**






**(ፎቶ ከገዳሙ ቤተ መዘክር)**

አሁን ያለው ቤተክርስቲየን በንግሥት ዘውዲቱ ቢጀመርም ፍጻሜውን ያገኘው መጋቢት ወር በ1923 ዓ.ም፣ በእቴጌ መነን አማካይነት በራስ ደስታ ተቆጣጣሪነት ነው፡፡ በየካቲት 16 ቀን 1924 ዓ.ም በብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ተባርኮ እቴጌ መነንና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት ተመርቋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በዚህ ገዳም ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይፈጸሙበታል፤ የተለያዩ የንግሥ በዓላትም አሉ፤ የሚካኤል ጽላት በመኖሩ ጥር 12 /ቀን የቃና ዘገሊላ ዕለት ይነግሣል/፤ የካቲት 16 ቀን /የኪዳነ ምሕረት ዕለት/፣ ግንቦት 1 ቀን /የድንግል ማርያም ልደት/ እንዲሁም ነሐሴ 16 ቀን /የፍልሰታ እለት/ በዓለ ንግሥ ናቸው (ዳንኤል 1999፡ 25፣ መስፍን 2011፡ 20፣)፡፡

### 3.2.3. የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም አመሠራረት

የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በስተሰሜን በኩል እንጦጦ ቴክኒክና ሙያ ት/ቤት አጠገብ የሚገኝ ገዳም ነው፡፡

አሁን ያለው ቤተክርስቲያን ከመሠራቱ በፊት ታቦተ ሕጉ በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጪ በተለያዩ ሥፍራዎች ለሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ ሆኗል፡፡ አባ ተክለ ማርያም እንደገለጹት

*የዴር ሱልጣን[7] መድኃኔዓለም ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ፈቃዱ ሆነ… አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ በ1895 ዓ.ም መምህር ፈቃደ እግዚእ የተባሉትን መነኩሴ ለኢየሩሳሌም አለቅነት ሹመው በሚልኳቸው ጊዜ፣ ይህን ምዕራገ ጸሎት ወመስዋዕት የሆነውን ታቦት፣ ወይም ጽላት ዴር ሡልጣን መድኃኔ ዓለምን ይዘው እንዲሔዱ አዘዟቸው። በዚያው… በዴር ሡልጣን ገዳም ከ1895 ዓ.ም እስከ 1929 ዓ.ም ድረስ ኑሯል። የቅዳሴውንም ሆነ የጸሎቱን ሥነ ሥርዓት ሲያከናውኑ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ናቸው (ተክለ ማርያም 1962፡21-23)።*

በ1928 ዓ.ም ጣልያን ኢትዮጵያን ሲወር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሀገር ለቀው በስደት ለንደን በኖረበት ወቅት "የሃይማኖት ችግር እንዳያገኘን፣ የሚያድጉትም ልጆቻችን የሃይማኖት መሠረትን እንዳያጡ" በሚል የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለምን ጽላት ከተለያዩ ንዋያተ ቅዱሳት ጋር ከዐቢይ ጾም በፊት አባ ሐናን እና ሌሎች 4ት ልዑካን ጋራ በ1929 ዓ.ም ወደ ለንደን እንዲሄድ አድርገዋል።[8] በዚያም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የጸሎትና የቁርባን አገልግሎት እየተከናወነ እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ ቆይቷል። የጸሎት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩትም ኢትዮጵያውያን ነበሩ (ተክለማርያም 1962፡ 26-27፣ ዳንኤል 1999፡155፣ ከፈለኝ፡ 2009፣ 28-32)።[9]

ንጉሠ ነገሥቱ ምንም እንኳን በሚያዚያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ከሥደት ወደ ሀገራቸው ቢመለሱም ታቦቱ አብሯቸው አልመጣም ነበር። የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ጽላትና ንወያተ ቅድሳቱን፣ በነሐሴ 23 ቀን 1933 ዓ.ም ግርማዊት እቴጌ መነን አዲስ አበባ በገቡበት ቀን አባ ኃይሌ ብሩክ የተባሉት መነኩሴ ይዘውት ገብተዋል። ወደ አዲስ አበባ ከገባ በኋላ በቤተ መንግሥት የተለየ ቦታ ተወስኖለት በአባ ኃይሌ ቡሩክ ጸሎት አድራጊነትና አጣኝነት ለሁለት ዓመት ከቆየ በኋላ ሚያዚያ 27 ቀን 1935 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል /የአሁኑ የካቲት 12 ሆስፒታል/ ክበብ ውስጥ በታነጸው ቤተ ክርስቲያን ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም በመባል ተሰይሞ ተተከለ (ተክለማርያም 1962፡36-38፣ ማስታወሻ 1942፡43፣ ዳንኤል፡ 1999፡155-156)።

በዚሁ ግቢ ውስጥ በአባ ሐና እና በአባ ኃይሌ ቡሩክ መሪነት ሌሎች ስምንት አገልጋዮችን በመቅጠር (አራት መነኮሳትና አራት ዲያቆናት) የቅዳሴና ሌሎች የጸሎት ሥርዓቶች አገልግሎት

---

[7] ዴር ሱልጣን ማለት የንጉሥ ገዳም ማለት ነው።

[8] ወደ ኢየሩሳሌም በንጉሱ የተላከውን ደብዳቤ አባሪ 5 አድርጌ ከጀርባ አቅርቤዋለሁ።

[9] ልዑካኑ መ/ር ገብረ ኢየሱስ፣ .ክቡር አባ ሀና፣ አባ ማርቆስ፣ አባ ኃይሌ ብሩክና አባ ገብረ ማርያም ነበሩ (ተክለ ማርያም 1962፣ 28)።

እንዲጀምር ተደርጓል፡፡ በ1940 ዓ.ም የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ቅጥር ግቢ ውስጥ ወጥቶ ከተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት ክበብ ውስጥ እንዲሠራ ንጉሡ ሥለፈቀዱ ቦታው ከተዘጋጀ በኂላ ሚያዚያ 27 ቀን 1940 ዓ.ም ለአዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመሠረት ድንጋይ ተጣለ፡፡[10] የመሠረት ድንጋይ በተጣለ ማግስት የሕንፃ ሥራው ተጀምሮ ከሁለት ዓመታት በኂላ ሚያዚያ 27 ቀን 1942 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እቴጌ መነን፣ ጳጳሳትና ምዕመናን በተገኙበት አሁን በሚገኝበት ሥፍራ ቅዳሴ ቤቱ ተከበረ (ተክለማርያም 1962፣ 48፣ መጽሔት ዜና 2008፡ 2-4)፡፡

**ፎቶ 3፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም አሁን ያለው ቤተክርስቲያን**



**ፎቶ. (በአጥኚው)**

በምስካየ ኅዙናን አገልጋይ የነበሩት መነኮሳት በአንድነት ይኖሩ ነበር፡፡ ይህንን ስምምነት የፈጸሙት ግንቦት 16 ቀን 1937 ዓ.ም ነው፡፡ በወቅቱ የነበረው ደመወዝ ለመነኮሳት 15 ብር ለዲያቆናት 10 ብር ነበር፡፡ አጠቃላይ የወር በጀት 138 ብር ነበር (ተክለማርያም 1962፡ 32)፡፡ በወቅቱ በአንድነት ለመኖር ከወሰኑ በኂላ ብፁዕ እጨጌ ኃይለ ጊዮርጊስ /በኂላ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ/፣ መምህር ሠይፈ ሥላሴ የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል መምህር፣ መምህር

[10] በዚህ ቀን ንጉሡ ያደረጉትን ንግግር  አባሪ 4 አድርጌ አቅርቤዋለሁ፡፡

ወልደ ሚካኤል /በኋላ ብፁዕ አቡነ ሉቃስ እና ሌሎች ሊቃውንት ቤተክርስቲያንና የደብር አለቆች በተገኙበት የሕብረት ምሥረታው በዚሁ ቀን በቅዳሴ አክብረዋል፡፡ እስከ አሁንም ድረስ በየዓመቱ ግንቦት 16 ቀን በቅዳሴ ይከበራል (ዳንኤል 1999፡ 156፣ ተክለማርያም 1962፡ 42-43)፡፡

አባ ሀና ጅማ የመጀመሪያ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም አስተዳዳሪ ናቸው፡፡[11] ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ግርማዊት እቴጌ መነን እንዲሁም ከልዕልት ተናኜ ወርቅ ግንቦት 10 ቀን 1953 ዓ.ም ለገዳሙ 4 አክሲዮን አበርክተዋል፡፡ በ1954 ዓ.ም የስጋጃ መሥሪያ ማሽን በመግዛቱ ማኅበረ መነኮሳቱ የሥራና የገቢ አቅም ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በ1950 ዓ.ም ሥጋ ሜዳ ከሚገኘው የወረገኑ መሬት ላይ አንድ ጋሻ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ተሰጥቷል፡፡ በ1937 ወ/ሮ ጌጤነሽ አባ ታቦር ሐረር ጠቅላይ ግዛት ከሚገኘው ርስታቸው አንድ ጋሻ መሬት፡፡ አባ ሀና ስላሴ አውራጃ ከሚገኘው ርስታቸው አንድ ጋሻ መሬት በ1962 ዓ.ም ልዕልት ተናኘ ወርቅ በሐረር ግዛት አሰቦት አካባቢ ከሚገኘው ርስታቸው አምስት ጋሻ መሬት በርስትነት አግኝቷል(ዝኒ ከማሁ)፡፡

ገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ለመነኮሳቱና ለዲያቆናቱ መኖሪያ፣ ከመዋዕለ ሕፃናት እስከ 12ኛ ክፍል መደበኛ ት/ቤት፣ የተምሮ ማስተማር ሰንበት ት/ቤት ቤተ መጻሕፍትና አዳራሽ እንዲሁም የአገልግሎት ቢሮዎች፣ የክርስትና ማንሻ፣ ለአስተዳደርና ለአትክልት ቦታዎች ተከፋፍሎ አገልግሎት እየሰጠ ነው (መጽሔተ ዜና 2008፡2-4)፡፡

---

[11] አበምኔት የገዳም አስተዳዳሪ ማለት ነው፡፡

**ፎቶ 4፡ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም አሁን ያለው ቤተክርስቲያን**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ገዳሙ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር መሠረት ይመራል፡፡ በመሆኑም የሚተዳደረው በሊቀ ፓትርያርኩ ትዕዛዝ ነው፡፡ በሊቀ ጳጳስ የሚመራ አስተዳደር ቦርድ አለው፡፡ የገዳሙ አስተዳዳሪ የሚመሩት የአስተዳደር ጉባኤ አለ፡፡ ከዚሁም ጋር መጋቢ፣ ቄስ ገበዝ እና ሊቀ ዲያቆናት የራሳቸው ኃላፊነት አላቸው፡፡ ገዳሙን ከሌሎች ገዳማት የሚለየው የጸሎት ሥርዓቱ ነው፡፡ በዚህ ገዳም ከበሮ አይመታም፤ የጽናጽን ድምጽ አይሰማም፤ ይሁንና ሥርዓተ ቅዳሴ፣ የሰዓታት ጸሎት፣ የኪዳን ጸሎት፣ የሠርክ ጸሎትና የንስኀ መዝሙር ይቀርቡበታል (የገዳሙ ልዩ ዕትም መጽሔት 60ኛ ዓመት 2009፡52-53)፡፡

### 3.2.1. የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም አመሠራረት

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በፓትርያርኩ መቀመጫ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ ውስጥ የምትገኝ ገዳም ናት፡፡ የመጨረሻው ግብጻዊ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በ1921 ዓ.ም ከዐራቱ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት ጋራ ተሹመው እንደመጡ የካህናት መስጫ የነበረውን አዳራሽ ባርከው ታቦት እንጦስን አስገቡ፡፡ የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ በ1922 ዓ.ም ኢትዮጵያውያን በጐበኙበት ወቅት የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚመሠረትበትን ሥፍራ እንዲባርኩላቸው አደረጉ (ዳንኤል 1999፡89)፡፡

በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ዛሬ የምትገኝበት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን መሠረት የተጣለው ጥር 21 ቀን 1922 ዓ.ም ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ከተማ መስፋት አኳያ የቅድስት የድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን በቅርብ ባለመኖሩ ሕዝበ ክርስቲያኑ በየወሩ ለመሳለም  ወደ እንጦጦ ማርያምና መናገሻ ይሄድ ነበር፡፡ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ቅጽር ግቢ የቅዱስ እንጦንስና የአባ መቃርስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶ ስለነበር ምዕመናን አምልኳቸውን የሚፈጽሙት በዚህ ቤተክርስቲያን ነበር፡፡ በ1918 ዓ/ም ገደማ በግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ ጊዜ የድንግል ማርያም ታቦት ከኢየሩሳሌም መጥቶ በመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተቀምጦ ነበር፡፡ ይህንን ታቦት አሁን ያለው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መሠረቱ ከተጣለ በኋላ ከመናገሻ ወደመንበረ ፓትርያርክ እንዲመጣ ተደርጓል፡፡ በገዳሙ ቅጽር ግቢ ውስጥም ድንኳን ተጥሎ  የመናገሻ ካህናት ለዐርባ ቀናት ያህል ምሕላና ጸሎት ሲያደርሱ ቆይተዋል፡፡ በዚሁ ወቅት አቡነ ቄርሎስ የዘወትር አገልጋይ ካህናትን በመመደብ የሰርክ ሥርዓቱ በዐሥር ቀሳውስት፣ በስምንት ዲያቆናት፣ በስድስት መዘምራን በጠቅላላው በሃያ ዐራት ካህናት አገልግሎት እንዲጀመር አድርገዋል (ነቅዐ ጥበብ ዘፈለገ ሕይወት ልዩ ዕትም መጽሔት 1995 ዓም፣ በመንበረ ፓትርያርክ ቀድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ልዩ እትም መጽሔት 2011÷25)፡፡

የሕንፃው ንድፍ ከዛግዌ ወይም ከአክሱም ዘመን የሕንፃ ሥራዎች የተለየ ነው፡፡ ሰቀላማ ወይም በተለምዶ ካቴድራል ቅርጽ ዓይነት ነው፡፡ የቤተ መቅደሱ ሰሜንና ደቡብ ክንፍ ለብቻቸው የተሠሩ ተመሣሣይ መጸለያ ቤቶች አሏቸው፡፡

**ፎቶ 5፡ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ገዳሙ አሁን ላይ ያለውን ስያሜ ያገኘው በ1951 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በተሾሙበት ወቅት ነበር፡፡ በ1951 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ በስልዮስ የመጀመሪያው ፓትርያርክ ወርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ 113ኛው ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ሆነው በመንበረ ተክለ ሃይማኖት ተሹመዋል፡፡ መንበረ ጵጵስናውም ወደ መንበረ ፓትርያርክ ከፍ በማለቱ  የቅድስተ ድንግል ማርያም ገዳም "መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ገዳም" ተብሏል (በመንበረ ፓትርያርክ ቀድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ልዩ ዕትም መጽሔት 2011÷24)፡፡

**ፎቶ 6፡ የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም አሁን ያለው ቤ/ክርስቲያን**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ገዳሙ ዛሬ ያለበት ደረጃ እስኪደርስ በተለያዩ ጊዜያት እድሳት ተደርጎለታል፡፡ 1ኛ በ1937 ዓ.ም፣ 2ኛ በ1947 ዓ.ም፣ 3ኛ በ1956 ዓ.ም፣ 4ኛ በ1968 ዓ.ም እና 5ኛ 1987 ዓ.ም ዛሬ በሚታየው መልኩ በዕብነ በረድና በሞዛይክ ተሠርቶ ተመርቋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በገዳሙ መነኮሳትና ሕጋውያን ካህናት እንዲሁም ዲያቆናት የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ከዓመት እስከ ዓመት ሥርዓተ ቅዳሴ የሚከናወንበት፣ ምስጢራት የሚፈጸሙበትና ምዕመናን የሚገለገሉበት ገዳም ነው፡፡ የንግሥ በዓላቱም መስከረም ፩ / በዓለ ጽዮን/፣ ታኅሳስ 21 /ቅዱስ ገበርኤል ድንግል ማርያምን ያበሰረበት ቀን/፣ ጥር 21 /የአስተርእዮ ማርያም/፣ ግንቦት 21 /የደብረ ምጥማቅ/ ናቸው፡፡ በገዳሟ ከድንግል ማርያም ታቦት በተጨማሪ የቅዱስ ገብርኤልና የቅዱስ እንጦንስ ጽላቶች ይገኛሉ፡፡  (ዳንኤል 1999፣ 89፣ ዝኒ ከማሁ)፡፡

# ምዕራፍ አራት

## በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀተ ክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ

በዚህ ምዕራፍ ስር የክርስትና የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔዎችን ሂደት ለሥርዓተ ክዋኔው ከሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ጀምሮ እስከ ሥርዓቶቹ ፍጻሜ ድረስ ያሉ ተግባራት ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም በክዋኔው ሂደት ወስጥ የሚፈጸሙ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ሥርዓቶች ያላቸውን ፋይዳ፣ምሳሌና ትርጉም በትንታኔው ተዳሷል፡፡

### 4.1. የክርስትና አነሣሥ ሥርዓተ ክዋኔ

የክርስትና  ክዋኔ ራሱን የቻለ ሥርዓተ ጸሎትና መመሪያ አለው፡፡ ሥርዓቱ ከመካሄዱ ጀምሮ አስኪጠናቀቅ ድረስ በሃይማኖት አባቶች፣ በወላጆችና በታዳሚዎች የሚፈጸሙ ተግባራትና ዝግጅቶች አሉ፡፡ የእያንዳንዱን ክዋኔ ሂደት ያለውን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ማኅበረሰባዊ ፋይዳና ትርጉም በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

#### 4.1.1. ቅድመ ሥርዓተ ክዋኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምስጢራት ለሚባሉት ኹሉ መጀመሪያ ላይ የሚፈጸመው ሥርዓት፣ ጥምቀተ ክርስትና ነው፡፡ ምስጢረ ሜሮንና ቁርባንም ክርስትና በተነሣበት ዕለት ወዲያውኑ በተከታታይ ይፈጸማሉ፡፡ ሌሎችን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መሳተፍ የሚቻለው ከጥምቀት በኋላ ነው፡፡

የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ለመኾን መጀመሪያ ላይ የሚፈጸመው ጥምቀተ ክርስትና፣ ለሰው ልጆች ኹሉ የሚፈጸም ሥርዓት ነው፡፡ “ሰው ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ካልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግሥት ዐያያትም” የሚለውን (ዮሐ. 3÷5) መሠረት በማድረግ  በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ሦስት ሥለ ጥምቀት ተጽፏል፡፡ ሥርዓተ ጥምቀትን ለመፈጸም ወይም ክርስትና ለመነሳሣት የተለያዩ መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም የመጀመሪያው መማር፣ ኹለተኛው ማመን ነው፡፡ ክርስቲያን ለመኾን ክርስትና ከመነሣት በፊት ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች ውስጥ መማርና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ቀዳሚዎቹ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለሚፈጸመው ጥምቀተ ክርስትና የራሱ ሥርዓት ተሠርቶለት በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥርዓት መጻሕፍት ውስጥ በቅደም ተከተል ሠፍሮ ይገኛል፡፡ ለእያንዳንዱ ክዋኔ ኀላፊነት የተሰጠው ከዋኝ አለው፡፡ ማንኛውም የክዋኔ አካል ከተሰጠው የሥራ ድርሻ ውጪ

መፈጸም አይችልም፡፡ ይህም በሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ በፍትሐ ነገሥት፣ በዲድስቅልያ፣ በቀሌምንጦስ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት የሚፈጸመው ሥርዓት ወጥነት ያለው መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይኹንና በክዋኔው ኺደት ውስጥ የሚታዩ ሀገረ ሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚገቡ የተለያዩ ትውፊቶች አሉ፡፡ ይህንንም አጥኚው በምልከታው ወቅት አረጋግጧል፡፡

ፍትሐ ነገሥት፣ የጥምቀትን አጠቃላይ ሥርዓት ይናገራል፡፡ "በእንተ እለ ይበውኡ ኀበ አሚን" ወደ ሃይማኖት የሚገቡትን ማስተማር እንደሚገባ፤ "በእንተ እለ ይበውኡ ኀበ አሚን ንኡሰ ክርስቲያን"፣ ወደ ሃይማኖቱ የሚገቡ አዳዲስ ክርስቲያኖችን ማስተማር እንደሚገባ፣ አስተምሮ ማጥመቅ እንደሚገባ ይናገራል፡፡ ጥምቀት ለሴቶችም ለወንዶችም የሚሰጥ ስለኾነ አስተምሮ ማጥመቅ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው የሚል ሥርዓት ሰፍሯል (ፍት. መን.አን. ሦስት 1958÷ 44)፡፡[12]

ክንፈ ገብርኤል ፍትሐ ነገሥትን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት ከመጠመቅ በፊት ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ተጠማቂው ዕድሜው ከፍ ያለ ከኾነ የክርስትናን ትምህርት ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ትምህርቱም አስተማሪ ተመድቦለት ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጠንቅቆ ከተማረ በኋላ ከመጠመቁ በፊት ማመኑ ይመረመራል፡፡ እምነቱ ተመርምሮ ከተረጋገጠ በኋላ፣መጠመቅ ይችላል ይላሉ (ፍት መን. አን. ሦስት ሥርዋጽ 2፣ ክንፈ ገብርኤል 1983፣31)፡፡

ለዚህ መነሻቸው "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" የሚለው (በማር. 16÷16) የተገለጸው ሐሳብ ነው፡፡ ይህንን ቃል የተናገረው ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ስለዚህም ‹‹እምነት ለሌሎች ተግባራት ኹሉ መሠረት ነው›› በማለት ክርስቲያን መኾን የሚፈልግ መጀመሪያ መማር እንዳለበትና ዋናው መሠርቱም እምነቱ እንደኾነ ያስረዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን ማለትም ወንዶችን በተወለዱ በ40ኛው ቀናቸው፣ሴቶችን ደግሞ በ80ኛው ቀናቸው ታጠምቃለች፡፡ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ያሉ ሰዎችም ክርስትና መነሣት ይችላሉ፡፡ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ሕፃናት በተገኙበት ዕድሜ

---

[12]‹‹ በእንተ እለ ይበውኡ ኀበ አሚን ንዑስ ክርስቲያን…›› የሚለው ዐረፍተ ነገር ከአማርኛው ይልቅ የግዕዙ እንዳለ ቢኾን ፍቺው የተሻለ ይመስለኛል፡፡

በመጠመቅ ክርስቲያን መሆን ይችላሉ፡፡ ‹‹ማንኛውም ሰው መጠመቅ ቢፈልግ ለሌላ ቀን ብለው አያሳድሩት፤ እምነቱንና የተሰጠውን ትምህርት መረዳቱን አረጋግጠው ያጥምቁት›› በማለት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በ(ፍት. ነገ.ፍመ. አን.3፣ 1958፣ 34) ገልጸዋል፡፡ ሕፃናት 40 እና 80 ቀን ሳይሞላቸው "ሞት" የሚያሠጋቸው ከኾነ በሞግዚት ታዝለው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመኼድ እንዲጠመቁ ይደረጋል (ፍት. ነገ. አን. 3 ሥር. 2፣34፣ ክንፈ ገብርኤል 1983፡ 33)፡፡

በኢኦተቤ ማኅበረ ቅዱሳን የወንጌል መምህር የኾኑት ፈቃዱ ሣህሌ መጋቢት 6 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገው ቃለ መጠይቅ እንደገለጹልኝ ሕፃናት ጥምቀተ ክርስትናን ለማግኘት ወንዶች በተወለዱ በአርባኛው ቀናቸው ሴቶች ደግሞ በሰማኒያኛው ቀናቸው ክርስትና ይነሣሉ፡፡ ይህ ምሳሌና መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ አዳም በተፈጠረ በአርባኛው ቀን፣ ሔዋን በተፈጠረች በሰማኒያኛው ቀን በመላእክት ታጅበው ገነት መግባታቸውን መሠረት ያደረገ ሥርዓት እንደኾነ አስረድተውኛል፡፡ በኢኦተቤ ለሕጻናት ቀን ተወስኖ ክርስትና የሚያነሡበት ምክንያት አንዱ ከአዳምና ሔዋን ወደ ገነት መግባት ጋራ በማገናኘት እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

መምህር ያሬድ ክብረት መጋቢት 8 ቀን 2010 ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ ስለሕፃናት ጥምቀት የሚከተለውን ገልጸውልኛል፡፡"እግዚአብሔር አምላካችን ለሙሴ በሰጠው ሕግ መሠረት የኛ ቤተክርስቲያንም በትውፊት ተቀብላ ወንዶችን በተወለዱ በአርባኛው ቀን ሴቶችን በተወለዱ በሰማንያኛውቀን ታጠምቃለች፡፡ ይህም መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው"፡፡ ይህም (ዘሌ 12÷፩-ፍም) የተገለጸ እንደኾነ አስረድተውኛል፡፡

በኦሪት ሥርዓት ሴቶች "ከኅርስ" የሚነጹበት ጊዜ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40ኛው ቀን ሴት ልጅ ደግሞ በተወለደች በ80ኛው ቀን ነበር፡፡ በዚህ ዕለት ሕፃናትን ወደ ቤተ መቅደስ ይዘው እንዲኼዱ ሥርዓት መሠራቱን ገልጸውልኛል፡፡ በዚህ ሥርዓት መሠረት ሕፃናትን ወደ ቤተ መቅደስ በማምጣት እንዲባረኩ ያደርጉ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን የምታጠምቅበት አንዱ ምክንያት ይህንን መሠረት አድርጋ እንደኾነ ተናግረዋል፡፡

ሥለ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራትና ሥርዓት የጻፉት ፈቃዱ ሣህሌ ሥለ ሕፃናት ጥምቀት የሚከተለውን አስፍረዋል፤

> *ሐዋርያት አባቶቻችን አማኞችን ባጠመቁ ጊዜ እንደ ክርስቶስ 30 ዓመት እስኪሞላቸው የሚጠብቁ አልነበረም፡፡ ኹሉንም በተገኙበት ዕድሜ በማጥመቅ ሀብተ ወልድና ስመ*

*ክርስትና ያሰጧቸው ነበር። .... ሕፃናት ባመኑ ወላጆቻቸው እምነት ይጠመቁ እንደነበር (የሐዋ. 11÷14፣ 16÷15፡ 30÷34፤ 1ኛ ቆሮ. 1÷16) ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ዋቢ በማድረግ አስረድተዋል (2008÷43)።*

በተጨማሪም በየትኛውም የዕድሜ ክልል ያለ ሰው ‹‹የእግዚአብሔርን አምላክነት፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ከድንግል ማርያም መወለድ፣ ተሰቅሎና ሞቶ ዓለምን እንዳዳነ ካመነ መጠመቅ ይችላል›› ብለዋል።

ሥርዓተ ጥምቀት ከመከናወኑ በፊት ክርስትና የሚነሡ ሕፃናትና ሌሎች አማኞች ከወላጆቻቸው ውጪ የክርስትና አባት እና እናት ያዘጋጃሉ። ወንዶችን ክርስትና ማንሣት የሚችሉት ወንዶች ብቻ ናቸው። ሴቶችን ሴቶች ብቻ፤ ወንድን ሴት፣ ሴትን ደግሞ ወንድ ማንሣት አይችልም። ይህ ሥርዓት በዲድስቅልያ በ34ኛው አንቀጽ፣ ዘኒቂያ፣ ሦስት መቶ ዓሥራ ስምንቱ ሊቃውንት በሃያ አራተኛው አንቀጽ፣ “ወንዶች ሴቶችን፣ ሴቶች ወንዶችን አያንሡ፤ ወንዶች ወንዶችን፣ ሴቶች ሴቶችን ያንሡ እንጂ” ማለታቸው ተገልጿል (ፍት.ነ አ.3 1957፡ 44)።

የክርስትናን አባትና እናት በሚመለከት ለቀሲስ ኃይለ መስቀል ጸጋዬ (መጋቢት 8 ቀን 2010 ዓ.ም) በተደረገ ቃለ መጠይቅ ሴቶች ሴቶችን፣ ወንዶች ወንዶችን የሚያነሡበትን ምክንያት እንዲህ አስረድተዋል።

የክርስትና አባትና እናት ዓላማው ክርስትና ያነሧቸውን ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው በክርስትና ሃይማኖት ሥርዓት እያስተማሩ ኮትኩተው እንዲያሳድጓቸው ነው። በዚህ ወቅት ወንዱ የሴቲቱን፣ ሴቷ ደግሞ ወንዱን ማስተማር አይችሉም። የተለያየ ፆታ ከሆኑ ትምህርተ ክርስትናን በሚያስተምሩበት ወቅት መቀራረብ በየጊዜው መገናኘት ይኖራል። በዚህ ወቅት ሥጋዊ ፍላጎት የመቀስቀስ ዕድሉ ሰፊ ነው። ስለሆነም በዝሙት ኀጢአት እንዳያጋልጣቸው፣ በፍትወትም እንዳይፈተኑ ተመሳሳይ ፆታ እንዲሆን አባቶች ሥርዓት ሠርተዋል። ባጋጣሚ እንኳን የተለያየ ሥፍራ የሚኖሩ ቢኾንና ከጊዜ ብዛት መረሳሳት ቢከሠት ሳይተዋወቁ ሊጋቡ ይችላሉና ሴት ወንድን፣ወንድ ድገሞ ሴትን ክርስትና ማንሳት አይችሉም። በተጨማሪም ሥጋ ወደሙ በሚያቀብሉበት ወቅት ወንድ በሴት፣ ሴት ደግሞ በወንድ ቦታ ኾነው ማቀበልም ስለማይገባ ነው። የክርስትና እናትና አባት ዋናው ዓላማም ሃይማኖትን እያስተማሩ ማሳደግ ነው ብለዋል።

መጋቢት 9 ቀን 2010 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ አገልጋይ የኾነውን ዲያቆን ሚሊዮን ተሾመን ስለ ክርስትና አባትና እናት ኃላፊነት ጠይቄው ነበር። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕፃናትን ክርስትና ስታነሣ ከወላጆቻቸው በተጨማሪ ለወንዶቹ የክርስትና አባት፣ ለሴቶቹ ደግሞ የክርስትና እናት በክርስትና እምነት ኮትኩተው እንዲያሳድጓቸው ኀላፊነት ትሰጣለች። ኀላፊነቱን የሚቀበሉት ክርስትና በሚነሳበት ዕለት ሥርዓቱን በሚያስፈጽሙ ካህናት፣ ቃል እንዲገቡ በማድረግ ነው። የዚህ መሠረታዊ ዐላማው ሃይማኖትን ከመሠረቱ ማስተማር ነው። በክርስትናው ዕለት ክርስትና አንሺዎች ጸሎተ ሃይማኖትን እንዲደግሙ ይደረጋል። ይህም ስለ ሃይማኖት የሚያስተምር ጸሎት ነው፤ ሴት ሴትን ወንድ ወንድን የሚያነሱበት ዋና ዓላማ ሃይማኖትን በተመሳሳይ ፆታ ማስተማር ነው። ክርስትና አባት ወይም እናት ማለት ክርስቲያናዊ ትውፊትን ጠብቀው በመጠየቅ፣ በማስተማር የሚሳድጉ ናቸው በማለት አስረድተውኛል።

በአጠቃላይ ቅድመ ክርስትና ክዋኔዎች ከጥንት ጀምሮ በቅብብል የመጡ ትውፊቶችን የሚያሳዩ ናቸው። የአዳምንና የሔዋንን ወደ ገነት መግባት መነሻ በማድረግ፣ በኦሪቱ ጊዜ ሕፃናት ወደ ቤተ መቅደስ ለመባረክ በወላጆቻቸው ይወሰዱ ነበር። እነዚህ ምሳሌዎች  ደግሞ በድግግሞሽና በክዋኔ ለትውልድ ሲተላለፍ የቆዩ ናቸው። ከክርስትና መምጣት በኋላም ለክርስትና መነሻ ቀን ወስነው የጥንቱንም ጠብቀው በቅብብል እየከወኑት ይገኛሉ። ክርስትናውን ተቀብለዋል፤ ጥንት የነበረውን ሥርዓትም በትውፊት እያስቀጠሉ እስካሁንም ድረስ መተላለፋቸውን መረዳት ይቻላል።

## 4.1.2 ሥርዓተ ክዋኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥምቀተ ክርስትና ሥርዓት ተሠርቶለት፣ ከዋኝና አስከዋኝ ተዘጋጅቶለት የሚፈጸም ሥርዓት ነው። ሥርዓተ ክዋኔውን ለማስፈጸም የሚመድቡት ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ክህነት የሌለው ማንኛውም ግለሰብ የማጥመቅም ኾነ ሜሮን የመቀባት ሥርዓት መፈጸም አይችልም።

በቤተ ክርስቲያኒቱ አባል የኾነ ሰው ልጅ ሲወልድ በ7ኛው ቀን ንስሐ አባቱን ወደ ቤት በመጥራት ጠበል እንዲረጭለት ያደርጋል። የተወለደው ሕፃን ወንድ ከኾነ 40ኛው ቀን ሴት ከኾነች ደግሞ 80ኛውን ቀን መቼ እንደሚውል ከንስሐ አባታቸው ጋራ ሆነው ይወስናሉ።

ወላጆች ወደ ቤተ ክርስቲያን ኼደው ወይም በንስሐ አባታቸው አማካይነት የክርስትናውን ዕለት ያስመዘግባሉ፡፡ የሕፃናቱ መጠመቂያ ቀን ከእሑድ እስከ እሑድ በየትኛውም ቀን ላይ ቢውል ጸሎተ ቅዳሴ ይዘጋጅላቸዋል፡፡

የክርስትናን ሥርዓተ ክዋኔ ለመረዳት የመጀመሪያ ምልከታዬን ያደረግሁት የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ በሰላሌ ሀገረ ስብከት፣ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ነው፡፡ ዕለቱ ማክሰኞ ዐቢይ ጾም ከገባ ኹለተኛው ቀን ሲኾን፣ በቦታው የኼድኩት ከአራት ቀን በፊት ዓርብ ስለነበር ማክሰኞ ዕለት ክርስትና እንደሚኖር ቀድሜ ዐውቄያለሁ፡፡ ማክሰኞ ከጠዋቱ 12፡30 ደርሼ ጸሎተ ኪዳን ከተጠናቀቀ በኋላ የክርስትና ማንሻ ቦታውን ተመለከትኩ፤ ሰዓቱንም አረጋገጥኩ፡፡

አጠቃላይ የዕለቱን ሥርዓት እንደሚከተለው ተከታትየዋለሁ፡፡ የክርስትና ሥርዓቱ የተጀመረው በ5፡30 ላይ ነው፡፡ ሥርዓቱ ከመጀመሩ በፊት ክርስትና የሚያስነሡት ወላጆችና አቋቋሚዎች ከገዳሙ ግቢ ውስጥ በስተደቡብ በኩል ተቀምጠው ተመለከትኩ፡፡ ኹሉም ነጭ ልብስ ስለለበሱ ክርስትና የሚያስነሡ መኾናቸውን ከአለባበሳቸውና ከብዛታቸው ገምቻለሁ፤ ከዚያም በአቅራቢያቸው ቆምኩ፡፡ አንድ መነኩሴ መጡና ወደ ቤተ ክርስቲያኑ እንዲገቡ ነገሯቸው፡፡ እየተሳለሙና ጫማቸውን እያወለቁ በፊት ለፊቱ በር በኩል ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ እኔም ዐብሬ ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ ቦታው በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ፣ ከመሬት በታች፣ በስተደቡብ አቅጣጫ ይገኛል፡፡ በዚህ ስፍራ ውኃ እንዲይዝ ተደርጎ ለጥምቀተ ክርስትና የተዘጋጀ የማጥመቂያ ገንዳ አለ፡፡ ገንዳው ሕፃናትን ለመዝፈቅ እንዲመች ኾኖ በአንስተኛ ጥልቀት የተሠራ ነው፤ በግምት 4x4 ሜትር ስፋት ሲኖረው በክብ ቅረጽ የተሠራ ነው፡፡ በገንዳው ዙሪያ ዐምዶች አሉ ከገንዳው ቢያንስ የኹለት ሜትር ርቀት ይኖራቸዋል፡፡ አጠቃላይ የክርስትና ማንሻው ሥፍራ ገጽታው የክብ ቅርጽ አለው፡፡ ግድግዳው ዙሪያውን በተለያዩ የቅዱሳን ሥዕሎች የተሞላ ነው፡፡

## ፎቶ 7 የክርስትና ማንሻው ገንዳ በከፊል



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ወጣቱ መነኩሴ ሴቶችን ከክርስትና ማንሻው በስተደቡብ፣ ወንዶችን ደግሞ በስተሰሜን በኩል እንዲቆሙ ነገሯቸው፡፡ የሕፃኗ ወላጅ እናት ወንበር ተሰጥቷቸው ቁጭ እንዲሉ ተደረገ፡፡ አቀማመጣቸውም ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው ነበር፡፡

የሕፃኗ ክርስትና እናትና እና ሕፃኗ አንድ ዐይነት ነጭ የሀገር ባህል ልብስ ለብሰዋል፡፡ ሌሎቹ በአጃቢነት የቆሙትም የለበሱት ነጭ ልብስ ነው፡፡ ሴቶቹ ከላይ ነጠላ ደርበዋል፡፡ ቀሚሳቸው ጫፍ ላይ ያለው ጥለት ከነጠላው ጥለት ጋራ ተመሳሳይ ነው፡፡ የጥልፍና የቀለሙ ዐይነት የእያንዳንዳቸው የተለያየ ነው፡፡ አባት እንደኾነ ጠይቄው የነገረኝ በልብሱም ቀድሜ የገመትኩት ከባለቤቱ ጋር ተመሳሳይ የኾነ ጥለት ያለው ነጭ ልብስ ለብሷል፡፡ወንዶቹም አጃቢዎች ነጭ የሀገር ባህል ለብሰዋል፡፡ሌላ ዐይነት የለበሱም ነበሩ፡፡ ሁሉም ነጭ ነጠላ መስቀልኛ አጣፍተው ለብሰዋል፡፡ ሴቶቹ ኹሉም ራሳቸውን ተከናንበዋል፤ ቀሚሳቸው እስከተረከዛቸው ድረስ የሚሸፍን ረዥም ነበር፡፡

ልክ 5፡30 ሲኾን ሥርዓተ ክዋኔውን የሚያስፈጽሙት ካህናት ወደ ክርስትና ማንሻው ቦታ መጡ፡፡ ወደ ውስጥ ሲገቡ አንደኛው መነኮስ ካህን ጽናሕ በቀኝ እጃቸው ይዘው ነበር፡፡ በግራ እጃቸውም ከዕንጨት የተሠራ መስቀል ይዘው ማዕጠንቱን እያጠኑ ሦስት ጊዜ የክርስትና

ማጥመቂያውን ገንዳ ዞሩት። ከመጡት አገልጋዮች ውስጥ ልብሰ ተክህኖ ያልለበሱት መነኩሴ ማተብ ይዛችኋል በማለት ባለጉዳዮችን ጠየቁ። ክርስትና የምታነሣዋ እናት ሦስት ዓይነት ቀለም (ነጭ፣ ቀይና ጥቁር) ያለው ክር ሰጠች። ቅብዐ ሜሮን ከያዘው ጠርሙስና ከውኃው አጠገብ አስቀመጡት።

ገባሬ ሠናዩ ካህን መጽሐፈ ክርስትና የሚባለውን መጽሐፍ በግዕዝ በማንበብ ጸሎተ ክርስትናውን ማድረስ ጀመሩ። መጽሐፉ በግዕዝና በአማርኛ የተጻፈ ነው። ካህኑ ጸሎቱን ሲያደርሱ ፊታቸውን ወደ ማጥመቂያው ገንዳው አዙረው ነበር። ሕፃኗን ያቀፈችው እናት ብቻ ተቀምጣለች። ሌሎቹ ግን ኹሉም ልክ ጸሎቱን ሲጀምሩ ከመቀመጫቸው ተነሱ። ንፍቁ ካህን የነበሩት ወደ ውስጥ ከገቡበት ሰዓት ጀምሮ ማጠኛውን ወደፊትና ወደ ኋላ በማድረግ ሲያጥኑ ነበር፤ ማጠኛው ከታች ፍም ለመያዝ እንዲመች ተደርጎ የተሠራ ነው። እጅ መያዣው ድረስ በቀጭኑ የተወጠሩ ዐምስት አውታሮች አሉት፤ ጫፉም ላይ የመስቀል ምልክት አለበት።

**ፎቶ 8፡ የሕፃኗ እናት ፊቷን ወደ ምሥራቅ አዙራ ተቀምጣ እና ቄሱ ዕያጠኑ**





**(ፎቶ በአጥኚው)**

መሪው መነኩሴ በግራ እጃቸው ዘወትር ከሚያዘው የእጅ መስቀል በመጠኑ ከፍ ያለ፣ ከዕንጨት የተሠራ መስቀል ይዘዋል። ከጎናቸው የቆሙት ካህን በቀይ ልብስ የተሸፈነው አትሮንስ ላይ በማስቀመጥ ጸሎት ማድረስ ጀመሩ። ዐልፎ ዐልፎ ድምፃቸውን ሳያሰሙ እንዳንዴም እየተሰሙ በግዕዝ ቋንቋ ማንበብ ጀመሩ። አንደኛው ዲያቆን በሰው ቁመት ልክ በዕንጨት ላይ የተሰካና የጨርቅ መያዣ ያለው ትልቅ መስቀል ይዟል። ከጎኑ ጥላ የያዘ ሌላ ዲያቆን ቆሟል። ኹለቱም የለበሱት አንድ ዓይነት የመቀደሻ ልብስ ነው። ሕፃኗን ካቀፈቻት

እናት ፊት ለፊት በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ ቆመዋል፡፡ ከዲያቆናቱ በተቃራኒ አቅጣጫ በስተምዕራብ በኩል ዋናው መነኩሴ ቆመዋል፡፡

ከዚያ ቀጥሎ ሦስተኛው ካህን መዝሙረ ዳዊትን ድምፃቸውን በማሰማት መጸለይ ጀመሩ፡፡ እኒህ መነኩሴ ቅብዐ ሜሮን ያለበትን በመጠኑ አነስ ያለ ጠርሙስ እና ለክርስትናው የሚጸለዩ መጻሕፍትን በማጥመቂያው አጠገብ በሚገኝ ስፍራ ላይ ሲያስቀምጡ የተመለከትኳቸው ናቸው፡፡ ሥርዓቱን ለማስፈጸም የቀረቡት ካህናት አብዛኞቹ ቆብ ጭነዋል፡፡ በወጣትነት ደረጃ የሚገኙ መስቀልኛ ነጠላቸውን አጣፍተው ለብሰዋል፡፡ ሻሽ ያልጠመጠሙ፣ መቋሚያ የያዙና ባዶ እጃቸውን የቆሙም ነበሩ፡፡

**ፎቶ 9 በክርስትናው ወቅት የነበሩ ካህናት አቋቋም በከፊል**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

በጥምቀተ ክርስትና ወቅት የሚጸለየው ጸሎት በመጽሐፈ ክርስትናው ላይ በቅደም ተከተል ሰፍሯል፡፡ በቃል፣ በንባብና በዜማ ቅብብሎሽ ያቀርቡታል፡፡ በዜማ የሚጸለዩት ምን እንደሚባል በዕለቱ መሪው ካህንን ጠይቄ ነበር፡፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ወቅት የሚከናወን እንደኾነ ነግረውኛል፡፡ በማስከተልም በሥርዓቱ የሚባለውን የመጀመሪያውን የዜማ ጸሎት ዲያቆኑ “ተንሥኡ ለጸሎት” “ለጸሎት ተነሡ” በማለት ጀመሩ፡፡ የዚህ የጸሎት ኺደት በግል ብቻ የሚባል አልነበረም፡፡ ካህኑ ያዜማሉ ሌሎች ካህናት በዜማ መልስ ይሰጣሉ፡፡ ካህኑ ይቀጥላሉ፤ ዲያቆናቱና ሕዝቡ ይቀበላሉ፡፡ ከታዳሚዎች ውስጥ በተሰጥዎው ወቅት ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ በቅብብልና በዜማ ሲቀርብ የነበረው ጸሎትና በየድርሻቸው ተከፋፍለው በንባብ ያቀረቡት ሥርዓት ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ነበር፡፡

በሥርዓተ ክርስትና ወቅት የሚጸለየው ጸሎት አጠቃላይ ምን ምን እንደሚባል ዲያቆን ተመስገንን ጠይቄ እንዲህ ነግረውኛል፡፡ የመጀመሪያው ጸሎተ ጥምቀት በመጽሐፈ ክርስትናው የመጀመሪያ ክፍል የቀረበ ነው፡፡ ይዘቱም ዐዲስ ተጠማቂዎች በመንፈስ ቅዱስ ሀብት የጸኑ እንዲኾኑ፣ ፈጣሪ ብርታት እንዲሰጣቸው፣ ከዚህ ቀደም የሠሩትን ኀጢአት ይቅር እንዲላቸው፣ የተማሩትን የእግዚአብሔን ቃል እንዲያስተውሉ የሚጸለይ ነው፡፡ በተጨማሪም በጥምቀት ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ ለመወለድ ዝግጁ እንዲኾኑ፣ ክርስቲያን ኾነው አምላካቸውን በማወቅ እንዲያመሰግኑና አጽናኝ የኾነውን መንፈስ ቅዱስ እንዲያገኙ የሚጸለይ ነው፡፡ ሌላው በዘይቱ ላይ ይጸልያሉ፡፡ ይህም ዘይቱ የተቀደሰና አጋንንትን ኹሉ የሚያርቅ እንዲኾን ነው፡፡ በዚህ ወቅት ዘይቱ ለኹለተኛ መወለድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ማኅተምነት ዝግጁ ይኾናል፤ በመንፈስ ቅዱስም ይለውጠዋል በማለት ገልጸውልኛል( የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡

ዲያቆኑ ጸልዩ ይላሉ፡፡  ስለ ስማቸው ካህኑ ይጸልያሉ፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንዲኾኑና ለበጎ ሥራ ኹሉ የተዘጋጁ  የመንፈስ ቅዱስ ንጹሕ ዕቃ እንዲኾኑ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይጸልያሉ፡፡ ካህኑ ሜሮኑን ካነሡ በኋላ በመስቀል አምሳል እያመሳቀሉ ውኃው ላይ ከፍ አድርገውና ባርከው የበንባብ ጸሎት ማድረግ ጀመሩ፤ በመቀጠልም  ውኃው ላይ ሦስት ጊዜ እፍ አሉበት፡፡

የዚህን ምሳሌ መረጃ አቀባዮቼ እንዲህ  ገልጸውልኛል በውኃውና ዘይቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ እንዲረብበት፣ በጥምቀት ለሚገኘው አዲስ ልደት እና ዕጥበት ስጦታ የተዘጋጀ እንዲኾን፣ በውኃውና በዘይቱ ላይ የእግዚአብሔር ኃይልና ቅዱስ መንፈስ እንዲያድርበት ይጸልያሉ፡፡ ወደ ጥምቀተ ክርስትና የመጡ ሰዎች ዳግመኛ ከመንፈስ ቅዱስ እንዲወለዱና ከኀጢአታቸው የነጹ

እንዲኾኑ የሚያደርጋቸው፣ ካህኑ ጸሎቱን አድርሰው ሜሮኑን በመስቀል አመሳቅለው ሲባርኩት ውኃው ፍጹም መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል፡፡ በፈጣሪ አምላካዊ ኃይል ዝግጁ ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡

ካህኑ ሲጸልዩ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ የታየውን ጸጋና ኃይል በዚህ ውኃና ዘይት አድርግ እያሉ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ውኃው የዮርዳኖስን በረከት የያዘ፣ የእግዚአብሔር ኃይል ያለበትና የተቀደሰ ውኃ ይኾናል ተብሎ ይታመናል፡፡ ተጠማቂዎች በዚህ ውኃ ሲጠመቁ ከኀጢአት የነጹና ዐዲስ ልጅነትም የሚያገኙ ይኾናሉ ሲሉ አስረድተውኛል፡፡

ካህኑ ዘይቱ ላይ ሲጸልዩ የዘይቱን ዕቃ ወደ ላይ አንሥተውት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ካህኑ ሕፃኗ ላይ እጃቸውን ጭነው መጸለይ ጀመሩ፡፡ በማስከተልም የሕፃኗን ልብስ አወለቁ፣ ወደ ምዕራብ እንድትዞርም አደረጉ፣ እናቲቱ እንዳቀፈቻት ነበር፤ የክርስትና እናቷ የሕፃኗን ቀኝ እጅ እንድትይዝ ከተደረገ በኋላ "በክርስቶስ አምላክነት አምናለሁ፤ ሰይጣንን ክጀዋለሁ" እያለች ጮክ ብላ ሦስት ጊዜ ተናገረች፡፡ ‹‹ጸሎተ ሃይማኖትንም›› በመጽሐፍ እንድታነብ አደረጉ፡፡

የክርስትና እናት ስለ ሕፃኗ ዋስ ኾና ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ መሰከረች፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት የክርስትና እናት፣ክርስትና የምታነሣትን ልጅ ከልጅነቷ ጀምራ ሃይማኖትን የማስተማር ኀላፊነት የሚሰጣት በዚህ ዕለት ስለኾነ ነው፡፡

ከወላጆቿ በበለጠ የሃይማኖቷ ምስክር ወይም ዋስ የክርስትና እናቷ እንደኾነች በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 3 በመጽሐፈ ክርስትና (ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን 1944፣ 30) ተገልጿ፡፡ ወላጆች በሥጋ እናትና አባት ሲኾኑ ክርስትና ያነሣችዋ ሴት መንፈሳዊት እናት ትባላለች፡፡ ወደ ቤተክርስቲያን እንድትኼድና የሃይማኖት ትምህርት እንድትቀሥም የምታደርጋት፤ ዋስ ኾና የምታስነሣት፤ የክርስትና እናቷ እንደኾነች ተገልጿል፡፡

የካቲት 12 ቀን 2010 ዓ.ም በሰሜን ምዕራብ ሸዋ ዞን፣ ሰላሌ ሀገረ ስብከት፣ በደብረ ሊባኖስ ገዳም የምልከታዬ ዕለት የወ/ሮ ሐና ደምሠውን ልጅ ክርስትና ያነሡትን እናት ለምን ክርስትና እንደሚያነሡ ጠይቄያቸው ነበር፡፡ እኔ ክርስትና የማነሣው ከልጂቱ ቤተሰቦች ጋራ በጣም ስለምንቀራረብ ልጃቸውን ክርስትና ሳነሣ ዝምድናችንን የበለጠ ለማሳደግ ነው፡፡ ቤተሰባዊነታችንንም ከዚህ የተሻለ እንዲጠናከር በማሰብ ነው ብለውኛል፡፡ የነርሱን ልጅ ለማንሣት ሦስት ሴቶች እኩል ጠይቀን ነበር፤ መጨረሻ ላይ በዕጣ ተለየን፡፡ እኔ እንዳነሣ ዕጣ

ወጣልኝ፤ በጣም ደስተኛ ነበርኩ ብለውኛል። በቃለ መጠይቁ ወቅት ፊታቸው ላይ የደስታ ፈገግታ እየተመለከትኩ ነበር።

ሕፃኗ በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ እንድትወለድ ካህኑ እጃቸውን ጭነው ጸሎት መጸለይ ጀመሩ። የሚጸልየው ጸሎት ይዘቱ ተጠማቂዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጸንተው ከአጋንንትና ከርኩሰት፣ ከኀጢአትም ኹሉ ነጻ የወጡ እንዲኾኑ፣ በነፍሳቸው ሃይማኖትን የሚያጎድል ሐሳብ ኹሉ በርሱ ስም ከአዕምሯቸው እንዲሸሽ፣ ከአጋንንት ተንኮል የነጹ እንዲኾኑ ነው። ይህን ከጸለዩ በኋላ፣ ተጠማቂያዋን ዲያቆኑ ፊቷን ወደ ምዕራብ እንድትዞር አደረጓት። ወደ ምዕራብ ዞራ የነበረችው ሕጻን ወደ ምሥራቅ እንድትመለስ አደረጓት።

**ፎቶ 10 መነኩሴው ዲያቆን ሕፃኗን ወደአራቱም አቅጣጫዎች ሲያዞሯት**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

መጀመሪያ ወደ ምዕራብ፣ ከዚያም ወደ ምሥራቅ ፊቷን እንድትመልስ የተደረገበትን ምክንያት አባ ኪዳነ ቃል ጠይቄያቸው ነበር። ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ መመለሳቸው፣ ምዕራብ ፀሐይ የምትጠልቅበት ስለኾነ የጨለማና የዲያብሎስ ማደሪያ፣ የሲዖል ምሳሌ ነው። የዲያብሎስ ተግባራት በጨለማ ይመሰላሉ። ጨለማ የዲያብሎስ ማደሪያ ነው ተብሎ ይታመናል፤ ምሥራቅ ደግሞ የፀሐይ መውጫ ስለኾነ የብርሃን ምሳሌ ነው። ብርሃን የሥላሴ ማደሪያ ነው ተብሎ ይታመናል። አንድም ተጠማቂዎች በጥምቀተ ክርስትና፣ ከኀጢአትና ከአለማመን የጨለማ ምሳሌ ወደ ማመን፣ ክርስቲያን መኾን የብርሃን ምሳሌ እየመጡ ስለኾነ ነው። አንድም ጨለማ የገሃነም እሳት፣ ብርሃን ደግሞ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናቸው።

በመኾኑም ተጠማቂዎች በጥምቀተ ክርስትና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግባታቸውን በምሳሌ የሚያሳይ ነው ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ (ቃ.መ. መጋቢት 13 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡

ከዚያ በመቀጠል መሪው ካህን ለሕፃኗ ስያሜ ሰጡ፣ በተጠማቂዋ ራስ ላይ እጃቸውን ጭነው መጸለይ ጀመሩ፡፡ ይህንንም "አንብሮተ እድ"[13] እንደሚባል ነግረውኛል፡፡ ካህኑ የተጠማቂዋን ስም "ስምኪ ይኩን ወለተ ሚካኤል" ብለው ስም አወጡላት፡፡ ሌላኛው ካህን ለክርስትና እናቲቱ እና ለልጂቱ አባት ‹‹ይህ የክርስትና ስሟ ነው፤ በማስታወሻ መዝግባችሁ ያዙ፤ ስታድግ ትነግሯታላችሁ›› አሏቸው፡፡ ስለ ስም ስያሜው ለምን እንደሚሰጥ በሐመረ ኖኅ ሰንበት ትምህርት ቤት የ0ምስተኛ ዓመት /ኀምሳይ ክፍል/ ተማሪዎችን በቡድን ባወያየሁበት ጊዜ ጠይቄያቸው ነበር፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የሚያውቀው በክርስትና ስሙ ነው፡፡ ይህም ክርስትና በተነሣ ጊዜ የሚሰጠው ስያሜ ነው፡፡ በዚህ ዕለት ክርስትና የተነሡ ሕፃናት በማይታይ ቅዱስ ምስጢር የመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ሲያገኙ ከኢየሱስ ክርስቶስ አባል ይኾናሉ፡፡ ከነቢያት፣ ከሐዋርያትና ከቅዱሳን አባቶች የክርስትና መሠረት የሚደመሩት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትናን ሲያገኙ እንደኾነ ገልጸውልኛል፡፡

በመቀጠል ሌላኛው ካህን በግዕዝ ንባብ ማድረስ ጀመሩ፡፡ በተከታታይ ጸሎተ ጥምቀት የሚባለውን የመጨረሻ ጸሎት ስለ ሰላም፣ ስለ ማኅበር፣ ስለ ጳጳሳት፣ ስለ ሕዝበ ክርስቲያን እና ስለ ሀገር፣ ሥርዓተ ቅዳሴ ላይ የሚባለውን ከተንሥኡ ለጸሎት እስከ ኪዳን ድረስ ያለውን፣ በመጽሐፈ ክርስትናው የሰፈረውን፤ በቅደም ተከተል በዜማና በንባብ በመቀባበል፣በለሆሳስ አንዳንዴም ጮክ እያሉ በጋራ ጸለዩ፡፡

ዋናው መነኩሴ ኹለት እጃቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረው ከፍ ባለ ድምፅና በዜማ መጸለይ ጀመሩ፡፡ "መስቀሉን ውኃው ውስጥ እየነከሩ ውኃውን ባረኩት፡፡ ‹‹አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ›› በማለት ጸለዩ፤ታዳሚዎችም ተሰጥዎውን ይመልሱ ነበር፡፡ ከዚያ በመቀጠል ወደ ውኃው ተጠጉ፡፡ አነስ ባለ ጠርሙስ ውስጥ የነበረውን ቅብዐ ሜሮን በቀጭን ዕንጨት እየነከሩ ወደ ማጠመቂያ ውኃው ውስጥ ሦስት ጊዜ ጨመሩት፤ አራቱንም ማእዘናት እየዞሩ ውኃውን በመስቀል ባረኩት፤ ከዚያም ውኃውን በመስቀል ባረኩት፡፡

[13]እጅ በመጫን መንፈስ ቅዱን ማሳደር ለማት ነው፡፡

"ብሩክ እግዚአብሔር ዘያበርህ ለኵሉ ሰብእ"[14] እያሉ ነበር ሜሮኑን የጨመሩት፤ ውኃው ላይም ሦስት ጊዜ እፍ አሉበት።

**ፎቶ 11 መሪው ካህን አሐዱ አብ ቅዱስ... ሲጸልዩ።**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ዲያቆኑ ሕፃኗን ከእናቷ ላይ ዕራቁቷን ተቀበሏትና ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ፣ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከደቡብ ወደ ሰሜን በአራቱ ማእዘን "ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ አሰግድሻለሁ" እያሉ ጮክ ብለው ተናገሩ። ዲያቆኑ ሲናገሩ ቄሱ ሕፃኗ ፊት ላይ መስቀሉን እያደረጉ ነበር። ይህ ምሳሌነቱ ምን እንደኾነ መምህር ፈቃዱ ሣህሌን ጠይቄ በተረዳኹት መሠረት።

ዲያቆኑ ጮክ ብለው የተናገሩት ስለ ሕጻኗ ነው። ነገር ግን ሌሎች ነፍስ አዋቆች ሲጠመቁ፣ ከሌላ እምነት ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የክርስትና እምነት የሚመጡ ዐዳዲስ ክርስቲያኖች፣ ካመኑ በኋላ የጥምቀተ ክርስትና ሥርዓት ሲፈጸምላቸው ይህን ቃል የሚናገሩት ተጠማቂዎቹ ራሣቸው ናቸው። ዲያቆኑ ትእዛዝ በማስተላለፍ አቅጣጫውን ይጠቁሟቸዋል። ምሳሌነቱ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማመናቸውን የሚያረጋግጡበት ኺደት ነው በማለት ገልጸውላኛል።

[14]ለሰው ልጆች ኹሉ ብርሃንን የሚሰጥ እግዚአብሔር የተመስገነ ነው ለማለት ነው።

ከዚያ በመቀጠል ካህኑ ሕፃኗን ወደ ማጥመቂያ ገንዳው ወሰዷት፤ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ እያደረጉም ውኃ ውስጥ ዘፈቋት፡፡ ግንባሯ ላይ መስቀል አድርገው "አጠምቀኪ በስመ አብ፣ አጠምቀኪ በስመ ወልድ፣ አጠምቀኪ በስመ መንፈስ ቅዱስ ወስምኪ ይኩን ወለተ ሚካኤል›› እያሉ፣ ሌላኛው ካህን ጭንቅላቷ ላይ ውኃውን እያፈሰሱ ሦስት ጊዜ አጠመቋት፡፡ ተጠምቃ እንደጨረሰች መሪው መነኩሴ ግንባሯ ላይ ሦስት ጊዜ እፍ አሉባት፡፡[15] ሦስት ጊዜ እፍ ያሉበትን ምክንያት ጠይቄ ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስን እያሳደሩባት እንደኾነ ገልጸውልኛል፡፡ ካህኑ እፍ እያሉ "ቅዱስ የኾነው መንፈስ ይደርብሽ" ባሉ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያድርበታል ተብሎ ይታመናል፡፡

የምስካየ ሕዙና መድኀኔ ዓለም ገዳም አገልጋይ የኾኑት አባ ኪዳነ ቃል በቃለ መጠይቅ (መጋቢት 17 ቀን 2010 ዓ.ም) እንደነገሩኝ በውኃ የመጠመቃችን የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ክርስቶስ ተሰቅሎ ነፍሱን ከሥጋው እንደለየ፣ የሰው ልጆች በጥምቀተ ክርስትና ወቅት በውኃ በተጠመቁ ጊዜ ከኀጢአት ይለያሉ፡፡ ካህኑ ተጠማቂዎችን ውኃ ውስጥ  ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ያደርጋቸዋል፡፡ የዚህ ምሳሌነት ኢየሱስ ክርስቶስ በመቃብር ውስጥ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት አድሮ እንደተነሣ  ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ ብለው ከውኃ ውስጥ ይወጣሉ ብለዋል፡፡ ሌላው ጥምቀት በውኃ የኾነበት ምክንያት ውኃ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳል፤ጥምቀትም ለሰው ልጅ ኹሉ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ይደርሳል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብር ሲነሣ ብርሃነ መለኮቱ ሳይለየው መለኮቱን ለብሶ ነው፡፡ ተጠማቂዎችም በውኃ ተጠምቀው ሲወጡ የመንፈስ ቅዱስን ብርሃን ለብሰው፣ ብርሃን ተጐናጽፈው ይወጣሉ በማለት የተጠማቂዎችን ከውኃ ውስጥ መውጣት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ጋራ በማመሳሰል፣ የውኃን በኹሉም ስፍራ መገኘትን ከጥምቀት ለኹሉም ሰው መሰጠት ጋራ አነጻጽረው ተርከውልኛል፡፡

ክርስቲያኖች በውኃ ለምን ይጠመቃሉ? የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ቀሲስ ኃይለ መስቀል ፀጋዬ ሐዋርያው ጳውሎስን ዋቢ አድርገው እንዲህ በማለት ገልጠውልኛል ‹‹የመጀመሪያው ሰው አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረሰ፤ በዚህም ምክንያት በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ እንዲቀጣና ወደ ገሃነም እንዲወርድ ተፈረደበት፡፡ ይህም በደልና ኩነኔ ለልጆቹ ኹሉ በውርስ ተላለፈ፡፡ ስለዚህ ሰው ሁሉ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ እንዲወለድ የግድ አስፈለገ››፡፡[16]

---

[15] በአብ በወልድ በመንፈስ ቀዱስ ስም አጠምቅሻለሁ ለማለት ነው፡፡
16 በመጽሐፈ ክርስትናው 1988፡5 ተገልጿል፡፡

ጥምቀት በውኃ ለምን እንደሚሰጥ፣ ምሳሌነቱ ምን እንደሆነ ለዲያቆን ተመስገን እና ለመርጌታ ተስፋ ዓለምነው {መጋቢት 20 ቀን 2010 ዓ.ም) ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው እንደሚከተለው ገልጸውልኛል፡ *በውኃ የምንጠመቅበት የመጀመሪያው ምሳሌ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚመላለስበት ወቅት ወደ ዮሐንስ ኼዶ የተጠመቀው በውኃ ነው። ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ውኃ የሰው ልጆች ያለ ምንም ችግር፣ ገንዘብ ሳያወጡ ማግኘት ስለሚችሉ ነው። ስለሆነም ጥምቀት ድኃና ሀብታም የማይለይ መኾኑን ለመግለጽ ነው። በተጨማሪም የውኃ ባሕርይ የሰውን ልጆች ከቆሻሻ፣ ከዕድፍ ያጠራቸዋል። ጥምቀት በማርና በወተት ቢኾን ሰውነትን ያቆሽሻል እንጂ አያነጻም፤ ለመታጠብ ተጨማሪ ውኃ ያስፈልጋል። ጥምቀትም ተጠማቂዎችን ከኀጢአት ያነጻቸዋል። ካህኑ ውኃውን በማጥመቂያው ገንዳ ወይም በብረት አድርገው ሥርዓተ ጸሎቱን ፈጽመው ሲባርኩት ውኃው ይለወጥና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጎን የፈሰሰውን ውኃና ደም ይኾናል ተብሎ ይታመናል።*[17]

ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅት ለንጊኖስ የሚባል ወታደር ፣ ‹‹ይህ ሰው አልሞተምን? ወይስ ሞቷል?›› ብሎ ለማረጋገጥ ኢየሱስን ጎኑን ቢወጋው ከጎኑ ውኃና ደም ወጥቷል ተብሎ ይታመናል። ስለዚህም ጥምቀት በውኃ የኾነበት አንዱ የዚህ ምሳሌ ነው። በካህናት ጸሎትና ቡራኬ ውኃው ወደ ኢየሱስ "ማየ ገቦ" እንደሚለወጥ፣ በውኃው ሲጠመቁ በርሱ  የጎኑ ውኃ እንደተጠመቁ ያምናሉ። ከዚያም በውኃ ተጠምቀው ክርስቲያን በኾኑ ጊዜ ከእግዚአብሔር ረቂቅ የኾነ መወለድን እንደሚያገኙና ከኀጢአትም እንደሚድኑ ያምናሉ። ለዚህም ማስረጃ የሚከተለውን ጥቅስ ነግረውኛል "*ከሥጋ የተወለደ ሥጋ* ነው፤ ከመንፈስ የተወለደ ግን መንፈስ ነው" የሚለውንና በ(ዮሐ 3÷6) የተገለጸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፣ለጥምቀት የተሰጠ ትእዛዝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በሐመረ ኖኅ ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ሰንበት ት/ቤት በቡድን ውይይት ወቅት መረጃ አቀባዮቹ እንደገለጹት በውኃ የምንጠመቅበት ሌላኛው ምክንያት የውኃ ባሕርይ ንጹሕ ነው። የሰው ልጅ ሰውነቱን በማር ወይም በወተት ቢታጠብ ሰውነቱን አቆሸሸ እንጂ አልነጻም። ስለዚህ ተጨማሪ ውኃ ያስፈልገዋል። ጥምቀትም በውኃ የኾነበት አንዱ ምክንያት ንጹሕ የሚያደርግ ስለሆነ ነው። የሰው ልጆች "ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ በጥምቀተ ክርስትና በተወለዱ ጊዜ ከኀጢአት የነጹ ይኾናሉ። በዙሪያቸውም የመንፈስ ቅዱስን *ሥራዎች* የሚሠሩ ከኀጢአት የራቁ ከቅዱሳን ሐዋርያትና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋራ አባል የኾኑ የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ይኾናሉ ተብሎ ይታመናል።

---

[17]*ማየ ገቦ ተብሎ የተገለጸውን፣ ወይም ለንጊኖስ የሚባለው ወታደር ኢየሱስን ጎኑን በወጋው ጊዜ የፈሰሰውን ውኃና ደም የሚገልጽ ነው።*

በተጨማሪም ክርስቲያኖች በውኃ የሚጠመቁበት ምሳሌ፣ ውኃ ኹሉም ሰው በእኩል ደረጃ የሚያገኘው ነው። ውኃ ሀብታምና ድኻ እኩል ያገኙታል። ኢየሱስ ክርስቶስም በውኃ የተጠመቀው ክርስትና ኹሉንም እኩል አንድ የሚያደርግ ነው ሲል ነው። ተከታዮቹን ሐዋርያትንም "ኺዱና በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፣ የሰው ልጅ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም" ብሎ ያስተማራቸው ለዚህ ነው ሲሉ ገልጸውልኛል።[18] (መጋቢት 22 ቀን 2010ዓ.ም)።

ሲያጠምቋት ወለተ ሚካኤል በአብ ስም፣ በወልድ ሰም፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቅሻለሁ እያሉ ሦስት ጊዜ አጠመቋት።

**ፎቶ 12 ካህናት በውኃ ሲያጠምቁ በከፊል**





**(ፎቶ በዳዊት ብርሃኑ)**

[18] ጥምቀት በውኃ እንዲኾን ሐዋርያት በኹለተኛው ቀሌምንጦስ በሠላሳ አራተኛው አንቀጽ ጥምቀት በውኃ ይኹን አሉ። በፍትሐ ነገሥት ፍት. መን.አን. ሦስት (1958፡45) ጥምቀት በውኃ መኾኑ ተገልጿል።

ተጠማቂዋ ስትጠመቅ የዳዊትን መዝሙር 50ኛውን[19] እንድታነብ በመጽሐፈ ክርስትናው ላይ ተገልጿል፡፡ ካህኑ በዐማርኛ ‹‹ወለተ ሚካኤል መንፈስ ቅዱስን ተቀባይ›› አሉ፡፡ በግዕዝ «ንሥኢ መንፈስ ቅዱስ" እያሉ ሦስት ጊዜ ፊቷ ላይ እፍ አሉባት፡፡[20]

ከተመለከትኳቸው አብያተ ክርስቲያናት ላይ ሜሮን ከመቀባታቸው በፊት በተጠማቂዎች ላይ እጃቸውን የመጫን ሥርዓት ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚያ በመቀጠል ጥቁር፣ ነጭና ቀይ ቀለም ያለውና በአንድነት የተገመደ ክር አንገቷ ላይ አሰሩላት፡፡ ማተብ በክርስትና ወቅት ለምን እንደሚታሰርና ምሳሌነቱ ምን እነደሆነ መረጃ አቀባዮቼን ጠይቂ ነበር፡፡ አንደሚከተለውም ገልጸውልኛል፡፡ ማተብ ዐዲስ ክርስቲያኖች ሲጠመቁ የሚያስሩት ክር ነው፡፡ ማተብ ዐተበ ከሚለው ግስ የወጣ አመለከተ፣መለያ ወይም ምልክት ማለት ነው፤ ለተጠመቁ ክርስቲያኖች ለሃይማኖት ምልክትነት፣መታወቂያነት፣መለያነት ከተጠመቁ በኂላ በአንገታቸው ላይ የሚታሰር ክር ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስንም ለማስታውስ በክሩ ላይ መስቀል አድርገው አንገታቸው ላይ ያስሩታል ብለውኛል፡፡

አዲስ ለተጠመቁ ክርስቲያኖች የክር ማተብ ለሃይማኖት ምልክትነት ወይም መታወቂያነት በአንገታቸው ይታሰርላቸዋል፡፡ ይህ ማተብ ማሰር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን ከሌሎች ክርስቲያኖችና ልዩ ልዩ የእምነት ተከታዮች መለያ ምልክትነት የሚያገለግል እንደኾነ መረዳት ይቻላል፡፡

አባ ኪዳነ ቃል  (መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም) በተደረገ ቃለ መጠይቅ ምልክት ማድረግ በዐዲስ ኪዳን የተጀመረ አይደለም ብለዋል፡፡ በኦሪት ዘመን ፈጣሪን የሚያመልኩ ሰዎች፣ ከጣኦት አምላኪዎች የሚለዩበት ምልክት ነበራቸው፡፡ አሁን ክርስቲያኖች የሚያስሩት ክር ከዚያ እየተወራረሰ የመጣ መኾኑን (ሮሜ 2÷11) ያለውን ጥቅስ ዋቢ አድርገው ገልጸዋል፡፡ አብርሃም በእምነቱ የግዝረትን ምልክት ተቀበለ በሐዲስ ኪዳንም የኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥት ወራሾች ለመኾን ጥምቀት ምልክት ሆኗል በማለት ምልክት ማድረግ በኦሪቱም የነበረ፣ በሐዲስ ኪዳንም የቀጠለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

19 50ኛውን መዝሙር ስለህጻኗ ክርስትና እናት ወይም አባት እንዲያነቡ መጽሐፈ ክርስትናው ላይ ተገልጿል፡፡ ነፍስ አዋቆች ከሆኑ ደግሞ መዝሙሩን የሚያነቡት ተጠማቂዎች ናቸው፡፡

[20]እነሆ መንፈስ ቅዱስን ተቀበይ ማለት ነው፡፡ ሐዋርያት በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን ያሳድሩ እንደነበር ምሳሌ በማድረግ ነው፡፡ በሐዋርያት ሥራ ተገልጿል ፡፡

መረጃ አቀባዮቼ (መስከረም 28 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገ ውይይት ) የማተብ ማሰር ምሳሌ ምን እንደኾነ የሚከተለውን ተረክ ገልጸውልኛል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ እናቱ ድንግል ማርያም አውራ ጣቱን አስራለች፡፡ ይህም ሦስት ምክንያቶች አሉት የመጀመሪያው ሕፃን ስለሆነ እንዲያጸናው ነው፡፡ ኹለተኛው ጣቱን ባይታሰር ምትሃት ነው እንዳይሉ፣ የርሱ መወለድ አሁንም ድረስ ጥያቄ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በወቅቱ የርሱን መወለድ የተመለከቱ ሁሉ ጣቱ ላይ ክር መታሰሩን መስክረዋል፡፡ ይህም ምትሀት አለመሆኑን ማስረገጫ ምስክርነት ነበር፡፡ ሦስተኛው አይሁዶች ልማዳችን ቀረብን እንዳይሉ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ልጅ ሲወለድ አይሁዶች ጣት ላይ ክር የማሰር ልማድ ስለነበራቸው የዚያን ልማድ አስቀረችብን እንዳይሉ አስራለች፡፡ ይህ ጣትን ማሰር እንደ ማተብ አብነት ሆኗል በማለት ማሠር፣ ምልክት ማድረግ በተለያዩ ቅዱሳት መጻሕፍት በተለያየ ዘርፍ መጠቀሱን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ማተብ የማሰርን ምሳሌ እንደሚከተለው አስረድተውኛል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበት ዓላማ የሰው ልጆችን በርሱ የበረከትና የምህረት ጥሪ ሰብስቦ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማውረስ ነው፡፡ በመጨረሻው ዘመኑ መስቀል ላይ ተሰቅሎ፣ ከመስቀል በኋላ ወደ ከርሰ መቃብር ወስደውት ነበር፡፡ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በዕለት ዐርብ ከመስቀል አውርደው ክር በማሰር በመግነዝ ሥርዓት ገንዘውታል፡፡ ያንን መግነዝ ለማጠየቅ፣ ለማሰብ ማተብ ይታሰራል በማለት ማተብ የማሰር ምክንያት አንዱ የኢየሱስ ክርሰቶስን መግነዝ ለማስታወስ እንደሆነ ገልጸውልኛል፡፡

ሌላኛው ተረክ ማተብ ማሠር የእስክንድርያ ክርስቲያኖችን ያስተምር የነበረው ሶርያዊው ያዕቆብ እንበረዲ በ5ኛው ምዕተ ዓመት ንስጥሮሳውያን እርሱ በሚያስተምራቸው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያኖች መካከል እየገቡ ስላስቸገሩት የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን ከንስጥሮሳውያን ለመለየት ጥቁር፣ ቀይ እና ነጭ/ቢጫ ክር በአንድነት ገምዶ ያስርላቸው ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወደ እስክንድርያ ክርስቲያኖች ከዚያም ወደ ኢትዮጵያ እንደገባ ይነገራል ብለውኛል፡፡

ኢትዮጵያውያንም በትውፊት አዲስ ክርስቲያኖች ሲጠመቁ ሦስት ዓይነት ክር ማሰር እስከ አሁንም ድረስ ቀጥሏል ፡፡ ሦስቱ ቀለማትም የራሳቸው ትርጉም አላቸው፡፡ የመጀመሪያው አንድ ላይ መገመዳቸው የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስን አንድነት፣ ሦስት መሆናቸው የሦስትነታቸው ምሳሌ ነው፡፡ ጥቁር መሆኑ የዘመነ ሰማዕታት ወይም በክርስትና ያለን መከራ ለማሰብ፣ ቀዩ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሰጠውን ሥጋና ደም ምሳሌ ነው፡፡ ነጭ ነው ቢሉ የጥምቀት፣ ቢጫ ነው ቢሉ ተስፋ መንግስተ ሰማያትን ለመጠየቅ እንደሆነ ገልጸውልኛል፡፡

የገዳም መነኮሳት ቢጫ ልብስ ይለብሳሉ የተስፋ መንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነው፡፡ አባቶች አምላካችን መንግሥተ ሰማያትን ያወርሰናል ሲሉ ቢጫ ይለብሳሉ፡፡ ተስፋ መንግሥተ ሰማያት አለን መንግሥቱን ያውርሰናል ተስፋ አለን የምናመልከው የምንገዛለት እግዚአብሔር የምንሻትን ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ያወርሰናል ሲሉ ቢጫ ይለብሳሉ በማለት የቢጫ ክር ትረጉምም ተስፋ መንግሥተ ሰማያት ምሳሌ እንደኾነ አስረድተውኛል፡፡

አባ ኪዳነ ቃል የአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫን አባባል ዋቢ አድርገው ሲያስረዱ ‹‹ሥላሴ ማኅተበ ብርሃን ኃይለ ሃይማኖቶሙ ለክርስቲያን›› ሥላሴ ለክርስቲያኖች ኹሉ የሃይማኖታቸው መታወቂያ ጉልበት የብርሃን ማዕተብ ወይም ምልክት ናቸው፡፡

ይህ ማዕተብ ምልክት እንደኾነ ኹሉ ጉልበትም ብርሃንም ኃይልም ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንደ ትምክህት ወይም በመስቀሉ ወይም በሥላሴ እንደ መመካት አድርገው ክርስቲያኖች ይጠቀሙበታል፡፡ ለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አለ ይላሉ፡፡ (ገላ. 6÷17) “እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜያለሁ” ይህ ማኅተም በሥጋው መሸከሙ በሥጋው ምልክት መያዙ ነው፡፡ በእኛ ሀገር ግንባራቸው ላይ መስቀል፣ እጃቸው ላይ፣ በግራ ቀኝ እጃቸውና በሥጋቸው ላይ የክርስቶስን መስቀል ምልክት ያደርጋሉ፡፡ በጥንቱ አስተምህሮ አካላቸው ላይ የመስቀል ማኅተም እየቀረጹ ማኅተም እያደረጉ ይታያሉ፡፡ (መኃልየ ማኅልይ ዘሰሎሞን 8÷6) “እንደ ማኅተም በልብህ እንደ ማኅተም በክንድህ አኑረኝ” ይላል፡፡ ይህ ማኅተም አሁንም ምልክት ሆኖ የሚታሠር በክንድ የሚያዝ፣ በአንገት የሚጠለቅ እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ነው ይላሉ፡፡

ማተብ ማሰሩ አኹን በቤተ ክርስቲያን ቀኖናዊ በኾነ መልኩ በያዕቆብ ዘእንበረዲ ቢጀመርም በመጽሐፍ ቅዱስ እየተብራራ እየተገለጸ የመጣ ትውፊትም ነው ብለዋል (ቃ.መ መስከረም 28/2011 ዓ/ም)፡፡ እኔም በምልከታዬ እንዳረጋገጥኩት ክርስትና የሚያስነሡ ግለሰቦች ሦስት ዓይነት ክር በክርስትናው ዕለት ይዘው ይመጣሉ፡፡ ለዚህ ጥናት በተመረጡት አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ባሉ ሱቆችም እነዚህ ክሮች ሲሸጡ ተመልክቻለሁ፡፡

**ፎቶ 13 ካህኑ ለተጠማቂዋ ማተብ ሲያስሩላት በከፊል**





**(ፎቶ በዳዊት ብርሃኑ)**

መነኩሴው ዲያቆን ሕፃኗን ዕራቁቷን እንዳቀፏት፣ መሪው መነኩሴ ከጠርሙሱ ውስጥ በጣታቸው እየጠቀሱ በመስቀል ምልክት ቅብዐ ሜሮኑን እያደረጉ በመጀመሪያ ግንባሯ ላይ ግራና ቀኝ ኹለት ቦታ ላይ ቀቧት፤ ከዚያም እፍ አሉባት፡፡

ከጥምቀቱ በኋላ አጥማቂውን ካህን የዚህን ትርጉም ጠይቄያቸው ነበር ዮሐንስ ኢየሱስን ክርስቶስን በዮርዳኖስ ውኃ ባጠመቀው ጊዜ ‹‹ይህ የምወደው ልጄ ነው›› የሚል ቃል ከሰማይ ከደመና መጥቷል፡፡ ይህም ቃል እንደተሰማና መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል እንደወረደ፣የባሕርይ አምላክ መሆኑን እንደመሰከረለት በማቴዎስ ወንጌል ያለውን ጥቅስ መሠረት አድርገው ገልጸውልኛል፡፡ ካህኑም በንፍሐት መንፈስ ቅዱስን እንደሚያሳድር ምሳሌቱም መንፈስ ቅዱስን ወደ ተጠማቂው ማሳደር እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

‹‹ወለተ ሚካኤል ቅብዓተ ሜሮን፣ ቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ እቀባሻለሁ›› እያሉ ግንባሯን በመስቀለኛ ሁለት ጊዜ ቀቧት፣ ፊቷን ቀቧት፣ ሁለቱን ዐይኖቿን፣ አፍንጫዋን፣ አፏን፣ ጆሮዋን ቀቧት፣ ‹‹በዘላለም ሕይወት አንድ ለመሆን ቅዱስ ቅባትን እቀባሻለሁ›› እያሉ ነበር የቀቧት፡፡ እርሳቸው የተናገሩት በግዕዝ ቢሆንም እኔ በአማርኛው ፍቺ አስቀምጬዋለሁ፡፡ የእጇን መኻል፣ ውስጡንና ውጪውን፣ ክንዶቿን፣ ሆዷን፣ እንብርቷንና ብልቷን፣ ጉልበቷን፣ እግሯን፣ የውስጥና የውጪውን፣ አንገቷን፣ ትከሻዋን “መሢሕ የሚሆን የአምላካችንን ልዩ ቅብዓት የማይፈታም ማኅተም የኾነ” እያሉ ቀቧት፡፡ ደረቷን፣ ጭኖቿን ‹‹በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እቀባሻለሁ›› እያሉ ቀቧት፡፡ በማስከተልም እጃቸውን ጭነው በንባብ

መጽሐፈ ክርስትናው ላይ በግዕዝ ማንበብ ጀመሩ፡፡ “የንባቡ ይዘትም በመንፈስ ቅዱስ በረከት የተሞላችሁ ሁኑ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የእግዚአብሔር ንጹሕ ሀብት ኹሉ የሚል ነበር፡፡

**ፎቶ 14 መሪው ካህን የሕፃኗን የተለያዩ የአካል ክፍሎች ሜሮን ሲቀቧት በከፊል**



**( ፎቶ በአጥኚው)**

እኔ በተመለከትኳቸው የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ሠላሳ ስድስቱ ሕዋሳት እንዲቀቡ ተጽፏል፡፡[21] ይኹንና በምልከታዬ ወቅት ባየኋቸው ሥርዓተ ክዋኔዎች በየትኛውም ቤተክርስቲያን ውስጥ እነዚህ የተጠቀሱት ሕዋሷት ሲቀቡ የማየት ዕድል አልገጠመኝም የተወሰኑትን ብቻ ቀብተው ይተዋቸዋል፡፡

የሠላሳ ስድስቱ ሕዋሳት ሜሮን የመቀባት ምሳሌ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ለመምህር ያሬድ ክብረት አቅርቤላቸው ቅብዐ ሜሮን ከጥምቀት በኋላ የሚፈጸምና ክርሰቲያኖች መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባቸው  የሚያረጋግጥ ማኅተም ነው፡፡ ተጠማቂዎች ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለዳቸው የሚረጋገጠው በሜሮን ማኅተምነት ነው ብለዋል፡፡

---

[21] (ክንፈ ገብርኤል፣ 1998፣35-36)፣(ፈቃዱ ሣህሌ፣ 2008፣56-88) ሜሮን የሚቀቡትን 36 ሕዋሳት በቅደም ተከተል አስፈረዋል፡፡

*የዚህ ምሳሌነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ሲወጣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ ዐርፎ የአብ የባሕርይ ልጅነቱ ተረጋግጧል፡፡ በመኾኑም አማኞች ሲጠመቁና በሜሮን ሲቀቡ የጸጋ ልጅነታቸው ይረጋገጣል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ አብራክ፣ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ መወለዳቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ አካላቸው በቅዱስ ሜሮን የከበሩላቸው ተጠማቂዎች ኹሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናቸው፡፡ በምድር ላይ ሲኖሩ ከኃጢአት የራቁ፣ መልካም ሥራዎች የሚፈጽሙ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች፣ የእግዚአብሔር ንጹሕ አካሎች ናቸው (ቃ.መ 26/07/2010)፡፡*

ከጥምቀት በኋላ በሜሮን ተቀብቶ የከበረ አካል በእምነቱ ተከታዮች የጸጋን ልጅነት ማግኘቱ የተረጋገጠ፣ የመንፈስ ቅዱስን ማኅተም የያዘ አካል ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህ አካል ደግሞ የእግዚአብሔር ማደሪያ፣ የክርስቶስ አካል ይኾናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የከበረ ሰውነት እጁ ከሌብነት፣ አፉ ክፉ ነገር ከመናገር የተቆጠበ ይኾናል፡፡ ከዝሙት የራቀና በጎ ለሚባሉ ተግባራት ብቻ የተሠራ አካል ነው ተብሎም ይታመናል፡፡

በተጨማሪም መረጃ አቀባዮቹ እንዳስረዱኝ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ሠላሳ ስድስት የአካል ክፍሎች እንዲቀቡ የታዘዘው፣ የሰውን ልጅ ሙሉ ሰው ኾኖ አካሉ እንዲቆም፣ ልጅ በመውለድ ዘር በመተካት በዚህ ዓለም እንዲኖር ያደረጉት እነዚህ ሕዋሳት እርስ በርስ ተሳስረውና ተገጣጥመው ስለኾነ ተለይተው ቅባቱ ይከናወናል፡፡ የዚህም ምሳሌነቱ ክርስቲያኖች ሲጠመቁ በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ልደትን ተቀብለው ሙሉ የእግዚኣብሔር ሰው እንደሚኾኑ ይታመናል፡፡ አንድም በዘር መርገም ሲተላለፍባቸው የነበረው ኀጢአታቸው ተወግዶላቸው በጥምቀት ንጽሐ ጠባያቸው ይመለስላቸዋል፡፡ በጥምቀት የእግዚኣብሔርን ልጅነት አግኝተውና ከብረው የመንግሥቱ ወራሾች እንደሚኾኑ የእምነቱ ተከታዮች ያምናሉ፡፡፡፡ እንዲሁም እነዚህ የአካል ክፍሎች እንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱና በሥጋዊ ሕይወቱም ጠንካራ ሰው ኾኖ እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ አንድ ሰው በጥምቀት ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል፤ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያድረበታል፤ ይህ ኃይል ብርታትን የሚሰጥ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለሆነም ቅዱስ ሜሮን ሰው በተሰጠው አካል፣ አዕምሮና ዕውቀት ጠንካራ ኾኖ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያደርግ ነው፡፡ መንፈሳዊና ሥጋዊ የሚባሉ ነገሮች የተሳሰሩ ናቸው፡፡ መንፈሳዊ ለመኾን በሥጋ መቆም ይጠበቅበታል፡፡ መንፈሳዊ ጥንካሬ የሚባለው አካልና መንፈስ ተለይተው አይደልም፤ በጥምቀት የሚገኘው በሜሮን የተረጋገጠው የእግዚአብሔር ኃይል፣ ጸጋና በረከት መንፈሳዊ አቅምን በጨመረ ቁጥር ሥጋንም እየቀደሰ ሰዎች በሥራቸው ብርቱና

ስኬታማ እንዲኾኑ ያደርጋል ብለው ያምናሉ፣በነፍሳቸውም በእግዚአብሔር ፊት ያለነቀፋ እንዲቆሙ የሚያደርግም ነው (ቃ.መ መስከረም 28/2011 ዓ.ም)፡፡

ከሜሮን የሚገኘውን ጥቅም እንዲገልጹልኝ በማኅበረ ቅዱሳን ስድስት መምህራን በቡድን ባወያየሁበት የሚከተለውን ሐሳብ ገልጸውልኛል፡፡ ምእመናን በጥምቀት ያገኙት የመንፈስ ቅዱስ ሀብተ ጸጋ የሚረጋገጠውና የሚጸናው በሜሮን ማኅተምነት ነው፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ በጥምቀት ተጀምሮ በሜሮን ታትሞ ይጸናል፡፡ በዚህ ቀን ዐዲሱ ተጠማቂ የቤተ ክርስቲያን ልጅ፣ የክርስቶስ አባል ይኾናል፡፡ ሕፃናት ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚዘጋጁት በዚህ ቀን በተሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው፡፡ የሰው ልጅ ለተፈጠረበት ዓላማ የሚሠራ ኾኖ የሚዘጋጀው በዚህ ቀን ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያን አባልነቱ ተረጋግጦ ክርስቲያን ይኾናል፡፡ አማኞች በፈጣሪ ጸጋ በክርስቶስ ጸጋ ያድጋሉ፡ የሃይማኖትን ፍሬ እንዲያፈሩ፣ የመልካም ፍሬ መገለጫዎች እንዲኾኑ የሚያበቃቸው በዚህ ቀን ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ተሰጥቷቸው፣ በሜሮን የመንፈስ ቅዱስ ማኅተምነት ጸንቶ ሲረጋገጥ ነው ብለዋል፡፡ (መጋቢት 26 ቀን /2010 ዓ.ም)፡፡

ሕፃኗ ስትጠመቅ ጸጉሯን ተላጭታና ዕራቁቷን ኾና ነበር የተጠመቀችው፡፡ ‹‹ንዑስ ክርስቲያን›› አዲስ አማኞች ሲጠመቁ የተሠሩትን ሹሩባ ይፈታሉ፤ በየትኛውም አካል ላይ ያሉ ጌጣጌጦችን ያወልቃሉ፡፡ ለምን ዕራቁቷን እንደኾነችና ጸጉሯን ተላጭታ ተጠመቀች ብዬ መሪጌታ ተስፋዬ ዓለምነውን ጠይቄአቸው የሚከተለውን ብለውኛል፡፡

ከሰው ልጆች አፈጣጠር ስንነሳ ጌጣጌጦች በኋላ የመጡ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የሰው ጥንተ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው ፡፡ መቀደስ ያለባቸውም መጀመሪያ የተፈጠሩት እንጂ በኋላ ሰው በፈጠራቸው ጌጣጌጦች አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ መጀመሪያ ባለተፈጠረ አካል ላይ አያድርም፤ጥምቀት የሰውን ልጅ ንጹኅ ባሕርይ ለመመለስ ስለኾነ መንፈስ ቅዱስ የሚፈልገው ንጹህ አካልን ነው ብለውኛል፡፡ይህ ሐሳብ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በፍትሐ ነገሥት (ፍት. መን. 1958፡ 46) ሰፍሯል፡፡ ሴቶች የሰብአ ሰገል ምሳሌ ናቸው፡፡ አንድም የሐዋርያት ምሳሌ ስለኾኑ ሲጠመቁም ከዐዲስ አማኞች ቀጥሎ ነው፡፡ ጸጉራቸውን የሚፈታበት ምክንያት ጸጉር መሠራት በኀጢአት የመያዝ ምሳሌ ነው፡፡ መፈታት፣ ከኀጢአት የመለየት ምሳሌ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሥጋዊ ጌጥ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ ጌጣችሁ መንፈሳዊ ነው ሲሉ ጌጣቸውን ያወልቃሉ፡፡ ሴቶች በእጃቸው፣ በጆሯቸው ፣ በአንገታቸውና በእግራቸው የተለያዩ ጌጣጌጦችን አድርገው አይጠመቁ፡፡ ይህ ሥጋዊ ጌጥ ነው፤ እንግዲህ ጌጣቸው መንፈሳዊ ነውና

‹‹አንድም እንኳን ከሰውነቱ የተለየ ማናቸውን ይዘው ወደ ውኃው አይውረዱ›› ብለው ሐዋርያት በዲድስቅልያ በተለያዩ መጻሕፍት እንዳሠፈሯቸው ገልጸዋል፡፡[22]

በተጨማሪም አዲስ አማኞች ሲጠመቁ ልክ እንደ ሕፃናት ኹሉ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ እንዲያዞሩ ዲያቆኑ ትዕዛዝ ይሰጣሉ፡፡ እነርሱም ያዞራሉ ‹‹በክርስቶስ አምላካችን እናምናለን ዲያብሎስን እንክደዋለን›› ይላሉ፡፡ ከዚያም ወደ ምስራቅ ይመለሳሉ፡፡ ‹‹በክርስቶስ አምላካችን እናምናለን ዲያብሎስን እንክደዋለን›› ይላሉ፡፡ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች የሚዞሩበት ምክንያትና ምሳሌ መረጃ አቀባዮቹ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

> *ፊታቸውን ወደ ምዕራብ ዞረው ዲያብሎስን እክደዋለሁ የሚሉበት ምክንት ምዕራብ የዲያብሎስ ማደሪያ ቤቱ እንደኾነ ይታመናል፡፡ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ እንዳመኑ ይናገራሉ፡፡ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ እንዲመልሰው ካህኑ ትእዛዝ ይሰጣሉ፡፡ ይህም አዳም በገነት ሰባት ዓመት የመኖሩ ምሳሌ ነው፡፡ ከዚያም ወደ ምዕራብ ይመልሱታል፡፡ አዳም ወደ ገሃነም የመውረዱ ምሳሌ ነው፡፡ አንዱ ቄስ ቀኝ እጁን ይዘው ወደ ምስራቅ ይመልሱታል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ሥጋ ለብሶ አዳምን የማዳኑ ምሳሌ ነው፡፡ አዳም ትዕዛዝ አፍርሶ ከገነት በተባረረ ጊዜ ፈጣሪ ከራሱ ከአዳም የልጅ ልጅ ተወልዶ እንደሚያድነው ቃል ገብቶለት ነበር፡፡ አዳምም ተስፋውን ሰምቶ ወርዷልና ወደ ምሥራቅ ይመልሱታል ሲሉ ቀሲስ መስተዋል ባሕሪው ገልጸውልኛል ቃለ መጠይቅ (መጋቢት 20 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

ሕፃኗ ሜሮን ከመቀባቷ በኋላ መነኩሴው ዕራቁቷን እንደኾነች ለክርስትና እናቷ ሰጧት፡፡ ክርስትና እናቲቱ ነጭ ልብስና ማቀፊያ ይዛ ነበር፤ በኹለት እጇ በነጭ ልብሱ አቅፋ ተቀበለቻቸው፡፡ መነኩሴውም ከልጇ አልለያትም፣ የሃይማኖትን ትምህርት አስተምራታለሁ በይ እያሉ ሴትዮዋን ሦስት ጊዜ አስማሏት፡፡

ሕፃኗ በነጭ ማቀፊያ እንድትጠቀለል የተደረገበትን ምክንያት መረጃ አቀባዮቹን ጠይቄ ነበር፡፡ ይህ ቀን ሕፃኗ መንፈስ ቅዱስን የምትቀበልበትና ዐዲስ ልጅነትን የምታገኝበት ቀን ነው፡፡ ነጭ ልብስ ደግሞ ጸዐዳ ነው፤ የንጽሕና፣ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌም ነው፡፡ ዐዲስ አማኞችም ኾኑ ሕፃናት ነጭ ልብስ ይለብሳሉ፡፡ ሌላኛው ምሳሌ ከዚህ ቀን ጀምሮ ኀጢአታቸው የተሠረየላቸው፣ ከኀጢአት የነጹ፣ ንጹሓን ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህን ነጭ ልብስ በሚለብሱበት ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስ የማያረጅንና የማያልፍ ጸጋን፣ ዘላለማዊ ሕይወትን አልብሶ መንፈስ ቅዱስን

[22] የዚህ ምሳሌነት በፍትሐ ነገሥት (ፍት. መን. አንቀጽ 3 ፣ረስጠብ 3 1958፣ 46) ተገልጿል፡፡

በላያቸው የማልበሱ ምሳሌ ነው  በማለት መረጃ አቀባቼ አስረድተዋል (ቃ.መ. መጋቢት 26 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡

ተጠማቂዎች አኹን ዳግመኛ ተወልደዋል፣ በሥላሴ የጸጋን ልጅነት አግኝተዋል፤ የክርስቲያን አባል ኾነዋል፤ ከአኹን በኋላ የኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥቱ ወራሾች ናቸው፡፡ ከኀጢአት ኹሉ የራቁ የመንፈስ ቅዱስ ንጹሕ ንዋያት ኾነዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህም ነጭ ልብስ ይለብሳሉ፤ ነጭ ልብስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መኾኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

መነኩሴው ጠበሉን በመቅጃ አደረጉና እናቲቱን፣ አባትዬውንና የተወሰኑ ሌሎች አጃቢዎችን ራሳቸውን ላይ ረጩቸው፤ በእጃቸው እያደረጉም ውስጥ ያሉ ታዳሚዎችን ኹሉንም ረጩቸው፡፡ የጥምቀተ ክርስትናውን የመጨረሻ ማሳረጊያ ጸሎት አደረጉ፤ ኹሉም አኀነበሱ፡፡ ጸልየው ከጨረሱ በኋላ ‹‹እግዚአብሔር ይፍታ፤ ‹‹የሠራችኹትን ኀጢአት ይቅር ይበላችሁ›› አሉ፡፡ ሕዝቡም ‹‹ይፍቱኝ›› ብሎ እጅ ነሥቶ ቀና አለ፡፡

አጃቢዎችም ጭምር ወደ ፎቁ አመሩ፡፡ ሴቶች በስተደቡብ፣ ወንዶች በስተሰሜን በኩል ቆመዋል፡፡ የቅዳሴ ሥርዓቱ ሊጀመር ስለነበር ኹሉም በጸጥታ  ግማሹ ተቀምጧል፤ ግማሹ የግል ጸሎቱን በለኆሳስ ያደርሳል፤ አንዳንዶች የተለያዩ መጻሕፍትን ይዘው ይደግማሉ ለሰባት ሰዓት ዐሥር ያህል ደቂቃዎች ሲቀሩት የቅዳሴ ሥርዓቱ ተጀመረ፡፡

ካህኑ ሜሮን ሲቀቡ ተጠማቂዋ አዲስ አማኝ፣ አዋቂ ሴት ከኾነች ቅብዐ ቅዱሱንና ሜሮኑን ኤጲስ ቆጱሱ ከአንገትዋ በላይ ከቀቧት በኋላ ሌላውን አንስታዊ ብልቷን የምትቀባት ግን ዲያቆናዊት ሴት ነች ሲሉ መረጃ አቀባዮቼ ገልጸውልኛል፡፡ ዲያቆናዊት ሴት ዕድሜዋ ከ60 በላይ የኾነች መነኩሴ ወይም በሥጋ አምላክ ተወስና የምትኖር መበለት ነች፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለዚህና ለሌሎች አገልግሎቶች የምትራዳ ነች ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ማይ በመቅዳት፣ የግብር ስንዴ በማዘጋጀት ወዘተ የምታገለግል ነች፡፡ ዲያቆናዊት የቅብዐ ሜሮን ላይ ተራዳኢ መኾኗ በትውፊት ይነገራል እንጂ መረጃ አቀባዮቼ እንደገለጹልኝ በየትኛውም የኢኦተቤ ውስጥ በተግባር አይስተዋልም፤እኔም አልተመለከትኩም፡፡[23]

የቅዳሴ ሥርዓቱ ከኹለት ሰዓት በላይ ፈጅቷል፤(8፡ 40) አካባቢ ሲኾን የቁርባን ሥርዓቱ ተጀመረ፤ መጀመሪያ የቆረበችው ሕፃኗ ነበረች፣ ከርሷ በኋላ ሌሎች ሕፃናት ቆረቡ፤ ከዚያ በኋላ

[23] ይህ ሥርዓት በፍትሐ ነገሥት (ፍት. መን. አን. 3 1958፣ 44) እንዲተገበር ተገልጿል፡፡

ትልልቅ ወንዶች፣ ቀጥሎ ትልልቅ ሴቶች ቆረቡ። የቁርባኑን ቅደም ተከተል በሚመለከት መረጃ አቀባዮቼ እንዲህ ገልጸውልኛል።

የቁርባን ሥርዓት መጀመሪያ ላይ ካህናት ይቀበላሉ። ከዚያ በኋላ የ40 ቀን ወንድ ሕፃናት፣ በመቀጠል የ80 ቀን ሴት ሕፃናት ከዚያም ንኡሰ ክርስቲያን (በዕለቱ ክርስትና የተነሡ ዐዲስ አማኞች)፣እነዚህ ከተቀበሉ በኋላ ሕፃናት፣ መነኮሳት፣ ወንድ ሕፃናት፣ ሴት ሕፃናት፣ ሴት መነኮሳት፣ እና ሌሎች ቆራቢዎች በቅደም ተከተላቸው ይቀበላሉ ብለውኛል።

ሥርዓተ ቅዳሴው እንደተጠናቀቀ ኹሉም ሰው ከቤተ ክርስቲያኑ መውጣት ጀመረ። ሕፃኗን የክርስትና እናቷ አቀፈቻት። ረፋዱ ላይ ከነበሩት ታዳሚዎች በተጨማሪ ሌሎችም ተጨምረው ነበር። ኹሉም እንዳጀቧት ከቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ወጣን፤ ከግቢው ውጪ አንዲት በ30ዎቹ የምትጠጋ ሴትና በ20ዎቹ አካባቢ የሚኾን ወጣት የተቆረሰ ዳቦ ማደል ጀመሩ። እሱን እየበላን በእግራችን በዚያው በገዳሙ አካባቢ በቅርበት ባለ ቤት ኹሉም አጃቢዎችም ጭምር ኼድን። እንጀራ በሳህን እየተደረገ አቀረቡልንና በላን፤ ወዲያውኑ ተነሡ ተባለና ወደ ሰላሴ ፍቼ የሕፃኗ ወላጆች ቤት ጉዞ ጀመርን።

ከቤተ ክርስቲያን እንደተወጣ ዳቦ የተበላበት ምክንያት ሥጋ ወደሙ የተቀበለ ሰው ልክ ሥጋ ወደሙ እንደተቀበለ አፉን ያፍናል። እህል ከመቅመሱ በፊት ከማንም ሰው ጋራ መነጋገር አይፈቀድለትም፤ ከቤተክርስቲያን እንደወጣ እህል ይቀምሳል፤ ከዚያ በኋላ መነጋገር ይችላል፤ ይህም ለቁርባኑ ክብር መስጠት እንደኾነ ይታመናል። ከዚህ ባሻገር ጠበል ጠጥቶ የቀረ ካለ እንኳን እህል ሲቀምስ ዐብሮ ይወርዳል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ሌላኛው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጥቶ በካህን ተባርኮ ማንኛውንም ምግብ መቅመስ ለቀመሰው ሰው እንደ በረከት ይቈጠርለታል ተብሎ ይታመናል።

በዚህ ቀን በእናቲቱ በኩል የሚደረግ ጥንቃቄ ምን እንደኾነ የነገረኝ ዲያቆን እንዳለ ግዛው ሕፃኗ በዚህ ቀን ዳግመኛ ልደትን ያገኘችበት ቀን ነው። የሕፃኗ እናት እንዳታለቅስባት ጡት ደጋግማ ማጥባት አለባት እንድትተኛ ብታደረግ መልካም ነው። የለበሰችውን ልብስ ለዛሬ አታወልቅም። ማንም ሰው እንዲስማቸው አይፈቀድም፤ ብቻዋን ጥለዋት መኼድ የለባቸውም ብለውኛል። ይህ ኹሉ የሚደረገው ለቅዱስ ቁርባንና ለመንፈስ ቅዱስ ክብር እንደኾነ ገልጸውልኛል። በተጨማሪም ሕፃኗ ብቻዋን ከኾነች ሰይጣን ይታናኳለታል ተብሎ ስለሚታመን

በድንገት እንኳን ጥለዋት ቢኼዱ ብረት ራስጌዋ ያስቀምጡላታል ያለችኝ ደግሞ በዕለቱ ክርስትና የተነሣቸው ሕፃን አክስት ነች፡፡

## 4.1.3. ድኅረ ሥርዓተ ክዋኔ

የልጂቱ ቤተሰቦች ሰላሌ ፍቼ ልዩ ስሙ ኩማንዳ በሚባል አካባቢ ስለሆኑ ወደ መኪና ውስጥ ገባን፡፡ አሽከርካሪዎቹ ቀስ ብለው ነበር የሚነዱት፡፡ ከ30 ደቂቃ በኋላ መኖሪያ ቤታቸው ደረስን፡፡ ከመኪና ወርደን ኹላችንም ልጅቱን ወዳቀፈችው የክርስትና እናቲቱ ተሰበሰብን፡፡

ከ20 እስከ 25 የሚጠጋ የሰው ብዛት ነበር፡፡ በር ላይ አንዲት ዕድሜዋ ወደ 45 ዓመት የሚጠጋ ሴት በትልቅ ሌማት ነጭ የማኛ ጤፍ እንጀራ ይዛ ቆማለች፡፡ ሌሎች ብዙ ሴቶች እሷን አጅበው ቆመዋል፡፡ ሕፃኗ ከነአጃቢዎቹ በር ላይ ሲደርሱ ዕልልታውን አቀለጡት፤ አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም ደጋግመው ደጋግመው ዕልል... ዕልል... አሉ፡፡ ሕፃኗን እንጀራው ላይ አስተኟት፤ ከዚያም በእንጀራው ጠቀለሏት፡፡ ብዙ እንጀራ ነበር፤ ኹሉንም ሰውነቷን አለበሷት፡፡ ይህን የከወኑት መጀመሪያ በር ላይ በሌማት እንጀራውን የያዘቸውና ሌላ አንድ ሴት ነበሩ፡፡ ሕፃኗን ደጋግመው እንጀራው ላይ አንከባለሏት[24]፤ ሴቶቹም በጣም እልል ይሉ ነበር፡፡ ወንዶቹ ያጨበጭባሉ፡፡ ኹሉም ታዳሚዎች ደስታና ሣቅ ፊታቸው ላይ ይነበባል፡፡ በመቀጠል ሕፃኗን አነሧት፣ በእንጀራው ላይ ዐቅፈው በእግሯ አቆሟትና እንደመራመድ አደረጓት፡፡ እናቲቱየመጀመሪያ ልጇ ስለነበረች በትኩረት እየተከታተለች የጭንቀት፣ የሣቅ፣ የደስታ ስሜት ፊቷ ላይ ተመልክቼባታለሁ፡፡ ሕፃኗ ማልቀስ ስትጀምር ክዋኔውን የምታስፈጽመው ሴት ለእናቲቱ ሰጠቻት፡፡

---

[24] እንጀራ ላይ የማንከባለል ሥረዓቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሰነዶች መጽሐፈ ክርስትና ላይም ሆነ ፍትሐ ነገሥት ላይ እንደ ሥርዓት አልተቀመጠም፡፡ የሃይማኖት አባቶችንም ጠይቄ እንዳረጋገጥኩት ሃይማኖታዊ ሥርዓት እንዳልሆነ ገልጸውልኛል፡፡ ማኅበረሰቡ ከባህሉ ለእንጀራ ከሚሰጠው ትርጉም እንደሚከውኑት እናቶችን፣አረጋውያንና የሃይማኖት አባቶችን ጠይቄ አረጋግጫለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ምልከታዬ በሁሉም ጥምቀተ ክርስትናዎች ላይ ክርስትና የተነሡ ሕጻናትን ከቤተ ክርስቲያን መልስ ቤታቸው ሲደርሱ እንጀራ ላይ አንከባለዋቸዋል፡፡

**ፎቶ 15፡ ሕፃናት እንጀራ ላይ ሲንከባለሉ በከፊል[25]**







**(ፎቶ በአጥኚው)**

ኹሉም ታዳሚዎች እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ ቤቱ ቀጤማ ተጐዝጉዟል፤በትልቅ መሶብ ድፎ ዳቦ ተሹሞ ፊት ለፊት ላይ ቆሟል፡፡ ከሰሉ ተንተርክኮ አጠገቡ ጀበና እና ሲኒ ተቀምጧል፡፡ ፈንድሻና ቆሎ ከጀበናው አጠገብ ተቀምጧል፡፡

አንዲት በግምት በ30ዎቹ የምትጠጋና የሀገር ባህል ነጭ ልብስ የለበሰች ሴት አጠገቡ ተቀምጣለች፡፡ ጥግ ላይ ትልቅ የምግብ ጠረጴዛ አለ፡፡ በጠረጴዛው ሙሉ የተለያዩ የምግብ ዐይነቶች ተቀምጠዋል፡፡ ከአክርማና ስንደዶ እንደተሠራ በነገሩኝ ድርብ በሚባለው ሙሉ ያልተቆረሰ እንጀራ የምግብ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል፡፡ ከጎኑ የተቆረሰ የሥንዴ ዳቦ አለ፡፡ የሥንዴ ዳቦውን የያዘው ከጥለት የተሰፋ የዳቦ መሶብ ነው፡፡ ከተዘጋጁት የወጥ ዐይነቶች ውስጥ አንድም ከሥጋ የተሠራ ነገር አልነበረም፡፡ ወቅቱ የዐቢይ ጾም ስለነበረ ነው እንጂ እርድ ይኖር ነበር ብለውኛል፡፡

25 መሃል ላይ ያለው ፎቶ እንጀራው ላይ ከማንከባለላቸውም በተጨማሪ እንጀራውን አልብሰውታል በተወሰኑት ምልከታዬ መላ አካሉን እንጀራወን የማልበስ፣ ራቁታቸውን አድርገው ከላይም ከታችም እንጀራውን ሲያለብሷቸው ተመልክቻለሁ

**ፎቶ 16 የክርስትና ምግብ ዝግጅት በከፊል**





**(ፎቶ በአጥኚው)**

ሕፃኗ የተንከባለለችበት እንጀራ በጣም በትንንሹ ተቆረሰ፤ ከእናቲቱ ጀመሩና ኹሉም ታዳሚዎች ተሰጣቸው። አንድም እንጀራውን ያልበላ ሰው አልነበረም። እንጀራ ይስጥሽ! እንጀራ ይውጣልሽ! እያሉ ኹሉም መረቋት። እያንዳንዱ ሲመረቅ ከውስጣዊ ስሜት ነበር፣ ፊታቸው ላይ ደማቅ የኾነ ፈገግታ ይታያል። ተራ በተራ ይመርቃሉ። ያሳድግሽ! የሚሉ አሉ፤ እንጀራ ይውጣልሽ! የሚሉ ነበሩ፤ ሰርግሽንና ምርቃትሽን ያብላን! የሚሉም ነበሩ፤ ኹሉም በየተራ መረቋት። እናቲቱ እንዳቀፈቻት እንቅልፍ ወሰዳት።

እንጀራ ላይ ለምን እንዳንከባለሏት እንጀራ ላይ ሲያንከባልሉ የነበሩትን እናት ጠይቄአቸው ይህን መልሰውልኛል ሕፃኗ ዛሬ እድሏን የምትቀበልበት ቀን ነው። ፈጣሪ ይህቺን ምንም ኀጢአት የሌለባት ሕፃኗ በዛሬው ዕለት ወደፊት የምትበላውን እንጀራ ይሰጣታል። እኛም እንደዚህ የሚያምርና ዐይኑ የበዛ እንጀራ ይስጥሽ! እያልን እንመርቃታለን። ፈጣሪም የዚህን ኹሉ ምርቃት ይሰማል። ሕፃኗን “እንጀራ የወጣላት” ያደርጋታል። ዛሬ ዕድሏን ኹሉ የምትቀበልበት ቀን ነው በማለት ገልጸውልኛል።

ሌላኛዋ ስታንከባልል የነበረችው ደግሞ የሚከተለውን ብላኛለች። ዛሬ ሕፃኗ በረከትን ያገኘችበት ነው። በዚህ ቀን ክርስትና ተነሥታለች፤ ክርስቲያን ኾናለች። ወደፊት በዚህ በሚያምር እንጀራ ዐይን ልክ የበዛ ሀብት፣ የተትረፈረፈ እንጀራ እንዲሰጣት እየመረቅናት ነው። ፈጣሪም በረከት የሞላበት እንጀራ ወደፊት ይሰጣታል። ይህ ቀን ለእርሷ የበረከት ቀን ነው በማለት ገልጻለች።

ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው በዚህ ቀን ሕፃኗ በሃይማኖቷ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላለች፡፡ የክርስትና መነሣት፣ የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበል፣ የጸጋ ልጅነት ወይም ከምንፈስ ቀዱስ ደግመኛ መወለድ ከሚለው አስተምህሮ ባሻገር በባህላቸው ከዘወትር ምግባቸው እንጀራ፣ የወደፊት እንጀራዋን ታግኝ ብለው ይመርቃሉ፡፡ ለሕፃኗ የበረከት፣ የምርቃት የእንጀራ ቀኗ ዛሬ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

እንጀራው በበረከት ተመስሏል፡፡ ሕፃኗ ወደፊት ስትኖር በኑሮዋና በሥራዋ በእንጀራው ዐይን ልክ የበዛ፣ የማያንስ፣ የማይጎድልና በቂ የኾነ እንጀራን ወደፊት እንዲኖራት በዚህ ቀን ተመርቃለች፡፡ የወደፊት በረከቷንም ታገኛለች ተብሎ ይታመናል፡፡ “እንጀራ ይውጣላት” እንጀራን ከሀብት ጋራ አገናኝተው ተርጉመውታል፡፡ በወደፊት ሕይወቷ ችግር የማታይ፤ በሀብቷ ለራሷም ለሌሎችም የምትተርፍ፣ ለቤተሰቧ፣ ለአካባቢዋ የምትተርፍ ባለጸጋ ትኾናለች፡፡ ይህም እንጀራ ወጣላት፣ ሀብታም ኾነች ማለታችን ነው ሲሉ አስረድተውኛል፡፡

ሌላኛው የዕለቱ ታዳሚ ለምን እንጀራ ላይ እንደምትንከባለል ጠይቁአቸው ዛሬ ፈጣሪ ለሕፃኗ የ 40 ቀን ዕድሏን የሚሰጥበት ቀን ነው፡፡ ስለዚህ እንጀራው ላይ ስናንከባልላት የወደፊት ሐብቷን ፈጣሪ እንዲያቀናላት እየተመኘን ነው፡፡ እንጀራ የሰውን ልጅ በሕይወት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ሰው ኹሉ የሚለፋው፣ ተግቶ የሚሠራው ለእንጀራ ነው፡፡ ለሕፃኗም የተሻለ እንጀራ እንዲሰጣት፣ ሥራ እንዲሰጣትና እንጀራ ያለው ባል እንዲሰጣት እያልን መርቀናታል ብለዋል፡፡ ሌላኛው መረጃ አቀባዬ ድግሞ እንደገለጸልኝ ሕፃኗ በዚህ ቀን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላለች፣ በዚህ ቀን የምንመርቃት ለርሷ የተሰጣትን ጸጋ ወደፊት በተግባር ላይ እንድታውል ያድርጋት ማለታችን ነው ብሎኛል፡፡

ፈጣሪ በዚህ ቀን ለሕፃኗ የወደፊት እንጀራዋን፣ ባርኮ የሚሰጥበት ዕለት ነው፡፡ ሕፃኗ ምንም ኀጢአት የሌለባት ስለኾነች በዚህ ስፍራ መገኘታችን ለእኛም በረከት እናገኛለን ብለው ያምናሉ፡፡ እንጀራው ሕፃኗ ከተንከባለለችበት በኋላ በትንንሹ ቁርስርስ አደረጉት የተቆራረሰውንም እንጀራ ለእያንዳንዱ ታዳሚው ኹሉ እንዲደርስ ተደረገ፤ ኹሉም ቀመሰ፡፡ ምክንያቱንም ጠይቄ ነበር፤ ይህቺ ሕፃን በዚህ ቀን መንፈስ ቅዱስ አድሮባታል፤ ሥጋ ወደሙ ተቀብላለች፣ ጸጋ በረከትን አግኝታለች፡፡ እኛም በዚህ የታደምነው እርሷ የተንከባለለችበትን እንጀራ ስንበላ የርሷን በረከት እናገኛለን ብለውኛል፡፡ ጠበል ተጠምቃ፣ የክርስትና ስም ወጥቶላታል፡፡ በካህን ተባርካ፣ ቅዱስ ቁርባኑን ተቀብላለች፡፡ እሷ የተንከባለለችበት እንጀራ ማለት የተቀደሰ ነው ተብሎ ይታመናል፤ ያንን መመገብ በረከትን ያሰጣል፤ እሷ ያገኘችውን ጸጋ እኛም እናገኛለን ብለው ያምናሉ፡፡

በመቀጠል የተከናወነው ሥርዓት ለዕለቱ የተዘጋጀውን ምግብ መብላት ነው፡፡ ካሉት ታዳሚዎች ውስጥ በዕድሜ ትልቅ የኾኑት እንዲነሡ ተደረገ፣ ሴቶችም ወንዶችም በየእዕድሜያቸው ቅደም ተከተል እየተነሡ የሚበቃቸውን ምግብ አነሡ፡፡ ጠላ አሳላፊው በትልቅ ማንቆርቆሪያ የያዘውን ጠላ ከሽማግሌው ጀምሮ ማደል ጀመረ፡፡ እየተመገቡ እያለ ሌላኛው አሳላፊ ብርጭቆ መስጠት ጀመረ ከጠላው መቅጃ ከፍ ባለ ማንቆርቆሪያ ጠጅ ተቀዳላቸው፡፡ ኹሉም በየፊናው ጠላውንም ጠጁንም ይጠጣል፣ የየግሉን ወሬ ያወራል፣ ረዘም ያለ ጊዜን የፈጀ የምሳ ዝግጅት ነበር፡፡ ታዳሚዎች ከቤተክርስቲያን የመጡት ብቻ አልነበሩም፡፡ ሌሎች ከጎረቤት፣ ራቅ ካለ ስፍራ የመጡ በመጡበት ሰዓት የተዘጋጀውን ምግብ እያነሡ ይቀመጣሉ፡፡ የተለያዩ የስጦታ ዐይነቶችን ይዘው ይመጣሉ፡፡ መጠጥ ይዘው የመጡም ነበሩ፤ ልብስ ይዘው የመጡም ተመልክቻለሁ፡፡

የሕፃኗ ወንድ አያት ጠርሙስ አረቂ ይዘው መጡና ያልተቆረሰ ደቦ ካለበት አጠገብ አስቀመጡት፤ መጀመሪያ ላይ ምግብ እንዲያነሡ የታዘዙት ሽማግሌ እንዲመርቁ ተደረገ፤ ከሕፃኗ ጀምረው ኹሉንም መረቁ፤ ስለ ሀገር ሰላም መኾን፣ ስለ ዝናም መዝነም፣ ስለ እህል በረከት መረቁ፣ የሚመርቅ ሽማግሌን፣ አድባሩን ያቆይልን እያሉ መረቁ አንድ ሽማግሌ ብቻ አልነበሩም የመረቁት እየተቀባበሉ ከመረቁ በኋላ አንድ ወጣት ልጅ ተቀበላቸው፤ መለኪያ የያዘው ልጅ ከፊት ከፊት እየሰጠ መጀመሪያ ከመረቁት ሽማግሌ ጀምሮ ቀዳላቸው የተወሰኑ ሰዎች በተለይም ሴቶችና አንዳንድ ወጣት ታዳሚዎች አረቂ ያልጠጡም ነበሩ፡፡

ቡናው መቆላት የጀመረው በዚሁ ሰዓት ነበር፡፡ ቡናውን በ30ዎቹ የምትጠጋዋ ሴት እየቆላች በነበረችበት ወቅት የቤቱ አባወራ ዳቦውን ቆረሰ፡፡ ይህ ዳቦ ጠረጴዛው ላይ መጀመሪያ የተቆረሰው አይደለም፡፡ ለቡናው ሰዓት ተብሎ የተዘጋጀ እንደኾነ ተመልክቻለሁ፡፡ የተቆረሰውን ዳቦ ወጣት ወንድ በትሪ እያደረገ ማደል ጀመረ፡፡ ቡናውም ወዲያውኑ ፈላና ያፈላቺው ልጅ በቡና ማቅረቢያ አነስ ያለ ዕቃ ስኒዎችን እየደረደረች ከሽማግሌዎች ጀምራ ወደ አሮጊቶች፣ ከዚያም ወደ ወጣቶቹ በቅደም ተከተል የሚጠጡትን እየጠየቀች አዳረሰች፡፡

በአጠቃላይ ክዋኔው በቅደም ተከተል ተከናውኗል፡፡ ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ጀምሮ ከዋኝ፣ አስከዋኝ፣ ታዳሚዎች ነበሩ፡፡ እያንዳንዳቸው የየራሳቸው ድርሻ ነበራቸው፡፡ የማጥመቁን፣ ሜሮን የመቀባቱን፣ ማተብ የመሰሩን ተግባር የከወኑት ካህኑ ብቻ ነበሩ፡፡ በጸሎቱ ጊዜ ካህኑ፣ ዲያቆኑና ሕዝቡ የየራሳቸው ድርሻ ነበራቸው፡፡ ሕዝቡ ተሰጥዎውን ይመልስ ነበር፡፡ ዲያቆኑ ጸሎቱን እንዲያደርጉ ያዝ ነበር፡፡ ሕፃኗን በአራቱም አቅጣጫዎች እንድትዞር ሲያደርግ የነበረው

ዲያቆኑ ነው። ኹሉም ድርሻቸውን በቅደም ተከተል ተግብረዋል። ክዋኔውም መጀመሪያ፣ መሀከልና መጨረሻ ነበረው። በቤት ውስጥ እንጀራው ላይ ከማንከባለል ጀምሮ እስከ ቡና ማፍላት ድረስ በየድርሻቸው ሲተገብሩ ነበር። ለመመረቅ፣ ዳቦ ለመቁረስ፣ ጠጅና ጠላ ለማሳለፍ የተሳተፉት ኹሉም በየድርሻቸው እንደነበር ተመልክቻለሁ።

ከክርስትናው በኋላ ለሚከናወኑት የክርስትና እናትና አባት ተግባራት የክርስትና አባትና እናት ለመኾን መስፈረቶቹ ምን ምን እንደሚኾኑ፣ በቡድን ውይይት የሃይማኖትን አባቶች፣ በዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ሴቶችንና ወንዶችን፣ እንዲሁም የክርስትና ልጅ ያላቸውንና የሌላቸውን ጠይቄ ነበር።

የክርስትና እናት ዝምድናዋን የምትጀምረው ከክርስትና ሦስት ቀን በኋላ ወይም ከሰባት ቀን በኋላ ነው ብለውኛል። ክርስትና እናት ዳቦ ደፍታ ክርስትና ያነሣቻትን ልጅ ጥየቃ ትኼዳለች። የልጅቱም ቤተሰቦች ቡና አፍልተው፣ ምግብ አዘጋጅተው ይጠብቋታል። የምትመጣበትን ቀን ቀድማ ስለምትናገር እንደየሰው የኑሮ ኹኔታ ጠላና ሌላ መጠጥ የሚጠምቅም እንዳለ ነግረውኛል። ቤተ ክርስቲያን ከልጇ አልለያትም ብላ የገባችውን ቃል ከዚህ ቀን ጀምራ ተግባራዊ ታደርጋለች ብለውኛል።

መረጃ አቀባዮቼ እንደገለጹልኝ የክርስትና አባት ወይም እናት ለመሆን በተለያዩ መንገዶች ሊከናወን ይችላል ብለውኛል። ከወላጆች ዝምድና የሚፈልጉ ሰዎች መጀመሪያ በእረግዝና ሰዓት ልጅሽን ለክርስትና ስጪኝ ይላሉ፤ ኹለተኛው ወላጆች ተመካክረው ልጃችንን ለእከሌ እንስጥ በማለት ለሚቀርቡትና ዝምዳነውን ለሚፈልጉት ሰው፣ ለጎረቤታቸው፣ ለመስሪያ ቤት ባልደረባቸው ይሰጣሉ። ሦስተኛው ሕፃናቱ ከተወለዱ በኋላም በወላጆች ስምምነት ቤተሰቦች ላለመራራቅ ለእኩያ ሕፃናት ልጆች ክርስትና እንዲነሣሡ ያደርጋሉ። አራተኛው ለታቦት የሚሰጡት ነው። የሚዘክሩት ታቦት ካለ፣ለሰበካቸው ታቦት ወይም በስለት ልጅ ወልደው ከኾነ ለመረጡት ታቦት የሰጣሉ። ለታቦት መስጠትን የሃማኖት አባቶች ትክክል አይደለም ብለውኛል ምክንያቱም በዕለቱ በታቦቱ ስም ኃላፊነት ወስዶ ቃል የገባው ዲያቆን እንደክርስትና አባትና እናት ሃላፊነቱን ሲወጣ አይስተዋልም ስለዚህ ለሰው መሰጠት ነው ያለበት ብለውኛል። ይሁን እንጂ እኔ መረጃ ስሰበስብ ብዙ የታቦት ነኝ ያሉኝ ምዕመናን አጋጥመውኛል።

ከላይ በተገለጹት መስፈርቶች መሠረት ክርስትና አባት ወይም እናት መኾናቸውን ያረጋገጡ ሰዎች ከክርስትናው ቀን ቀደም ብለው ሕፃናቱ በዕለቱ የሚለብሱትን ልብስና የክረስትና ማንሻ

ነጭ ማቀፊያውን ያሚላሉ፡፡ ከዚህ በፊት ክርስትና አንስተው ያውቁ እንደሆነ የጠየቅኳቸው አቶ ተስፋዬ ቦጋለ እንደገለጹልኝ

*ገና ተማሪ እያለሁ ክርስትና አንሥቼ አውቃለሁ፡፡ የክርስት ልጅ አለኝ፡፡ ያኔ ክርስትና ለማንሣት ሕፃኑ ሲሰጠኝ የእኔ ቤተሰቦችና የሕፃኑ ቤተሰቦች የጠበቀ ወዳጅነት ነበራቸው፡፡ ምንም እንኳን የሥጋ ዝምድና ባይኖረንም ቤተሰብ ነበርን ማለት ይቻላል፡፡ የበለጠ ዝምድናችን እንዲጠነክር፣ አብረው ያድጋሉ፣ ታላቅ ወንድም ይኾነዋል በማለት ቤተሰቦቼ ክርስትና እንዳነሣው አድርገውኛል፡፡ በወቅቱ ክርስትናውን ለማንሣት ከአባቴ ጋራ ስኼድ የልጁን ነጭ ልብስ (የክርስትና ማንሻ) የገዛኹት እኔ ነኝ ብለውኛል፡፡ ከዚያም በኋላ ትልቅ እስከሚኾን ድረስ አባቴ ለበዓላት ለኔ ልብስ ሲገዛልኝ ለወንድምህም እያለ አብሮ አንድ ዐይነት ልበስ ይገዛልን ነበር (ቃለ መጠይቅ መጋቢት 14 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

ክርስትና አባት ወይም እናት የኾኑ ሰዎች ልብስ የሚገዙት ለክርስትና ማንሻ ብቻ አይደለም ፡፡ ከክርስትናው በኋላ በዓላትን ምክንያት በማድረግ፣ በልደታቸው ጊዜ በስጦታ መልክ እያደረጉ ከልጆቻቸው እኩል አንዳንዴም ከልጆቻቸው በበለጠ እንደሚገዙላቸው መረጃ አቃባዮቼ ገልጸውልኛል፡፡

*ክርስትና ልጅ እንዳላቸው የነገሩኝ ወ/ሮ ጦቢያው መንግሥቱ የክርስትና ልጅ አለችኝ፡፡ አኹን ዐስራ አንድ ዓመቷ ነው፡፡ ለስድስት ዓመታት ያህል ጎረቤት ነበርን፡፡ ለቡሔ ዳቦ ደፍቼ ኹሌም እጠይቃታለሁ፤ ለዐዲስ ዓመት፣ ለጥምቀት ልብስ እየገዛሁላት እኼዳለኹ፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ይዣት እየኼድኩ ዐብረን እሑድ እሑድና ለክብረ በዓላት እናስቀድሳለን፤ ከቤተሰቦቿ ጋራ የሥጋ ዝምድና የለንም፡፡ ያኔም ክርስትና ለማንሣት የፈለግሁት ጉርብትናችንንና ዝምድናችንን ለማጠናከር ብዬ ነበር፡፡ አኹን አካባቢ ቀይረው ሰሚት ገብተዋል፤ ነገር ግን እኔም ጥያቄዬን አላቋረጥኩም፤ እነርሱም እየመጡ ይጠይቁኛል፡፡ ልጇም ልክ እንደ ወላጅ እናቷ ነው የምትወደኝ፤ ከልጆቼ ጋራ ሲገናኙም፣ ድሮም ልጅ ኾነው ፍቅራቸው ከሥጋዊ እኅትና ወንድም በላይ ነው፡፡ እስካሁንም ቤተሰባዊነታችን ቀጥሏል ብለውኛል፡፡(ቃለ መጠይቅ መጋቢት 16 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

የሥጋ ዝምድና ባይኖራቸውም ክርስትና ዘመድ አድርጓቸዋል፤ቀረቤታቸው ተጠናክሯል፡፡ መጀመሪያም ክርስትና ማንሣት የፈለጉት ለጉርብትናቸውና ለዝምድና ፍላጎት ነው፡፡ ልጆቻቸውም እንደ ሥጋዊ ዘመዳሞች ኾነዋል ለመጠያየቅ አካባቢያቸውን ቢለወጡም የቦታው ርቀት አልገደባቸውም ክርስትናው ለማኅበራዊ ትስስራቸው ትልቅ ድርሻ እንዳለው ከዚህ ሐሳብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክርስትና እናት ወይም አባት ለመኾን

በዕድሜ ትልቅ መኾን አይጠበቅም፤ በየትኛውም የዕድሜ ክልል ላይ እናት ወይም አባት መኾን ይቻላል፡፡

> *የ11 ዓመት እያለሁ ክርስትና ልጅ ነበረኝ ያለችኝ ወጣት አመቤት ጌትነት እንደገለጸችልኝ በወቅቱ እኔ ክርስትና እናት ነበረኝ፡፤ ክርስትና እናቴ ልብስ ትገዛልኝ ነበር፤ ዳቦ ይዛ ለቡሔ፣ ከቡሔ ውጪም እየመጣች ታየኝ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ የዘጠኝ ዓመት እያለሁ ነበር ክርስትና ያነሳሁት፡፡ እናቴ ክርስትና ልጅ ይኖርሻል ብላ ዐዲስ ነጭ ልብስ ገዝታ ቤተ ክርስቲያን ዐብረን ኼደን ጣት ይዣለሁ፡፡ አኹን ያኔ ምን እንዳልኩ በእውነት አላስታውስም፡፡ እናቴ ዳቦ እየደፋች ዐብረን እየኼድን እንጠይቃት ነበር፡፡ አሁን እኔ እዚህ ዐዲስ አበባ በመምጣቴ እንደ ድሮው ዳቦ እየደፋሁ ባልጠይቃትም፤ በስልክም እንጠያየቃለን፤ ሀገር ቤት ስኼድም በእንግድነት አቀባበል ታደርግልኛለች፤ ከዘመዶቼ በፊት የምጠይቀው እሷን ነው፡፡ አብረን ነው ያደግነው፤ እንደ ታናሽ እህቴም ነው የማያት፡፡ እሷ ባገባች ሰዓት እናቷ የጥሎሽ ቀሚስ ስትለብስ እኔም ለብሻለሁ ብላኛለች፡፡ እኔም ጥያቄዬን አክል አድርጌ ‹‹የጥሎሽ ቀሚስ ምንድነው?›› አልኳት (ቃለ መጠይቅ መጋቢት 16 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

‹‹የክርስትና ልጄ ስታገባ ባሏ ለልጅቱ ወላጅ እናት ሙሉ ልብስ ያለብሳል፡፡ እኔም ከእናቷ እኩል ቀሚስ እለብሳለሁ፡፡ በባህላችን የክርስትና እናት እና ወላጅ እናት እኩል ነው የሚለብሱት፡፡ በሰርጓ ዕለትም ከእናት ጎን በመቀመጥ ትከሻ ሲሳም፣ ከእናትና አያት እኩል እኔም ትከሻ ተስሜያለሁ፡፡ ይህ ባህላችን ነው›› ብላኛለች፡፡

ክርስትና እናትም የክርስትና ልጅ ስታገባ አንደ በዐቅሟ ስጦታ ታደርጋለች፡፡ በተጨማሪም ለሰርጉ አንድ ጋን ጠላና በድርብ እንጀራ ታቀርባለች፡፡ የክርስትና እናት ተብሎ በቤት ውስጥ በሰርጉ ዕለት ጋን ይሾማል፡፡ ባህሉ አሁንም እየተቀባበለ መቀጠሉን ነግረውኛል፡፡ሰዎች ከሚወዱት ጎረቤታቸው፣ ከሌላው ሰው ጋራ ላለመራረቅ ሲፈልጉ ልጄን ከልጅሽ ጋራ ክርስትና አሥነሣለኹ በማለት ዝምድናቸውን ያስቀጥላሉ፡፡ ገና ሕፃን እያለሁ በቤተሰቦቼ ቃል ገቢነት ልጅ ነበረኝ ያሉኝ ወ/ሮ እጅጋየሁ ደመረ የሚከተለውን ሀሳብ ገልጸውልኛል፡፡

ኹለታችንም ነፍስ የማናውቅ ሕፃን ነበርን፡፡ ቤተሰቦቻችን ላለመራራቅ ብለው የኔን እጅ ያነሣኒት እጅ ላይ ይዘው ቃል የተገባቡት እነርሱ ናቸው፡፡ አሁን ኹለታችንም አድገን ልጅ ወልደናል፡፡ ያኔ ስንጠያይቅ ለፋሲካ እነርሱ ልጆቻቸውን ይዘው ተሰብስበው ይመጣሉ፡፡ እኛም ተሰብስበን እንጠብቃቸዋለን፡፡ የሚመጡበት ሥፍራ ዲምቱ አቦ ከሚባል ገጠር ስለነበር ዳቦ

ደፍተው ቅቤ ዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚያም አድረው፣ ታጫውተውና ውለው የሚኼዱበት ጊዜ አለ፡፡ እኔ ተማሪ ስለነበርኩ ቤተሰቦቼ የሚገዛውን ዕቃ፣ልብስ አዘጋጅተው ይጠብቃሉ፡፡ ክርስትና እህቴን አልብሰው ቅቤ ቀብተው ይሸኟቸዋል፡፡

የክርስትና አባት ሌላኛው በጥምቀተ ክርስትና የሚገኝ ዝምድና ነው፡፡ ክርስትና አባት በሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ‹‹ከልጄ አለይም›› ብሎ በገባው ቃል መሠረት ከልጆቹ እኩል በማየት ሃይማኖታዊ ሥርዓትን ያስተምራል፡፡ባለቤቴ ክርስትና ልጅ አለው እኔም የክርስትና ልጅ ነበረችኝ ያሉኝ ወ/ሮ አፀደ ማሞ ስለ ክርስትና ልጆቻቸው የሚከተለውን ገልፀውልኛል፡፡

> *ለክርስትና ልጄ ገና ከሕፃንነቷ ጀምሮ ወተት ከቤቴ እወስድላት ነበር፤ ካደገች በኋላም ለተወሰነ ጊዜ ልብስ አልበሻታለሁ በኋላ ብንራራቅም ትምህርት ቤት ስትገባም ደብተር ብዙ ጊዜ ገዝቼላታለኹ፡፡ አኹን ካገባሁ በኋላ ባለቤቴ ከልጄ አለይም ብሎ የሕፃኑን ጣት ይዞ ክርስትና አንሥቷል፡፡ የርሱን ልጅ ለመጠየቅ በተለያዩ በዐላት ልብስ ገዝተን ፤ለቡሔ ዳቦ ደፍተን እንጠይቀዋለን፡፡ የፋሲካለት ከባሌ ጋራ ኾነን ልብስ ገዝተን በየዐመቱ እንኼዳለን፡፡ የልጁ ቤተሰቦች በሳምንቱ ወደኛ ቤት ዳቦ፣ አረቂ የአክፋይ ይዘው ይመጣሉ፡፡ የክርስትና ልጃችንን እንደ ልጆቻችን እናለብሳለን፤ እነርሱም ይጠይቁናል፡፡ ዝምድናችን በዚህ ጠንካራ ኾኖ እስካሁንም ቀጥሏል (ቃለ መጠይቅ ሰኔ 2 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

በክርስትና ተዛምደዋል፤አብረው ሲኖሩ በባህላቸው የሚያዘጋጇቸው ምግቦች አሉ፡፡ እነዚህን ምግቦች በሰርጋቸው፣ በክርስትናቸውና በእምነታቸው ውስጥ በሚኖሩ ክብረ በዓላት ያቀርቧቸዋል፡፡ የትንሣኤን በዐል ምክንያት በማድረግ በክርስትና ዝምድና የታሰሩ ሰዎች የአክፋይ በማለት ባህላዊ የኾኑ ምግቦችን ዳቦ፣አረቂ ይዘው በመኼድ ከእምነታቸው ጋር አገናኝተው ዝምድና እንዳጠናከሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የክርስትናን አባት ተግባር  በሚመለከት ክርስትና አባት ነበረኝ፡፡ እኔም አባት ኾኜ ዐውቃለሁ ያሉኝ አቶ ግርማ ዐያሌው ጥያቄ አቅርቤላቸው የሚከተለውን ገልጸውልኛል፡፡

> *እኔ የክርስትና አባት ኾኛለሁ፤ በወቅቱ አባት የኾንኩት የልጁ አባት ጓደኛዬ ስለነበረ እና አንድ መሥሪያ ቤት ዐብረን ስለምንሠራ ነበር፡፡ መቀራረባችንን የበለጠ ለማሳደግ በመንፈሳዊ ዝምድና፣ በክርስትና ተሳሰረን፤ አበ ልጅ ኾንን፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሚስት እስከማገባ ድረስ አንዳንዴ እናቴ፣ ዐልፎ ዐልፎ ደግሞ እኅቶቼን እያስያዝኩ ለቡሔ ዳቦ ይዤ ልጄን እጠይቀዋለሁ፡፡ ደብተር አባቱ ቢገዛለትም ባይገዛለትም ዐዲስ ዓመት ሲመጣ ከልብስ ጋራ ይዤ እኼዳለሁ፡፡ እስከ ምርቃቱ ድረስ አባትነቴ አልተለየም፡፡ ከዩኒቨርሲቲ በኢንጅነሪንግ በተመረቀ ሰዓት የቤተሰብ ድግስ ላይ አንድ በግና አንድ እንሥራ ጠላ ይዤ ኼጃለሁ፡፡ ዐብረን በደማቅ ኹኔታ ነው ያከበርነው ብሎኛል (ቃለ መጠይቅ ሚያዚያ ሰኔ 11 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

የክርስትና እናትና አባት  የክርስትናን ሃይማኖት ለማስተማር ቢኾንም ዋናው ጉዳይ  ይሁንና ኅብረተሰቡ እየተጠመቀበት ያለው ቤተሰባዊ ትስስርና ዝምድናን መፍጠሪያ ነው። በሥጋ የማይዛመዱ ግለሰቦች የበለጠ ዝምድናቸውን ለማጠናከር ክርስትና ልጅ ያነሣሉ፤ አበ ልጅ በመባባል በብዙ ማኅበራዊ ጉዳዮች ይደጋገፋሉ፤ የክርስትና አባት ከወላጅ አባት ያልተናነሰ ክብር ይሰጠዋል። እርሱም እንደ አባት እየመከረ፣ እየቀጣ እያለበሰ ከራሱ ልጅ እኩል ያሳድጋል።

የሠርጌን ጥሎሽ የቻለልኝ ክርስትና አባቴ ነው ያለኝ ደግሞ አቶ ጳውሎስ ተካልኝ የሚከተለውን ነግረውኛል፤ ክርስትና አባቴ ከልጅነቴ ጀምሮ ልብስ ይገዛልኝ ነበር፤ አባቴ ከሚገዛልኝ በላይ የክርስትና አባቴን ልብስ እንደ ብርቅ ዐየው ነበር። ከክርስትና አባቴ ቤተሰቦች ጋራ የሥጋ ዝምድና እንደሌለን አኹን ነው ያወቅሁት። የሥጋ ዝምድና አይኑረን እንጂ እኛ ቤት ማኅበርም ሲኖር፣ በሰርግ፣ በክርስትና በደቦ ጊዜ ሥራውን እኩል ሙሉ ቤተሰቡ ነው ዐብሮን የሚሠራው። እኅቴና የክርስትና አባቴ ሴት ልጅ እኅትምአማቾች ነው የሚባሉት፤ ትምህርት ቤት፣ ቤተ ክርስቲያን ዐብረው ነው የሚኼዱት። በእኛ አካባቢ አበ ልጅ ናቸው ከተባለ፣ ቤተ ዘመድ ናቸው ማለት ነው። በምንም ማኅበራዊ ሕይወታችን ውስጥ አሉ። እኔ ሳገባ ለባለቤቴ ቤተሰቦች የሚሰጠውን ጥሎሽ የቻለው የክርስትና አባቴ ነው። በተጨማሪም የክርስትና አባት ለብቻው ጠላ ጠምቆ ጋን  ይሾማል፤ እንጀራ በድርብ ያቀርባል (ቃ.መ ሰኔ 11 2010 ዓ.ም)።

ከዚህ ሐሳብ የምንረዳው የክርስትና እናትና አባት ከሃይማኖታዊ አስተምሕሮው ባሻገር ባህላዊ የዝምድና ትስስሩ በልጦ መታየቱን ነው። ልጃቸውን ክርስትና እንዲያነሣላቸው የሚፈልጉት ዝምድናቸውን የበለጠ ለማጠናከር ከሚያስቡት የቅርብ ጓደኛቸው፣ ጎረቤታቸው እንደኾነ ነው። በአበ ልጅነት የተሳሰሩ ቤተሰቦች በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በማኅበር በጋራ የዕርሻ ሥራዎች ተባብረው ይሠራሉ። ከሥጋ ዝምድና የበለጠ ዐብረው ይኖራሉ። በሐዘንና በደስታ ጊዜ አይለያዩም፤ ‹‹በኢኮኖሚ›› ይደጋገፋሉ። ይህም በትውፊት ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ እስከ አኹንም ድረስ ዘልቋል፤ በክርስትና ወዳጅነት ይጠነክራል፤ ማኅበራዊ መስተጋብር የበለጠ ያጠናክራል። በአበ ልጅነት የተዛመዱ ቤተሰቦች አይጋቡም እኅትና ወንድሞች ናቸው። ሃይማኖታዊው የክርስትና ማንሣት ሥርዓትና ትውፊት እንዳለ ኾኖ፣ ማኅበረሰቡ ክርስትናን ለዝምድና መፍጠሪያ፣ ለቤተሰባዊ ቅርርብና ለጉርብትና ማጠናከሪያ እንደሚጠቀሙበት መረዳት ይቻላል።

ክርስትና እናት ወይም አባት የክርስትና ልጆቻቸው ዋስ ናቸው። ከልጁ አለያት፤ አለየውም ብለው የክርስትና ትምህርትን እንዲያስተምሩ ቃል ገብተዋል። ከልጃቸው እኩል ወይም በተለየ እንክብካቤ ያደርጋሉ። በሥነ ምግባር ያንጻሉ፤ ያስተምራሉ። የክርስትና አጃቢዎችም በክርስትናው ላይ መታደም ብቻ  አይደለም ተግባራቸው። ሕፃናቱ ክርስትና ሲነሡ ምስክሮች ኾነው የቀረቡ ናቸው። የክርስትና አቋቋሚዎች በክርስትናው ዕለት ነጭ የባህል ልብስ ለብሰው ከመኼዳቸውም በተጨማሪ እንደየአቅማቸው ገንዘብ በማዋጣት የአቋቋሚ ብለው ክርስትና በሚያነሡት ሰዎች በኩል ይሰጣሉ። ይህም ወላጆችን በገንዘብ በመደጎም ከጎናችሁ አለንላችሁ ማለታቸው እንደኾነ መረዳት ይቻላል ። አመጣጣቸውም በወላጆች ጥሪ ብቻ አይደለም፤ ክርስትና በሚያነሡት ሰዎች ጥሪም ነው። ልብስ በመግዛት ልዩ ልዩ ስጦታዎች ብቻ ሳይሆን በውጪም አብረው በመጋራት የድግሱ ተካፋይ ይኾናሉ። የደስታው እድምተኞች ኾነው አብረው ይደሰታሉ፤ ይበላሉ፤ እልል ይላሉ ፤ያጨበጭባሉ፤ ይመርቃሉ፤ ሐሴት ያደርጋሉ። ይህ አንድን ማኅበረሰብ ከሚያቀራርብና ከሚያስተሳስሩ ትውፊቶች ውስጥ አንዱ እንደሆነ የሚጠቁም ነው። ሥጋዊ ዝምድና የሌላቸው በሕፃኗ ምክንያት የተገኘው መንፈሳዊ ሥርዓት በመካከላቸው ማኅበራዊ ዝምድናን እንዲፈጠሩ ምክንያት ኾኗል። ደስታቸው የጋራ ነው፤ ይህም ባህላቸው፣ እሴታቸውና ወጋቸው ኾኖ በዘላቂነት በትውልድ ውስጥ እያለፈ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

## 4.2. የተክሊል አፈጻጸም ሥርዓተ ክዋኔ

### 4.2.1. ከተክሊል በፊት የሚደረግ ሥርዓተ ክዋኔ

ተክሊል ሰውነታቸውን ከሥጋዊ ፍላጎታቸው በመቅጣት፣ በክርስትና ሕግ ጸንተው ለሚገኙ፣ ራሳቸውን ከዝሙት ጠብቀው በድንግልና ለቆዩ ክርስቲያኖች የሚፈጸም የጋብቻ ሥርዓት ነው። የተክሊል ጋብቻ ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ብቻም የተሠራ አይደለም። ራሳቸውን ከዝሙት አርቀው፣ በድንግልና እንኖራለን ብለው፣ ከወሰኑና በተፈጥሮ  ጃንደረቦች ከኾኑ ሰዎች በስተቀር ለሰው ኹሉ የተሠራ ሕግ ነው። ድኻና ባለጸጋ፣ ጌታና  ሎሌ መኾን በተክሊል ሥርዓት እኩል ናቸው።

ለመረጃ አቀባዮቼ የተክሊል ጋብቻ ለመፈፀም ምን ምን መስፈርቶች መሟላት አለባቸው የሚል ጥያቄ አቀርቤ ነበር። የተክሊልን ጋብቻ ለመፈጸም የመጀመሪያው መስፈርት ክርስቲያን መኾንና ራስን ከዝሙር አርቆ በድንግልና መቆየት ነው፤ኹለተኛው መተጫጨት ነው። ለመጋባት ፈቀደኛ የሆኑ፣ ተገቢውን የክርስትና ትምህርት የወሰዱ፣ ዕድሜያቸው ለዐቅመ

አዳምና ሔዋን የደረሱ፣ ከ15 ዓመት በላይ ዕድሜ ያላት ድንግል ከ20 ዓመት በላይ ዕድሜ ካለው ድንግል ጋራ መተጫጨት ይችላሉ። ኹለቱ ዕጮኛሞች ወደ ቤተ ክርስቲያን በመኼድ በራሳቸው ፈቃድ ለመጋባት መወሰናቸውንና ቤተሰቦቻቸው ፈቃደኛ መኾናቸውን በንስሐ አባታቸው አማካይነት ለኤጲስ ቆጶሱ ይገልጻሉ። ኤጲስ ቆጶሱም ቃላቸውን ይቀባሉ፤ ሥጋዊና መንፈሳዊ ዝምድና እንደሌላቸው ያረጋግጣሉ። በቤተ ክርስቲያን ደንብ ለጋብቻ የሚበቁ መኾናቸውን ከተረዱ በኋላ ይፈቀዱላቸዋል።

በተጨማሪም ቀሲስ ኃይለ መስቀል ጸጋዬ የሚከተለውን ገልጸውልኛል፤ የተክሊል ሥርዓት የሚፈጸመው በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው። ኤጲስ ቆጶሱ ኹለቱን ተጋቢዎች ከጋብቻ ሊከለክል የሚችል ነገር ካለ፣ ያረጋግጣል። በሕጋዊ ጋብቻ አንድ አካል ከኾኑ በኋላ ሊለያዩ ስለማይገባ አስቀድመው የማጣራቱን ተግባር ያከናወናሉ። ኹሉንም በሚገባ ካጣሩ በኋላ ይፈቅዱላቸዋል። ከሰርጉ ቀን አስቀድሞ ከኤጲስ ቆጶሱ  የተሰጣቸውን ማስረጃ በአቅራቢያቸው ላለው ቤተ ክርስቲያን ያቀርባሉ። ፣ከዘመዶቻቸው ጋራ በሽማግሌዎች ወይም በምስክሮች ፊት የፊርማ ሥርዓት በቤተክርስቲያን ይፈጽማሉ (ቃለ መጠይቅ  ግንቦት 6 ቀን 2010 ዓ.ም)። የተክሊሉ ሥርዓት ከመፈጸሙ አስቀድሞ በኤጲስ ቆጶስ ወይም በቄስ አማካይነት የመፈራረም ሥርዓት እንደሚፈጸም በምልከታዬ አረጋግጫለኹ ።

## 4.2.2. የተክሊል ሥርዓተ ክዋኔ

ሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ለእያንዳንዳቸው የሚፈጸም የራሳቸው የሆነ መጽሐፈ ጸሎትና የአፈጻጸም ሥርዓት እንዳላቸው (ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ 1988÷29)፣ (ክንፈ ገብርኤል 1983፣ 29-30) ገልጸዋል። ሥርዓተ ተክሊልም የራሱ የኾነ ጸሎትና ሥርዓት አለው።[26] በቀን 28/08/2010 ዓ.ም በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ገዳም የነበረኝ ምልከታ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ። ወደዚህ ገዳም ደብዳቤዬን ካሥገባሁ በኋላ  በዚህ ቀን ሰርግ መኖሩን ከሰበካ ጉባዔ ካረጋገጥኩ በኋላ ፎቶ እንዲያነሱልኝ ኹለት ዲያቆናትን ትብብር ጠየቅሁ እነርሱም ፈቃደኛ ኾነው እገዛ አድርገውልኛል።

---

[26] ጋብቻ ያለ ሥርዓተ ተክሊል ሊፈጸም እንደማይገባ (በፍ. ነገ አንቀጽ 24 ሐምስ ክፍል፣ ደግሞ መጅ፣ 1958…) ተገልጿል።

የተክሊሉ ሥርዓት ከ10፡00 በኋላ እንደሚጀምር ቀድመው ነግረውኛል፡፡ እኔም በዕለቱ በቤተ ክርስቲያኗ የተገኘሁት ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ነበር፡፡ ልክ ቤተ ክረስቲያን ስደርስ ግቢው ተከፍቶ አገኘሁት፡፡ ወደ ውስጥ በቀጥታ ስዘልቅ ብዙ ነጭ ልብስ የለበሱ ሰዎችን ተመለከትኩ፡፡ ሴቶች ከቤተ ክርስቲያኗ በስተደቡብ በኩል፣ ወንዶች ደግሞ በስተሰሜን በኩል ቆመው ነበር፡፡ እኔም ነጠላዬን መስቀልኛ አጣፍቼ ወደ ወንዶቹ ተጠጋኹ፡፡ በዋና ረዳትነት ያነጋገርኳቻን ዲያቆን ሚሊዮንን መምጣቴን ነግሬ ውጪ መጥተው ሰላምታ ተለዋውጠን፡፡ ምን ምን መቅረጽ እንዳለባቸው በቅደም ተከተል አስረዳኂቸው፡፡ እኔም አንዳንዴ በምልክት እንደማሳያቸው ነገርኳቸው፡፡ ልክ 10፡00 ሰዓት ሲሆን አንድ ዲያቆን መጡና ለወንዶቹ ኹሉ ጧፍ ሰጣቸው፡፡ ሌላኛው ዲያቆን ለሴቶቹ ሰጧቸውና ወደ ቤተ ክርስቲያኗ የምዕራብ መግቢያ ብር አውደ ምሕረቱ አጠገብ ቀረቡ፡፡ ሴቶቹ በዚያው በስተደቡብ ወንዶቹ በስተሰሜን እንደኾኑ ጧፉን ለኮሱት፤ስም እየጠሩ አምስት ቦታ ከፈሏቸው፤ በቡድን በቡድን ኾነው አምስት ቦታ ስመለከታቸው የሙሽሮቹ ዘመዶችና አጃቢዎቻቸው መስለውኝ ነበር፡፡ ይሁንና በዚህ ቀን የተካኼደው ሰርግ አምስት ስለነበር ነው፡፡

**ፎቶ 17 ሙሽሮች ጧፍ እያበሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ**



**(ፎቶ በዲ/ን ሚሊዮን ተሾመ)**

ሙሽሮቹንና ሚዜዎቻቸው ከፊት ፣ አጃቢዎቻቸውና ዘመዶቻቸው ከኋላ ኾነው ጫማቸውን እያወለቁና እየተሳለሙ በየተራ ወደ ቤተክርስቲያኗ መግባት ጀመሩ፡፡ ኹሉም ጧፋቸውን እያበሩ ነበር፡፡ ነጠላቸውን መስቀልኛ አጣፍተዋል፡፡ እኔም ዐብሬ ወደ ውስጥ በመግባት ከቅድስቱ ተጠግቼ ከሚዜዎቹ ጀርባ ቆምኩ፡፡

ሙሽሮቹ ለብቻቸው ወንበር ተዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ከመቅደሱ ፊት ለፊት ከፍ ብሎ በተሠራና የብረት መከለያ አጥር ካለው ቦታ ላይ ተነጥለው እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ ሙሽሮቹ አስር ስለሆኑ ጥንድ ጥንድ ሆነው ሴቶቹ በስተ ደቡብ አቅጣጫ፣ ወንዶቹ ደግሞ በስተሰሜን አቅጣጫ ነበር የተቀመጡት፡፡ ሚዜዎቻቸው ኹሉም ከኋላ እንዲቆሙ ተደርገ፤ ሚዜዎቹም ሴቶቹ በስተ ደቡብ ወንዶቹ በስተሰሜን ነበሩ፡፡ አጃቢዎች ከካህናቱ ማኅሌት ከሚቆሙበት ፊት ለፊት ከምዕመናን ጋር አብረው ቆመዋል፡፡ ኹሉም ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ነበር፡፡

**ፎቶ 18 ሙሽሮች ከመቅደሱ ፊትለፊት ሥርዓቱ ሲጀመር በከፊል**





**(ፎቶ በአጥኚው)**

ከሙሽሮቹ እስከ መቅደሱ ድረስ ቀይ ምንጣፍ ተነጥፏል፡፡ በምንጣፉ ላይ ሌላ ባለ አበባ ምንጣፍ፣ ሙሽሮቹ እግር ሥር ተነጥፏል፡፡ ከፊት ለፊታቸው በቀይ ግምጃ የተሸፈነ ክብ ጠረጴዛ ላይ በጠርሙስ የተቀመጠ ዘይት አለ፡፡ ከጠርሙሱ አጠገብ ወርቃማ ሽፋን ያለው ትልቅ መጽሐፍ ተቀምጧል፡፡ ሽፋኑ ላይ የመስቀል ሥዕል አለበት፤ ከመስቀሉ ሥር መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የሚል ጽሑፍ አለበት፡፡ ድንግል ሙሽሮች ራሳቸው ላይ የሚደፉት አክሊል አጠገቡ አለ፡፡ አንደኛው ጥንድ አክሊል ነጭ ነው፣ ኹለቱ ጥንድ

አክሊሎች ወደ ቡኒ የሚጠጋ ደማቅ ያልሆነ ቀይ ቀለም አለችው። ሦስተኛው ጥንድ ሽሮ መልክ አለው። ከአክሊሎቹ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ካባ ላንቃዎች በሙሽሮቹ ቁጥር ልክ ተቀምጠዋል። አክሊሎቹ መኻከል ላይ ከነሐስ የተሠራ ወርቃማ ቀለም ያለው መስቀል አላቸው። ከካባዎቹ ጀርባ ላይ የመስቀል ምልክት አለ።

ካህናቱ በዜማ ጸሎት እያደረሱ ነበር። በሴቶቹ መቆሚያ በኩል በዝምታ የቆሙ ሴቶች ነበሩ። መጽሐፍ ይዘው ድምጻቸው ሳይሰማ የሚጸልዩም ነበሩ። ሁሉም ሴቶች ራሳቸውን ተከናንበዋል፤ ቀሚሳቸውም እስከ ተረከዛቸው ድረስ ረዥም ነው። በወንዶቹ በኩል መጽሐፍ ይዘው የሚጸልዩ አሉ። ከካህናቱ ጋር በዜማ አብረው የሚጸልዩም ነበሩ። ኹሉም ነጠላቸውን መስቀልኛ ለብሰዋል፤ ነጠላ ያልለበሰ አንድም ሰው አልነበረም። ካህናቱ በአራቱም ማዕዘን መስመር ሰርተው ነው የቆሙት። ከሕዝቡ የሚለያቸው በአራቱም አቅጣጫ ወንበር አለ። ከካህናቱ መኻል ላይ ኹለት ከበሮ ተቀምጧል፤ አጠገቡ ጸናጽን አለ። እያንዳንዳቸው መቋሚያ ይዘዋል። ከምዕራብ በኩል የቆሙት ካህናት ፊታቸውን ወደ ምሥራቅ አዙረዋል። በምሥራቅ በኩል የቆሙት ወደ ምዕራብ፣ በደቡብ በኩል የቆሙት ወደ ሰሜን፣ በሰሜን በኩል የቆሙት ፊታቸው ወደ ደቡብ አቅጣጫ የዞረ ነበር።

ከሙሽሮቹ ፊት ለፊት አትሮንስ ላይ አደረጉና ‹‹ተአምረ ማርያም›› አንድ ቄስ አነባቡ። ከዚያም በመቀጠል የኢየሱስ ክርስቶስ የጠዋት ምስጋና የሚባለውን ኪዳን ዘነግህ መጸለይ ጀመሩ። ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ታዳሚ በሙሉ በጋራ ሲጸለዩ ነበር። የዚህ ጸሎት መሪ የነበሩት ካህን ብቻ በተለያየ አቅጣጫ ሕዝቡን በመስቀል እየባረኩ ያዜማሉ። ኹሉም ሰው ፊቱን ወደ ምሥራቅ አዙሮ በዜማ ከእርሳቸው እየተቀበለ ያዜማል። የጸሎቱን ዓይነት ምን እንደሚባል ጠይቄነበር ኹልጊዜም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በኹሉም አብያተ ክርስቲያናት ከቅዳሴ በፊት ዘወትር የሚጸለይ ጸሎት ነው ። ቅዳሴ በማይኖር ቀንም ይህ ጸሎት ዘወትር እንደሚጸለይ መረጃ አቀባዮቹ ነግረውኛል።

ከዚያም "መጽሐፈ ተክሊል" ላይ ያለውን ጸሎት መሪው ቄስ በአማርኛ ማንበብ ጀመሩ። "የተወደዳችሁ ምዕመናን ኸይ ዛሬ በዚህች ቀን ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን በተቀደሰች ጋብቻ አንድ ልናደርጋቸው ተሰብስበናል" አሉ እያንዳንዳቸውን በክርስትና ስማቸው እየጠሩ ነበር። ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ለሕዝቡ ኹሉ እየተሰማ መጽሐፈ ተክሊሉ ላይ ያለውን ጽሑፍ በአማርኛም፣ በግዕዝም አነበቡት። ቄሱ ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ሙሽሮቹ ነበር። ልብሱ ላይ፣ ዘይቱ ላይ እና አክሊሉ ላይ የሚጸለዩትን በቅደም ተከተል ጸለዩ።

በመቀጠልም መሪው ካህን በየክርስትና ስማቸው ጠሯቸው። አምስቱም ጥንድ ሙሽሮች በየተራ ወደፊት ለፊት ወጡ። እጃቸውንም በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ እንዲያደርጉ ካህኑ አዘዟቸው። በመጀመሪያ ወንዱን እንዲህ አሉት "ልጄ ይህችን ሴት ሚስትህ ልትኾን፤ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዝም በሕግ አግብተኻት ከእሷ ጋራ ልትኖር ትወዳለህን? በድካሟስ ጊዜ ታጸናታለህን፤ በሐዘኗስ ጊዜ ታረጋጋታለህን፤ በሥራህስ ደስ ታሰኛታለህን፤ ባለ ዘመንህ ሁሉ ትከታተላለህን ?›› ብለው ጠየቁት። እርሱም በንባብ እርሳቸው የተናገሩት እያደገመ ‹‹ያሉኝን ኹሉ ለማድረግ ቃል እገባለሁ›› አለ። እርሷንም ‹‹ይህን ሰው እንደ ጌታችን ትዕዛዝ በሕግ አግብተሽ እየታዘዝሽለት ሁልጊዜ ፈቃዱን እየፈጸምሽ፤ ባለ ዘመንሽ ሁሉ እሱን እየተከተልሽ ከእርሱ ጋር ልትኖሪ ትወጃለሽ?" አሏት ‹‹አዎን ፈቃዴ ነው›› አለች። ይህን ቃለ መሀላ እጃቸውን በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አድርገው ቄሱ ከመጽሐፉ እያነበቡላቸው ሙሽሮችም እየተቀበሉ ተናገሩ። አምስቱም ሙሽሮች በየተራ እጆቻቸውን ደራርበው ቄሱ የሚሏቸውን በመድገም ከውነውታል።

**ፎቶ 19 ሙሽሮች ቃል ሲገቡ በከፊል**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

ከዚህ በመቀጠል ወንዶቹ ሙሽሮች የሴቶችን ቀኝ እጃቸውን ያዙ። አሳዳጊዎቻቸውና ሚዜዎቻቸው ወደ እነርሱ ቀረቡና ሙሽሮቹ ወንዶቹም፣ ሴቶቹም በየተራ የሚከተለውን ጽሑፍ ለሕዝቡም እየተሰማ ጮክ ብለው አነበቡት።

*እኔ እገሌ እገሊትን እያንዳንዳቸው ስማቸውን የጠቀሱት በክርስትና ስማቸው ነበር። እኔ እገሌ እገሊትን ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ወድጄ ተቀብያታለሁ። ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ በሥራዋ ኹሉ በተቻለኝ እረዳታለሁ፤ በሕመሟ፣ በጤናዋ፣ በደስታዋና በኀዘኗም ጊዜ ከእርሷ ጋር እኾናለሁ። መካነች፣ ሰነፈች፣ ጠቆረች በማለት ይህንንም በመሳሰለው ምክንያት ኹሉ በልዑል እግዚአብሔር ትዕዛዝ ከሷ በሞት እስክለይ አልተዋትም፤ ወድጄ ተቀብያታለኹና ለዚህም በእግዚአብሔርና በተቀደሰችው ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ፊት በመሀላ ቃሌን እሰጣለሁ።*

ሙሽራይቱም ከላይ የቀረበውን በተመሳሳይ እኔ እገሊት እገሌን….) በማለት ቃለ መሐላቸውን ፈጸሙ። አምስቱም ጥንዶች በየተራ አነበቡት። ሙሽሮቹ ቀኝ እጃቸውን በማደራረብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ መሀላቸውን ከፈጸሙ በኂላ ቀለበቶቻቸውን በመያዣ እያደረጉ ለቄሱ ሰጧቸው ቄሱም ከመሪው ቄስ ፊት አኖራቸው። ካህኑም የቀለበት ጸሎት መጸለይ ጀመሩ ጸሎቱን እንደጨረሱ ቀለበቶቹን በያዙት ትልቅ እፀ መስቀል ሦስት ጊዜ ባረኳቸው በመጀመሪያ የሰጡት ነጭ ካባና፣ ነጭ አክሊል፣ ነጭ መጎናጸፊያ ለለበሱት ሙሽሮች መጀመሪያ ለወንዱ ነው። ሙሽራውም ለሙሽራይቱ በግራ እጇ አራተኛ ጣት አደረገላት። በክርስትና ስሟ እየተጣራ “እገሊት ሆይ ከዛሬ ጀምሮ ሚስቴ ልትሆኚ አግብቼሻለሁ” አላት ለማግባቴም ምልክት ይሆነኝ ዘንድ ይህን ቀለበት አደረኩልሽ። ከዛሬ ቀን ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ያገኘሁትን ሁሉ ካንቺ ጋር አንድ አደርጋለሁ። ለዚህም ምስክሬ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ናቸው። እያለ ተናገረ። ሙሽራይቱም “አሜን” ትል ነበር። በመቀጠል ቄሱ ለሙሽራይቱ ሰጧት እሷም በተራዋ እሱ ያለውን በክርስትና ስሙ” በተመሳሳይ እያለች በአራተኛው የግራ እጅ ጣቱ ቀለበት አደረገችለት። አምስቱም ሙሽሮች በተመሳሳይ ቀለበታቸውን አደረጉ። የሚመሩት ቄሶች ሦስት ነበሩ ሌሎች ዲያቆናትና ረዳት ካህናትም ነበሩ። ነጩን የሙሽራ ልብስ የለበሱት የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪ ሙሽሮች ናቸው ። ሌሎቹ ሙሽሮች የለበሱት ወደ ቡኒ  የሚጠጋ ቀለም ያለው ነው። የቀለበቱ ሥርዓት እንደተፈጸመ ቄሱ መጸለይ ጀመሩ።

ሙሽሮቹ እያንዳንዳቸው ያደረጉት ቀለበት ልሙጥና ክብ ነበር። በላዩ ላይ ምንም ዓይነት ፈርጥና መስመር አልነበረውም የቀለበቱን ምሳሌነት ምን እንደሆነ በቡድን ውይይት ወቅት እንዲህ ነግረውኛል። ቀለበት  የሃይማኖት ምሳሌ ነው። ሙሽሮች ቀለበት በሚያደርጉበት ጊዜ ቃል ኪዳናቸው የማይቀየርና የማይለወጥ፣ እስከ መጨረሻው ዕለተ ሞታቸው ድረስ የጸና መኾኑን የሚያሳይ ነው። ቀለበት በክብነቱ ፍጻሜ የለሽ ነው። በተክሊል የሚጋቡ ሰዎችም ከሕይወት ፍጻሜ በስተቀር በትንንሽ ነገሮች ጋብቻቸውን አያፈርሱም። በዚህም ቃላቸው

ለዘለዓለም የጸና መኾኑን፣ ጋብቻቸውም በማያልቅ የሃይማኖትና የፍቅር መሠረት ላይ የታነጸ እንደኾነ የሚያስረዳ ነው። ልሙጥና ምንም ዓይነት ፈርጥ የለበትም፤ የተክሊል ጋብቻም ያለማንም አስገዳጅነት በኹለቱ ተጋቢዎች መፈቃቀድ ቃላቸው የጸና መኾኑን ለማመልከት ነው። ከኀጢአት ራሳቸውን በንጽሕና ጠብቀው የቆዩ በመኾናቸው ንጽሕናቸውንም የሚያጠይቅ ነው በማለት ቀለበት የታማኝነትና የሃይማኖት ምሳሌ እንደኾነ ተናግረዋል።

መሪው ካህን ካባው ላይ እና አክሊሉ ላይ የሚጸለየውን ጸሎት ከጸለዩ በኋላ አምስቱንም ጥንዶች ካባውን አለበሷቸው። ተክሊልን በሚመለከት ባደረኩት የቡድን ውይይት የእያንዳንዱን የንዋያተ ቅዱሳት አገልግሎት እና ምሳሌ እንደሚከተለው ተርጉመውልኛል። ሙሽሮች በቀኝ እጃቸው ወንጌልን ወይም መስቀልን በእጃቸው ጨብጠው ቃል ይገባሉ። ሙሽሮች በሕይወት ከማኅበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ የተለያዩ የሃይማኖትና ሥጋዊ ፈተናዎች አሉባቸው። እነዚህን ፈተናዎች ለመወጣት መከራን ይቀበላሉ ትግል ያደርጋሉ። ይህን ትግል በሚያደርጉበት ወቅት የሚያደርጉትን ፈተና ያመለክታል። ምክንያቱም ደግሞ ተጋቢዎች በመስቀሉ ኃይል ወይም በወንጌሉ ትምህርት ፈተናውን ድል እንደሚያደርጉ ይታመናል። ወንጌልና መስቀል የድል አድራጊነት፣ የአሸናፊነት፣ ከፈተና በድል የመውጣትና ወድቆ የመነሳት ምልክት ተደርገው ተወስደዋል።

ሙሽሮች ከነሚዜዎቻቸው ነጭ ልብስ ለብሰዋል። በዚያ ላይ ደግሞ ካባ ደርበዋል። ነጭ ልብስ ሙሽሮች የሚቀበሉትን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ምሳሌ እንደሆነ ይተረጎማል። አንድም ክርስቲያን ናቸውና አንድ ልብስ ለብሰው አንድ ክብር ወርሰው በዚህ ዓለም በጋብቻ የመኖራቸውን ያህል በወዲያኛው ዓለም ከክርስቶስ ጋር ይኖራሉ፣ መንግሥተ ሰማያትንም እንደሚወርሱ ይታመናል።[27]

በደብረ ሊባኖስ ባደረግሁት ምልከታ በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ከካባው በተጨማሪ መጎናጸፊያ አልብሰዋቸው ተመልክቻለሁ። የዚህንም ምሳሌ በቡድን ውይይት ወቅት እንዲህ ገልጸውልኛል አንድ መጎናጸፊያ መልበሳቸው ኹለቱ ሙሽሮች ከዚህ በኋላ አንድ አካል አንድ አምሳል መኾናቸውን ለመግለጽ ነው። በተጨማሪም ክብርንና ትንሣኤን እንደሚያመለክት ገልጸውልኛል። ይህ ክብር የሚደረግላቸው ሥጋቸውን ከኀጢአት አርቀው የአምላካቸውን ፈቃድ በመፈጸማቸውና ኹለቱም ክብር ስለሚገባቸው ነው ሲሉ አስረድተውኛል።

---

[27]ሙሽሮቹ በቃለ መሀላ ወቅት ያነበቡት ጽሑፍ በመጽሐፈ ተክሊል (1956፡ 25) ጸሎተ ተክሊል (1956÷1) ሰፍሯል

አባ ኪዳነ ቃል አካሉ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም የሀዲስትና ብሉያት መምህር፣ (በማቴዎስ ወንጌል 19÷4) የተገለጸውን መሠረት አድርገው ይህንን ጉዳይ ሲገልጹ "ስለዚህ ወንድ አባቱንና እናቱን ይተዋል፤ ሚስቱንም ይከተላል፤ ኹለቱም አንድ አካል ይኾናሉ። በማለት ኹለቱ ሙሽሮች አንድ መጎናጸፊያ የለበሱት በቅዱሱ የተክሊል ጋብቻ አንድ የመኾናቸውን ምሳሌ፣ አንድም ሊለያዩ የማይችሉ መኾናቸውን፣ አንድም አንድ አካል ላደረጋቸው ጸጋ የበቁ መኾናቸውን የሚያስረዳ እንደኾነ ተናግረዋል። የተለያዩ ኹለት ጾታዎች አንድ አካል ኾነዋል። ኹለት አንድ የሚኾንበት ፣ አንድ የሚያደርጋቸውን ጸጋ በተክሊል ተቀብለዋል። ይህም የሙሽሮቹ ጋብቻና ተዋሕዶ የክርስቶስና የአማኞቹ ምሳሌም ነው። ነጭ መጎናጸፊያ መልበሳቸው ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ያላቸው የሥላሴ ልጆች መኾናቸውን ለመጠየቅ ነው። አንድም ነጭ ልብስ ጸዐዳ ነውና የንጽሕናቸውና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መኾኑን ተተረጉሟል። በተጨማሪም የሙሽሮቹን በነጭ መጎናጸፊያ በአንድነት የሚለብሱትን በመጽሐፍ ቅዱስ (ኤፌ 5÷32) የተገለጸው ዋቢ አድርገው የሚከተለውን ገልጸዋል፤ "ዐቢይ ውእቱ ዝ ነገር አንሰ እብሎ ላዕለ ክርስቶስ ወላዕላ ቤተ ክርስቲያን" በማለት የሙሽራውና የሙሽራዩቱ ተዋሕዶ እጅግ ትልቅ ነገር ነው። ይህም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ተዋሕዶ ምሳሌ ነው። አንድም ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያን ኅብረት ስለሆኾነ የኹለቱ አንድ መኾን የክርስቶስና የምዕመናኑ አንድነት ምሳሌ ነው ሲሉ አስረድተዋል።"

**ፎቶ 20 ሙሽሮች ካባ ለብሰው በከፊል**





**(ፎቶ በአጥኚው)**

ከዚያ በመቀጠል ከአምስቱ ሙሽሮች ለአራቱ ራሳቸው ላይ አክሊል አደረጉላቸው፡፡ ከአምስቱ አንደኛው በመዓስባን የሚጋቡ ስለነበሩ አክሊል አልተደረገላቸውም፡፡ መረጃ አቀባዮቼን ከአምስቱ አንደኛው ተክሊል ያልደፉበትን ምክንያት ጠይቄ ምን እንኳን አብረው ይቁሙ እንጂ አክሊል ያልተደረገላቸው ሙሽሮች በቁርባን የሚጋቡ ናቸው፡፡ ወይም በመዓስባን የሚጋቡ እንደሆኑ ገልጸውልኛል፡፡ ጸሎቱም ሆነ ሥርዓቱ ተክሊል ከተፈጸመላቸው የተለየ ነው፡፡ ይህ የጋብቻ ዓይነት በድንግልና ጸንተው ላልቆዩ፣ ባል ወይም ሚስት በሞት ተለይቷቸው ሌላ ለሚያገቡና አግብተው ለፈቱ የሚደረግ ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህም የክብር ተክሊል አይደረግላቸው ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ በዕለቱ በማዓስባን(በቁርባን) ለተጋቡት ሙሽሮች ከሌሎቹ አራቱ ሙሽሮች አጠገብ ለብቻቸው ካህናት አስፈጻሚዎች ተመድበው ጸሎት ሲደረግላቸው ተመልክቻለሁ፡፡

**ፎቶ 21 ሙሽሮች ካባ ለብሰውና አክሊል ከተደረገላቸው በኋላ በከፊል**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

በድንግልና ተክሊል ለፈጸሙት ሙሽሮች ራሳቸው ላይ አክሊል የጫኑላቸውን ትርጉም መረጃ አቀባዮቼ በቡድን ውይይት ወቅት እንደገለጹልኝ፡፡ ሙሽሮቹ ለዚህ ክብር የበቁት ከብዙ ሥጋዊ ፈተናና ውጣ ውረዶች በኋላ ነው፡፡ የአፍላ፣ የእሳተነትና የአስቸጋሪ የወጣትነት ጊዜያቸውን በእግዚአብሔር ረድኤት አልፈው፣ በድንግልና ቆይተው፣ ለዚህ ታላቅና መንፈሳዊ ጋብቻ ሲደርሱ ቤተ ክርስቲያን ለክብራቸው መገለጫ እንዲኾን የምትሸልማቸው አክሊል ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያኒቱ አሰተምህሮ “አክሊል” ሰማያዊ ክብርን የመቀዳጀት ምሳሌ ነው፡፡ ሰዎች በሰማዕትነት ሲሞቱ የእግዚአብሔርን የክብር አክሊል ተቀዳጁ ይባላል፡፡ በድንግልና ቆይቶ ለተክሊል ክብር ሲበቁ አክሊሉ ለክብራቸው መገለጫ ሽልማት ነው፡፡ አክሊሉን ሲያደርጉላቸው ትዳራችሁን ጠብቃችሁ ከኖራችሁ፣ አንድም ሰማያዊ የክብር አክሊልን ትቀዳጃላችሁ ሲሉ

በምሥጢር የማብሠር ምሳሌ ነው፡፡ በተጨማሪም በተክሊል የተጋቡ፣ በሥጋ ወደሙ የከበሩ ስለሆነ በጾም፣ በጸሎት በንሥነ፣ በመልካም ምግባራት ኹሉ ጸንተው እንዲኖሩ ይጠበቃል፡፡ አክሊል መቀዳጀታቸው በሕይወት ዘመናቸው በተስፋ እንዲጸኑ ያስችላቸዋል ተብሎ ይታመናል፡፡[28]

ከዚያ ቀጥሎ የተካኼደው ሥርዓት ሜሮን የመቀባት ሥርዓት ነው፡፡ መሪው ካህን ሜሮኑ ላይ ጸሎት ማድረስ ጀመሩ፡፡ ከጸሎቱ በኋላ ሦስት ቄሶች ቅብዐ ሜሮኑን በእጃቸው እያደረጉ የሚታዩ የአካል ክፍሎቻቸውን መቀባት ጀመሩ፡፡ ከግንባራቸው ጀምረው፣ በመስቀል ምልክት እያደረጉ "ጉንጫቸውን፣ ዐይናቸውን፣ አፋቸውን፣ አገጫቸውን፣ እጃቸውን ውስጡንና ውጩን ቀቧቸው፡፡ በክርስትና ጊዜ ሜሮን ተቀብተዋል፡፡ አሁን በድጋሚ በጋብቻቸው ወቅት የሚታዩ አካሎቻቸው ሜሮን ቀቧቸው፤ የዚህ ትርጉም ምን እንደኾነ ጠይቄ መምህር ፈቃዱ ሣህሌ እንዲህ ነግረውኛል፡፡

> *ሜሮን መንፈሳዊ ልጅነት የሚታተመበት ቅዱስ ዘይት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ ለአማኞች የሚሰጥበት ምስጢርም ነው፡፡ ሙሽሮቹ ቅብዐ ሜሮኑን ሲቀቡ መንፈስ ቅዱስ ያድርባቸዋል፡፡ በትዳር ዘመናቸው ኹሉ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የማይለያቸው መኾኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ክርስትና በተነሡ ጊዜ አካላቸው የክርስቶስ መኾኑን በሜሮን ማኅተምነት አረጋግጠዋል፡፡ ሥጋቸውን ከዝሙት አርቀው በድንግልና የቆዩ ናቸው፡፡ በተክሊል ጋብቻም በሜሮን ከብረው የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለብሰዋል፡፡ እነዚህ ሙሽሮች ከልጅነታቸው ጀምሮ በክርስቶስ ጸጋ ያደጉ ናቸው፡፡ አሁንም በድንግልና ቆይተው የሃይማኖት ፍሬያቸውን ተክሊል አድርገው ለሌሎች አርአያ ኾነው አሳይተዋል፡፡ ይህን ያገኙት ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ማደጋቸውና የተማሩትን መተግበራቸው እንደኾነ (በቆሮ 6÷13) የተገለጸውን ጥቅስ ዋቢ አድርገው ገልጸውልኛል (ቃለ መጠይቅ ግንቦት 11 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡*

መርጌታ ዲበኩሉ ሥዩም ስለ ተክሊል ጋብቻ ክብር መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ እድርገው የሚከተለወን ገልጸውልኛል፡፡ "ሥጋችሁም ለእግዚአብሔር ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፣ እግዚአብሔርም ለሥጋችሁ ነው፡፡.... ሥጋችሁ የክርስቶ አካል እንደሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን አካል ወስዳችሁ የአመንዝራ አካል ታደርጉታላችሁን? አይገባም፡፡ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር ለተቀበላችሁት በእናንተ አድሮ ላለ መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደኾነ አታውቁምን? ለራሳችሁ አይደላችሁም፡፡ በዋጋ ተገዛታችኊልና ስለዚህም እግዚአብሔርን በሥጋችሁ አክብሩት፡፡ በማለት (በቆሮ 6÷13) የተጻፈውን እያከበሩ ራሳቸውን

---

[28]ወኢይሜኒ ከመይኩን አዳም ባሕቲቱ" አዳም ብቻውን ሊኖር አይገባም፤ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ፡፡ ዘይረድኦ አለ፤ ሔዋን በአዳምነት እንዳለች ለማጠየቅ የምትረዳውን ሔዋንን እንፍጠርለት፡፡ ወመፍቅድ ቀዳማዊ ዘአውስቦ በእንተ ውሉደ ውሉድ እንደገና ያረባዋል በግቢ ጊዜ የሚኾን መጀመሪያው ፈቃድ ልጅ ለመውለድ ነው አንድም ተጋግዞ ለመኖር አንድም የፈቲውን ጾር ለማራቅ ነው (ፍነ. መን. አን. 24፣ 1958፣ 294)፡፡

የክርስቶስ ንጹሕ ቤተ መቅደስ አድርገው የቆዩ ናቸው፡፡ በክርስትና ወቅት በውስጣቸው ያደረውን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ አኹንም በክበረ ጋብቻቸው ጸንቶ እንዲኖር አድርገው ተቀብለውታል፡፡ ይህንንም በሕይወት ዘመናቸው ጠብቀውት እንደሚኖሩ ይታመናል (ቃ.መ ሰኔ 4 ቀን 2010 ዓ.ም)፡፡

ካህኑ ሜሮኑን ቀብተው እንዳበቁ ወደ ሙሽሮቹ ዞረው በአማርኛ ጸሎተ ተክሊል ላይ ያለውን አነበቡ፡፡ ምክርን የሚገልጽ ነበር፡፡ ሙሽሮቹ በጋብቻ ሕይወታቸው ታማኝ ኾነው እንዲኖሩ፤ በመከባበርና በመረዳዳት፣ በጾም በጸሎት ጸንተው በፍቅር እንዲኖሩ የሚገልጽ ነው፡፡ በመጨረሻም አባታችን ሆይ የሚለውን ኹሉም እንዲጸልዩ በማድረግ የተክሊሉን ሥረዓት አጠናቀቁ፡፡ የቅዳሴው ሥርዓት ከ 12፡10 ጀምሮ ተካኼደ ሙሽሮችም ሥጋ ወደሙ ተቀበሉ፡፡ በዕለቱ ዲያቆን ሙሽራ ስለነበር መጀመሪያ የቆረቡት እነርሱ ነበሩ፡፡ ከዚያ ሦስቱ አክሊል የደፉት ቆረቡ፤ በመጨረሻ በመዓስባን ያገቡት ቆረቡ፡፡ መዘምራን ካህናት ቅኔ አቀረቡ፡፡ ቅዳሴውን የመሩት ካህን ሕዝቡን ከማሰናበታቸው በፊት የቤተክርስቲያኗ ካህናት ሙሽሮችን በሚመለከት ወረብ አቀረቡ፡፡ ‹‹ትብሎ መርዓት ለመርዳዊሐ፣ ቃልከ አዳም›› እያሉ ሰንበት ተማሪዎች የማኅበረ ቅዱሳን መዘምራን አመሰገኑ፡፡ ወረብ ያቀረቡት ካህናት ነጭ ጥንግ ድርብ ለብሰው ነበር፡፡ የልብሱ ጥለት በጣም ሰፊና መንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም የሚል ጽሑፍ መኻከሉ ላይ አለበት፡፡ በጥለቱ ጫፍ ዙሪያውን የመስቀል ምልክት አለበት፡፡ መዘምራኑ ራሳቸው ላይ ነጭ ሻሽ ጠምጥመዋል፡፡ መቋሚያና ጸናጽን ይዘዋል፡፡

**ፎቶ 22 ክህናቱ ከሙሽሮቹ ፊት ወረብ ሲያቀርቡ**





**(ፎቶ በአጥኚው)**

ለ 25 ደቂቃ ያህል በዜማ ወረቡን አቀረቡ፤በመጀመሪያ አንድ ካህን ዜማውን ቃኙት ከዚያም በአንደኛው መስመር ያሉት በዜማ ተቀበሏቸው በመቀጠል በሌላኛው መስመር በኩል በተመሳሳይ ዜማ ቀጠሉ፤ በአራተኛው ኹሉም በአንድነት በቅብብል አዜሙ፡፡ ከዚያም በጸናጽን፣ በከበሮ፣ መቋሚያቸውን ትከሻቸው ላይ አድርገው በተለያዩ የእንቅስቃሴ ዐይነቶች ክዋኔያቸውን ቀጠሉ፤ ታዳሚዎች ግማሾቹ ያጨበጭባሉ፤ ሴቶቹ እልል ይላሉ፤ ካህናቱ ያሸበሸሉ ሙሽሮቹና ታደሚዎች ላይ የደስታ ፈገግታ ይታይ ነበር፡፡ ከዚያም ካህኑ ካሳረጉ በኋላ የሕዝብ ስንብተ ተደረገ፡፡ ዲያቆኑም ወደየቤታው በሰላም ግቡ ብለው ተናገሩ፡፡ በመቀጠል እያንዳንዳቸው ሙሽሮች ከሚዜዎቻቸውና ከዘመዶቻቸው ጋራ በየተራ ከቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ መውጣት ጀመሩ፡፡ ኹሉም ሙሽሮች የወጡት በቤተ ክርስቲያኒቱ የምዕራብ በር በኩል ነበር፡፡ ከወጡ በኋላ በቀኝ በኩል ከምዕራብ ወደ ደቡብ፣ ወደ ምሥራቅ፣ ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ ቤተ ክርስቲያኗን በመዝሙር ታጅበው አንድ ጊዜ ከዞሩ በኋላ ከየዘመዶቻቸውና አጃቢዎቻቸው ጋራ ከቅጥር ግቢው ወጡ፡፡

**ፎቶ 23 መዘምራን ሙሽሮችን አጅበው ቤተክርስቲያኑን ሲዞሩ**



**(ፎቶ በአጥኚው)**

አንደኛው ሙሽራ የገዳሚ ሰንበት ተማሪዎች እየዘመሩ አጅበውት ወደ አዳራሽ ገቡ፡፡ እኔ ደግሞ ትኩረቴን ወዳሰቡት ብዙ አጃቢና መዘምራን ወደነበሩበት በመቀላቀል የሚሉትን መዝሙር ማዳመጥ ጀመርኩ፡፡ የነዚህ መዘምራን ሴቶች ለብቻ ወንዶች ለብቻ፣ ወንዶቹ በስተሰሜን ሴቶቹ ደግሞ በስተደቡብ ኾነው ይዘምሩ ነበር፡፡ “ቀይና ሰፊ ጥለት ያለው ጥንግ ድርብ ለብሰዋል፣ ሴቶቹ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ የተሸፈኑ ናቸው፡፡ ጥለት የሌለው ነጭ ልብስ ለብሰዋል፡፡ “ደስ

አላት ቤተ ክርስቲያን በጣም ደስ አላት ሙሽሪት ሙሽራው በተክሊል በቁርባን ተዋሐዱላት" እያሉ፣ ከሙሽራው ፊት እያሸበሸቡ፣ ቤተ ክርስቲያኗን አንድ ጊዜ ዞሯት። ልክ በስተሰሜን ሲደርሱ ጥግ ላይ እንዲያርፉ ተደረገ፣ አንድ ነጭ ልብስ የለበሰ ወንድ እና የባህል ልብስ የለበሰች ሴት የተቆረሰ ዳቦ ማደል ጀመሩ። ከሙሽሮቹ ጀምረው ለአጃቢዎች በዙሪያው ላለው ሰው ኹሉ ሰጡ። ዳቦውን ተመግበው እንደጨረሱ እዚው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኪና ውስጥ ገብተው ከግቢው ወጡ እኔም አቅጣጫዬን ወደ አዳራሽ አደረግኹ።

ከዚያም አዳራሽ ውስጥ የሚካኼደውን ዝግጅት ለመከታተል ገባሁ። መጀመሪያ ኹሉም ሰው ወንበር ይዞ ተቀመጠ፤ ሙሽሮች በአዳራሹ ከፍ ብሎ በተሠራው መድረክ ላይ ወንበር ተዘጋጅቶላቸው ተቀመጡ። አንድ ቄስ በትሪ ላይ የተቀመጠውን ዳቦ ባርከው ቆረሱ። እሳቸው አንድ ቁርጥ አንስተው ቀመሱ፣ ለሙሽሮቹ፣ ለሚዜዎቻቸው፣ ለታዳሚዎች በቅደም ተከተል ታደለ። አሳላፊዎች መጀመሪያ ለካህናቱ ከዚያም ለሙሽሮቹ ጠላ ቀዱላቸው። በሰፊ ጠረጴዛ ላይ ምግብ ተቀምጧል በእድሜ ተለቅ ያሉት ካህን የቡራኬ ጸሎተ አደረጉ። "ማደ አብርሐምን የባረከ ሥላሴ ለኛም ይባርኩልን" በማለት ታዳሚው አባታችን ኾይን እንዲጸልይ አደረጉ። ለሙሽሮቹ፣ ሚዜዎቻቸው ምግብ በአንድ ማዕድ አቀረቡላቸው። በየተራ አዳራሹ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች ኹሉ በሳኅን ምግብ ተሰጠ። ሙሽሮቹ ሲመገቡ እየተጎራረሱ ነበር። በአብዛኛውን ጊዜ ሚዜዎቻቸው እየተነሡ ያጎርሷቸው ነበር። በየተራ ሴቶቹም ወንዶቹም እየተነሡ አጎረሷቸው። በዕለቱ ከነበሩት ሚዜዎች ውስጥ አንዱን ሚዜ የመጎራረሱን ፋይዳ ጠይቄቸው ነበር።

"ሙሽሪት ከሌላ ቤተሰብ ወደ አዲስ ቤተሰብ እየመጣች ነው። ምንም እንኳን ከሙሽራው ጋራ ቢተዋወቁም አብረው ግን ኖረው አያውቁም። ከእኛም ከሚዜዎቿ ጋር ገና እየተዋወቀች ነው። አኹን ስንጎራረስ ፍርሐቷን ታስወግዳለች፤ እኛንም እንደወንድሞቿ አድርጋ ትቀራረበናለች፤ ትውውቃችን እየጠነከረ ይኼዳል፤ ከዚህ በፊት ብቻዋን ወይም ከሌላ ቤተሰብ ጋር በአንድ ማዕድ ትመገብ የነበረች ሙሽራ አኹን ወደ አዲሱ ቤተሰብ ስትመጣ ቤተሰቡን እስክትቀላቀል እንድትለማመድ የሚያደርጓት ሚዜዎች ናቸው። ሴት ሚዜዎቿ ለአንድ ቀን አብረዋት ቢኖሩም በማግስቱ አይኖሩም፤ አልፎ አልፎ ሊጠይቋት ይችላሉ። በጫጉላ ጊዜያቸው አብረው የሚኾኑት ወንድ ሚዜዎች ስለኾኑ እየተጎራረሱ ቤተሰባዊነትን ያለማምዷታል። ይህ ጊዜ በአንድ ማዕድ አብሮ መብላትን ፍቅርን የሚያጠናክሩበት መንገድ ነው በማለት ተርከውልኛል። ጉርሻው በባህላዊ ሰርግም ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው አዚህም ኹሉም ይጎራረሱ ነበር ደስታ

ፈገግታ ፊታቸው ላይ ይነበባል አልቀበልም የሚል አልነበርም፣ ፍቅርን መላመድን መከባበርን መተሳሰብ የሚያሰይ እንደኾነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሰንበት ተማሪዎቹ ምግቡ እንደተጠናቀቀ በያሬዳዊ ዜማ ወረብ አቀረቡ፡፡ በመጨረሻም ቄሱ ከማሳረጋቸው በፊት "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ማንም ሊለየው አይችልም፤ ሰው እናትና አባቱን ይተዋል ሚስቱንም ይከተላል" በማለት አጭር ትምህርት ሰጡ፡፡ ከዚህ በኋላ እናንተ አንድ አካል ናችሁ፡፡ ከቤተሰቦቻችኹ ከዚህ ሰዓት ጀምሮ ተለይታችኋል፤ በሐሳባችሁ በሀብታችሁ እኩል እየተወያያችሁ በሃይማኖት ጸንታችሁ ኑሩ፡፡ በጾም በጸሎት እየተጋችሁ ፍቅራችሁን ትዳራችሁን አጽኑ ሲሉ ምክር ከሰጡ በኋላ "አቡነ ዘበሰማያት" በማለት አሣረጉ የዕለቱ ሥርዓትም በዚሁ ተጠናቀቀ፡፡

### 4.2.3 ድኅረ ሥርዓተ የተክሊል ክዋኔ

በተክሊል የተጋቡ ባልና ሚስቶች ከጋብቻቸው በኋላ አንድ ልብ ኾነው በመተማመን ይኖራሉ፡፡ በሀሳብ ቢለያዩም እየተመካከሩ ሀሳባቸውን ወደ አንድ እንዲያመጡ ያደርጋሉ እንጂ ሌላ ሰው ጣልቃ ማስገባት አይፈቀድላቸውም፡፡ ሌላ ሰው ጣልቃ እንዲያስገቡ አይመከርም፡፡ ጠንከር ያለ ችግር እንኳን ቢገጥማቸው በጾም በጸሎት ከመምህረ ንስሐቸው ጋራ በመመካከር ችግራቸውን ይፈቱታል፡፡ በተክሊል ከተጋቡ በኋላ መለያየት አይቻልም፡፡ በሥርዓተ ተክሊል የተጋቡ ሰዎች ከጋብቻቸው በኋላ ምን ይጠብቃቸዋል በማኅበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ምን ማድረግ አለባቸው? በማለት ለመረጃ አቀበዮቼ በቡድን ውይት ወቀት ጥያቄ አቅርቤ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ዋቢ በማድረግ ሰፊ ገለጻ አድርገውልኛል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያን በጠየቁት ጊዜ (በማቴ 19÷4-7) እንዲህ በማለት መልስ ሰጥቷቸዋል "እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይችልም"፡፡ በቅዱስ ጋብቻ ኹለቱ አንድ ኾነዋል በዚህም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናቸው፡፡ በተክሊላቸው ጊዜ ቃል ገብተዋል፡፡ ህመም፣ ልጅ ማጣትና ድህነት የመሳሰሉት እንዲለያዩ አያደርጋቸውም፡፡ ፈተና ቢበዛባቸውም ፈተናውን የሚወጡበት ትምህርት ተሰጥቷቸዋል፡፡ የገቡት ቃል ኪዳን መጠበቅ ይገባቸዋል እንጂ እንደ ዓላማዊ ጋብቻ በቀላሉ እንዲለያዩ አይፈቀድላቸውም በማለት የተክሊል ጋብቻ ከሌሎች ዓለማዊ ጋብቻዎች የሚለየው ቃል ኪዳንን በተግባር በመግለጹ ነው ሲሉ አስረደተውኛል፡፡

የተክሊል ተጋቢዎች፣ ጋብቻቸው በፈቃደ እግዚአብሔር የሚመራ ታላቅ ምስጢር ስለሆነ የሐሳብ አንድነት የጋራ መተሳሰብን እንዲያመጡ ይጠበቃል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ቤተ ክርስቲያን አንድ ለአንድ እንጂ ኹለተኛ ጋብቻን አትፈቅድም፡፡ ለአንዲት ሴት አንድ ወንድ፣ ለአንድ ወንድ አንዲት ሴት እንጂ ኹለት ጋብቻ የለም፡፡ ስለዚህም በቤተ ክርስቲያን የተጋቡ ደናግላን ለሌሎች አርአያ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ የተክሊላቸው ፍሬ የሚታየው ጸንተው በመኖራቸው ነው፡፡ በተጨማሪም (በ1ኛ ቆሮ 7÷2 “) የሰፈረውን ሃሳብ መሠረት በማድረግ ‹‹እንዳትስሰኑ ሰው ኹሉ በሚስቱ ጸንቶ ይኑር ሴትም በባሏ ጸንታ ትኑር” በማለት ባል ከሚስቱ ሚስትም ከባሏ ውጪ ተላልፈው እንዳይኖሩ በአንድ ተወስነው እንዲኖሩ ለሰው ኹሉ የታዘዘ ግዴት እንደሆኾነ ገልጸውልኛል፡፡ ባል ለሚስቱ የሚገባትን ኹሉ እንዲያደርግ ግዴታ አለበት፡፡ እንደዚሁም ሚስት ለባሏ የሚገባውን ኹሉ የመፈጸም ግዴታ አለባት፡፡ ለጾምና ለጸሎት በጋራ ተመካከረው ከተወሰነ ጊዜና ቦታ በስተቀር ባልና ሚስት መለያየት እንደሌለባቸው ተገልጿል፡፡ “ሰይጣን ድል እንዳይነሳቸው ባልና ሚስት ተጠባብቀው መኖር አለባቸው” እንጂ ተለያይተው እንዲኖሩ አልተፈቀደም፡፡ በመሆኑም የተክሊል ጋብቻ ፍቺን አይፈቅድም፤ በአንድነት መኖርን ተሳስቦ መኖርን የሚያሰድግ፣የትውልድን ቀጣይነትና የማኅበረሰብን ዕድገት የሚገነባ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

(በፍት. ነገ፣ አንቀጽ 24፣1958፣293 ) ባልና ሚስት ከግብረ ሥጋ ግንኙነት ውጪ መኾን የሚገባቸው ጊዜ ተገልጿል፡፡ ሩካቤ ሥጋ ለባልና ሚስት ንጹሕና የተቀደሰ እንጂ ከርኩሰት አይቆጠርም፡፡ (በዕራውያን 13÷4) “መጋባት በሁኹሉ ዘንድ ክቡር ነው፤ መኝታውም ንጹሕ ነው” በማለት ሐዋርያ ጳውሎስ የባልና ሚስቶች ሩካቤ፣ ንጹሕና የከበረ መሆኑን አስረድቷል፡፡ ስለዚህ ኹለቱ በመመካከር ተጠባብቀው መኖር እንደሚገባቸው፣ በተጨማሪም በ(1ኛ ቆሮ 7፥5፣ ኤፌ 5÷22) የሠፈረውን ሐሳብ ዋቢ በማድረግ ተገልጿል፡፡

ባልና ሚስቶች ከጋብቻቸው በኋላ ተዋደው፣ ተፈቃቅረው በአንድ ሀሳብና ልብ እንዲኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ ባሎች ሚስቶቻቸውን እንደራሳቸው አድርገው ሊወዷቸው ይገባል “ራሱን መጥላት የሚቻለው የለም ለሰው ኹሉ የተሰጠው የሕይወት መመሪያ የተፈጥሮ ወንድምህን እንደ ራስህ ውደድ ነው፡፡ ሚስቱንም የሚወድ ራሱን ወደደ” በማለት (በኤፌ 5÷25) ጀምሮ የተገለጸው ባልና ሚስቱን ሚስትም ባሏን እንድትወድ ነው፡፡ ሴቶችም በባሎቻቸው ዘንድ ታዛዥ እንደሆኑ… ባልና ሚስቱን በመውደድ እንደ ዐይኑ ብሌን እንዲጠብቃት አንድ ልብ አንድ አፍ ኾነው በመተማመን መኖር እንዲችሉ በሐሳብ መለያየትና መተማማት እንደሌለባቸው (በ1ኛ ጴጥ 3÷1-9) ተገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተክሊል የተጋቡም ኾኑ በቁርባን ፍቺ አልተፈቀደም፡፡ ከጋብቻቸው በኋላ በመመካከር በትዳራቸው እኩል እንደኾኑ አምነው የአቻነት ነፃነታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ እንጂ በልዩ ልዩ ምክንያት ቃል ኪዳናቸውን እንዲያፈርሱ አልተፈቀደም፡፡ በመተማመንና በፈሪሐ እግዚአብሔር አንድ ልብ ኾነው እንዲኖሩ ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም በሚመለከት በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ቦታ ተጽፎ ይገኛል (ማር 10÷2-10) በ(ማቴ 19÷1-7)፡፡ "እግዚአብሔር መጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው… አንድ ሥጋ አንድ አካል ናቸው እንጂ ኹለት አይደሉም›› በማለት ጋብቻ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፈቃድ ስለኾነ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ በመጽናት እንዲኖሩ ታዟል፡፡ በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ግጭት በመካከላቸው ቢፈጠር እንኳን በመነጋገር ወደ እርቅ ይመለሳሉ እንጂ እንዲፋቱ አልተፈቀደም፡፡ በተጨማሪም ሐዋርያው ጳውሎስ(1ኛ ቆሮ 7÷27) ‹‹አንተ ሰው ሚስት አግብተህ ከሆነ መፋታትን አትሻ" (ቆሮ 11÷11) "ሴት ከባልዋ አትለይ ወንድም ከሚስቱ አይለይ ኹለታችሁም በጌታችን ትእዛዝ አንድ ኾናችሁ ኑሩ" ሲል ገልጿል፡፡ እነዚህ ኹሉ ጥቅሶች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር ያሉ ክርስቲያኖች ከተጋቡ በኋላ መፋታት እንደማይችሉ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያኒቱ አስተምህሮ መፋታት የሚቻለው በሞት ምክንያት ነው፡፡ ይህም (በፍት. ነገ. ፍት. መን. አንቀጽ 24 ክፍል 9፣ 1958÷11) ተገልጿል፡፡ ሌላኛው በዝሙት ምክንያት ነው፡፡ "ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የፈታ፤ የተፈታችውንም ያገባ አመነዘረ (በማቴ 5÷31፤19÷7) የሚል ተጽፏል፡፡ በቃለ መሃላ ያጸኑትን ጋብቻ በቀላሉ እንዲያፈርሱ፣ እንደ ዐለማዊ ጋብቻ እየፈቱ እንዲጋቡ ለክርስቲያኖች አለመፈቀዱን መረዳት ይቻላል፡፡

በሞት ምክንያት ከተለዩአቸው ማግባት እንደሚችሉ (በፍ ነገ አንቀጽ 24፣ በሮሜ 6÷1-4) ተጽፎ ይገኛል፡፡ "ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ በሕግ የጸናች ነች ባልዋ የሞተ እንደሆነ ግን ከገባችለት ቃል ኪዳን ነፃ ናት"፡፡ … ባሉዋ የሞተ እንደኾነ ግን ሌላ ብታገባ ዝሙት አይሆንባትም፡፡ ወንድ ሚስቱ ከሞተች ከአንድ ዓመት በኋላ፣ ሴት ደግሞ ባሏ ከሞተ ከ10 ወር በኋላ ማግባት እንደሚችሉ (በፍት ነገ. አን. 24 1958 ÷43) ተገልጿል፡፡

ለተቀደሰ የተክሊል ጋብቻ የበቁ፣ በቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል የተሣሠሩ ተጋቢዎች፤ የገቡትንም ቃል፤ ከሞት በቀር ምንም ሊለዩት አይችሉም፡፡ የሚገጥማቸውን ፈተና ተቋቁመው ለማለፍ እንዲችሉ ረድኤተ እግዚአብሔር እንዳይለያቸው ጾምና ጸሎት እንዲያደርጉ፣ ከቤተ ክርስቲያን ዘወትር እንዳይለዩ፣ ከመምህረ ንስሃቸው ጋር በየጊዜው እንዲመካከሩ እንዲሁም

አንድ ልብ ኾነው በፍቅር እንዲኖሩ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በፍትሐ ነገሥት በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተጽፎ ይገኛል። ይህንንም ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሐዋርያት፣ መምህራን ሊቃውነተ ቤተክርስቲያን በማስተማር እስካሁንም ድረስ በቅብብል ለትውልድ እየተላለፈ ቆይቷል። ጋብቻን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ፈቅዶ የሰጠው ዘር ለመተካት፣ እርስ በርስ ለመረዳዳትና ከዝሙት ጦር ለመዳን ነው። የሰው ልጆችም ይህን ዐውቀውና ተረድተው በመተሳሰብ በመረዳዳት ቃላቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ ነው።

## 4.3 የሦስቱ ሥርዓቶቹ ተማሳሎና ልዩነቶች

ተክሊልን ደጋግሞ መውሰድ አይቻልም። ጥምቀትም እንደዚሁ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማይደገሙ ምስጢራት ከሚባሉት ውስጥ ሥርዓተ ጥምቀት አንዱ ነው፤ ሌላኛው ደግሞ ተክሊል ነው። ጥምቀት የሚፈጸመው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። የተክሊል ተጋቢዎችም በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ፍቺ ቢፈጸሙና ጋብቻን ለመፈጸም ቢወዱ ተክሊል በድጋሚ አይፈጸምላቸውም። የሜሮን ሥርዓት በጥምቀት፣ በተክሊልና በክህነት ይፈጸማል። አንድ ሰው በሦስቱም ሂደቶች ውስጥ ቢያልፍ የሜሮን ሥርዓት ሦስት ጊዜ ይፈጸምለታል።

ክርስትና የሚነሡ ግለሰቦች ከጥምቀት በፊት የመንፈስ ቅዱስ ልጅነትን ያላገኙ ናቸው ተብሎ ይታመናል። ከጥምቀት በኋላ የመንፈስቅዱስ ልጅነትን አግኝተዋል ወደ አዲስ እምነት ተሸጋግሯል። ጥምቀት ከብሉይ ይሕይወት ምዕራፍ ወደ ዐዲስ የሕይወት ምዕራፍ መሸጋገር ነው። ይህን አዲስ ልጅነት ለመቀበል ሥርዓቱ ግዴታ ነው። ሥርዓቱም ሃይማኖታዊም ባህላዊም ነው። ባህላዊውን ሲፈጽሙ ማኅበረሰቡ የተስማማበት ከአኗኗሩ፣ ከዘወትር ምግቡ ትርጉም በመስጠት፣ዋጋ ሰጥቶ ከደነገጋቸው፤ በቅብብል ከወረሳቸው ሥርዓተ ክዋኔዎች ውስጥ ተግባራዊ እያደረገ አዲስ ልጅነቱን ያቀብላል፤ ለልጁ ያወርሳል። በተክሊልም ከድንግልና፤፣ከኮረዳነት፣ ከጎረምሳነት ወደ አቶነት ወይዘሮነት አዲስ ሕይወት አዲስ አኗኗር የሚሸጋገርበትም ነው። ዲያቆን ከሆነ ደግሞ ወደ ቄስነት ሌላ አዲስ ሥልጣነ ክህነት ደረጃ ይሻገራል።

በክርስተና ወቅት 36 ሕዋሳት ቅብዐ ሜሮን ተቀብተዋል። በተክሊል ወቅትም የሚታዩ ሕዋሶቻቸው ቅብዐ ሜሮን ጸቀብቷል። የኹለቱም ማጠናቀቂያ ቁርባን መቀበል ነው ወዲያዉኑ በዕለቱ በዓለት ባይኖሩም ሥርዓተ ቅዳሴ ተዘጋጅቶላቸው ይቀርባሉ።

የተክሊል መዝሙሮች የሚከናወኑት በተክሊል ብቻ ነው፤ የመከወኛ ምክንያቱ ሰርግ ነው። የሚከውኑት ልብስ ለብሰው የመዝሙር ቁሶችን ይዘው ነው። ከዋኞቹ መዘምራን ካህናት ናቸው። ሕዝቡ ዜማውን አብሮ ያዜማል፤ በእልልታና በጭብጨባ ያጅባል። ፈጠራ ቅኔው ፈጠራ ነው። የሰርጉ መዝሙር ከቅኔውም ፈጥረዋል። ታዳምያን የራሳቸው ድርሻ ነበራቸው፤ ሲያጨበጭቡ እልል ሲሉ ሲያጅቡ ነበር። ተክሊል ያለ ቁሳቁሶች አይከናወንም ክርስትናም ያለቁሳቁሶች አይከናወንም። ቁሶቹ ማኅበረሰቡ ከአኗኗሩ፣ ከባህሉ፣ ከእምነቱ፣ በትውፊት እየተቀባበላቸው፣ በሥርዓት እየከወናቸው የተሸጋገሩ ናቸው። ይህም የክርስትና የተክሊልና የሜሮን ሥርዓተ ክዋኔ በዋናነት በሀገረሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል ውስጥ የሚካተት መኾኑን የሚያሳይ ነው። የተክሊል ሥርዓት ላይ ደብረ ሊባኖስ አማኑኤል ቤተክርስቲያን የተከናወነው ሰርግ ላይ ሙሽሮቹ አንድ መጎናጸፊያ ለብሰዋል፤ ወንዱ ሙሽራ መስቀል ይዟል። በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ምልከታዬ ሙሽሮች ካባ ብቻ ለብሰዋል፤ አበባ ይዘዋል። አንዱ ሙሽራ ሕፃናት የፊት ሚዜ ነበሩት። መረጃ አቀባዮቼም እንዳስረዱኝ በፊት ጊዜ ሙሽሮች በካባውላይ አንድ መጎናጸፊያ ይለበሱ ነበር ይህም የአንድነታቸው ምሳሌ ነው። አበባው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትም ትርጉም የለውም ከዐለማዊ ሰርግ የተወሰደ ነው። ከነዚህ ተግባራት በሂደት ተወስኑ ለውጦች በተክሊል በጋብቻ ወቅት መታየታቸውን መገንዘብ ይቻላል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና፣ የተክሊልና የሜሮን ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታን ማሳየት የሚል ዓላማ ይዞ የተነሣ ነው፡፡ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ቀደማይና ካልዓይ የመረጃ ዘዴዎች ተገባር ላይ ውለዋል፡፡ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ውይይት ተሰብስበዋል፡፡ መረጃዎቹን ለማጠናከርም በፎቶ፣ በመቅረጸ ድምጽና በቪዲዮ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተደግፏል፡፡ በሥርዓተ ክዋኔው ያሉ ፎክሎራዊ ገጽታዎችን ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ከከተማ ውጪ አንድ በከተማ ሦስት አብያተ ክርስቲያናትን በመምረጥ በሥርዓተ ክዋኔው ወቅት የሚታዩ ተምሳሌቶችን፣ የምስጢራቱን ምንነት ለመግለጽና ለመተርጎም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ካህናት ዲያቆናት ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው በክዋኔው ውስጥ ያሉ ልማዶችን ለመገንዘብ ምዕመናንን፣ በዕድሜ የገፉ እናቶችን፣ አባቶችን፣ ክርስትና ልጅ ያላቸው የተለያዩ ግለሰቦችን፣ በክርስትና እና በተክሊል ሥርዓት ላይ በመገኘት ለሙሽሮች፣ ለታዳሚዎች ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ በዚህ ጥናት ሥርዓተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለማሳየት ይቻል ዘንድ ገላጭ የምርምር ስልት እና የክዋኔ ቲዎሪ አገልግሎት ውለዋል፡፡

ጥምቀተ ክርስትና በኢኦተቤ ሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አምኖ ሲጠመቅ ክርስትና ተነሣ ይባላል፡፡ ጥምቀተ ክርስትና ሰዎች ኀጢአታቸው ተደምስሶ፣ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ ተወልደው፣ የክርስቲያን አባል ኾነው፣ የእግዚአብሔር ልጅነታቸው እንዲረጋገጥ ሲሉ በካህን አማካይነት በቤተክርስቲያን የሚፈጽሙት ሥርዓት ነው፡፡ ዓላማውም ክርስቲያኖች መንግስተ ሰማያትን እንዲወርሱ ማስቻል ነው፡፡

ክርስትና ለመነሣት የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶችና መስፈርቶች አሉ፡፡ እነርሱም የመጀመሪያው መማርና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ማመን ናቸው፡፡ የክርስትና የራሱ ሥርዓት ተሠርቶለት በቤተክርስቲያኒቱ የሥርዐት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ለእያንዳንዱም ክዋኔ ኀላፊነት የተሰጣቸው ከዋኞች አሉ፤ እነርሱም ካህናት ናቸው፡፡ ከካህናት ውጪ ጥምቀተ ክርስትና መፈጸም አይቻልም፤ አፈጻጸሙም በኹለት ዐይነት መንግድ ነው፡፡ የክርስቲያን ልጆች ለኾኑ ሕፃናት ወንዶች በተወለዱ በ40ኛው ቀናቸው ፣ሴቶቹ ደግሞ በተወለዱ በ80 ቀናቸው ክርስትና ይነሣሉ፡፡ ነፍስ ዐዋቆች ባመኑ ጊዜ በየትኛውም የዕድሜ

ክልል ላይ መጠመቅ ይችላሉ። በጥምቀተ ክርስትናን የመሠረተውና ትእዛዝ የሰጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከዚያም ሐዋርያት አስፋፍተውታል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት በ40ኛውን በ80ኛው ቀናቸው ክርስትና የመነሣታቸው መነሻው የአዳምና ሔዋንን ወደ ገነት መግባት መሠረት ያደረገ ነው።

ልጃቸውን ክርስትና የሚያስነሡ ወላጆች ከክርስትናው ቀድመው ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ። የክርስትና እናትና አባት ያዘጋጃሉ፣ ክርስትና አባት ወይም እናት ለመኾን የተለያዩ መንገዶች አሉ የመጀመሪያው ከወላጆች ዝምድናን የሚፈልጉ ልጃችሁን ለክርስትና ስጡን ይላሉ፤ ኹለተኛው ወላጆች ዝምድናውን ለሚፈልጉት ሰው ይሰጣሉ፤በስለት ወይም ለሚፈልጉት ታቦት ይሰጣሉ።

ወንዶች ክርስትና ማንሣት የሚችሉት ወንዶችን ብቻ ነው፤ሴቶችን ሴቶች ብቻ፤ ወንድን ሴት፣ ሴትን ወንድ ማንሣት አይችሉም። ዓላማውም የክርስትና ሃይማኖትን በተመሳሳይ ፆታ መስተማር ነው። አቋቋሚዎች የክርስትና ተነሺዎች ምስክሮች ሲኾኑ፤ ክርስትና እናትና አባት ዋሶች ናቸው።

የክርስትና ሥርዐት የሚከናወነው በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ለክርስትና ተብሎ በተሠራ ወይም ከቤተክርስቲያኑ ጋራ አብሮ በተሠራ የክርስትና ማንሻ ቦታ ነው። ሥርዐቱን ለማከናወን የሚያስችል ቦታና ለማጥመቅ የተዘጋጀ ገንዳ አለው። በዕለቱ ክርስትናውን የሚያስፈጽሙት ካህናት ልብሰ ተክህኖ፣ መስቀል፤ጽናህና ሌሎች የሚያስፈልጉ ቁሶችን አሟልተው በቦታው ይገኛሉ።

በጥምቀተ ክርስትና ሥርዐተ ክዋኔ ላይ የተፈጸሙ ተግባራት በዋናነት የክርስትና ሥርዐተ ጸሎት፣ ተጠማቂዎችን በዐራቱም ማዕዝናት ማዞር፣ ማዕጠንት ማጠን፤ ውኃውን መባረክ፣ጣት መያዝ፣ ቃል መግባት፣ ተጠማቂዎችን ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቀ በማድረግ ማጥመቅ፣ ሜሮን መቀባት ፣ማተብ ማሰር፣ በነጭ ልብስ ተጠማቂዎችን መቀበልና ቁርባን ናቸው። እነዚህ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሲፈጸሙ ከህናት በመሪነት በንባብና በዜማ ታዳሚዎች በቅብብል ነው። ጥምቀቱን የሚፈጸምበት ሂደት ካህኑ ውኃውን ይባርካሉ። ተጠማቂዎች ግንባር ላይ መስቀል አድርገው ሦስት ጊዜ ገንዳው ላይ ይዘፍቋቸዋል ወይም በራሳቸው ላይ ያፈሱባቸዋል ማተብ ማሠር፣ ሜሮን መቀባትና ቁርባን በዕለቱ በቅደም ተከትል የተከናወኑ ሥርዓቶች ናቸው።

ክርስትና በቤተ ክርስቲያን በሚደረግ ሥርዐት ግኝት ብቻ አይጠቃለልም። ማኅበረሰቡ ከቤተክርስቲያን ወደቤት ሲመለስ እንደ ባህሉ ያዘጋጀውን ድግስ ይመገባል። ሕፃናት ክርስትና ሲነሡ የጸጋ ልጅነትን እንዳገኙ አረጋግጠዋል፤መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል ። ከዚያ የጸጋ ልጅነት በመነሣት ወደቤታቸው ሲገቡ ገና በር ላይ ከዘወትር ምግባቸው እንጀራ ላይ ክርስትና የተነሱ ሕፃናትን ያንከባልሏቸዋል። የወደፊቱን እንጀራ ያግኝ ወይም ታግኝ ብለው ከእንጀራው ጋራ በረከትን ዕድልን አገናኝተው ለእንጀራው ትርጉም በመስጠት ይመርቋቸዋል። ጸጋቸውን በተግባር የሚያውሉ፣የሚጠቀሙ ያድርጋቸው ብለው ይመርቃሉ። በዚህ ቀን ዕድላቸውን የሚቀበሉበት ቀን ነው ብለው ስለሚያምኑ ታዳሚው ኹሉ መልካም ምኞቱን እየገለጸ መኾኑን መገንዘብ ተችሏል። ያንን እንጀራ ወዲያውኑ ተቆራርሶ ታዳሚው በሙሉ ይመገበዋል። ታደሚዎቹ ሲመገቡት በረከትን እናገኛለን፣ ክርስትና የተነሡትም በዚህ ቀን እንጀራ ላይ መንከባለላቸው መመረቃቸው ወደፊት እንጀራ ያገኛሉ፤ ሀብት ያገኛሉ ማለታቸው እንደኾነ ጥናቱ አመላክቷል።

ክርስትና ከሃማኖታዊው አስተምህሮ ባሻገር ባህላዊ የዝምድና ትስስሩ በልጠ መታየቱን በጥናቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም ክርስትና ዝምድና እንዲፈጠር ከፍተኛ ሚና ያለው መሆኑን መረዳት ተችሏል። ወላጆች የልጆቻቸው ክርስትና እናትና አባት እነዲኾኑላቸው የሚፈልጉት ዝምድናቸውንና ጉርብትናቸውን የበለጠ ለማጠናከር የሚፈልጉትን ሰው ነው። በክርስትና የተዛመዱ ቤተሰቦች በተለያዩ ማኅበራዊ ተግባራት ይረዳዳሉ። በሰርግ፣ በልቅሶ በማኅበር ተባብረው ይሠራሉ። ከሥጋ ዝምድና በላቀ ሁኔታ አብረው ይኖራሉ። ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ በቅብብል እየተላለፈ መኾኑን መረዳት ተችሏል። በክርስትና ወዳጅነት ይጠናከራል፤ በክርስትና የተዛመዱ ቤተሰቦች አይጋቡም፤ ወንድምና እህቶች ናቸው። ስልኾነም ክርስትና ማኅበራዊ መስተጋብርን በማጠናከር ደረጃ ሚናው ከፍተኛ መሆኑ የሚያሳይ ነው። ስለዚህ የክርስትና ሥርዐተ ክዋኔ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ እና ፎክሎራዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት መረዳት ተችሏል። የክርስትና ሥርዓተ ክዋኔ በሃይማኖቱ ሥርዓት ተሠርቶለት በትውፊት በቅብብል የሚሸጋገር ነው። ማኅበረሰቡም ከአኗኗሩ፣ ከልማዱ የራሱን ሥርዓት ሠርቶ ለትውልድ ያስተላልፈዋል። ክዋኔው ትውፊታዊ ሥርዓቶችን የሚከተል በመሆኑ በሀገሰባዊ ልማድ ነው።

በክርስትናቸው ዕለት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በሽማግሌዎች ተመርቀው፣ በክርስትና እምነት ውስጥ አድገውና በሜሮን ተቀብቶ የተቀደሰ ሰውነታቸውን ከዝሙት አርቀው፣ በድንግልና የቆዩ ወጣቶች ለጋብቻ ሲደርሱ የተክሊል ሥርዓት ይፈጸምላቸዋል። ተክሊል የሥጋ ፈተናን

ተቋቁመው በድንግልና ለቆዩ ክርስቲያኖች የሚፈጸም የጋብቻ ሥርዓት ነው። በተክሊል ለመጋባት የመጀመሪያው መስፈርት ክርስቲያን መኾንና በድንግልና መቆየት ናቸው። ይህን መሥፈርት ያሟሉ ወጣቶች በካህናት አማካይነት እንዲተጫጩ ይፈቀድላቸዋል።

የተጫጩ ተጋቢዎች ከጋብቻቸው ዕለት አስቀድመው የሰርግ ዝግጅት ያደርጋሉ፤ ሙሽራውና ሙሽሪት ሚዜዎችን ያዘጋጃሉ። የሥጋ ዝምድና እና በክርስትና ያልተዛመዱ መኾናቸውን በንስሐ አባታቸው ይረጋገጣል። ከሰርጉ ቀን አስቀድመው ወደ ቤተ ክርስቲያን በመኼድ፣ በኤጲስቆጶሱ አማካይነት፣ በምስክሮች ፊት ይፈራረማሉ። በጋብቻው ዕለት ከአጃቢዎቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋራ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይኼዳሉ። ካህናት ለተክሊሉ ክዋኔ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን፣አክሊል፣ ካባ ሜሮን፣ መጎናጸፊያ፣ ማዕጠንት፣ከበሮና ጸናጽን ያዘጋጃሉ። ቅዳሜ፣ ዕሁድ፣ ማክሰኞና ሀሙስ ለተክሊል ጋበቻ ተመራጭ ናቸው ምክናያቱ ደግሞ የተክሊል ጋብቻ በጾም ዕለት ስለማይከናወን ነው።

በተክሊሉ ዕለት  የተፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሙሽሮች ከነአጃቢዎቻቸው ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በቤተ ክርስቲያን መገኘት፣ነጭ ልብሳቸውን ለብሰው ጧፍ እያበሩ ወደ ቤተክርስቲያን መግባት፣ ከመቅደሱ ፊት ለፊት በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ላይ መቀመጥ፣ ቃለ መሀላ መፈጸም፣ የቃል ኪዳን ቀለበት ማሰር፣ ሜሮን መቀባት፣ ካባ መልበስ፣ አክሊል መድፋትና ሥጋ አምላክ መቀበል ናቸው። እነዚህ ተግበራት ሥርዓቱን በሚመሩት ካህናት ጸሎተ ተክሊል ይደርሳል ፣በንባብ፣ በዜማና በቅብብል ይጸልያሉ፣ ተራዳዒው ካህን በጽናኅ ማዕጠነቱን በሁሉም ቁሶች ላይ እና ወደ ሙሽሮቹ እንዲሁም በዐራቱም ማዕዘናት እየዞሩ ያጥናሉ፣በተክሊሉ ቁሶች ( በአክሊሉ፣ በካባው ፣በቀለበቱ ና በሜሮኑ) ላይ መሪው ካህን ጸሎት ያደርጋሉ። ቃል ማስገባት ሜሮን መቀባት በመሪው ካህን ይከናወናሉ። ከቆረቡ በኋላ መዘምራን የሰርግ መዝሙርና ቅኔ ያቀርባሉ፣ ይህ የቤተክርስቲያኑን ሥረዓት ማጠናቀቂያ ነው።

በክርስትና ወቅት 36 ሕዋሳት ሜሮን ተቀብተዋል እነዚህ የሰው ልጅ ሰውነቱ ቆሞ እንዲኼድ የሚያደርጉ የመገጣጠሚያ አካላት፣ የመራቢያ አካላትና የተለያዩ ተግባራትን የሚከውንባቸው ሕዋሶቹ ናቸው እነዚህም ሰው በ40ኛውና በ80ኛው ቀን የተሰጠውን ጸጋ ተጠቅሞበት በሥጋውም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑ ተረጋግጦ በመንፈሳዊም ጠንካራ ኾኖ ትውልዱን በቅብብል እንዲያስቀጥል የሚያስችሉ ናቸው።

በተክሊሉ ሥርዓት ላይ ጸሎት ተደርጐባቸው ሙሽሮች የለበሷቸው ካባዎች፣ መጎናጸፊያ፣ አክሊል፣ ሜሮን፣ ቀለበትና ቁርባን ተክሊሉን ሙሉ የሚያደርጉ አስፈላጊ ቁሶች ናቸው፡፡ አክሊል የሚደረግላቸው በድንግልና ቆይተው ለዚህ ክብር በመብቃታቸው የክብራቸው መገለጫ ሽልማት ነው፡፡ ይህም ሰማያዊ የክብር አክሊል ምሳሌ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ካባው መንፈስ ቅዱስን የመልበሳቸው ምሳሌ፣ ነጭ ልብስ ድገሞ ጸአዳ ስለኾነ የንጽሕናቸው ፣የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ  እነደኾነ ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡ አንድ መጐናጸፊያ መልበሳቸው በቅዱስ ጋብቻ አንድ መኾናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሚታዩ የአካል ክፍሎቻቸው ሜሮን ተቀብተዋል፡፡ ጋብቻቸው በመንፈስ ቅዱስ የተቀደሰና የተባረከ መኾኑን በሜሮን መኀተምነት የተረጋገጠ ነው፡፡ ሥጋ አምላክ መቀበላቸው የተክሊሉ የመጨረሻ ዓላማ ነው፡፡ ይህም በንጽህና ፣በቅድስናና በፍቅር ኖረው መንግስተ ሰማያትን መውረስ እንደኾነ መረዳት ተችሏል፡፡

በተክሊል ሥርዓተ ጋብቻን መፈጸም፣ በመተማመን፣ በመከባበር መኖርንና አንድነትን በማጎልበት በቀላሉ ፍቺ እንዳይፈጸም በማድረግ ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ በኢኦተቤ በተክሊል የተጋ ሰዎች ፍቺ አለመፈቀዱን ኹለት ጋብቻ እንደሌለ አምነው ዐውቀው ይፈጽሙታል፡፡ በመሆኑም በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን በመመካከር፣ በጾም በጸሎት፣ ከነርሱም ሲያልፍ ከመምህረ ንስሐቸው ጋራ በመወያየት ችግሮቻቸውን ይፈታሉ እንጂ እንደዓለማዊ ጋብቻ አይፋቱም፡፡ በጋብቻቸው እኩል እንደኾኑ አምነውና ዐውቀው፣ በመተማመን በፈሪሃ እግዚአብሔር አንድ ልብ ኾነው ይኖራሉ፡፡ ስለዚህ የተክሊል ጋቻ ፍቺን ስለሚቀንስ እኩልነትን፣ ፍቅርን የማሳደግ ትልቅ ተግባር አለው፤ የቤተሰብ አንድነትንና የጋብቻ ዘላቂነትን በማሳደግ፣ልጆችን እንዳይበተኑና ትውልድ ቀጠይነት እንዲኖረው በማድረግ፣ ለማኅበረሰብና ሀገር ግንባታ ከፍተኛ ሚና ያለው መኾኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ። (1979 ዓ.ም)። *ትምህርተ ክርስትና፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤት ክርስቲያን እምነትና ትምህርት።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

____________። (1974 ዓ.ም)። *ትምህርተ ክርስትና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት።* ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ።

____________። (1963 ዓ.ም)። *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት።* ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

____________። (1956 ዓ.ም)። *ጸሎተ ተክሊል።* አዲስ አበባ፣ በብርሃንና ሰላም፣ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ሉሌ መላኩ።(1986 ዓ.ም)።*የቤተክርስቲያን ታሪክ።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን (አዘጋጆች)። (1988 ዓ.ም)። *መጽሐፈ ተክሊል።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት።

____________። (አዘጋጆች)።(1944 ዓ.ም)። *መጽሐፈ ክርስትና።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት።

____________። (አዘጋጆች)። (2010 ዓ.ም)። *መጽሐፈ ክርስትና።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት።

____________። (አዘጋጆች)።(1990 ዓ.ም)። *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናትና ዛሬ። አዲስ አበባ፣* ንግድ ማተሚያ ቤት።

____________። (አዘጋጆች)። (1958 ዓ.ም)። *ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው።* አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ሊቃውንተ ጉባኤ። (ተርጓሚዎች)። (1936 ዓ.ም)። *ገድለ ተክለ ሃይማኖት በግዕዝና በአማርኛ።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

______________ ::(አዘጋጆች):: (2008 ዓ.ም):: "*መጽሔተ ዜና ዘተምሮ ማስተማር* 59ኛ ዓመት *ልዩ ዕትም*"፣ አዲስ አበባ፣ ንግስተ ሳባ ማተሚያ ቤት::

______________ :: (አዘጋጆች):: (1942 ዓ.ም):: *መነሻና መድረሻ ለሚኼድበት አገር መሪ ከምስካየ ኀዙናን ቤተ ክርስቲያን*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

______________ :: (አዘጋጆች)::(1936 ዓ.ም):: *የቤተክርስቲያን ጸሎት*፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

______________ :: (አዘጋጆች):: (1955 ዓ.ም):: *መድኃኒት በጥምቀት::* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣

______________ :: (ተርጓሚዎች):: (*1946 ዓ.ም):: ገድለ ተክለ ሃይማኖት:: አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት::*

*ሊያ መዝገቡ*:: (2003 ዓ.ም):: "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስልጣነ ክህነት አሰጣጥ *ሥርዓተ* ክዋኔ":: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ *ሥነ* ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የኤም. ኤ ዲግሪ *ማሟያ* ጽሑፍ::

ልሳነወርቅ በዛብኅ (አዘጋጅ):: (1978 ዓ.ም):: *"ትንሣኤ መጽሔት ቁጥር ዘጠና ስድስት"::* የደብረ ሊባኖስ ገዳም አመሰራረት:: ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ሐዲስ የሻነው:: (1998 ዓ.ም):: *ፍንጭ ፍተሻ::* አዲስ አበባ::

*መ*ርስዔ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ:: (1999 ዓ.ም):: *የሐያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ:: የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት 1896-1922*፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

*መ*ስፍን ጽጌ:: (2011 ዓ.ም):: *"ሐመረ ኖኅ"* የእንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት ገዳም:: ልዩ እትም መጽሔት:: አዲስ አበባ፣ ሚሊኒየም ማተሚያ ቤት::

*መ*ጽሐፍ ቅዱስ:: (1953 ዓ.ም):: *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት::* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም፣ ቀዳማዊ ኃይለ *ሥ*ላሴ ማተሚያ ቤት::

*ሥ*ርግው ሐብለ *ሥ*ላሴ (አዘጋጅ):: (1969 ዓ.ም):: "የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት":: (ያልታተመ)::

__________::(አዘጋጅ):: (1982 ዓ.ም):: "የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት"::
(ያልታተመ)::

ሰሙ ምትኩና ቸሬ አበበ:: (2000 ዓ.ም):: *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ::* አዲስ አበባ፣ አልፋ
አሳታሚዎች::

ሳሙኤል:: (2000 ዓ.ም):: "የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ አምልኮ":: *የኢትዮጵያ ቤተ
ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ (፳፻) 2000*፡ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)::

በኢኦተቤ ማኅበረ ቅዱሳን (አዘጋጆች):: (1985 ዓ.ም):: *"መለከት ፩ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት"::*
አዲስ አበባ፣ ዋኖስ አሳታሚ ድርጅት::

ብጹዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን (አዘጋጆች)::(1988 ዓ.ም):: *የኢትዮጵያ
ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት::*
አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት::

ተምሮ ማስተማር:: (2009 ዓ.ም):: "*በኢኦተቤ የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም*" ተምሮ
ማስተማር ሰ/ት/ቤት 60ኛ ዓመት ልዩ እትም መጽሔት:: (ማተሚያ ቤት የሌለው)::

ቴዎድሮስ ገብሬ:: (2001 ዓ.ም):: *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባብ::* አዲስ አበባ፣ አዲስ
አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ::

ኃይለ መስቀል ገብረ መድኅን:: (1960 ዓ.ም)::*ሥርወ ሃይማኖት::* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

____________:: (1997 ዓ.ም):: *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ::*
አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት::

አበራ በቀለ:: (1996 ዓ.ም):: *ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት::* አዲስ አበባ፣
ንግድ ማተሚያ ቤት::

አባ ተክለማርያም:: (1962 ዓ.ም):: *የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም አመሠራረት
የሚገልጽ ማስታወሻ፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

ከፈለኝ ኃይሉ። (2009 ዓ.ም)። "የተምሮ ማስተማር ማኅበር አመሠራረትና አገልግሎት"። የተምሮ ማስተማር ማኅበር ስያሜውን ያገኘበት 60ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የቀረበ የዳሰሳ ጥናት። (ያልታተመ)።

ከፍ ያለው መራሒ። (1982 ዓ.ም)። *ሥርዓተ ጋብቻ።* ማተሚያ ቤት የሌለው።

ኪዳነ ማርያም ጌታሁን። (1957 ዓ.ም)። *ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ።* ከሣቴ ብርሃን ማተሚያ ቤት።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። (1948 ዓ.ም)። *መጽሐፈ ሰዋስው ወግሰ መዝገበ ቃላት ሐዲስ።* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ክንፈ ገብርኤል አልታየ። (2000 ዓ.ም)። "የክርስትና ሥርዓተ አምልኮ በኢትዮጵያ"። *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ* (፳፻) *2000።* (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)።

____________። (1983 ዓ.ም)።*ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን።* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት።

የዝና ወርቁ። (2009 ዓ.ም)። "በሰሜን ጎንደር የሚካኤል የእሜቴ አይከል ሀገረሰባዊ እምነትና ክዋኔ" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ።

ያሬድ ክብረት። (2009 ዓ.ም)። *ፍኖተ አሚን*፡ አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት።

ያሬድ ገብረ መድኅን። (1996 ዓ.ም)።*ኖኅተ ሰማይ*። አዲስ አበባ፣ (ማተሚያ ቤት ያልተገለጸ)።

ደስታ ተክለ ወልድ:: (1962 ዓ.ም)። *ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት::* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክስ ማተሚያ ቤት።

ዳንኤል ክብረት። (1999 ዓ.ም)። *የቤተክርስቲያን መረጃዎች።* አዲስ አበበ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጎርጎርዮስ ። (1991 ዓ.ም)።*የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ።* (ማተሚያቤትያለተገለጸ)።

ፈቃደ አዘዘ። (1991 ዓ.ም)። *የሥነ ቃል መምሪያ*፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ፈቃዱ ሣህሌ። (2008 ዓ.ም)። *የቤተ ክርስቲያን ምስጢራትና ሥርዓት*፡ አኮቴት አሳታሚዎች።

ፍሬህይወት ባዩ። (2000 ዓ.ም)። "የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የንዋያተ ቅድሳት ሃይማኖታዊና ፎክሎራዊ ገጽታ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም. ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ።

Bascom, William. (1965). *"Four Function of Folklore".* The journal of American folklore. vol. 67, No. 266. pp 333-349, p 3-20.

Bauman, Richard. (1992). (ed). *Folklore cultural performances and popular entertainment.* New York: Oxford University Press.

__________. (1984). *Story, Performance and event, contextual studies of Oral narratives.* Cambridge: Cambridge University press.

Dan Ben, Amos. (1993). *"*‹Context› in context." *The journal of American folklore.* Vol.52,No 2/4/9 P.2009-226.

Ephram, Isaac. (1971). "Socail Structure of Ethiopian Church." *Journal of Ethiopian observer.* Vol. XIV No 4. Published in Ethiopia and Britain.

Finnegan, Ruth. (1992). *Oral Tradition and the Verbal arts*. London and Newyork: Routledge.

Kapchan, Deborah A. (1995). "Performance." *Journal of American folklore.* Vol. 108, No 430, American Folklore. Vol. 108, No 430. American folklore society.

Martha, C. Sims, and Martine, Stephens. (2005). *Living Folklore: An Introduction to the study of people and their Traditions. Ohio:* Utah State University Press.

Mary, Hafford. (1995). "Context." *Journal of American Folklore.* Vol. 108, No 430. American folklore society.

Okpehu, Isidore. (1992). *African Oral Literature*, *Backgrounds, Characters and continuity.* Bloomingto: Indiana University Press.

Rapport, Roya. (1999). *Ritual and Religion in the making of Humanity*. Uk: United Kingdom at University Press.

Richard, M. Dorson (ed.). (1972). *Folklore and Folk life an Introduction.* Chicago and London: The University of Chicago press.

# አባሪዎች


## አባሪ 1 የተለያዩ ፎቶዎች





በክርስትና ወቅት የተጠሩ ሰዎች እና አቋቋሚዎች በመመገብ ላይ





ህጻኑ በመጠመቅ ላይ





አጥኚው በምልከታ ወቅት በደብረ ሊባኖስ ገዳም በከፊል









ለተክሊል ሥርዓተ ክዋኔ የቀረቡ ቁሶች በከፊል





ሙሽሮች ጧፍ እያበሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ በከፊል የሚያሳይ



ሙሽሮች ከቆረቡ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ



ሙሽሮች ከቤተ ክርስቲያን ሲወጡ



ሙሽሮች ከሚዜዎቻቸው ጋር



አጥኚው በተክሊል ምልከታ ወቅት





አጥኚው በመረጃ ሰጪዎች ቢሮ መረጃዎችን ሲሰበስብ



አጥኚው በቃለ መጠይቅ ወቅት

# ጥናቱ የተካሄደባቸው አብያተ ክርስቲያናት በከፊል





የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም ቤተ ክርስቲያን




የምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም ቤተ ክርስቲያን



የደብረ ሊባኖስ ገዳም አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን





እንጦጦ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምህረት ገዳም ቤተ ክርስቲያን

## አባሪ 2

## የመረጃ ሰጪዎች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | እድሜ | የሚኖሩበት አካባቢ | መረጃውን የሰጡበት ቦታ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አባ ኪዳነቃል አካሉ | ወንድ | 50 | አዲስ አበባ | ምስካየ ኅዙናን መድኃኔዓለም ገዳም | የገዳሙ የወንጌል መምህር |
| 2. | መ/ር ፈቃዱ ሣህሌ | ወንድ | 58 | ለገጣፎ | ማኅበረ ቅ/ማዕከል | በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማ/ቅዱሳን የስነ መለኮት መምህር |
| 3. | መ/ር ያሬድ ክብረት | ወንድ | 40 | ኮተቤ | መንበረ ፓትርያርክ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን | የካሤቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ መምህር፣ ጥናትና ምርምር አስተባባሪ ፣የቅ/ጳ መንፈሳዊ ኮሌጅ ም/ዲን |
| 4. | ቀሲስ ኃይለመስቀል ፀጋዬ | ወንድ | 45 | አዲስ አበባ | መንበረ ፓትርያርክ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን | የታሪክ መምህር<br>በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ የሐዲስ ኪዳን መምህር |
| 5. | መርጌታ ተስፋዬ አለምነው | ወንድ | 48 | ገላን | ኪዳነምሕረት ቤተክርስቲያን | የዝማሬ መዋስት መምህርና የሐመረ ኖሕ ኪ/ቤ አገልጋይ |
| 6. | ሊቀጠበብት ዲበኩሉ ስዩም | ወንድ | 64 | ሰላሌ ፍቼ | ደ/ሊባኖስ ገዳም | የብሉይና ሐዲስ መምህር |
| 7. | አባ መላከሰላም ኃ/ሥላሴ ብርሃኑ | ወንድ | 75 | ሰላሌ | ደ/ሊባኖስ ገዳም | የገዳም አበምኔት የነበሩ በምንኩስና ሕይወት የሚኖሩ |
| 8. | አቶ ተስፋዬ ቦጋለ | ወንድ | 42 | ኮተቤ | መንበረ ፓትርያርክ ቅ/ማርያም | በአ/አ HIV/AIDS መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት የማኅበረሰብ ንቅናቄ ኬዘረ ቲም አስተባባሪ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9. | ወ/ሮ አፀደ ማሞ | ሴት | 55 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት | አካውንታንት |
| 10. | ወ/ሮ አስቴር አበራ | ሴት | 50 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት | መረጃ ትንተና |
| 11. | ወ/ሮ እጅጋየሁ ደመረ | ሴት | 47 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነምሕረት | ሕትመትና ማባዣ ክፍል |
| 12. | ወ/ሮ እመቤት ጌትነት | ሴት | 28 | አዲስ አበባ | ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን | መምህር |
| 13. | ወ/ሮ ሙሉዬ ጠብቀው | | 29 | እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት | ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን | በመንግስት መ/ሪያ ቤት ግዢ ክፍል |
| 14. | አቶ ብርሃኑ ገመቹ | ወንድ | 48 | ገላን | ማኅበረ ቅዱሳን ሕንፃ | በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/ማ/ቅ የሥነ መለኮት መምህር |
| 15. | አቶ ሰለሞን አባተ | ወንድ | 33 | አዲስ አበባ | ማኅበረ ቅዱሳን ሕንፃ | በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/ማ/ቅ የሕፃናት ክፍል መምህር |
| 16. | ወ/ሮ ኅመጀ የሻነው | ሴት | 62 | ሰላሌ ፍቼ | ደ/ሊ ገዳም | የቤት እመቤት |
| 17. | ጳውሎስ ተካልኝ | ወንድ | 38 | ሳሪስ አቦ | ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን | የእንስሳት ሀኪም የምስጢራተ ቤ/ክ የኮርስ መምህር |
| 18. | ግርማ አያሌው | ወንድ | 38 | ሰላሌ ፍቼ | ደ/ሊባኖስ ገዳም | የግብርና ባለሙያ |
| 19. | ጦቢያው መንግስቴ | ሴት | 63 | ሰላሌ ፍቼ | በመኖሪያ ቤት | የቤት እመቤት |
| 20. | አቶ ባልከው ተሰማ | ወንድ | 66 | አዲስ አበባ | በመኖሪያ ቤት | ጡረተኛ |
| 21. | ደምሰው በለጠ | ወንድ | 58 | አዲስ አበባ | የክርስትናው ዕለት በመኖሪያ ቤት | ነጋዴ |
| 22. | ሀብታሙ በዳሳ | ወንድ | 28 | አዲስ አበባ | ደ/ሊባኖስ ገዳም | የግብርና ባለሙያ |
| 23. | ዘመኑ ከፍያለው | ወንድ | 26 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት | ሀምሳይ ክፍል ተማሪ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 24. | ሜሮን ደምሴ | ሴት | 23 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት | ሀምሳይ ክፍል ተማሪ |
| 25. | ራሔል ዘመድኩን | ሴት | 24 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት | ራብዓይ ክ/ፍ ተማሪ |
| 26. | መገርሳ ዲባባ | ወንድ | 67 | አዲስ አበባ | ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት | ራብዓይ ክ/ፍ ተማሪ |
| 27. | አቶ ገዛኸኝ ደፋሩ | ወንድ | 65 | ሰላሌ | ሰላሌ ፍቼ መመኖሪያቤት | የገዳሙ ነዋሪ |
| 28. | ወ/ሮ መሠረት ደመቀ | ሴት | 57 | ደ/ገ | ሰላሌ ፍቼ መመኖሪያቤት | የገዳም ነዋሪ |
| 29. | ወ/ሮ ዓለምነሽ ተስፋዬ | ሴት | 47 | አዲስ አበባ | ኪ.ቤ ምዕመን | የግል |
| 30. | ወ/ሮ ነፃነት ይርጋ | ሴት | 42 | ገላን | ኪ.ቤ ምዕመን | የግል |
| 31. | ዲ/ን ሚሊዮን ተሾመ | ወንድ | 37 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ቅድስት ማርያም አገልጋይ |
| 32. | ዲ/ያ ግዛው እንዳለ | ወንድ | 33 | ሰላሌ ፍቼ | ሰላሌ ፍቼ | የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የኮርስ መምህር |
| 33. | ዲ/ን አያሌው አታኩራቸው | ወንድ | 35 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | የሥነ መለኮት መምህር |
| 34. | ዲ/ን ተመስተገን አድነው | ወንድ | 30 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ሰ/ተማሪ |
| 35. | ርብቃ ጌታቸው | ሴት | 22 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ሰ/ተማሪ |
| 36. | ሔኖክ ደመቀ | ወንድ | 24 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ሰ/ተማሪ |
| 37. | መብራት መሀሪ | ሴት | 27 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ሰ/ተማሪ |
| 38. | ፍሥሀ ሔኖክ | ወንድ | 26 | አዲስ አበባ | አዲስ አበባ | ሰ/ተማሪ |

# አባሪ 3

## ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

### ጥምቀተ ክርስትናን በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማን ጀመረው
2. በምስጢረ ጥምቀት ውስጥ ጥምቀተ ክርስትና ምንድን ነው?
3. ወደ ክርስትና አዲስ ለሚመጡ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን መምህር ትመደባለች?
4. ጥምቀተ ክርስትና ለመፈጸም ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው?
5. የክርስትና አባትና እናት ሃላፊነት ምንድን ነው?
6. ጥምቀት ለምን በውኃ ሆነ?
7. የጥምቀት መሥራቹ ማን ነው?
8. በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ ጣት መያዝ ምሳሌነቱ ምንድን ነው? ለምን ቀኝ እጅ ሆነ
9. ካህኑ ሜሮኑን ውኃው ውስጥ ከጨመሩ በኂላ ሦስት ጊዜ እፍ ይሉበታል የዚህ ትርጉሙ ምንድን ነው?
10. በክርስትና ወቅት ተጠማቂዎች ቅብዐ ሜሮን ለምን ይቀባሉ?
11. ቅብዐ ሜሮን 36 ሕዋሳት ለምን ይቀባሉ?
12. በጥምቀተ ክርስትና ጊዜ ተጠማቂዎች ለምን ፀጉራቸውን ይላጫሉ? ጌጦቻቸውን ለምን እንዲያወልቁ ይደረጋል?
13. አጥማቂው ተጠማቂውን መጀመሪያ ወደ ምዕራብ ከዚያ ወደ ምስራቅ ለምን ይመልሰዋል?
14. ካህኑ በተጠማቂው ራስ ላይ እጁን የሚጭነው ለምንድን ነው?
15. ሦስት ጊዜ የሚያጠምቋቸው ለምንድን ነው?

16.ማተብ ማሠር ምሳሌነቱ ምንድን ነው?

17. ማተብ ማሰር መቼ እንደተጀመረና የት እንደተጀመረ ማወቅ ይቻላል?

18. በክርስትና ወቀት የሚታሰረው ማተብ ለምን ሦስት ዓይነት ኾነ?

19. በጥምቀተ ክርስትና ወቅት ተጠማቂዎችን ለምን በነጭ ልብስ ይቀበሏቸዋል? ምሳሌነቱ ምንድነ ነው?

20. የጥምቀተ ክርስትና አጥማቂው ማን ነው?

21. ከጥምቀተ ክርስትና የሚገኝ ጥቅም ምንድን ነው?

22. በክርስትና ወቅት አቋቋሚ ምንድን ነው?

23.የክርስትና ስም ምንድን ነው?

## ለምዕመናን የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ክርስትና ልጅ አለዎት?
2. ለክርስትና ልጅዎ ምን አድርገው ያውቃሉ?
3. ክርስትና እናት ለመሆን እንዴት መረጡ?
4. ክርስትና አባት ለመሆን እንዴት መረጡ?
5. መቼ መቼ ትጠይቂያታለሽ/ለህ
6. ምን ምን ታደርጋለህ/ሽ
7. በክርስትና ወቅት አቋቋሚ ምንድን ነው?
8. ቤተሰባዊ ግንኙነታችሁ ምን ይመስላል?
9. በክርስትና ወቅት አቋቋሚ ምንድን ነው?
10. ከክርስትና ቤተሰብ ጋር ያላችሁ ቤተሰባዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?

11.ክርስትና አባት/እናት ሆነው ያውቃሉ?

12.ክርስትና ባነሳህበት/ሽበት ወቅት ምን ብለህ/ሽ ቃል ገባህ/ሽ?

13.ከክርስትና የሚገኝ ጥቅም ምንድን ነው?

## ተክሊልን በሚመለከት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የተክሊል ጋብቻ ከሌሎች ዓለማዊ ጋብቻዎች በምን ይለያል?
2. በተክሊል ለመጋባት መሥፈርቱ ምንድን ነው ከተጋቢዎች ምን ይጠበቃል?
3. በተክሊል የመጋባት ጥቅሙ ምንድን ነው?
4. በተክሊል የተጋቡ ሰዎች ከጋብቻቸው በኋላ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሲኖሩ ምን ይጠበቅባቸዋል?
5. በተክሊል የሚጋቡ ሰዎች ለምን አንድ መጎናጸፊያ ይለብሳሉ?
6. ሙሽሮቹ የሚለብሱት ካባ፣ ራሳቸው ላይ የሚደፉት አክሊል ተምሳሌትነቱ ምንድን ነው?
7. የተክሊል ጸሎት ከሌሎቹ ተለይቶ ለምን ይጸለያል?
8. ሴቶቹ በቀኝ ወንዶቹ በግራ ለምን ይቆማሉ? ጣልቃ፣ ጣልቃ መግባት ይችላሉ?
9. የቀለበት ትርጉም ምንድን ነው?
10. ሜሮን ለምን ይቀባሉ?
11. ሙሽሮቹን ነጭ  መጎናጸፊያ ለምን ይለብሳሉ?
12. በተክሊል የተጋቡ ሰዎች መፋታት ይችላሉ? ለምን?
13. ሚዜዎች በቤተ ክርስቲያን ትርጉም ምሳሌ አላቸው?
14. ሙሽሮች መስቀልን /ወንጌልን/ በእጃቸው ጨብጠው ቃል ይገባሉ የዚህ ምሳሌና ትርጉም ምንድን ነው?

15. ሙሽሮች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ መብራት ይይዛሉ ሲወጡም መብራት ይይዛሉ የዚህ ምሳሌ ምንድን ነው?

16. የቀለበት ምሳሌ ምንድን ነው?

17. የተክሊል ጋብቻ ስርዓት ስሜቱ ምን ይመስላል?

18. የተክሊል ጋብቻ እና አለማዊ ጋብቻ ለእርስዎ ልዩነቱ ምንድን ነው?

19. ከዚህ በፊት የነበረዎት ማኅበራዊ አኗኗር ምን ይመስላል?

20. ለዚህ ታላቅ ምስጢር ሥጋዊ ፈተናን ተቋቁመው እንዴት ሊበቁ ቻሉ?

21. አሁን በጋብቻ ህይወት ውስጥ ሲኖሩ ያለዎት ማኅበራዊ አኗኗር ምን ይመስላል?

22. ሜሮን በመቀባትዎ ምን ተጠቅመዋል?

23. በተክሊል በመጋባትዎ ያገኙት ፋይዳ ምንድን ነው?

# አባሪ 4

## ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለምን የዐዲሱን ቤተክርስቲያን የመሠረተ ድንጋይ ሲያኖሩ ያደረጉት ንግግር

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፵ ዓ.ም

ሚያዚያ ፳፯ ቀን ወደ መናገሻ ከተማችን የገባንበትና በናፍቆት ሲጠብቀን የነበረ ሕዝባችን ከጠላት እጅ ወጥቶ የተገኘንበት ዕለት ስለሆነ ከ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ጀምሮ በየዓመቱ የሚከበር የታላቁ በዓላችን መታሰቢያ ነው።

የዚሁ በዓል ሰባተኛው ዓመት በሚከበርበት በዛሬ ቀን ሚያዚያ ፳፯ /፲፱፻፵/ ዓ.ም ለምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለም ዐዲሱን ቤተ ክርስቲያን ስንመሠርትና የመጀመሪያውን ድንጋይ በመሠረቱ ላይ ስናኖር ከዚህ ሰዓት ላደረሰን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን።

የበዓሉን መታሰቢያ በየዓመቱ ሚያዚያ ፳፯ ቀን የምናከብርለት ይህ ምስካየ ኀዙናን መድኃኔ ዓለም ጽላቱ በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በኢትዮጵያ ገዳማችን በዴር ስልጣን ቤተ ክርስቲያን ይኖር ነበር። በዘመነ ስደት አውሮፓ በነበርንበት ጊዜያት አምስት መነኮሳት ጽላቱን ይዘው ወደ እንግሊዝ አገር እንዲመጡ አድርገን ለጊዜው ማረፊያ ሆኖን በተቀመጥንበት፣ ባት ከሚባል ስፍራ ከሚገኘው ቤታችን አንድ ቤተ ጸሎት አሰናድተን በሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱን አክብረንለት ነበር።

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ተስፋው ደርሶ እንደ ዛሬው ቀን /ሚያዚያ ፳፯ ቀ/ የነፃነት ምልክት ሰንደቅ ዓላማችንን ያቆምንበትና ድልን ያረጋገጥንበት ዕለት ሆነ።

ከዚያም በኋላ ታቦተ መድኃኔ ዓለም ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ አድርገን ስማችን በሚጠራበት በሆስፒታላችን ክበብ ውስጥ በታነጸው ቤተ ክርስቲያን ሚያዚያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ተከልነው።

አሁን ደግሞ በተፈሪ መኮንን ተማሪ ቤት ክበብ ውስጥ ይህን ያዲሱን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ስንመሠርት በዚህ ተማሪ ቤት የሚማሩት ክርስቲያናውያን ወጣቶች፣ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸውን ሥርዓት እንዲጠብቁበት ሥርዓተ ጸሎትና ሥርዓተ ቁርባን በመፈጸም እንዲጠቀሙበት አስበን ነው።

የጥበብ መዠመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ሃይማኖቱን የማያከብር ሃይማኖት የሌለው እርሱም የሚያምነው ደገፋ የሌለው እርሱንም ማንም የማያምነው የሁለት ዓለም ስደተኛ ነው።

ፍሬውንም ለማየት ተስፋችን እርሱ ምስካየ ኀዙናን መድኃኔዓለም ነው። (መነሻና መድረሻ ማታወሻ 1942 ፣43)።

# አባሪ 5

## የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ዴር ሱልጣን ገዳም የተላከ ደብዳቤ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩም እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

ይድረስ።

ለብፁዕ አባቴ ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ። እንደ ምን ሰንብተዋል። እኛ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነን። እስከ አሁን ድረስ ባለነው አኳኋን የምናስበው ለእናንተ ነው እንጂ ወደ እኛ ምንም የሚያሳስብ የለም። ይልቁንም የእኛም እዚህ መሆን በየጊዜው ጀኔብ በሚደረገው ስብሰባ ቢፈቀድልን የእኛ መሔድ ባይፈቀድልንም መልእክተኞቻችን መላክ ለመጣንበት ጉዳይ ዋና ረዳታችን ስለሆነ የፈጣሪያችን ፍርድ የኢትዮጵያን ጉዳይ እስከ አጠቃለልን ድረስ እዚሁ ሆኖ ማዳመጥ የሚያስፈልግ መሆኑን ስለተረዳነው የፈጣሪያችንን ቁርጥ እስክናውቅ ድረስ በእዚሁ ሁኖ ማዳመጥ በእንግሊዝ አገር ለመቆየት ቆርጠናል። የእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት ፈቅዶልንና አሰናብቶን ወደ ኢየሩሳሌም እስከምንመጣበት ቀን ድረስ የሃይማኖት ችግር እንዳያገኝን የሚያደርጉትም ልጆቻችን የሃይማኖታቸውን መሠረት እንዳያጡት አስበን አንድ ጽላትና አምስት መነኮሳት የሚያስፈልጉትን ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍት ሰጥተውት ይዞ እንዲመጣ አባ ሐናን ልኬዋለሁና ከመምህር ገሪማ ጋር ተመካክራችሁ ዓቢይ ጾም ሳይገባ እንዲደርስ አድርጋችሁ እንድትልኩልን ይሁን።

በየጠረፋችንም ተሰደው በሰው ግዛት ላሉትም ሰዎቻችን እንደዚሁም ሰው መላክ አስፈላጊ ሳይሆን አይቀርምና እየተመካከራችሁበትና ፈቃዱ የሚሆን መነኵሴ እየመረጣችሁ እስክናስታውቃችሁ ድረስ መጠበቅ ነው።

ጥር ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ሎንደን

**ማረጋገጫ**

**እኔ ዐያሌው አማረ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ተማሪ ያቀረብኩት ጥናት የራሴ መሆኑን የተጠቀምኩባቸው ተዛማጅ ጽሑፎች በአግባቡ የተጠቀሱ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡**

**ስም ----------------------------------------**

**ፊርማ -------------------------------------**

**ቀን ----------------------------------------**